# እንባዬ ወረቀ



2971/2000
ሰዓዳ

ከሰዓዳ መሐመድ

# እሾሃማ ወርቅ

Addis Ababa City Government
Public Library

ከሰዓዳ መሐመድ

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት
1992

© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት 1992

ስልክ ቁጥር 504470

504496

የመ.ሣ.ቁጥር 12684

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የሽፋን ስዕል መሥፍን ሀብተማሪያም

# ምዕራፍ አንድ

ጥቅምት፣ 1983፤ ሳዑዲ አረቢያ:: በሀየር በዋዲ ሰፈር መንገዶችና በየቤቱ ደጃፍ የቆሻሻ በርሜሎች ተገሽረዋል:: የምግብ ሽቀጣሽቀጥ ለመሸመት ከየቤቶቻቸው የወጡ ነዋሪዎች ወደገበያው ማዕከል ይጣደፋሉ:: ሀየር በዋዲ፣ መሀል ጅዳ የሚገኝ ሰፈር ሲሆን ነጭ አረቦችና «አስሊ» የተባሉ ጥቁር አረቦች ይኖሩበታል:: አብዛኛዎቹ ነጭ አረቦች የናጠጡ ሀብታሞች ናቸው:: ጥቁሮቹ አረቦችም በነጮቹ የበላይነታቸውን ከመነጠቃቸው በፊት የሀገሪቱ ቀደምት ዜጎች እንደነበሩ ይነገራል:: ከነዚህ በተጨማሪ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸውና የሌላቸው የውጭ አገር ዜጎችም በሰፈሩ ይኖራሉ:: አብዛኞቹ የውጭ አገር ዜጎች ህግ ተላላፊዎች ናቸው:: ይሁንና የአካባቢው በሀብታም አረቦች መጥለቅለቅ ህገ ወጦቹን እንዲረሱ አድርጓቸዋል::

በዚሁ መንደር ከሚገኘው ባለ ስድስት ፎቅ ህንፃ፣ ሶስተኛው ላይ «ማዑሰሀ» (ንፁህ ውሀ) ተሞልቶ የሚሸጥበት የላስቲክ መያዣ ስምልክት ተቀምጧል— ውሀ ተሞልቶ::

እገበያው ማዕከል ጀርባ ካለው የውስጥ ለውስጥ መንገድ እንዲት ነጭ ማርቼዲስ እየፈሰሰች መጥታ የውሀ መያዣ ላስቲኩ ከተሰቀለበት ህንፃ ስትደርስ ቆመች:: ለሶስት ደቂቃ ያህል ያለማቋረጥ ቀይ ፍሬቻ ካበራች በኋላም በመጣችበት አኳኋን ተመለሰች::

«ከሪም?! ከሪም?!»፤ ከአፓርታማው የውስጥ ሳሎን መጋረጃ ጀርባ ተከልሎ የውጭውን ትዕይንት ይመለከት የነበረ አጠር፣ ወፈር

ያለ ወጣት ወደተዘጋው በር ዞሮ ተጣራ:: መልስ የለም:: ደግሞ ተጣራ:: የራሱ ድምፅ መልሶ አስተጋባ:: እየተቻኮለ ትልቁን ሳሎን ከውስጠኛው ሳሎን ወደሚለየው ተጣጣፊ በር ሔዶ ወደጐን ሰበሰበውና ከፈተው:: ከሪም የዘገየ የቀትር «የዝሁር» ሶላት ላይ ነበር::

ፍሰሃ ቢቸኩልም ስግደቱ እስኪያልቅ መጠበቅ ነበረበት:: ምርጫ የለውም:: የመንፈስ እርጋታ የሚታይበት፣ ቀጠንና ረዘም ያለው ከሪም በሶላት ላይ ያለውን ጠንካራ አቋም ፍሰሃ ያውቀዋል፤ ያስገርመዋልም:: በህገ ወጥ የመጠጥ ንግድ እየተዳደሩ ከፈጣሪ ጋር በቀን አምስቴ ለመገናኘት መሞከር ለፍሰሃ ታጥቦ ጭቃ መሆን ነው::

«ኀአም (አቤት) ፈለግኸኝ ፊሽ?» አለ ከሪም ስግደቱን እንዳጠናቀቀ::

«አንድ ደንበኛ መጥቷል::»

«ማነው እሱ?» ሲል ጠየቀ ከሪም ግንባሩን ቋጥሮ::

«ባለነጭ ማርቼዲሱ ነዋ! ይልቅ ውሃውን አዘጋጅ::» ፍሰሃ የውጭውን ትዕይንት ወደሚመለከትበት መስኮት ሲጣደፍ ከሪም ሪዙን እያፍተለተለ ወደኮሪደሩ አቀና::

«የቆየ ደንበኞችን ነው፤ አይዞህ» አለ ፍሰሃ ከፍ ባለ ድምፅ:: የከሪም ስጋት ገብቶታል:: ከሪም ሁሉን ነገር በእርጋታ ማጤን ይፈልጋል:: ፍሰሃ ግን ሁሌም እንደቸኮለ ነው:: «የኛ ስራ አደጋ የሞላበት ነው:: ገንዘብ ማግኘት እስከፈለግን ድረስ መስራት፣ መጣደፍ ብቻ ነው ያለብን!» የሚል ፈሊጥ አለው::

አፓርታማው በከሪም ስም የተያዘ ይሁን እንጂ ከፍያው የሚሸፈነው አርአያ እና ሙአዝ በሚባሉ ሌሎች ሰዎች ነው:: በመጠጥና ዕፅ ዝውውር የተካኑት አርአያና ሙአዝ ለዚሁ ስራቸው ከሪምንና ፍሰሃን መልምለዋቸዋል::

ሁለት ሳሎኖች፣ ሁለት መኝታ ክፍሎች፣ ሁለት መታጠቢያ ቤቶችና አንድ ማዕድቤት ያለው የከሪም አፓርታማ ከፍሰሃ ሌላ ተጋሪ የለውም:: በዚህ አፓርታማ ውስጥ በንፅህና የተያዘና በቀን ለተወሰነ ሰአት ብቻ የሚከፈት ክፍል ይገኛል:: ከሪም ከመጋረጃው ጀርባ ቆሞ እየተቅበጠበጠ ወደውጭ የሚመለከተውን ፍሰሃን በመገረም ተመለከተና ኮሪደሩን አቋርጦ ከተዘጋው ክፍል ሲደርስ በእጁ ካንጠለጠለው የቁልፍ ዘለበት መካከል አንዱን መርጦ በሩን ከፈተ:: ከዚያም ወደውስጥ ዘልቆ በሩን በላዩ ላይ ዘጋ:: በጨለማ የተዋጠው ክፍል በመጠጥ ሽታ ታውዷል:: በዳበሳ የመብራቱን ቁልፍ ተጫነ:: በክፍሉ ውስጥ ከጣሪያው ወረድ ብሎ እስከግድግዳው አጋማሽ ድረስ ከግድግዳው ላይ ተለጥፈው የተሰሩ ኮመዲኖዎች ይታያሉ:: የክፍሉን አጋማሽ የሸፈኑት ሳጥኖች በውስጣቸው የተለያዩ መጠጦች ታጭቀውባቸዋል:: ከሪም ከወደጥግ ያለውን ሳጥን ሲከፍት የውስኪ ካርቶኖች አፈጠጡበት:: አንድ ጠርሙስ አነሳና ከመደርደሪያው ላይ ካሉት ባዶ የውሃ ላስቲኮች በአንዱ ውስጥ ገለበጠው::

ፍሰሃ ከመስኮቱ አጠገብ ቆሞ በትንሹ በተገለጠው መጋረጃ ውጭውን ይቆጣጠራል:: የከሪምን ኮቴ ሲሰማ ዞር አለና፣ «አመጣኸው?» አለ እግሩ ስር ያስቀመጠውን ሳምሶናይት እያነሳ::

«አዎን፣ በተቻለህ መጠን ተጨማሪ ከፍያ ለማግኘት ሞክር:: በኛ ሩጫ የሚገኘው የውስኪ ገቢ የጋራ መሆኑ ቀርቶ

ለነአርአያ ብቻ እንደሚውል አትዘንጋ:: ከብዙ ድካምና ጭንቀት በኋላ የምናስገባው ገቢ ተግበስብሶ ከነሱ ኮሮጆ ሲታጨቅ፣ የኛ ድርሻ ግን እራፊ ጨርቅ አይገዛም» አለ ከሪም ሪዙን እያፍተለተለ አይኖቹ ቅዝዝ ብለው ከመጋረጃው ባሻገር እንደተተከሉ::

«ምናልባት...» አለ ፍሰሃ እንደጓደኛው በሀዘን በተሰበረ ድምፅ፣ «ምናልባት ያሁኑ ዘዴያችን ሊክሰን ይችላል::»

«የትኛው?» አለ ከሪም ወደፍሰሃ ዞሮ::

«ከተለመደው ዋጋ በላይ የምንጠይቀው ክፍያ ራሳችንን እንድንችል ያደርገን ይሆናል:: እንደአለቆቻችን የውስኪ ካርቶኖችን በማከማቸት የራሳችንን ደንበኞች ለማፍራት ማቀዳችን ግን የአድማስ ጠርዝን ለመዳሰስ የመንጠራራት ያህል ነው::»

«ፊሽ ተስፋህኮ ፈጥኖ አብቦ ወዲያው መክሰም የለበትም» አለ ከሪም በተግሳፅ::

«ችግሩ በርካታ የውስኪ ካርቶኖችን መሸመት የሚያስችለን ገንዘብ ያለመኖሩ ነው:: እንዲያም ቢሆን ግን በነአርአያ መበለጣችን መቀጠል እንደሌለበት አምናለሁ:: ቢያንስ ከምናስገባው ገቢ ላይ የራሳችንን ድርሻ ማግኘት አለብን ...»

«ይሄማ እንዳይሆን የሙአዝና የአርአያ አመራር ተንሠራፍቷል:: እስከዛሬ በነሱ ተፈትሎ የተሸመነ አሰራራቸውን ተከናንበን ኖረን አሁን ይነሳልን ብንል ችግር ውስጥ መውደቃችን አይቀርም :: ከሁሉም በላይ ደግሞ የሙአዝን አልጠግብ ባይነት ታውቀዋለህ:: ስለዚህ ደንበኞቻችንን ተጨማሪ ክፍያ በማስከፈል የምናገኘው ገቢ በስድስት ወራት ውስጥ ራሳችንን የሚያስችለን መሆን አለበት» አለ ከሪም ረጋ ባለ አነጋገር::

«እሱም ቢሆን ራሳችንን ችለን ለሽመታ እንድንበቃ አያደርገንም» አለ ፍሰሃ በመቅበጥበጥ::

ከሪም፤«ሁሌም ለችኩልነትህ ልጓም እንድታበጅለት ስመክርህ ኖሬያለሁ:: ዛሬም እደግመዋለሁ:: መቶ የሚደረሰው አንድ ተብሎ ነው:: በሁለት እግራችን መቆም እንችል ዘንድ እስክንጠናከር መጠበቅ አለብን» አለ በቆራጥነት:: ፍሰሃ በመስማማት አንገቱን ነቀነቀ::

«ተጨማሪ ክፍያ የምትጠይቃቸው ሰዎች ግን ከነአርአያ ጋር ያላቸው ግንኙነት የላላ መሆኑን አስቀድመህ ማወቅ እንዳለብህ አትዘንጋ::»

«ልክ ነህ፤ከአምስት ደቂቃ በኋላ እመለሳለሁ» ብሎ ፍሰሃ እየተቻኰለ ወጣ:: ከሪም አይኖቹን የተዘጋው በር ላይ ተክሎ ስለነሮው ያሰላስል ገባ::

አርአያና ሙአዝ ከመለመሉት ወዲህ በሚያገኘው ገቢ ረክቶ አያውቅም:: ሁሌም በነአርአያ ገንዘብ ተገዝተው የመጡ መጠጦችንና ዕፆችን ሸጠው ገቢውን ያስረክባሉ:: ከዚያም እነሱ የሚሰጧቸውን አነስተኛ ገንዘብ ይቀበላሉ:: በአንድ ወቅት ከሪምና ፍሰሃ ድርሻቸውን አጠራቅመው ራሳቸውን ለመቻል ሞክረው ነበር:: ሆኖም አሠሪዎቻቸው እዳቸውን እንዲከፍሉ አስገደዷቸው:: ከሪም ከሁለት አመት በፊት የመኖሪያ ፈቃድ ለማውጣት በፈለገበት ወቅት ጉድሎበት የነበረውን አራት ሺ ሪያል የተበደረው ከአርአያ ላይ ነበር:: ከሪምና ፍሰሃ የሚጠቀሙባትን መኪናም የነከሪም ጉረቤት ከሆነ አንድ ፓኪስታናዊ ላይ ስትገዛ ወጪውን የሸፈነው ሙአዝ ነበር:: በመሆኑም ከሪምና ፍሰሃ የያዟትን ጥሪት ለነአርአያ አስረክበው ባዶ እጃቸውን ቀሩ::

*　　　*　　　*

«አሰላሙ አለይኩም?» አለ ፍሰሃ ከመሪው ጀርባ የተቀመጠውን ስልክክ ያለ አፍንጫና የገጠመ ቅንድብ ያለውን የሳዑዲ ዜጋ በጉን እያየ::

«ወአለይኩም አሰላም» ሲል መለሰለት ሳዑዲያዊው:: እርባዎቹ ውስጥ ይሆናል:: የአገሬው ወንዶች የሚለብሱትን ነጭ ረጅም ቀሚስ ለብሷል:: ነጭ ሻሽም እናቱ ላይ ጣል አድርጓል:: ፍሰሃ የያዛትን ጥቁር ሳምሶናይት ለአፍታ ገርመም አደረጋትና መኪናዋን አንቀሳቅሶ ወደዋናው መንገድ አቀና:: «ስጦታዎቻችንን እንለዋወጣ?» አለ ወዲያውኑ::

«ውስኪ ነው ያመጣሁልህ» አለ ፍሰሃ በአረብኛ:: ለአራት አመታት ጅዳ ስለኖረ አረብኛ አጣርቶ ይናገራል::

«የዘወትር ምርጫዬን ታውቁታላችሁ:: የመጣልኝ በትልቁ ማዑስህ እንደሆነም ተስፋ አለኝ» አለ ሳዑዲያዊው ፈገግ ለማለት እየሞከረ::

«በእሱው ነው ያመጣሁልህ::»

«መልካም፤ ሶስት መቶ ሪያል ከዚህ ፖስታ ውስጥ ታገኛለህ» አለ ሳዑዲያዊው ሾጠጥ ያለ አገጩን ከፀሀይ መከላከያው ስር ወደተወሸቀው ፖስታ እያሾለ::

«ይቅርታ ዛሬ ሳናስቀይምህ አንቀርም...»

«እንዴት?»

«በችግር የተገኙ ጥቂት የውስኪ ካርቶኖች ነው ያሉን::»

«ኤሽ ሀዳ ሙሽኪላ?! (የምን ችግር ነው እሱ?!) ሲል ተቆጣ ሳዑዲው::

«ላ! ያለውን ሁኔታ ...»

«ጠይብ! ስንት ልጨምርልህ?» የፍስሃን ንግግር አቋርጦ እጁን ወደቀሚሱ ኪስ ሰደደ::

«ሁለት መቶ ሪያል::»

እንደዋዛ ከብዙ ኖቶች ውስጥ ሁለቱን ነጥሎ አወጣና እጁን ወደፍሰሃ ዘረጋ:: ፍሰሃ ተጨማሪውን ሪያል ፖስታው ውስጥ ጨምሮ ኪሱ ከተተና ከሳምሶናይቱ ውስጥ ያወጣውን መጠጥ ወንበሩ ስር አጋድሞ ከመኪናዩቱ ወረደ::

ነጯ ማርቼዲስ ወደመከረና የሚወስደውን ቀጥተኛ አስፋልት ትታ በስተቀኝ ካለው ተደራቢ የመኪና መንገድ ሽቅብ ከአይኑ ስትሰወር ፍሰሃ በእርካታ ፈገግ ብሎ ወደ አፓርታማው ጉዞውን ቀጠለ::

ፀሀይዋ ታንገበግባለች:: ውርውር ከሚሉት የቤት መኪናዎችና ታክሲዎች በስተቀር ሰው አይታይም::

ፍሰሃ ከነጭ ቱታው ስሪ ኪስ አንድ ሪያል አወጣና ከዘንባባው ዛፍ ሥር ወደቆመ የለስላሳ መጠጦች መሸጫ መሣሪያ አመራ:: ሪያሏን በስተቀኝ ባለው ቀዳዳ አሾልኮ አስገባት:: ይኼኔ በስተግራ ያለው ትንሽ መስኮት ተከፍቶ አንዲት የቆርቆሮ ፔፕሲ ብቅ አለች:: በፍጥነት ከፍቶ ያለማቋረጥ አንደቀደቃት:: ነፍሱ መለስ አለችለት:: ባዶዋን ጣሣ በአቅራቢያው ካለው የቆሻሻ በርሜል ወርውሮ ወደቤቱ ማዝገሙን ቀጠለ:: ወደቤቱ ሲቃረብ ግን አይኑ የውሃ ላስቲክ ከተሰቀለበት መስኮት ትይዩ ከቆመች መኪና ላይ አረፈ:: አይኖቹን አጥብቦ ፍሬቻዋን ብልጭ ድርግም የምታደርገውን መኪና ሾፌር አትኩሮ ተመለከተ:: በአካባቢው የሚዘዋወር የፖሊስ መኪና ባይታይም ፍርሀት ሰውነቱን ሲቧጥጠው ተሰማው::

ወደኋላው መለስ ብሎ ከአንድ የዘንባባ ዛፍ አጠገብ ቆመ:: መኪናዋ ያለማቋረጥ ፍሬቻዋን በግ እልም ታደርጋለች:: ወዲያውኑ ሾፌሩ ወደመስኮቱ አንጋጠጠ::

«ይክርብ ቤተክ! (ቤትህን ያፍርሰው) መጅድ» ሲል ፍስሃ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ ተራገመ:: ከሶስት አመታት በፊት ጓደኞቹ ላይ ጠቁሞ ያስያዛቸው ሞሮኮአዊው መጅድ ነበር::

ፍስሃ ሲናደድና ሲጨነቅ እንደሚያደርገው ላብ የቋጠረ የአፍንጫውን ጫፍ ያለማቋረጥ ያፍተለትል ጀመር:: ለአንድ ካርቶን ውስኪ ጓደኞቹን ያስቀላውን አረመኔ አሻግሮ በጥላቻ ተመለከተው:: ከወራት በፊት ሙአዝ በዱቤ የወሰደበትን የስድስት ሺ ሪያል መጠጥ ዋጋ ሳይከፍለው ወደሀገሩ ሱዳን በመሄዱ መጅድ አርአያን እንዲከፍለው ከጠየቀው ሁለት ሳምንት አልሆነም:: አርአያ የሙአዝን እዳ ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑም ተጣልተው ነበር የተለያዩት:: ፍስሃ ግራ ተጋብቶ ሳለ ከሪም የህንፃውን መግቢያ አቋርጦ ከመጅድ መኪና ላይ ሲሳፈር ተመለከተ:: «የፈጣሪ ያለህ!» አለ ጮክ ብሎ:: ከሪምን ጉትቶ ሊያወርደው ተንቀሳቀሰ:: መልሶ ደግሞ ፈራ:: ፖሊሶች በአካባቢው ተሰማርተው ከሆነስ? ግራ ቀኙን ተመለከተ:: አንዲት የፖሊስ መኪና ከሱ ትይዩ ካለው ህንፃ ስር ብቅ ብላ ወደቀኝ ታጠፈች:: አይኑን ጨፈነ:: «ይክርብ ቤተክ መጅድ! ይክርብ ቤተክ! ይክርብ ...»

# ምዕራፍ ሁለት

ጅዳ ከሚገኙት ዕዳት የጉደላቸው ሰፈሮች አንዱ ቁለይል ነው:: አፓርታማዎቹ የተገጣጠቡ ናቸው:: የአየር ማቀዝቀገርዎቹ የሚተፉት ውሃም አፓርታማዎቹን የሚያነቡ አስመስሏቸዋል::

ጥቋቁርና ግዙፎቹ የቁለይል ብዙሃን ነዋሪዎች ትኩሮኒዎች ይባላሉ:: ድሆችና ጉስቋሎች ናቸው:: ብዙዎቹ ወንዶች በሌብነት ወይም ዕፅ በማዘዋወር ተግባር ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ፣ ጥቂቶቹ ግን ከበርቴ አረቦች ዘንድ በጉልበት ሠራተኝነት ተቀጥረው ይሠራሉ::

የትኩሮኒ ሴቶች አለባበስ ከሀገሬው ህግና ስርአት ጋር በከፊል ይቃረናል:: ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ረጅም ቀሚስ ቢለብሱም እንደሌሎቹ እጅጌ ያላቸውን ልብሶች አይወዱም:: ወፋፍራም ጣቶቻቸውንም በጓንት አይሸፍኑም:: ትከሻቸውን የሚያጋልጥ ጃፓኒ ይለብሳሉ:: ነጫጭ የሳዑዲ ሴቶች እንደሚያደርጉት ፀጉራቸውን በሻሽ ቢሸፍኑም ለፊታቸው መከለያ አይነርግብ አያደርጉም:: ከፊሎቹ ፍራፍሬ ተሸክመው በየመንገዱ ሲዞሩ፣ የባለባቸው ደግሞ በሀብታም ሳዑዲዎች መኖሪያ ሰፈሮች እየተዘዋወሩ ቆሻሻ በመድፋትና ልብስ በማጠብ ይተዳደራሉ:: ቀሪዎቹ ከቆሻሻ መጣያ በርሜሎች ውስጥ የለስላሳ መጠጥ ቆርቆሮዎች ሰብስበው ለኩባኒያዎቹ መቶዎቹን በአስር ሪያል ሒሳብ በመሸጥ ይተዳደራሉ::

በቁለይል ከትኩሮኒዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን፣ ሱዳናውያን፣ ሶማሌያውያንና ፓኪስታንያውያን ይኖራሉ::

አይዳ ከነዚህ ነዋሪዎች አንዷ ናት፡፡ እያስከለከች ሰማያዊ በር ካለው ህንፃ ምድር ቤት ስትደርስ ደወሉን ተጫነችው፡፡

«ማን?» የሚል ቀጭን የሴት ድምፅ ተሰማ፡፡

«አይዳ ነኝ ሰሚራ፣ ክፈቺ» አለች በአማርኛ፡፡ የማጮለቂያው ቀዳዳ ተከፍቶ ተዘጋና በሩ ወለል አለ፡፡

«ፀሃዩ በላኝኮ» አለች እንደገባች፡፡ ከዚያም ጥቁር ረጅም ቀሚሷን ካወለቀች በኋላ የፊት መሸፈኛዋን ፊትታ ሶፋው ላይ አስቀመጠችው፡፡ ከሽፍንፍኗ ስትወጣ ቀይ ገፅታዋ በላብ ወዝቷል፡፡ ከውስጥ በለበሰችው ቀይ ቀሚስና ነጭ ሸሚዝ ሆና ቡኒ ቀለም የተቀባ ረጅም ፀጉሯን ወደጀርባዋ ለቀቀችው፡፡ የአይዳ ልበ ቅርፅ ከንፈር እንደወትሮው በወይንጠጅ ቀለም ደምቆ ዳርዳሩ በጥቁር ኩል ተውቧል፡፡

ጥግ የተቀመጠው ባለ አስራአራት ኢንች ቴሌቪዥን በአስር ሰዓት የሚጀምረውን የልጆች ፕሮግራም ከሳዑዲ አረቢያ የቴሌቪዥን ጣቢያ ያስተላልፋል፡፡

«የሚጠጣ ላምጣልሽ?» ሰሚራ ከአየር ማቀዝቀዣው የሚወጣው አሰልቺ ጩኸት ድምጿን እንዳይውጥባት ጮክ ብላ ጠየቀች፡፡

«ቀዝቃዛ ከሆነ ደስታውን አልችለውም፡፡» በዝንጀሮና በጦጣ ተመስለው የሚጫወቱት ተዋናዮች የሰለቿት አይዳ ጣቢያውን ቀየረችና የግብፅ ቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ አደረገችው፡፡ በዚያም ስለጥንት የሃይማኖት መሪዎች ገድል የሚያወሳ ታሪካዊ ድራማ በመተላለፍ ላይ ስለነበረ በተሰላቸ ሥሜት ዓይኖቿን ጨፈነቻቸው፡፡

ሰሚራ በቀዝቃዛ ውሃ የተበጠበጠ የፍራፍሬ ዱቄት በረጅም ብርጭቆ ሞልታ ከአይዳ ራስጌ ተጠግታ ተጣራች:: አይዳን እንቅልፍ ሸለብ አድርጓት ነበር:: ስሟ ሲጠራ ስትሰማ እንደመባነን ብላ «እ? ሰሚራ አመጣሽው?» አለችና ተነስታ ተቀመጠች::

«ፍሰሃ ጥዋት መጥቶ ነበር፤ ካደርሽበት አለመመለስሽን ነገርኩት::»

«ምናለሽ?» አለች አይዳ ቀጭኑንና ቀዝቃዛውን ጭማቂ ባንድ ትንፋሽ ጨልጣ ወደኋላዋ እየተንጋለለች::

«ስለትላንትናው ገቢ ሲጠይቅሽ ...» የሰሚራ መልስ ሳይቋጭ ተቋረጠ::

«ይኼ ቅል ራስ በነፍስ ስጋዬ ተጫውቶብኝ ሲያበቃ 'ገቢ ምናምን' እያለ ይቀባጥራል? አንገታችን ቢቀላ፣ ደማችን ቢመጠጥ እሱ ምን ተዳው?! በሞት ተከበን የምንሸጠው አካላችን የሚያስ ገኘውን ገቢ እኩል ይካፈላል::»አይዳ በንዴት ከተንጋለለችበት ተነስታ ተቀመጠች::

«ለመሆኑ የትላንትናው ገቢ ስንት ነበር?» ስትል ሰሚራ እንደዘበት ጠየቀች ::

«አራት መቶ ሪያል!» አለች አይዳ በሻከረ ድምፅ::

«ምን ይፈይዳል ይኼ?» የሰሚራ አይኖች ተጉረጠረጡ:: ጣቶችዋም ወደቅንድቦችዋ ተቀሰሩ:: «ያላንዳች ዋስትና ተከትለሽው ከምትሔጅው ሰው ካመጣሽው ከዚህ ገንዘብ ላይ ደግሞ ግማሹ ሲነሳለት ሁለት መቶ ሪያል ብቻ እንደሚቀርሽ አይገነዘብም?»

አይዳ ከት ብላ ሳቀች::

«ምን ያስቅሻል እንቺ?»

«የትላንቱም ገቢ'ኮ ሙሉ በሙሉ አልደረሰኝም» አለች አይዳ ሳቋን ሳታበርድ::

«ለምን?!»

«የትላንቱ አሳዳሪዬ የቆየ ደንበኛዬ ነው ...»

«ቢሆንስ ታዲያ?!»

«የሰጠኝ ሁለት መቶ ሪያል ብቻ ነዋ:: ቀሪውን በተመሳሳይ ፕሮግራም ስንገናኝ እንደሚያሟላልኝ ቃል ገብቷል» አለች አይዳ ፈገግ እንዳለች::

«እና ይሄ ያስቃል?» ሰሚራ በንዴት አንባረቀች::

«በኔ ቦታ ብትሆኚ ያስቅሽ ነበር:: ምክንያቱም ገንዘቡን በሙሉ ካልሰጠኝ ደምበኝነታችን እንደሚቋረጥ ስነግረው ያሳረፈብኝን ጥፊ ሳስታውሰው ያስገርመኛል:: የፍስሃም ገንዘብ አለኝ ብሎ መድከም ያስቃል» አለች አይዳ ፀጉሯን እየደባበሰች::

«ለምን ያስቅሻል? ፍሰ̃ሃ እስካቃጠረሽ ድረስ ድርሻውን መጠየቅ አለበት'ኮ» አለች ሰሚራ ጠንከር ባለ አነጋገር::

«ልሰጠው አልችልማ» በእጁ ያለው'ኮ የራሴ ድርሻ ብቻ ነው:: ከፈለገ የራሱን ሔዶ ከደንበኛዬ ጠይቆ መቀበል ይኖርበታል::» የአይዳ ፊት አሁን ተለወጠ:: ድምጿም መሻከር ጀምሯል:: «እሱ እንደሆን አይዳ ብትሞት የሚያቃጥራት ሴት አያጣ! ያለክፍያ ከሚሸኝ አውሬ ጋር ቢሰደኝ፣ በርካሽ ቢደራደርብኝ ይደንቃል? እኔስ ታዲያ ድርሻውን ብነፍገው ምን ይገርማል?» አለች አይዳ ወደግድግዳው ዞራ::

«ከንግዲህ ግን በርካሽ ዋጋ እንዲዋዋልብን ልንፈቅድለት አይገባም!» አለች ሰሚራም በቁጣ::

«ስሚራ መኖር፣ መብላት፣ መተንፈስ አለብንኮ። በአስር ሪያልም ቢሆን የምንስማማበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው።»

«አስር ሪያል!?»

«አዎን፣ የገባንበት ሰፈር ለዚህ ስራ አመቺ እንዳልሆነ ታውቂያለሽ። በዚያ ላይ ሃየር በዋዲ የነበሩት ደንበኞቻችን ቤት በመቀየራችን ሊያገኙን አይችሉም። ስለዚህ ለረጅም ሳምንታት ያለ ስራ ተቀምጠናል። የጐደለው እስኪሞላ የግድ መዳኖ ይኖርብናል።»

ሰሚራ በረጅሙ ተነፈሰችና «እከራያችንም ትላንት እንደወጣሽ የመብራት ክፍያ መጠየቂያ አምጥተዋል» አለች።

አይዳ ፊቷን ቅጭም አድርጋ «ስንት ቆጠረ?» ስትል ጠየቀቻት።

«አንድ መቶ ሃምሣ ሪያል።»

«አቤት የወጪው አበዛዝ» አለች አይዳ ወደጣራው አንጋጣ።

«ፍስሃ ግንኮ ቢያንስ የሚያመጣቸው ወንዶች ጠቀም ያለ ገንዘብ እንዲከፍሉን ሊደራደር በተገባ . . .»

«ምን አስጨነቀው ብለሽ? ይልቅ ተነስቼ ልተጣጠብ። ሳልዘጋጅ ከመጣ የአርአያን ጩኸት አልችለውም።»

«ፍስሃ የዛሬውንም ሰውዬሽን አርአያ ቤት ነው የቀጠረልሽ?» አለች ሰሚራ

«አዎን። ... ሌላማ የት ይሆናል?» አይዳ ከተቀመጠችበት ስትነሳ የበሩ ደወል ተንቃጨለ።

«ማነው ደግሞ በዚህ በጠራራ ፀሃይ የመጣው?» አለች ሰሚራ በታከተ ስሜት።

«አርአያ ይሆናል። እንደፈራሁት ሳልዘጋጅ ...» አይዳ እየለፈለፈች ወደሳሎኑ ስታመራ የበሩ ደወል ያለማቋረጥ ይጮህ ጀመር። አይዳና ሰሚራ ተያዩ። አይዳ ወደኋላዋ መለስ ብላ

የሚጮኸውን የአየር ማቀዝቀገር አጠፋችው:: ከዚያም ወደ ሰሚራ ዞር ብላ በሹክሹክታ «ይኼ ነገር የጤና ይመስልሻል?» አለቻት::

ሰሚራ የተረበሸ መንፈሷን ለማረጋጋት እየጣረች «ምናልባት ...» ከማለቷ የደወሉ ጩኸት ተቋርጦ በሩ በእጅ ይደበደብ ጀመር::

«ጉድ ፈላ!» አለች ሰሚራ በሹክሹክታ::

«ይንአል አለይኩም! (መአቱን ያውርድባችሁ)እናንት ጥጋበኞች ሃበሾች አትከፍቱም?!» የሚል ድምፅ የበሩን ጓንታ ተከትሎ ተሰማ::

«ተመስገን አምላኬ! ይኼ ስግብግብ ሽማግሌ ነው» አለች አይዳ ድምፁን እንደሰማች:: ቤት ያከራዩአቸው ሼህ ኢብራሂም ነበሩ የሚጮሁት::

«ሐጂና ክፊችለት!» አለች ሰሚራ በአከራዩ ስርዓት ማጣት ተበሳጭታ::

«እሽሽ፣ አትጩኺ'ንጂ! ተይው ይንጨርጨር:: ነገ ይከፈለዋል» አለች አይዳ ድምጿን ዝቅ አድርጋ:: በሀሳቡ የተግባቡ ይመስል ዝም አሉ:: በሩ ተደጋግሞ ተደበደበ፤ ከውስጥ ግን መልስ አልነበረም::

«እናንተ ተለምናችሁ ካልሆነ አትከፍሉም ማለት ነው? የቤት ኪራይ ተለምናችሁ፣ የመብራት ተለምናችሁ:: ከንግዲህ እኔ ኢብራሂም በየወሩ የናንተን ደጅ አልጠናም:: የምሰራውን አውቃለሁ! ደግሞ ለሃጅነብይ (ለውጭ ዜጋ) ልስገድ'ንዴ? ሊያውም ለሃበሽ? አሰራልሻለሁ! ማንነትሽን የማላውቅ መሰለሽ? ያወስኽ! ... ኢንሻ አላህ ... » የሽማግሌው ድምፅ እየተቆራረጠ እየራቀ፣ እየራቀ ሔደና ጠፋ::

# ምዕራፍ ሶስት

ከተማይቱ በደማቅ መብራቶች ተንቦግቡጋለች:: ከበላይዋ በተንጣለለው ጥቁር ሰማይ ላይ የተሰኩ የሚመስሉት ከዋክብቶችም የጅዳን ከተማ ድምቀት የሚያደንቁ ይመስላሉ:: ጅዳ ቀን ስታንቀላፋ ውላ ማታ ትነቃለች፤ትደምቃለች:: ዘመናዊዎቹ ሕንፃዎች አናት ላይ የተሰኩት ባለቀለም መብራቶች፣ ዳርና ዳር የተሰቀሉት የመንገድ ላይ ፍሎረሰንቶች፣ የሚሽከረከር ብርሀን የሚፈነጥቁ የማስታወቂያ ስሌዳዎች ህይወት ይሰጧታል:: የገበያ ማዕከሎች ይጨናነቃሉ:: ሀያ አራት ሰአት አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎችና ነዳጅ ማደያዎች ፤ሱቆችና ሆስፒታሎች እንቅስቃሴ ይጨምራል:: በምሽት ቁጥራቸው የሚጨምረው ሊሞዚን ታክሲዎች እንደ ሠርገኛ ተግተልትለው ይከንፋሉ:: ሰፊውን የሻሪዕ ቁረይሽና የሻሪዕ ፍልስጤም የመኪና መንገድ የሚያጨናንቁት የቤት መኪኖች ወደየጉዳያቸው ይበርራሉ::

ጃቢር ባለቤቱ ሳሚያን ከሶስት አመት ልጇ ጋር እተኛችበት ትቷት ሁለቱን የስድስትና የአምስት አመት ወንድና ሴት ልጆቹን ይዞ በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ሀራጅ ገበያ ሄዷል:: ጃቢር በሽረፊያ መኖሪያ መንደር ውስጥ ባለሁለት ፎቅ አፓርታማ አለው:: በመንደሯ ውስጥ ወደሀያ የሚጠጉ ሌሎች ባለሁለትና ሶስት ፎቅ አፓርታማዎችም ይገኛሉ::

እጃቢር ቤት ለሁለት አመታት በፅዳት ሰራተኛነትና በሞግዚትነት ሲያገለግሉ የቆዩ አንዲት ፊሊፒናዊትና አንዲት ኢትዮጵያዊት ይገኛሉ:: ሰራተኞቹ እንደሌሎቹ የከተማዪቱ

ነዋሪዎች ሁሉ ከባዱን የዘወትር ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ምሽት ላይ ነው::

ሞግዚቷ ሒክመት የልጆቹን ራት በማዘጋጀት ላይ ነበረች:: በአጭር፣ ቀጭን ሰውነቷ ላይ ያጠለቀችው ረጅም ልቅ ቀሚስ ድንች በምትጠብስበት ዘይት ፍንጥቅጣቂ ደረቷ አካባቢ ወዛዝቷል::

በዕዳት ሰራተኛነት የተቀጠረችው ኢትዮጵያዊት ደግሞ ሀያት ትባላለች:: ሀያት ሁለተኛ ፎቅ ከሚገኘው የልብስ መተኮሻ ክፍል ውስጥ የልጆቹን የደንብ ልብስ ተኩሣ እየጨረሰች ነበር:: የቀይ ዳማ ፊቷ በላብ ተሸፍኗል:: በእመቤቲቱ ትዕዛዝ ራሷ ላይ የምትጠመጥመው ወፍራም ሻርፕ ከካውያው ሙቀት ጋር ተደማምሮ አስጨንቋታል:: በሻሽ እንድትሸፍን የታዘዘችውም እርሷ ብቻ ነበረች:: ምክንያቱም እመቤቲቱ የሀበሻ ሴቶች አይነ ግቡ ናቸው የሚል እምነት ስላላት ነው:: ሀያት የእሲልን ሸሚዝ ተኩሳ እንደጨረሰች ወደማዕድ ቤቱ ወረደች:: በሩ ላይ ስትደርስ እመቤቷ ሳሚያ ፊሊፒናዊቷ ላይ ትጮህለች::

«የቤቱን ስርዐት እንድትጥሱ የፈቀደላችሁ ማነው?» ሀያት የእመቤቷን የቁጣ ድምፅ ስትሰማ በሩ ላይ ተገትራ ቀረች::

«ማዳም፣ ምንም የምንበላው ነገር አልነበረም» አለች ሒክመት፤ ከእመቤቷ ጥፊ ለማምለጥ እያፈገፈገች::

«ከመቼ ወዲህ ነው ሰራተኛ 'ኤሽ ፈረንሲ' የሚበላው?» አለች ሳሚያ፣ በላስቲክ ታስሮ ከተቀመጠው 'ኤሽ ፈረንሲ' ዳቦ አንዱን መዝዛ ለሒክመት እያሳየች፤ «ንገሪኝ! ከመቼ ወዲህ ነው እናንተ ይህን ለመብላት የበቃችሁት? ደግሞ ለናንተ 'ኤሽ ሉብናኒ' አነሳችሁ? እሱም ሲበዛባችሁ ነው...» ስትል እልህ እየተናነቃት ተንጣጣች::

የእመቤቲቱ ጩኸት ጋብ ሲልላት ሒክመት እጆችዋን እያፍተለተለች «ኤሽ ሉብናን በቤቱ ውስጥ አልነበረም:: ማታ እንኳን ራታችንን የበላነው ከመደርደሪያው ላይ ያገኘናቸውን የተሰባበሩ ዳቦዎች ለቃቅመን ነው» አለች::

«ቢሆንስ? ሰማሽ?! ሁላችሁም ሽቃላ ናችሁ:: እኔ 'ለሽቃላ' (ለገረድ) 'ኤሽ ፈረንሲ' አብልቼ አላውቅም:: 'ኤሽ ሉብናንም ሲበዛባችሁ ነው:: ከዛሬ ጀምሮ እዚህ ቤት ያለ ሰራተኛ ይህን ዳቦ ቢበላ ወዮለት!» ስትል አስጠንቅቃቸው ወጣች::

ሂክመት ወደሀያት ዞራ ከት ብላ ትስቅ ጀመር::

«ምን ሆነሻል?» አለቻት ሀያት::

«እንደጨው የነጣ ፊትሽን አተኩረው ሲያዩት እንዴት ያስቃል መሰለሽ?» አለች ሒክመት ከሳቋ ጋር እየታገለች::

ሀያት ዝም ብላ ስትመለከታት ቆይታ፣ «በጣም ትገርሚያለሽ» አለች::

«ለምን?»

«በሴትየዋ ቁጣ ስትንዘፈዘፌ እንዳልቆየሽ ሁሉ ገና ስትወጣልሽ ይህን ያህል ማሽካካትሽ ነዋ የሚገርመው::»

«እዬዬዬን ማቅለጥ ነበረብኝ ታዲያ?» አለች ሂክመት ወደግንባሯ የመጣ ዘንፋላ ፀጉሯን ወደኋላ እየመለሰች::

«ወላሂ፣ እኔ ባንቺ ቦታ ብሆን ያንን ነበር የማደርገው» አለች ሀያት ትከሻዋን እየሰበቀች::

«ላ! ሞኝ ነሽ፤ ለምን ታለቅሻለሽ?» አለች ወዳቋረጠችው ድንች ጠበሳ ለመመለስ ያጠፋችውን ጋዝ እየለኮሰች:: « ... እሷ'ኮ የማመዛዘን ችሎታዋን ድሎት ያዛባባት ከንቱ ፍጡር ናት:: ለንደዚች አይነቷ ሴት እንባዬን የማባክንበት ምክንያት አይታየኝም:: ከሀገሬ

የወጣሁት ስርቼ ከችግር ለመላቀቅ ነው እንጂ እንደሷ ሰውኮ ነኝ። አላህ ለሷ የሰጣት ነገር ቢኖር ገንዘብ ብቻ ነው፤ ገንዘብ!» አለች ሂክመት የምታገላብጠውን ድንች ተወት አድርጋ ጣቶችዋን በማፍተልተል ገንዘብ የመቁጠር ምልክት እያሳየቻት። «...የሷ ገንዘብ ግን ከፈጣሪ የተነፈጋትን ማስተዋል አይገዛላትም። ሊያስገኝላት የሚችለው እንደ እኔና እንዳንቺ ያሉትን ድሆች ብቻ ነው።» ሂክመት የመጨረሻውን ቃል ረገጥ አድርጋ ነበር የተናገረችው።

ሀያት በፍርሀት ወደበሩ ተገላመጠችና ሂክመትን በምልክት ዝም እንድትል አሳሰበቻት።

ሂክመት ግን አሁንም ያንን ሲሪር የሚለውን ቀጭን ሳቋን ደግማ፣ «ለምን ትፈሪያለሽ? ፍርሀትና ትግልኮ አብረው አይሔዱም» አለቻት።

«የምን ትግል?» ሀያት በመደናገር ሂክመት ላይ አፈጠጠች።

«ልታሸንፊው የምትታገይውን ድህነት ካንቺ ይበልጥ ደፋር ሆኖ እንዲገኝ እድል ልትሰጭው አይገባም። ስለዚህ ስድቦችን፣ ቁጣዎችንና ጩኸቶችን እንደምርቃት መቁጠርና መልመድ አለብሽ። በጌቶቻችን ድንፋታ ከመሸማቀቅ ይልቅ መዝናናት አለብን። መሳቅ! ያኔ የሚደራረቡብንን መከራዎች በመጠኑ ልንቀንሳቸው እንችላለን። እንባችን ወደውጭ ከሚፈስ ይልቅ ወደውስጥ ቢንቀረቀር ይሻለናል። ይግባና ይጠራቀም። በቤተሰብ ናፍቆት፣ በባዕድነት ቅዝቃዜ ከተኮራመተ ልባችን ላይ ይጋገር። ፅናትን ይሰጠናል! ወደውጭ ካፈሰስነው ግን ማዲያት ያበለዘውን ፊታችንን ከመመላለጥና ሀዘናችንን ከማባባስ ውጭ ምንም አይፈይድልንም።» ሂክመት ፊቷን ወደስራዋ መልሳ በትንሹ አስካካችና የበሰለውን ድንች አውጥታ ሌላ ጨመረች።

ሀያት በሂክመት ጥንካሬ ቅናት ቢጤ ሸጡ አለባት:: ወደእቃ ማጠቢያው ገንዳ ስትሔድ እርሷም እንደ ሂክመት እንባዋን በሳቅ ልትከልለውም ወሰነች::

ሀያት ከዕቃ ማጠቢያ ገንዳ ውስጥ የተከመሩትን እቃዎች በተከፉ አይኖቿ ታያቸዋለች:: ከመብዛታቸው በቅባት መጨመላለቃቸው ሃሞትዋን አፈሰሰው:: የጣቶችዋ ቁስሎች አመርቅዘዋል:: ውሃ ሲነካቸው ደግሞ ይበልጥ እንደሚቆጠቁጧት ታውቃለች::

«ይቺ ከይሲ!» አለች በእልህ ጥርሷን ነክሳ የቆሰሉ ጣቶቿን ደግማ እያየች::

«ማነች ከይሲዋ?»

ሀያት፣«ተመልከቺ፣ ጣቶቼንኮ ከጥቅም ውጭ አድርጋ ቸዋለች!» ብላም እጅዋን ወደሂክመት ዘረጋች:: ሂክመት የተመላለጡና ያባበጡት ጣቶች ህመም የተጋባባት ይመስል ፊትዋን አጨፈገገች::

«ዛሬ ጠዋት ሴትየዋ ባኞውን በክሎሮክስ አሳጥባኝ ነው እንዲህ የሆንኩት::» ሂክመት የቆሳሰሉትን የሀያት ጣቶች እየነካካች፤ «ያለጓንት በክሎሮክስ ታሳጥብሻለች? ነይ አንቺ ይህን ድንች ጠብሰሽ አውጭው:: እቃውን እኔ አጥበዋለሁ አለች::»

ሀያት የተጠበሱትን የድንች ቁርጥራጮች አውጥታ በክብ የተቆራረጡትን ዳቦዎች ወደሚፍለቀለቀው ዘይት ውስጥ ስትጨምር የዘይት ፍንጣቂዎች የቆሰለ ጣቶቿ ላይ አረፉ:: ህመም ዘልቆ ተሰማት:: እንባዋ ተንቆረዘዘ:: ከሀገሯ የወጣችበትንም ቀን ረገመች::

ከሀገሯ ያስወጣት ድህነት ነው:: አባቷ ጭነት ማመላለሻ ድርጅት ለሰላሳ አመታት በሾፌርነት ሲያገለግሉ ቆይተው በጡረታ ተገልለዋል:: ስለዚህም ስድስት ልጆቻቸውን ለማሳደግ አጥራቸውን

ቀድደው ትንሽ ሱቅ ከፈቱ። ምንም አልፈየደችላቸውም። በዚህ ሁናቴ ተስፋ የቆረጠችው ሀያት አንድ ምሽት ላይ የወጠነችውን ሀሳብ ለአባትዋ አካፈለቻቸው።

«አባባ ጅዳ ብሔድስ?» አለቻቸው።

«ወስነሻል?»

«አዎን» አለች ደፈር ብላ።

የሀያት ሀሳብ አባቷን አስደስቷቸዋል። «እንግዲያውስ ትሔጃለሽ» አሏት በርግጠኝነት።

«በምን ገንዘብ አባዬ?»

«እሱን በኔ ተይው፤ የእድር ዳኛ መሆኔን ዘነጋሽው እንዴ?» አሏት ፈገግ ብለው።

«ብትሆንስ?»

«የሚያስፈልግሽን ወጪ አደርጋለሁ። ከሁለትና ሶስት ወራት በኋላ ስርተሽ ትልኪልኛለሽ።»

«ስራው ቶሎ ባይገኝስ?» አለቻቸው በስጋት።

የሀያት ድንገተኛ ጥያቄ የአቶ አሊንም ልብ አሸበረው። ልጃቸው ስራ አጥታ በእዳ ሲያዙ፣ እድርተኛው አምኗቸው ያስቀመጠውን ገንዘብ አጉድለው ፍርድ ቤት ሲገተሩ፣ ያዘመመች የድህነት ጐጇቸው ስትወድቅና ልጆቻቸው ጐዳና ሲወጡ ታያቸው።

ወዲያውኑ ግን ወዳጃቸው የሆነው የመናዊው ደላላ ሼህ ረፊቅ ታወሳቸው። ልጃቸው በፀሎት ሰበብ ሳይሆን በቀጥታ በስራ ኮንትራት መሄድ እንደምትችል ተገነዘቡ።

ከአንድ ወር በኋላ የሀያት ጉዞ ተሳክቶ ወደጅዳ አቀናች። እነሆ ጃቢር ቤት ከተቀጠረች ሁለት አመታት አለፉ።

## ምዕራፍ አራት

«ሀሎ! አርአያ ነህ?» ፍሰሃ ከቤቱ ትይዩ ከሚገኘው ሱቅ የውጭ ግድግዳ ላይ የተሰጠፈውን የህዝብ ስልክ መነጋገሪያ እንቆ ከወዲያኛው ጫፍ ምላሽ ይጠብቃል።

«አዎን ነኝ» አለ አርአያ።

«መጅድ ከሪምን በመኪናው ይዞት ሔዷል።» ፍሰሃ የሚቆራረጥ ትንፋሹን ለመሰብሰብ ዝም አለ።

«ታዲያ ምንድነው ችግሩ?» ሲል ጠየቀ አርአያ ግራ ተጋብቶ።

«ባለፈው ጊዜ ካንተ ጋር መጋጨታችሁን አስታውስ እንጂ!»

«አስታውሳለሁ። ነገር ግን ገንዘቡን መቀበል የሚችለው ካበደረው ከሙአዝ ነው። ይህን እሱም ያምናል» አለ አርአያ በተሰላቸ መንፈስ።

«እኔ ግን መጅድ ሊበቀለን የፈለገ ይመስለኛል። ሙአዝ ጓደኛችን ነው። ከመጅድ ላይ የወሰደውን ገንዘብ ለመመለስ ባለመፈለጉም ይመስለኛል ድምፁን አጥፍቶ ወደሀገሩ የሄደው። መጅድ አረመኔ መሆኑን ደግሞ አንተም ታውቃለህ። እንኳን ለእኛ ለገዛ ጓደኞቹ የማይመለስ ነው። ከሪምን አዋዝቶ የወሰደው ለሰላም አልመሰለኝም» አለ ፍሰሃ።

«ኣ! እንደዛ ሊሆን አይችልም። ሰውየው ከዚህ በፊት ጓደኞቹን ለፖሊስ ጠቁሞ ያስያዛቸውም ለገንዘብ ብቻ ሲል

አልነበረም፡፡ ከሶስቱ ጓደኞቹ አንደኛው ያስቀመጣትን ሴት ሲያማግጥ ደርሶበት ነው፡፡» ፍሰሃን ፍርሀቱ ለቀቅ አደረገው፡፡

«ለበቀል ቢነሳሳም ደግሞ ጉዳዩ እኔንና ሙአዝን ብቻ የሚመለከት መሆኑን የሚያጣው አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም አንተና ከሪም በኛ ስር የምትንቀሳቀሱ መሆናችሁን አበጥሮ ስለሚያውቅ ከናንተ ምንም የሚያገኘው ነገር እንደሌለ ይረዳል፡፡ ሌላው ቀርቶ የተባለውን እዳ ግማሹን እንኳ ልትሰጡት እንደማትችሉ ያውቃል፡፡ ስለዚህ ዋናዎቹን ትቶ ጭፍሮቹን የሚበቀል አይመስለኝም፡፡ እናንተን በማስያዝ የሚጠቀመው ነገር የለም፡፡ ባይሆን ...»

«ነገሩን በስፋት መመልከት አለብንኮ» አለ ፍሰሃ የአርአያን ንግግር አቋርጦ፡፡ «የጭፍሮች መጥፋት አዛዦችንም ይጎዳል፡፡ እኛ ብንያዝ ለጊዜውም ቢሆን መዳከማችሁ አይቀርም፡፡ በሌላም መልኩ ብንመለከተው እኛ ፖሊሶች እጅ ከገባን ወደእናንተ እንድንጠቁም ልንገደድ እንችላለን፡፡ መጅድ እነዚህን ሁሉ አማራጮች ይዞ ተነስቶ ከሆነስ?»

«ፍሰሃ?» አለ አርአያ ረጋ ብሎ፣ «መጅድ ይህን ለማድረግ የሚደፍር አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም እሱም እንደኛ ህገወጥ እንደመሆኑ ስለኛ የሚነግራቸው ፖሊሶች ስለራሱም ማንነት ሳይጠይቁት አያልፉም፡፡»

«አርአያ ይህንማ በፍፁም አታስበው፡፡ እዚህ ሀገር እንዲህ ብሎ የሚጠይቅ የለም፡፡ 'ህይማኖት ሲጎድፍ፣ ወንጀል ሲስፋፋ አይቻለሁ' ካልክና ወንጀለኞችን ካመለከትካቸው የዚህ ሀገር ፖሊሶች ስለፈፀምከው በጎ ተግባር ከማመስገን ውጭ 'እንዴት አወቅህ? '

የሚል ጥያቄ አያነሱብህም፡፡ መጠቆም ቀላል እንደሚሆነው ሁሉ ከተጠያቂነት መዳንም ያን ያህል ቀላል ነው» አለ በስሜት እጆቹን እያወራጨ፡፡

አርአያ በረጅሙ ተነፈሰና በታከተ ስሜት «ምንም ዓይነት ችግር አይኖርም» አለው፡፡

ፍሰሃ በአርአያ እርግጠኛነት ተናደደ፡፡ «እሺ፣ በቃ መጥፎ ዜና ካለ እደውልልሀለሁ» ብሎ ስልኩን በንዴት ቦታው መለሰው፡፡ ያለው ምርጫ ሰቁ ውስጥ ሆኖ የከሪምን በሰላም መመለስ መጠባበቅ ብቻ ነው፡፡ ሰአቱን ተመለከተ፡፡ ከሪም ከመጅድ ጋር ከሔደ አንድ ሰአት አልፎታል፡፡ ቀና ብሎ ፀሀይዋን ተመለከታት፡፡ ወደምዕራብ እያዘቀዘቀች ነው፡፡ ጊዜው በገፋ ቁጥር የእሱም ተስፋ እንደ አመሻሿ ጀንበር ሊጠልቅ ተቃረበ፡፡

«እኛን እንጂ እናንተን ጭፍሮቹን...» አለኝ አርአያ ብሎም ከንፈሩን በቁጭት ነከሰ፡፡

ያለቀች ሲጋራውን ወለሉ ላይ ደፍጥጦ ወደበሩ ሲንቀሳቀስ የውሀ ላስቲክ ከተቀመጠበት የቤታቸው መስኮት ትይዩ የመጅድ መኪና ስትቆም ተመለከተ፡፡ ልቡ በስጋት እንደተወጠረች ትንፈራገጣለች፡፡ ወዲያው መጅድ መኪና ውስጥ ከሪምን አየው፡፡ በእፎይታ አጉተምትሞ በቀጭንና ዝቅተኛ ድምፅ አፏጨ፡፡

ባሻገር ከቆመችው መኪና ላይ አይኖቹን ሳይነቅል ሱቁን በዝግታ ለቆ ወጣ፡፡ ከሪም የመጅድን ትከሻ ቸብ፣ ቸብ አድርጐ ወደአፓርታማው እየተቻኮለ ሲገባ የፍሰሃ አይኖች እንባ አቀረሩ፡፡ ከሪም በሩን ሲከፍትለትም በሲቃ እየተናነቀ ተጠመጠመበት፡፡

«ምን ሆነህል?» ከሪም ግራ ተጋብቶ ጓደኛው ላይ አፈጠጠ። ፍሰሃ የጠረጠረውን ሁሉ ለጓደኛው አጫወተው።።

«እሱ እንኳን የፈለገኝ ለበጐ ነገር ነው» አለ ከሪም በመጨረሻ።

«ምን ለማለት ነው?»

«የበሰለ ስራ ተገኝቷል። ጉዳዩ እኔና አንተን ብቻ የሚመለከት ቢሆንም ለጊዜው ዝርዝሩን ይፋ አላደርግልህም። ነገ ከመጅድ ጋ ስመለስ ሁሉንም ትሰማዋለህ» አለው ከሪም ሶፋው ላይ ጋለል እያለ።

ፍሰሃ ጓደኛውን እያየ ዝም አለ።

«መጅድ ሁለታችንን ብቻ የፈለገበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ምናልባት አነአርእያ ገንዘቡን ስላልሰጡት ከነሱ ጋር ላለመስራት ወስኖ ይሆናል። ልክ እኛ ከነሱ ተነጥለን መቋቋም የምንፈልገውን አይነት ስሜት ...» አለ ከሪም ሪዙን እያፍተለተለ።

«የጭፍሮች መጥፋት ለአዛገሮችም ጉዳት አለው እንደሚባለው አይነት» አለ ፍሰሃ በምፀት።።

«ምን አልከኝ?»

«የበታቾች ራሳቸውን መቻል የአለቆቻቸውን ማጅት ያቀዘቅዘዋል ለማለት ፈልጌ ነው።» ከሪም ከት ብሎ ሳቀ። ፍሰሃም ፈገግ እንዳለ ተነስቶ ቆመ።

«ወዴት ነው?» አለ ከሪም ፍሰሃን አንጋጥጦ እያየ።

«አይዳን አርእያ ቤት የሚጠብቃት እንግዳ ስላለ ላገናኛት መሄዴ ነው። አዲስ ደንበኛ ነው» አለ ወደበሩ እየተራመደ።

«ቶሎ ከተመለስክ ጥሩ ራት ሰርቼ እጠብቅሃለሁ። ካመሸህ ግን ቀዝቅዞ ይጠብቅሃል። ዛሬ በጊዜ መተኛት አለብኝ» አለ ከሪም እየሳቀ።

ግንዲሰም ቶሎ እመለሳለሁ:: በርግጥ ከመምጣቴ በፊት ቶሰይል ጉራ ብዬ ስሜራን ማናገር አለብኝ:: እስከዚያው ጉድጉድ ለማለት ጊዜ ይኖርሀል::» ፍሰሃ በጉሩን ቀፈር ቀፈር አደረገና ስልኩን ተመልክቶ ከዚች ወጣ::

* * *

አይዳ ፍሰሃ ያጣመዳትን ሰውዬ ስረት አድርጋ ተመለከተችው:: የመኪናውን መሪ አጥብቆ ይዞ ከቱፑ የሚንቀረቀረውን የአረብኛ ሙዚቃ በፉጨት ያጅባል:: ረጃጅም የአይን ሽፋሽፍቶቹን አተኩራ አየቻቸው:: የአባቷን ይመስላሉ:: ደነገጠች::

አባቷ የአስራ ዘጠኝ አመት ለጋ ወጣት ሳለች ስለሕይወት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ የሌላት እንድዬ ልጃቸውን ከሀገር እንዳትወጣና ከአጠገባቸው እንዳትርቅ አጥብቀው ለምነዋት ነበር:: የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ውጤትዋ ያላስደሰታት አይዳ ግን በአባቷ የመኪና ዕቃ መሸዋወጫ መደብር ውስጥ መቀመጡም አልተዋጠላትም:: በዚህ ላይ ደግሞ ከእናቷ ጋር አይስማሙም:: በውሃ ቀጠነ ቱምስቅሷን ያሳዩዋታል::

በመጨረሻ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሰች:: ራሷን ለመቻል:: የራስ ጌታ ከመሆን የሚሻል ነገር የለም:: ለዚህ ደግሞ መንገዱ ቀላል ነው:: ሀሳቧን እናቷ ሲቀበሉት አባቷ ግን አጠንክረው ተቃወሙ:: እንዲያም ሆኖ ግን አይዳ ወደሳውዲ አረቢያ በረረች::

የምድር ገነት መሆኗ ይወራላት ወደነበረችው ሳውዲ አረቢያ ከመጣች በኋላ ግን ሀገሪቱን የችግሮች ቋት ሆና አገኛቻት- በተለይ

ስህገወጥ ነዋሪዎች:: የሚያማልሉት መንገዶች ጋሬጣ የበዛባቸው ናቸው:: የሚያጥበረብሩት ህንፃዎች ውስጥ ጉልበታቸውን ሽጠው የሚያድሩት ስደተኞች ለቅሶ የማያቋርጥ ሲሆን ጉዳናዎችን ሲያቆ ራርጡ በፖሊስ እጅ ላለመውደቅ ዙሪያ ገባውን መገላመጥ፣ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ከተዘጋ በርና መስኮት ጀርባ ሆኖ ከውጭ የሚመጣን ዱካ ለማዳመጥ ጆሮን ማቆም፣ ያለ ሙሉ ነፃነት በስጋት ተወጥሮ መግባትና መውጣት፣ መሽሎክሎክ. . .

ጅዳን ፍርሃት፣ ስጋትና ጥርጣሬ የነገሰባት ምድር ሆና ብታገኛትም ሌላ አማራጭ ያልነበራት አይዳ ሁሉን ችላ ለአስራ ሁለት ወራት በሳዑዲዎች ቤት በግርድና ሥራ ቆየች:: ይሁንና የወንዶችን አይን የሚነጥቀው ተክለ ሰውነትዋና ልብ የሚያሸፍተው ውበቷ ከእመቤቶቿ ጋር አላስማማት አለ:: አባወራዎች ሊያሽኮረ ምሚት ሲቃጡ ሚስቶቻቸው ይደርሱባቸዋል:: በአመት ቆይታዋ በቀያየረቻቸው አምስት ቤቶች የነበሩት የቤት እመቤቶች ከባሎቻቸው ፈቃድ ውጭ ከስራ አስናብተዋታል::

በመጨረሻ በሳዑዲ አረቢያ የሚኖሩ ተስፋ የቆረጡ ስደተኞች እንደሚያደርጉት ሁሉ ወደአስቀያሚው ባህር ልትጠልቅ ወሰነች:: ለእረፍት የምትሄድበት ሀየር በዋዲ ውስጥ የሚገኝ የሼህ ማህፉዝ ህንፃ ላይ ያሉት ሶስት ሴቶች ታወሷት:: ቤት ድረስ እየመጡ የሚወስዷቸው ወንዶች ጥሩ ክፍያ እንደሚሰጥዋቸው ጉርብትናቸው ባቀራረባቸው ወቅት በቅንጦት ዕቃዎች ያበደ ቤታቸውን ተመልክታ ተረድታለች:: የእሷ ማረፊያ ከሆነው አራተኛ ፎቅ ከሚኖሩት ሴቶች ይልቅ ሁለተኛ ፎቅ ያሉት ሴቶች በተሻለ ልብስና ጌጥ ይንቆጠቆጣሉ::

እንዲያም ሆኖ ግን መጨረሻ ትሰራበት ከነበረው ከአቡ መሀመድ ቤት ሳለች የረመዳን ፆም ፍቺ ዋዜማ ላይ አስከፊ አደጋ ስለደረሰባት ብቻ ነበር ቀርጣ ከሶስቱ ሴቶች ጋር የተቀላቀለችው። ሁለት አመታትንም በዚህ መልኩ አሳለፈች።

'የዛሬው ሰውዬስ ምን አይነት ይሆን?' ስትል ላፍታ አሰበች። ቀናም ብላ ገረመመችው። ሰውየው ፉጨቱን አቋርጦ፣ «የኔ ቆንጆ ደከመሽ?» ሲል ጠየቃት፣ አይኑን ከመንገዱ ላይ ሳይነቅል።

«አልደከመኝም» ስትል በአጭሩ መለሰችለት።

«አይዞሽ ደርሰናል። ጥቂት መንገድ ብቻ! ከዚያ ...» አለና በረጅሙ ስቆ ወደእሷ ዞረና ከንፈሩን በምላሱ እያራሰ ጠቀሳት። አይዳ መቻኮሉን ለመረዳት አልተቸገረችም። ካንገት በላይ ፈገግ ብላለት አይኖችዋን ከመንገዱ ትዕይንት ላይ አሳረፈች። ሰውየው ረጅሙን ሳቁን ደገመና ወንበሩ ላይ ለአፍታ ከተቁነጠነጠ በኋላ ፉጨቱን ቀጠለ።

የመኩረና የገበያ ማዕከል ከቀን ይልቅ በምሽት ይደምቃል። የልብስ ሱቆች፣ የጫማ መደብሮች፣ የጌጣጌጥ መሸጫዎች፣ የህፃናት አሻንጉሊት መሸጫ ሱቆች፣ የቤት እቃ መደብሮች ጠዞተ ተሰትረው ይታያሉ። ከሞቃታማው የቀን ግብይት ይልቅ የምሽቱን ሽመታ የሚመርጡ ገበያተኞችም በየመደብሩ ይርመሰመሳሉ። ሀፊዝ ፉጨቱን እያሰማ ደመቅ ያለውን የገበያ ስፍራ በስተቀኝ ትቶ ወደቤቱ ተጠጋ።

ሀፊዝ ጥቁር ፓትሮሉን እያሽከረከረ ሲገባ ህንፃው አናት ላይ ያሉት መብራቶች ግቢውን በብርሀን አጥለቀለቁት። ፓኪስታናዊው

ዘበኛ ከሀንዓጠ ፊንጠር ብሎ የተሰራው ማማ ላይ ወጥቶ ከጣሊያን ሬዲዮ ጣቢያ የሚተላለፈውን የምሽት ፕሮግራም ያዳምጣል።

የጐልማሳነት እድሜውን ያገባደደው ሀፊዝ አርባ አመት እስኪደፍን ድረስ ሚስት ለማግባት አልደፈረም። ቆየት ብሎ ግን ሀሳቡን ቀየረ። በባህሉ መሰረት የአባቱን የወንድም ልጅ ለማግባት ማሰቡንም አሳወቀ። ዘጠና ሺ ሪያል አፍስሶ የአጎቱን ልጅ አገባ። ትዳሩ ግን ከስምንት ወራት በላይ ሊዘልቅ አልቻለም።

ሀፊዝ አልጋ ላይ የተለየ ባህርይ ስላለው ከልስልሷና ከድንንጉጧ የአጎቱ ልጅ ጋር ሊዘልቅ አልቻለም። ናድያ እራሷ የፍቺ ጥያቄ በማቅረቧ በሸሪአ ህግ መሰረት ስታገባው ተሰጥቷት የነበረውን የቃል ማሰሪያ (መህር) መልሳለት ተለያዩ። ከዚያ በኋላ ሀፊዝን ብቸኝነት ተሰማው።

ስለዚህም ከህገወጥ ሰዎች ጋር ቅርበት ፈጠረ። መጠጥ በድብቅ ይሸጡለታል። ቆንጆ ማማረጡንም አስለምደውታል።

* * *

ሁለተኛ ፎቅ ከሚገኘው የሀፊዝ መኝታ ቤት የሁለት ሰዎች ንትርክ ይሰማ ጀምሯል።

«ለምን አትተኚም ሀቢብቲ?» ሀፊዝ በውስጥ ሱሪው ብቻ ሆኖ አልጋው ጫፍ ቁጭ እንዳለ ከፊቱ ቆማ የምትሞግተውን አይዳን ይማፀናል።

«ነገርኩህኮ! በቅድሚያ ክፍያው ይጠናቀቅ።» አይዳ ቡናማ ረጅም ፀጉሯን እየጠቀለለች ትሟገታለች።

«ፍሰሃ ደንበኛዬ ነው። ስለዚህ ልታምኚኝ ይገባል»አለ ሀፊዝ። ከዚያም ሰልካካ አፍንጫውን በጣቶቹ እየነካካ «እዚህ ድረስ አብረሽኝ ስትመጪም የተማመንን መስሎኝ ነበር» አላት።

«የሠለቸኝን ዲስኩር አታሰማኝ እባክህ።» ብላ አይዳ በፀጉር ማስያዣ የሰበሰበችውን ፀጉር ያለልቧ ፊትታ ወደጀርባዋ በተነችው።

ሀፊዝ በብስጭት የሚሸሽ ገላውን ቁልቁል ተመለከተ። ተነቃቅቶ የነበረው የወሲብ ስሜቱ ሙትት ብሏል። በመጨረሻ ተስፈንጥሮ ወደመልበሻ ክፍሉ ገባ። አይዳ በአይኖቿ ስትከተለው ቆየችና በሩን ሲዘጋ አይኖችዋን ወዳለችበት ክፍል መለሰች።

ከሰፊው አልጋ እራስጌ ባለው መደርደሪያ መሰል ባለመስተዋት ኮመዲኖ ላይ ፈሳሽ የፀጉር ሳሙናዎች፣ የወንድ ሽቶዎች፣ የጠረን ማጥፊያ ፈሳሾች ተደርድረዋል። ከመሀል ያለው ክፍት ቦታ ላይ አነስተኛ የአየር ማቀዝቀዣ መሣሪያ ተቀምጦበታል። ጥግ ትልቅ ዲጂታል ቴፕ ሪኮርደር ተኮፍሷል። ከመልበሻ ክፍሉ ትይዩ ከተዘጋው የመታጠቢያ ቤት ውስጥ ጠብቆ ካልተዘጋ ቧንቧ በቀስታ የሚወርድ ጠብ! ጠብ!... የሚል ድምፅ ይሰማል። ፀጥታው አይዳን አስፈራት። ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረችው የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ እየጠቀማት ስለሆነ ልትገፋበት ቆርጣለች።

«ጠይብ፣ ወደአልጋችን» አለ ሀፊዝ የጠየቀችውን ገንዘብ ሰጥቷት ከቦርሳዋ እስክታኖር ከታገሳት በኋላ።

ትክ ብላ እያየችው አንድ በአንድ ልብሷን ማውለቅ ጀመረች። ልብሶችዋን አጣጥፋ ከአልጋው ፊንጠር ብሎ ከሚገኘው ሶፋ ላይ አስቀመጠች። ነጣ ያሉ ረጃጅም እግሮችዋን በቅልጥፍና

እንቅሳቅሳ ለእቅፍ የተዘረጉትን የሀፊዝ እጆች እንዳላየች ሁሉ ብርድ ልብሱ ውስጥ ገባች።

ሀፊዝ ተጠመጠመባት። አይኖችዋን፣ አፍንጫዋንና አንገቷን በከንፈሮቹ ዳሰሳቸው፤ ጡቶቿን መጠጣቸው። አይዳ ግን የበድን ያክል ቀዝቅዛ በጀርባዋ እንደተንጋለለች አይኖችዋን ኮርኒሱ ላይ ሰክታለች። ከወንድ ጋር በተገናኘች ቁጥር የሚታወሳትን ትዕይንት ኮርኒሱ ላይ የምታይ ትመስላለች-ተደፍራ የተዋረደችበትን ቅዕበት።

*　　　*　　　*

የረመዳን ፆም ፍቺ ስለተቃረበ አይዳና እመቤቷ ለበዓሉ በመዘጋጀት ላይ ነበሩ። በዚህች የእስልምና ሀይማኖት መገኛ በሆነችው አረባዊት ሀገር ሀይማኖትን የሚያጉድፍ ዜጋ ጥብቅ እርምጃ ይወሰድበታል። በቀን እምስት ጊዜ ያልሰገደ፣ በስግደት ሰዓት ሲዘዋወር የተገኘ ይቀጣል። የሰላሳው ቀን የረመዳን ፆም ሲመጣም ቁጥጥሩ ከወትሮው ስለሚጠነክር ካዝናቸው የሞላና ሀይማኖቱን የማያጠብቁ ወጣቶችና ጉልማሶች ረመዳን ከመግባቱ በፊት ባህር ማዶ ይሻገራሉ።

እኩለ ሌሊት ላይ አይዳና እመቤቷ አብዛኛውን ሥራ ካገባደዱ በኋላ እመቤቲቱ ወደመኝታዋ ስትሔድ አይዳ ቀን ያጠበቻቸውን ልብሶች ለመተኮስ ወደፎቅ ወጣች። በእንቅልፍ እጦት የሚቆጠቁጡዋትን አይኖችዋን በቀዝቃዛ ውሃ እያራሰች ልብስ መተኮስዋን ስታጠናቅቅ የዘጠኝ ሰዓቱ ደወል ተሰማ።

ከማዕድቤቱ ትይዩ እሚገኘው መኝታ ክፍሏ እንደገባችም ሀይለኛ እንቅልፍ ወሰዳት። በመሀል የሆነ ድምፅ ቀሰቀሳት።

አይኖችዋን ስትገልጥ ከቀትር በኋላ ከካናዳ ከመጡ የአሠሪዎቿ ልጆች ጋር ተፋጠጠች:: ወጣቶቹ የሌሊት ልብሳቸውን እንደለበሱ ናቸው:: ታላቅየው ከወገቡ በላይ እርቃኑን ሆኖ የውስጥ ሱሪውን እንዳጠለቀ ወደ አልጋዋ እየተጠጋ ነበር:: ቦርጩ ከፍና ዝቅ ይላል:: ግንባሩ ላይ ያቸፈቸፈ ላቡን እየጠረገ ይጣራል::

እንቅልፍ በተጫጫናቸው አይኖችዋ ስትመለከታቸው ስጋዋን ዘልዝለው፣ ደሟን ሊጠጡ የተዘጋጁ አውሬዎች መስለዋት «ምን ትፈልጋላችሁ?» ስትል ጠየቀቻቸው፤ በፍርሀት መዝለል የጀመረች ልቧን በእጇ ሸፈን እያደረገች::

«ነህና ንሁቢክ ያአቢብትና (እኛ እንወድሻለን ውዴ)» አለ ታላቅየው ፈገግ እያለ::

«ውጡልኝ!» ብላ ተፈናጥራ ተነሳች::

«ዝም በይ!» አላት ታናሽየው::

ልትጮህ አፏን ስትከፍት ሀይለኛ ጥፊ ፀጥ አሰኛት:: አይኖችዋ ተጉረጠረጡ:: ሌላ ጥፊ ተከተለ:: ከዚያም ጠንካራ እጆች መልሰው ወደመኝታዋ ወረወሯት::

«የምናዝሽን ፈፅሚ!»አለ ትንሽየው በዝቅተኛ ድምፅ:: ጉርናና ድምፁ ያስፈራል::

አይዳ እጆችዋን ለማስለቀቅ ስትታገል ታላቅየው እግሮችዋ መሀል ለመግባት እየተጣደፈ ነበር:: ሆኖም አፍንጫውን በተረከዝዋ ስለመታችው ደም ማዝነብ ጀመረ:: ደመነፍሱን ወፍራም መዳፉን ሰነዘረ:: የተለያዩ ህብረቀለማትም ታዩአት:: ታናሽየው አፏን ጥርቅም አድርጎ ያዘው:: ከዚያም በዕፅ ተሳክረው በስጋዊ አምሮት የናወዙት የአሠሪዎቿ ልጆች ፈሰኩባት::

የንጋቱ የሰላት ጥሪ ሲሰማ ነበር አይዳ ህሊናዋን የገዛችው:: ሙሉ ለሙሉ ያልተገለጡት አይኖችዋ ይቆጠቁጥዋታል:: ሀይለኛ የራስ ምታትም ይተገትጋት ጀምሯል:: ቀኝ እጇን ተደግፋ ቀና አለች:: በደም የተኘርጕረጕረውን አንሶላ ስታይ የሚያሳድዳት እንዳለ ሁሉ ተስፈንጥራ ተነሳች::

ቁም ሳጥኑን በኃይል ከፍታም የተሰቀሉትን ልብሶች አውርዳ በፌስታል ጠቀጠቀች:: ከዚያም ጥቁር ልብሷን በትግል አጥልቃ አይነእርግቧን ተከናንባ ህንፃውን ለቀቀች::

*　　　*　　　*

ከላይዋ የሚያለከልክ ትንፋሽ በሰመመን ይሰማታል:: የሰው አይመስልም:: ወዲያውኑ ግን ከንዷ ላይና ጡትዋ ስር ተነከሰች:: ትኩስ ደም:: ሀፊዝ እያጓራ በረጃጅም ጣቶቹ ይቧጥጣታል:: ሀይሏን አጠራቅማ ፈንቅላው ተነስታ እየተንቀጠቀጠች ወደመታጠቢያ ቤቱ አፈገፈገች::

ሀፊዝ ሰፊው አልጋ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ሲወራጭና ትራሶቹን ሲያመሰቃቅል ከቆየ በኋላ እየቃተተ ዝርግትግት ብሎ አሸለበ::

አይዳ ህንፃውን ለቅቃ ወጣች:: በምሽት ብቻዋን የምትዘዋወር ሴት ለአደጋ የተጋለጠች መሆኗን አላጣችውም:: ሆኖም አማራጭ አልነበራትም:: ጕዳናውን አቋርጣ የኮካ ኮላ ማስታወቂያ ከተሰቀለበት ፊርማታ ስትደርስ ቆም ብላ ዙሪያዋን ቃኘች:: የሚዘዋወር የፖሊስ መኪና አይታይም:: «ሊሞዚን» የሚል ፅሁፍ የሚለጥፉት ታክሲዎችም የሉም:: ድንገት አንድ ቢጫ ፊያት አጠገብዋ ቆመ::

«እመቤት! ከኔ ጋር ትሔጃለሽ? አምስት ሙት ሪያል ይከፈልሻል» አለ ሾፌሩ::

እምቢታዋን በእጅ ምልክት ገለፀችለት:: መንገዱን ቀጠለ:: በዚህ አይነት ሶስት መኪኖችን ሸኘች:: ሆኖም ከቆመችበት ፊርማታ እስከታችኛው የትራፊክ መብራት ድረስ የተደረደሩት መኪኖች እሷን ለማነጋገር አቆብቁበው ሲጠባበቁ አየች:: ጂዳን ጨምሮ በሳዑዲ አረቢያ ታላላቅ ከተሞች በምሽትና ፀሀይዋ በምትገርበት ከስምንት ሰዓት እስከአስር ባለው ጊዜ ሴቶች ፍለጋ የሚዘዋወሩ በርካታ ወንዶች አሉ::

አይዳ በፍጥነት የመንገዱን ጠርዝ ይዛ ሽቅብ ሮጠች:: ጥቂት እንደሮጠች ሊሞዚን ስላየች አስቁማ ስትሳፈር የቤት መኪኖቹ ታክሲውን ተጠግተው ቆሙ:: ህንዳዊው ታክሲ ነጂ ጥቂት እንደተጓዘ የሚከተሏቸውን መኪኖች ስላየ፣

«ፊ ሙሽኪላ! (ችግር አለ!)»አለ በተደናገጠ ስሜት መኪናዋን ማቆም እየዳዳው::

«እባክህን የኔ ጌታ! እህቴን አሰሪዋ በቢላዋ እንደወጋቻት በመስማቴ ነው የተቻኮልኩት:: ብዙ ደም ሳይፈሳት ሆስፒታል እንዳደርሳት እርዳኝ» አለችው አይዳ የሾፌሩን ንግግር ያልሰማች በመምሰል::

«የምልሽን አልሰማሽኝም እመቤቴ? የሚከተሉንን መኪኖች ዞረሽ ተመልከቻቸው:: ካልወረድሽ ሊተናኮሉኝ ይችላሉ» አለ ጮክ ብሎ::

«እባክህ ከነዚህ አውሬዎች አድነኝ። እባክህ!...» እያለች አይዳ የሾፌሩን ትከሻ እየወዘወዘች ሳግ በሚተናነቀው ድምፅ ትለማመጠው ጀመር። ታከሲ ነጂው ጥቂት አሰብ አደረገና «ውሾች!» ብሎ ሸመጠጠ።

## ምዕራፍ አምስት

ሰሚራ ከሁለት አመታት ቆይታ በኋላ ከሳዑዲ አረቢያ የተመለሰችውን ጓደኛዋን ባገኘች ጊዜ ነበር የህይወት አቅጣጫዋ የተቀየረው:: በወርቅ የተንቆጠቆጠችው ሀና ለቤተሰቦቿ ስላስጫነችው የቤት መኪና፣ ስላመጣችላቸው የቤት እቃና ልብስ አተተችላት:: ይኸኔ የሰሚራ ልብ ሸፈተ:: በአካውንቲንግ ሙያ ለመመረቅ ሁለት ድፍን አመታት መቆየት ይኖርባታል:: ከዚያም ጠብ የማይል ደሞዝ የምትቆጥርባቸው አመታት ይከተላሉ:: እንደሀና ምርጫዋን ማስተካከል ብትችል ግን በሁለት አመት ብቻ ባለመኪና መሆንና ክርስቲያን በመሆኑ ከቤተሰቦቿ ሸሽጋ የያዘችውን ጓደኛዋን ኤርምያስንም ማግባት ትችላለች::

ያቃጠለችው አንድ አመት ቆጫት:: ከሀና ጋር ቆይታ ቢሆን ኖሮ የሷን ግማሽ ያክል ሀብት ባፈራች ነበር:: በመጨረሻ ትምህርቷን አቋርጣ ለመሔድ ወሰነች:: ቤተሰቦቿ ግን ተቃወሟት:: በተለይ ታላቅ ወንድሟ አርፋ እንድትማር ቢወተውታትም አልሰማችውም:: ኤርምያስም በሃሳቧ እንድትገፋበት ስላበረታታት በውሳኔዋ ፀናች::

ሳዑድ አረቢያን ግን የጣት ቀለበቶችና ያንገት ሃብሎች የተዝረከረኩባት ሙዳይ ሆና አላገኘቻትም:: ሀብት እንደዋዛ ይግበሰበስባታል የተባለችው ጅዳ በተቃራኒው በመከራ ጭጋግ የተሸፈነች ንፉግ ሆነችባት:: የሰሚራ ህልም መና እንደሆነ ሁለት አመታት ቢያልፉም ባዶ እጇን ወደሃገሯ ለመመለስ ግን ድፍረት አጣች::

ስለዚህም በቀላሉ ሀብት ሊያስገኝላት የሚችል ሌላ አማራጭ ስለመኖሩ ለማወቅ ጣረች:: አገኘችው:: ግን ኤርምያስስ? ላትክደው እንደገና ማለች::

ሆኖም ብዙም ሳትቆይ ወፈር ያለ ፖስታ ደረሳት:: ኤርምያስ በደብዳቤው ያደረገውን ሁሉ እንዳችም ሳያስቀር ዘርግፎታል:: የመስሪያ ቤት ባልደረባውን በሰርግ ማግባቱ ባይደንቃትም «አልጋ ላይ አትስማሚኝም» የሚለው ሀረግ ግን ክፉኛ በጠበጣት:: ደጋግማ አነበበችው:: ደብዳቤው በደረሳት ሳምንት ሀየር በዋዲ ከሚኖሩት ሴቶች ጋር ተቀላቀለች::

የሚያንቃጭለው የበር ደወል ሰሚራን ከሀሳቧ መለሳት:: የቁምጣዋን ዚፕ እየሳበች ወደበሩ ሔደች::

ማጮለቂያውን ከፍታ ከማየቷ በፊት «ሚን?» ስትል ጠየቀች::

«አኔ ነኝ ሰሚር!» የወንድ ድምፅ ምላሽ ሰጣት:: ሰሚራ ብቸኝነቷን የሚገፍላት ሰው በማግኘቷ እየተደሰተች በሩን ከፈተችና «ፊሽ ኬፊክ?» አለችው::

«አልሀምዱሊላህ:: አይዳን አርአያ ቤት ሔጄ አላገኘሁዋትም:: ከሀፊዝ ጋር ሔዳ ደረስኩ» አለና ወደውስጠኛው ሳሎን ገብቶ ከፍራሹ ላይ ተቀመጠ:: ፊቱ ጠቋቁሯል:: ድፍርስ አይኖቹ ጠጪ መሆኑን ያውጃሉ:: በአጭር ቁመናው ላይ አለመጠን የሰፋው ደረቱ ጎልቶ ይታያል::

«ለስራ ዝግጁ ነሽ?» አለ ፍስሃ የአናናስ ብጥብጥ አምጥታ እፊቱ ስታኖርለት::

«ዝግጁ ነኝ» ስትል ሰሚራ በዝቅተኛ ድምፅ መለሰች:: ለአምስት ቀናት ያስተናገደችውን የወር አበባዋን መሸኘቷን ማረጋገጧ ነበር::

«ጠይብ፤ ነገ ከአንድ ሰው ጋር ታድሪያለሽ» አላት ሲጋራውን እየተረኮሰ::

«ጥሩ ይከፍላል?» አለች የቀዘቀዘ ስሜት እየተነበበባት::

«አምስት መቶ ሪያል::»

«ከዚህ በፊት ታውቀዋለህ?»

«ላ! አዲስ ደንበኛ ነው::»

«ጠይብ!» አለች ፈገግ ለማለት እየሞከረች::

ፍስሃ ሁለተኛውን ሲጋራ ጨርሶ ቁራጩን መተርኮሻው ላይ ጣል አደረገና፣ «ሰውየውን ነገ ከዝሁር በኋላ አርአያ ቤት ይዤው እመጣለሁ:: ቀድመሽ ድረሽ» አላት በዝምታ ወደተቀመጠችው ሰሚራ ዞር ብሎ ለመሔድ እየተነሳ::

«ኢንሻ አላህ፤ እደርሳለሁ:: የቤት ኪራይ ውዝፋ'ኮ አፍንጫችን ደርሷል» አለችና ሼክ ኢብራሂም ያደረጓቸውን አጫወተችው:: ስሜት አልሰጠውም:: በሩ ሲደርስ ትዝ ያለው ነገር እንዳለ ሁሉ ቆም ብሎ፣ «አይዳን ...» ከማለቱ የበሩ ደወል ደጋግሞ አቃጨለ::

ሰሚራ በማጮለቂያ አየችና በሩን ከፈተች:: አይዳ እየተወላገደች ገብታ ወደ መሬት ስታሽቆለቁል የፍስሃ ክንድ ተቀበላት:: ስቃይዋን ለመቻል የምትታገለዋ አይዳን ደጋግፈው ወደውስጠኛው ክፍል አስገቡዋትና ፍራሹ ላይ አሳረፏት::

ፍስሃ አይዳ በምልክት የጠቆመችውን አካባቢ ለማየት ስለተጣደፈ የአባያዋን ቁልፎች በጣጠሳቸው:: በረጋ ደም የተሸፈነ ቁስል ከጡቷ ስር ተመለከተ::

«አልኮልና ጥጥ!» ሲል ሰሚራን ጮክ ብሎ አዘዛት:: ወጣ ስትልለትም በሹክሹክታ፣ «ምን ገጠመሽ አይዳ?» ሲል በችኮላ ጠየቃት::

አይዳ ከሚቆራረጠው ድምጿ ጋር እየታገለች፣ «ሰ ..ሰውየ..ው..ሳ..ሳዲስት ነው» አለችው::

«የምን ሳዲስት?» ግራ ተጋባ::

«ሰውን በማሰቃየት የሚረካ አውሬ» አለች አይዳ ጥርሷን ነክሳ::

ሰሚራ ወደክፍሉ ስትዘልቅ የመጨረሻውን አረፍተ ነገር ሰማች::

«ምንድነው የሆንሽው?» ስትል ሰሚራም በበኩሏ ጠየቀች::

«ሰውየው ...» አይዳ ዓረፍተነገሯን በፍስሃ ቁንጥጫ የተነሳ አቋረጠችው:: ለምን እንደቆነጠጣት ባታውቅም መናገሯን እንዳልፈለገ ግን ተገንዝባለች::

«ሠውየው ምን?!» ሰሚራ አፈጠጠችባት::

«ሳዲስት ነው» ስትል በድፍኑ መለሰችላት::

ይኸኔ የሰሚራ ገፅታ ሲፈካ፣ ሲከስል፣ ሲቋጠርና ሲፈታ ተስተዋለ:: ፍስሃ ግንባሩን እንደቋጠረ ነው:: የሚያመጣቸው ወንዶች በአንዷ ላይ ችግር ከፈጠሩ ሌላኛዋ እንዳትሰማ ምንጊዜም እንደጣረ ነው:: ምንጊዜም ደንበኞቹ ጨዋዎች እንዲባሉ ይሻል::

«ሳዲስት!» ስሚራ የአድናቆት በሚመስል ድምፅ ቃሉን ደገመች::

«ስሚራ! የስቃይ ማስታገሻ ኪኒን ካለ ብታመጪ?» አለ ፍስሃ ከረጅም ዝምታ በኋላ:: ጉሮሮው ውስጥ የተወተፈ ነገር ያለ ይመስል ድምፁ ስልል ብሏል:: የረጋውን ደም ጠራርጉ ሲጨርስ ጣቶቹን ከአይዳ ጡቶች ላይ በዝግታ አነሳቸው:: አራት ጥርሶች ጠልቀው የወጡበት የቀኝ ጡቷ እንደማበጥ ብሏል:: ፍስሃን ድብልቅልቅ ስሜት ወረረው::

እነአይዳን እያከራየ ጥቅሙን ማጋበሱን ሲያስበው የጥፋተኝነት ስሜት ዘልቆ ተሰማው:: እህቶቹን ወደሞት እየነዳ ከሚያገኟት ላይ ይቀራመታቸዋል:: ግና ምን ያድርግ? እርሱም እንጀራ ሆኖበት ነው:: ሀገር ቤት ያለችው እህቱ እጇን አጣጥፋ የምትጠብቀው የሱን እርዳታ ነው:: ከአራት ልጆቿ ጋር ትቷት በሞት የተለያት ባለቤቷ አንዳችም መተዳደሪያ አልተወላትም:: እዚህ ደግሞ የፍስሃን ድለላ የሚፈልጉ በርካታ ሴቶች አሉ:: ጭንቅላቱ በጭንቀት ተናጋ:: ደግነቱ ከሪም «የበሰለ ስራ ተገኝቷል፣ የሚሳካ ከሆነ...» ያለው ተስፋ ትውስ ስላለው ተፅናና:: «አዎን፣ ጉዳያችን ከተሣካ ይሄ ሁሉ ስቃይ ያበቃል! ሴቶቹን ወደመታረጃቸው ልኬ አስከሬናቸውን ታቅፌ ማንባቴም ያከትማል:: በጥፊ የበለዘ ጉንጫቸውን አይቼ መሳቀቁ ይቀራል:: እነአይዳን ለቀን ጅብ ሰጥቼ ሙዳ ስጋቸውን ገብረው ሲመጡ ጥጥና አልኮል ይዤ አልቀበላቸውም...» እያለ ለራሱ ቃል ይገባ ጀመር::

# ምዕራፍ ስድስት

ኑራ ከግማሽ ሰአት በላይ ስታለቅስ ቆይታ ፀጥ ብላለች። ሂክመት አባብላ እንዳስተኛቻት የገመተችው ሀያት ምሣ የሚበሉት አሰሪዎቿንና ሦስት ልጆቻቸው ከበውት የተቀመጡትን ጠረጴዛ እየዞረች የጐደለ ነገር እንዳለ ተመለከተች።

«እንደጥንብ አንሳ አትዙሪኝ! የሚጠጣ ነገር እፈልጋለሁ!» ሲል ጮኸባት ጃቢር።

«ማማ ዶሮውን እሳት ስለበዛበት አልነካውም!» የአሰሪዎቿ የመጀመሪያ ልጅ አሲል እፊቱ ያለውን ሰሀን ገፋ አድርጐ መነጫነጭ ጀመረ።

«አንቺ አህያ! ... እሳቱን ቀንሺ ስልሽ አልሰማ ብለሽ የሰራሽውን ታያለሽ?» አለች እመቤቲቱ በበኩልዋ። ሃያት አንገቷን ደፋች።

«ባባ? መወፈር የለብሽም ስትለኝ አልነበረም? ለምንድነው ታዲያ ሰላጣ ገዝተህ ያልመጣኸው?» አለች የአምስት አመቷ ነቢሀ ሩዝ የምትጐርስበትን ማንኪያ ወደአባቷ እየቀሰረች።

«እምጥቻለሁኮ የኔ ቆንጆ። ለምን አባሽ አላዘጋጀሽላትም አንቺ?» አለ ጃቢር ሀያት ላይ አፍጥጦ።

«ተዘጋጅቷል፤ እመቤቴ ትንሽ ይቀዘቅዝ ስላለች ፍሪጅ ከትቼው ነው።»

«የቀዘቀዘውን አብልተሽ ጉሮሮዋን ልታሳምሚያት ነው? ደደብ!» ብሎ ጃቢር ሚስቱን ወረፋትና ሀያትን «ብይ ቶሎ አምጭው!» አላት::

ሀያት ሀገሩንና ቋንቋውን ከመልመዷ ከአንድ አመት በፊት የአሰሪዎቿ ባህርይ ይረብሻት ነበር:: ቀስ ብለው መናገርን እንደነውር የሚቆጥሩ ይመስሏት ነበር:: ሳዑዲዎች ቤት የሚገኙ አብዛኛዎቹ ቁሳቁሶች የሚሰሩት በኤሌክትሪክ ነው:: የአየር ማቀዝቀዣው፣ ፍሪጅ፣ የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ የፍራፍሬ መጭመቂያ፣ የውሀ ማጣሪያ፣ የምግብ ማሞቂያ፣ ... ጥቅም ላይ ሲውሉ ከፍተኛ ድምፅ ያሰማሉ:: የመሣሪያዎቹ ድምፅ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው ሳዑዲዎችም ለመደማመጥ ሲሉ ጮክ ብለው መነጋገርን ልምዳቸው አድርገውታል:: ስለዚህ መሣሪያዎቹ ጥቅም ላይ ባይውሉም እንኳን ጩኸታቸውን መቀነስ ያስቸግራቸዋል::

ሀያት ባለሁለቱን ፎቅ ህንፃ ለማፅዳት ግማሽ ቀን ይፈጅባታል:: ተሰአቱን ደግሞ ልብስ በማጠብና በማድረቅ፣ የተበላባቸውን የምግብ ሳህኖች አጥባ በመወልወልና እመቤቷን በምግብ ማብሰል ስራ በመርዳት ተግባር ትጠመዳለች::

በቀን ሶስትና አራት ጊዜ እየታጠቡ ልብስ የሚቀየርላቸው የጌቶቿን ልጆች የምትንከባከበው ፊሊፒናዊቷ ሞግዚትም እረፍት የላትም:: ለሁለት አመታት አብረው የኖሩት ሂክመትና ሀያት በተሰጣቸው የስራ ድርሻ ሳይወሰኑ በጋራ ሁሉንም ያከናውናሉ::

ሀያት ምሣ የተበላበትን እቃ አጣጥባና ሕፃኗን አስተኝታ ከሂክመት ጋር ማዕድቤት ተቀመጠች::ባልና ሚስቱ ሁለቱን ወንዶችና ሴት ልጃቸውን ሰርግ ይዘው ለመሔድ በመሰናዳት ላይ ነበሩ::

በሠራተኞቹ የምግብ ጠረጴዛ ላይ ለሁለት ሰው የሚሆን ምግብ የያዙ ሳህኖች ተቀምጠዋል:: ተትረፍርፎ የሚደፋው ሩዝ ለሠራተኞቹ የሚሰጣቸው ተመጥኖ ነው:: ሀያት ሰላጣው ላይ የቆምጣጤ ፈሳሽ ከማንጠባጠቧ እመቤታቸው «ሂክመት?! ሂክመት?!» እያለች ስትጣራ ሰሙ:: ሂክመት ያነሳችውን ሩዝ በታው መልሳ በፍጥነት ወጣች::

«ወደሠርግ ቤት መሔዳችን ስለሆነ ሕፃኗ ከእንቅልፏ ስትነሳ አጣጥቢያትና አብያት» አለች ሳሚያ በችኮላ::

ወዲያውኑ ትልቁ በር ተከፍቶ ተዘጋ:: ሀያትና ሂክመት ተመግበው እንዳበቁ የበሉበትን ዕቃ አጥበው አደራረቁና ወደየስራቸው ሄዱ::

የአስራ አንድ ሰአቱ ደወል ተሰምቶ ጥቂት እንደቆየ ሀያት አንዳች የሚሰቀጥጥ ድምፅ የሰማች መሰላት:: የካውያውን ሶኬት ነቅላ ወደማዕድ ቤቱ ወረደች:: ሂክመት የለችም:: አፍንጫው ላይ ክብ ክዳን የተገጠመለት ማንቆርቆሪያ ስለፈላ ቀጭን ድምፅ ያሰማል::

የሚፍለቀለቀውን ውሃ አውርዳ ቡታ ጋዙን ካጠፋች በኋላ ቀና ስትል ሂክመት ፍም መስላ ፊቷን እየቧጠጠች ወደማዕድቤት ገባች:: መላ አካሏ ይንዘፈዘፋል::

«ምን ሆንሽ?» ሀያት በድንጋጤ ጠየቀቻት::

«ልጅ .. ልጅቷ ... መኪና .. ኑራ ... ጌታዬ ... ምንአልከሁ? አቤቱ ፈጣሪዬ!» ሂክመት መናገር አልቻለችም:: እሪታዋን አቀለጠችው:: ሀያት ግራ ቢገባት የውጭ ልብሷንና ሻሽዋን ደርባ ወጣች:: በርካታ ህፃናትና አዋቂዎች ከበውት ወደሚንጫጩበት

ሰማያዊ መኪና አመራች:: የአስሪዎቿ የመጨረሻ ልጅ ከጉማው በስተቀኝ ተዘርግታለች:: ጉንጮቿ አሸቦ መስለው እጆቿና እግሮቿ ተመሰቃቅለዋል:: ከመሬት ጋር የተላተመው ጭንቅላቷ በከፊል በደም ተጨማልቋል::

ህያት መጮህ ስትጀመር አዛውንቱ ጉረቤታቸው የተሰበ ሰቡትን ሰዎች እየገፈታተሩ የልጅቱን አስከሬን አነሱት:: ሰማያዊው መኪናም ልጅቷንና ሁለት ወንዶችን ጭኖ ወደሆስፒታል ከነፈ::

የአደጋውን መከሰት ያልሰማው ፓኪስታናዊ ዘበኛ ከእንቅልፉ አልነቃም:: የመኝታ ሰዓቱን ላለማስተጓጎል ምሳውን እንደነገሩ ቀማምሶ እንዳሸለበ ነው::

በስልክ ጥሪ የአደጋውን መፈጠር የሰሙት ባልና ሚስት ስነስርዐቱን አቋርጠው ቤት የደረሱት ምሽቱ ለአይን መያዝ ሲጀምር ነበር:: ጃቢር ጥቁር ሲትሮይን መኪናውን ከቤቱ በር ትይዩ አቁሞ እየተጣደፈ ሲወርድ ሞተሩን አላጠፋውም::

የጌታውን የመኪና ድምፅ ለይቶ የሚያውቀው ዘበኛ ይሄኔ ነቃ:: በድንጋጤም በሩን ወለል አድርጐ ከፈተው:: ጃቢር በእንባ እየታጠበ ወደህንፃው ዘለቀ::

ባለቤቱ ሳሚያን ብርክ ይዟት ከሁለት ልጆቿ ጋር ህንፃው መግቢያ ደረጃ ላይ ቁጭ አለች:: የተደናገጡት የግቢው ነዋሪዎች ልጆቻቸውን ሰብስበው በየቤታቸው ተከተዋል:: በጃቢር ተጨምድዶ የተያዘ ረጅም ፀጉሯን ለማስለቀቅ የምትታገለውን ሂክመት ጐትቶ ከግቢው ካስወጣት በኋላ ወደመኪናው ሮጠ:: ከዚያም መሪውን ወደ ሂክመት አዙሮ መንዳት ጀመረ:: ይኸኔ ድርጊቱን በዝምታ ትመለከት የነበረችው ሂክመት መሮጥ ጀመረች::

አቅጣጫዋን ስትቀይር መኪናውም ይከተላታል:: ተስፋ ስለቆረጠች የድረሱልኝ ጩኸቷን ታሰማ ጀመር:: ማንም ግን ሊደርስላት አልቻለም:: ሳሚያ ብቻ ልጆቿን እንዳቀፈች፣ «ጃቢር ወንጀል እየፈፀምህ ነው:: የምትሰራውን የምታውቅ አልመሰለኝም:: ሰይጣን ሊያታልልህ አይገባም!» እያለች ትጮሃለች::

ፓኪስታናዊው ዘበኛ በበኩሉ፣ «እመቤቴ፣ የጌታዬ ጤንነት አጠራጥሮኛል:: አንድ ነገር ማድረግ አለብን...» ብሎ ሂክመትን ወደሚያራውጣት መኪና ተፈተለከ::

«ጌታዬ?! ረጋ ብለው ያስቡ:: ጌታዬ? የሰው ህይወት በእጅዎ ሊጠፋ ነው!» እያለ የጌታውን መኪና መከተል ሲጀምር ግን ጃቢር የኋላ ማርሽ አስገብቶ መጣበት::

ይሄኔ ዘበኛው ወደተከፈተው በር ሮጦ አመለጠ:: «ጌታዬ በርግጥ አብደዋል!» እያለም ስልክ ሊደውል ወደሕንፃው ገባ::

ሂክመት በደመነፍስ ወደአንዱ በር ተንደረደረች:: ሆኖም መኪናው ቀድሞ ገጫት::

በፍሎረሰንት መብራት የደመቀው ቅጥር ግቢ ሁሉን ነገር ወለል አድርጐ ያሳያል:: ለጥቂት ሰኮንዶች የተርገፈገፈው የሂክመት ሰውነት በፀጥታ ተጋድሟል:: ረጅሙ ዘንፋላ ፀጉሯ በትኩስ ደም ርሶ እርስ በርሱ መጣበቅ ጀምሯል:: በአፏ ግራና ቀኝ ደም ይፈሳል::

ሀያት ዘግናኙን ትርኢት ከሁለተኛው ፎቅ ስትመለከት ቆይታ በለበሰችው ጥቁር አባያና ሻሽ እንደሆነች ደረጃዎቹን

ጠረደች፡፡ ህንፃው መግቢያ ላይ በድንጋጤ ደርቃ የቆመችውን ሳሚያን ገፍትራ በሩጫ ቅጥር ግቢውን ለማቋረጥ እየሮጠች ሳለች ግን ጃቢር ስላያት የከበቡትን ሰዎች ገፈታትሮ ይከተላት ጀመር፡፡

ዘበኛው፣ «ሀያት?! ... ሀያት?! ለማምለጥ አትሞክሪ ፖሊሶች ደርሰዋል! ሀያት!...» ሲል ይሰማል፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ድምፁ እየራቃት ሄደ፤ በመጨረሻም ጠፋ፡፡ የት እንደምትሄድ አታውቅም፡፡ ቅያሬ ልብስም ሆነ ገንዘብም አልያዘችም፡፡ ከሞት የተረፈች መሆንዋን እንዳረጋገጠች ቆም ብላ ዙሪያዋን ቃኘች፡፡ ጭር ያለ አካበቢ ነው፡፡ በፍርሀት ተውጣ ሳለችም ከኋላዋ ተንሳጦ መኪና ሲቆም ሰማች፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

ከሪምና መጅድ በቀጠሮአቸው መሠረት ተገናኝተው ህይወታቸውን ሊለውጥ የሚችለውን ሥራ ሊከውኑ ተስማምተዋል። ቀጠሮው ቦታ ቀድሞ የደረሰው ከሪም ነበር።

'ያለችኝ ገንዘብ ላይ ከመጅድ የምበደረውን ጨምሬ ዕፁን እገዛለሁ። ፍሰህ ደግሞ ለፈላጊዎች ያዳርሳል። በቃ፣ ከዚያ አለፈልን ማለት ነው። ኢንሻአላህ አምላኬ ለዛገሬም ያበቃኝ ይሆናል' እያለ እንደተቀመጠ ያወጣል፣ ያወርዳል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት የማኔጅመንት ተማሪ የነበረው ከሪም ትምህርቱን ያቋረጠው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብላቴ ካምፕ እንዲገቡ ጥሪ በተደረገ ጊዜ ነበር። በእሰብ በኩል ወደ ጂዛን ሾልኮ ከዚያ ጅዳ ገባ። ያረፈው ከሚች እክስቱ ባል ቤት ነበር። ጥቂት ሳምንታት በሥራ እጥነት ሲንላላ ከቆየ በኋላ በአንድና ሁለት ሪያል የሸክም ሥራ ጀመረ። በዚህ መልኩ እንጆ መንፈቅ አስቆጠረ።

በመጨረሻም የእክስቱ ባል ባንድ የኰንስትራክሽን ኩባንያ ሥራ አስቀጠረው። ሊፍት ላይ ድንጋይና ሲሚንቶ በመጫን ስድስት ወራት እንደሰራ ግን የግንባታ ስራው ስለተጠናቀቀ አሰናበቱት። ሥራ እጥነት ዞሮ መጣች። በመሃሉ የሥራ ባልደረባው የነበረው ሙእዝ መጠጥ የማዘዋወር ሥራ እንዲሠሩ ጋበዘው። ሁለት ዓመት እንደሠሩም ፍሰሃ የቡድናቸው አባል ሆነ።

መጅድ ክላክስ ሲያደርግለት ከሪም እንደመጣን ብሉ የተከፈተለትን በር ዘልቆ እየተሽቆጠቆጠ መኪናዋ ውስጥ ተደላድሉ ተቀመጠ::

ስድስት መኪኖችን በረድፍ ሊያስኬድ ከሚችለው የመኪና መንገድ ዳርቻ ያለው ገላጣ ስፍራ በደረቱ ሣሮችና በጠወለጉ የዘንባባ ዛፎች ተሸፍኗል:: የሚነፍሰው ለስላሳ አየር ምሽቱን ተጠዳጅ አድርጎታል:: «መዲነተል ሁጃጅ» የሚባለውን ካምፕ ወደኋላ ትቶ ወደሳዑዲ አረቢያ አየር ማረፊያ የሚወስደውን ብቸኛ አስፋልት ተከትለው ሲሄዱ በስተቀኝ የተንጣለለው ቀይ ባህር በጥቁሩ ሰማይ ላይ የወጣችውን ሙሉ ጨረቃ ያሳያል::

መጅድ ድንገት «የፖሊስ መኪና!» አለ ሙብረክረክ የጀመረ እግሩን ከነዳጅ መስጫው ላይ በቀስታ እያነሳ::

ከሪምን የጓደኛው መርበትበት አላማረውም:: ጉሮሮውን ጠራረገና ረጋ ብሎ «አይዞህ እናመልጣቸዋለን:: ማፊ ሙሽኪላ» አለ::

በአስር የዱቄት ከረጢቶች የታሸገውን እፅ ሀየር በዋዲ ወደሚገኘው የከሪም አፓርትማ እየወሰዱ ነበር::

«ያ አኺ?! እንመለስ!» አለ መጅድ ወደጓደኛው ዞሮ:: የመጅድ አይኖች ፈጠዋል:: ፈጥኖ መኪናዋን ጥግ አስይዞ አቆማት::

እፊታቸው የነበረው የፖሊስ መኪና በዝግታ ወደባህሩ ዳርቻ እየተጠጋ ነበር::

«በሩን ክፈትና እባህሩ ውስጥ ጣላት!» አለ ሾፌሩ ወደኋላ ዞሮ::

«ባህሩ ውስጥ?» አለ ከልጅቱ ጐን የተቀመጠው ፖሊስ ግራ በመጋባት:: ልጅቱ ትንፋሿን ውጣ ህሊናዋን እንደሳተች መሆኗን ለማሳመን ጥረት እያደረገች ነበር::

«አዎን! መሞት አለባት?!» ሲል ሾፌሩ አጠገብ የተቀመጠው ፖሊስ ተናገረ::

ትዕዛዙን እንዲፈፅም የሚጠበቀው ፖሊስ ግን ተረብሿል:: «እረ እባካችሁ አላህ የማይወደው ሥራ አንሥራ» እያለ መለማመጥ ሲጀምር ግን፣ ሾፌሩ «ምን እባክ ትጠብቃለህ? መአ ሰላማ በላት!» በማለት ጮኸበት::

ከጐንዋ ተቀምጦ የነበረው ፖሊስ እጆች ተንቀጠቀጡ:: «ምን ላድርግ?» አለ እየተርበተበተ::

«በሩን ክፈትና ሙሉ ሀይልህን ተጠቅመህ አርቀህ ወርውራት!» አለው ሾፌሩ ጭካኔ በተመላበት ድምፅ:: ወዲያው የኋለኛውን በር አንደኛው ፖሊስ ተንጠራርቶ ከፈተለት:: ጥርሱን ነክሶ ከፍ አድርጐ አነሳት:: ሊጨክን ግን አልቻለም:: ሁለቴ አቃስተና ላላ አድርጐ ወረወራት:: «ለይለ ሰኢዳ! (መልካም ምሽት)» አለ በሀዘን:: ልጅቱም ወደባህሩ ተንከባለለች::

ጋቢና የተቀመጠው ፖሊስ አናቱ ላይ የደፋውን መለዮ በብስጭት መንጭቆ ወደውጭ እያየ «ሙሽኪዳ! (እንዲህ አልነበረም) አርቀህ ወርውራት ነበር የተባልከው» አለው::

ሾፌሩ ተንጠራርቶ ተመለከታት:: ከአንድ የቆሻሻ በርሜል ጋር ተላትማ ተዘርራለች::

«ያ - ኢላሂ! ያ - ኢላሂ!» ጮኸ ሾፌሩ:: «አንተ ደደብ! ወርደህ ወደታች አንከባላት» አለ ወደኋላ ዞሮ::

«ላ! ላ! ሱቅ ገዳመክ ቢሱርእ! ቢሱርእ! (አይሆንም፣ አይሆንም! በፍጥነት ወደፊት ንዳ!)» እያለ ሌላኛው ፖሊስ መጮህ ጀመረ::

«ለምን?»

«ከኋላችን የቆመ መኪና ይታየኛል !»

ከሪምና መጅድ በድንጋጤ ደርቀዋል:: የፖሊሶቹ መኪና ሲንቀሳቀስ፣ መጅድ «ምንድነው ይሄ?!» ሲል ጠየቀ:: ድምፁ እየተንቀጠቀጠ ነበር::

«ሰው ነዋ ... ሰ ...» ከሪም የሚቆራረጥ ትንፋሹን ለመግራት እየሞከረ መለሰለት::

«ጠይብ ወደመጣንበት እንመለስ!»አለ መጅድ እየተርበተበተ:: ከሪም በእምቢታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ::

«ምን ማለትህ ነው? አይንህ እያየ አንገትህን ለሰይፍ ትሰጣለህ?!»

«ማዳን የምችለውን ህይወት ጥዬ ብሔድ ...» አለና ከመኪናዋ ወርዶ ወደልጅቱ ገሰገሰ:: መጅድም መኪናውን አንቀሳቀሰ:: በርሜሉ ጋ ሲደርሱ በጥቁር ልብስ የተሸፈነች ሴት በደረቷ ተዘርራ አዩ:: ከሪም ገልበጥ አደረጋት:: አፍንጫዋ በደም ተለውሷል::

ከሶስት አመታት በፊት ያጋጠመው አደጋ ትውስ አለው:: የፍሰሃ ደንበኞች ከሆኑት ሶስት ሴቶች ጋር የእንቁጣጣሽ ዋዜማን እያከበሩ ሳሉ እኩለ ሌሊት ላይ ፖሊሶች መጡባቸው:: ፖሊሶቹ በሩን ሰብረው ከመግባታቸው በፊት በመስኮት ማምለጥ ነበረባቸው:: ያሉት ሶስተኛ ፎቅ ላይ ቢሆንም ከመስኮቱ ትይዩ የሚታየው ጅምር ህንፃ ጣሪያ ላይ ማረፍ ይችላሉ:: ፍሰሃ ቀድሞ ዘለለ፤ ቀጥሎ አንደኛዋ ሴት:: ሁለተኛዋ ግን ፈራች:: ከሪም ሶስተኛዋን አደፋፍሮ አዘለላት:: ሆኖም ወጣቷ የሚንቀጠቀጥ ሰውነቷን ተቆጣጥራ ወደፊት ብትወረወርም እነፍሰሃ ካሉበት ጣሪያ ልትደርስ አልቻለችም:: ከሪም አንገቱን በመስኮት ብቅ አድርጐ ቁልቁል ተመለከተ:: ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ነው::

«ፈቲያ! ፈቲያ!» እያለ ተጣራ:: የልጅቷ ጩኸት ግን እየራቀ ሔዶ ጠፋ::

«ተከሰከሰች! ከተቆፈረው ጉድጓድ ገባች!» እያለ ጮኸ ከሪም:: የአፓርትማው በር ሲሰበር ከሪምም ፈጥኖ ከነፍሰሃ ጋር ተቀላቀለ:: ሦስቱም በጅምሩ ህንፃ ሌላኛው ጫፍ ለግንባታ በተዘረጋ ፍርግርግ ተንጠላጥለው አካባቢውን ሲለቁ «እዚህ ስር የወደቀ ሰው አለ:: የሚያቃስት ድምፅ ይሰማል!» የሚል ድምፅ ይሰማ ነበር:: ያ የሚወደው የፈቲያ ጥርስ ተሰባብሮና ሰውነቷም በደም ተበክሎ ታየው::

ከደበዘዘው የፈቲያ ምስል ላይ የሌላ ሴት መልክ ደግሞ ተደርቦ ታየው:: በደም የተለወሰችው የተጋደመች ሴት አፍጥጣ የምታየው መሰለው:: ፈትያን ትቶ እንደፈረጠጠው ሁሉ ይችም እንዳይሸሻት የምትማጠነው መሰለው::

«ሀበሻ ሳትሆን አትቀርም» አለ ከሪም በቁጭት::

ይኸኔ የመኪና ድምፅ ሰምታ አይኖቿን ጨፍና የነበረችው ልጅ ተናጋሪውን ለማየት አይኖቿን በቀስታ ገለጠች፡፡ አንድ ወጣት ቁልቁል ይመለከታታል፡፡

«ማን ነህ?» አለችው በሰለለ ድምፅ፡፡ ከሪም የሰማውን አላመነም፡፡ በርከክ ብሎ የልቧን ትርታ አዳመጠ፡፡ «ተርፋለች!» አለ በመጨረሻ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

ልጅቱ ከመስኮቱ ትይዩ በተዘረጋው አነስተኛ የእንጨት አልጋ ላይ ተንጋላለች። ገርበብ ያሉት አይኖቿ ረጥበዋል። የደረቁት ከንፈሮቿ በመጠኑ ከፈት ብለው ትምችም ያሉ ነጫጭ ጥርሶቿን ያሳያሉ። ግንባሯ ላይ የተቀመጠው በውሀ የራሰ ፎጣ መድረቅ ጀምሯል። ቤቱ ውስጥ የሰፈነው ፀጥታ አልፎ አልፎ በምታሰማው ቅዠት ይደፈርሳል። ከአልጋው ግርጌ ደረቅ ወንበር ላይ የተቀመጠው አርአያ ያለማቋረጥ የጉፈረ ፀጉሩን ይቆፍራል። ትናንሽ አይኖቹ ደፍርሰዋል። የበሰዙ ጥርሶቹ ስስ ጥቁር ከንፈሮቹን ይነካክሳሉ።

«ፎጣውን ጭመቅና ሌላ ውሀ ነክረህ አምጣው» አለ አርአያ ከራስጌ በኩል ከፍ ባለ ወንበር ላይ ለተቀመጠው ከሪም።

በቀዝቃዛ ውሃ የራሰው ፎጣ ግምባሯ ላይ ሲያርፍ ልጅቱ ባነነች። ዙሪያዋን ደጋግማ ቃኘች። ሁለት ወንዶች ከላይና ከታች አልጋዋን ከበው ተቀምጠዋል። መጋረጃው በመጠኑ ገለጥ ባለበት የመስኮት መስተዋት የገባችው የረፋዷ ፀሀይ ሙቀቷን ትለግሳለች። በመጠኑ የተከፈቱ አይኖችዋን ወዲያውኑ መልሳ ከደነቻቸው።

ብዙም ሳትቆይ ግን ከሪም ቅዝዝ ባሉ አይኖቹ እየተመለከታት ሣለ በሀይል ጮሃ አይኖችዋን ገለጠች። በጣም ታለከልካለች። የሚያስፈራ ፍጡር እንዳየ ህፃን የከሪምን እጆች ጨምድዳ ያዘች።

«አይዞሽ» ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ እንባዋ ኮለል አለ።
«ማነህ? አንተ ማነህ? የት ነው ያለሁት?» አለችው።

«አብዱል ከሪም እባላለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡ ያለሽው እኔ ቤት ነው፡፡»

«ለምን? ለ..ምን? ማ..ማን አመጣኝ?» አለች በአማርኛ፡፡

«ከፖሊስ መኪና ተወርውረሽ አገኘሁሽ፡፡»

በፀጥታ ሲያዳምጣቸው የነበረው አርአያ በረጅሙ ተንፍሶ፣ «ስምሽ ማነው? እ?» አላት፡፡

«ሀያት ...» ብላ ዝም አለች፡፡ ፍርሀቷ እንደገና አገረሸ፡፡ አጥብቃ ይዛው የነበረውን የከሪምን እጅ በቀስታ ለቀቀችና እጆችዋን እንሶላው ውስጥ ሸሸገች፡፡ በድካም የተሰበሩት የበሽተኛዋ አይኖች እንደገና ተከደኑ፡፡

«ሚስኪን፣ ድንጋጤው ሊለቃት አልቻለም» አለ አርአያ ወደወንበሩ እየተመለሰ፡፡

«ሌሊቱንም እንዲሁ ነው ያደረችው፡፡»

አርአያ ሲጋራውን ለኩሶ «ስንት ሰአት ላይ አገኘሀት?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ከምሽቱ አራት ሰአት ገደማ ይሆናል፡፡»

«የመኪናውን ታርጋ ለመያዝ አልሞከራችሁም?»

«መጀመሪያ እኛን አይተው የቆሙ ስለመሰለን ወደኋላ ለመመለስ እያቅማማን ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ከመኪናቸው ውስጥ የተወረወረ ነገር መኖሩን ስናስተውል ቆምን፡፡ እነሱም ወዲያው ተፈተለኩ፡፡»

«መከተል ነበረባችሁ፡፡»

«ያን ላለማድረግማ ምክንያት ነበረን፡፡ ሙሀደራት (ዕፅ) ይዘናል፣ በዚያ ላይ ድንጋጤም አለ፡፡»

«ዕፁን ካመጣልህ ከመጅድ ጋር ነበርክ አይደል?» አለ አርአያ በዚህ አጋጣሚ ከሪም ከመጅድ እፅ ማግኘቱን የማወቅ እድል ስለገጠመው ተደስቶ፡፡

«እምን፤» አለው ከሪም በቅሬታ። አርአያ ዕፅ ማግኘቱን ማወቅ አልነበረበትም። አርአያ በረጅሙ ተንፍሶ ሲጋራውን አትኩሮ እየተመለከተ፣ «ሴቶቻችን ላይ የሚፈፀመውን አረመኔያዊ ድርጊት እንዴት መቋቋም እንደምንችል አላውቅም» አለ በዝቅተኛ ድምፅ።

«ማን ይሰማናል ብለህ አርአያ? እንደምታየው የመኖሪያ ወረቀት የሌለው ቀርቶ ያለውም እንኳ አቤት የሚልበት የለም» አለ ከሪም በተነሳው ርዕስ የዕፁ ጉዳይ መታለፉ አስደስቶት።«እኛ ራሳችን የተሰማራንበትን ተግባር አታየውም! ለአራትና አምስት አመታት ያህል መጠጥ፣ ዕፅና ጫት ስናዘዋውር ኑረናል። ግማሾቻችን እህቶቻችንን እናቃጥራለን። በሙቶዎች የሚቆጠሩ የሪያል ኖቶቻቸውን እየመነዘሩ መጠጦቻችንን፣ ዕፆቻችንን፣ ሴቶቻችንን የሚገዙን ወንዶችም በገፍ ናቸው። ታዲያ...» ብሎ ከሪም ንግግሩን ሳይጨርስ፣ ሀያት «እናንተ አርኩሶች ልቀቁኝ! አይሆንም ልቀቁኝ!... አባዬኮ ሱቁን አላደራጀም ... እማማም ለሶስቱ ወንድሞችሽ የትምህርት ቤት ክፍያ ላኪ ብላኛለች ... ደብዳቤውን ላሳያችሁ እንዴ--? ... ልቀቁኝ! አይሆንም! ልቀቁኝ! አይሆንም! አ!አ!አ!» አለች።

ሀያት እየጮኸች ተነስታ አልጋዋ ላይ ኩርምት ብላ ተቀመጠችና አካባቢዋን ቃኘች። ሁለቱ ሰዎች አሁንም አጠገቧ አሉ። ህሊናዋን ስትገዛ እንደመደናገር ብሏት፣«እናንተ እነማን ናችሁ? እነዚያ ፖሊሶችስ የት ሔዱ?» ስትል ጠየቀች። አልመለሱላትም።

«ፖሊሶቹ የት ሔዱኮ ነው የምላችሁ?!» አጠገቧ በቆሙት ሰዎች ላይ አፈጠጠችባቸው። ጥያቄዋን ከመመለሳቸው በፊት ግን

የበሩ ደወል ተንቃጨለ:: ሀያት በፍጥነት አንሶላውን ተከናንባ ተጠቅልላ ተኛች::

የመጣው ፍስሃ ነበር:: ሰሚራንና አያዳን አስከትሏል:: በሩ እንደተከፈተ ተከታትለው ወደውስጥ ዘለቁ:: ሴቶቹ እንግዳዋን ለማወቅ ይሁን ለማስተዛዘን ጓጉተዋል:: አርአያም ምናልባት ሴቶቹን ስታገኝ ጭንቀቷ ሊቀላት ይችል ይሆናል የሚል ግምት ነበረው:: ወደአልጋው ተጠግቶ «ሀያት! ሀያት!» ሲል በለሆሳስ ተጣራ:: ሀያት በቀስታ ፊቷን ገለጠች:: አምስት ሰዎች አልጋዋን ከበው ቆመዋል:: አንድ በአንድ ቃኘቻቸው::

የአይዳ አይኖች ፈጠጡ:: አይኖቿን ተጠራጠረች:: በጭን ቅላትዋ የተቀረፀው ስዕል ውልብ አለባት:: አክስቷ አውደዓመትን ጠብቃ ወደወላጆችዋ ቤት ስትመጣ፣ በቀጫጭን እጆችዋ የአክስቷን ስጦታ ስትቀበል፣ የእድሜ እኩያዋ የሆነችውን ያክስቷን ልጅ እየጐተተች ድብብቆሽ ለመጫወት ስትሮጥ፣ ከሰፈር ልጆች ጋር ገመድ ሲዘሉ፣ የአክስቷ ልጅ ገመድ ጠልፏት ስትወድቅ፣ ሮጣ ስታነሳት፣ ስታባብላት፣ አዲሱ ልብሷ የቃመውን አፈር በፍጥነት ሲያራግፉ... ራሷን ወዘወዘች:: ብዥ ያለው ነገር እየጠራ የሄደ መሰላት በሽተኛዋን አትኩራ ተመለከተቻት:: እሷም እያየቻት ነበር:: የሁለቱ መፋጠጥ ግራ ያጋባቸው እንከሪም በዝምታ ተዋጡ:: አይዳ ድንገት የቆሙ ጓደኞቿን ገፈታትራ ወደአልጋው ተጠግታ ድንጋጤ ባሰለለው ድምፅ «ሀያት?!» ስትል ጮኸች::

እክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁለቱም የአየር ማቀዝቀዣዎች ተከፍተዋል:: ከሀያት አልጋ ትይዩ ከተዘረጋው የስፖንጅ ፍራሽ ጫፍ ላይ የተቀመጠችው ሰሚራ ከፊቷ የደረደረቻቸውን ሲኒዎች ወደፊት ገፋ አደረገቻቸው:: ከጋዝ ምድጃ ላይ ተጥዶ የምትደነፋውን

የሀበሻ ጀበና አውርዳ ከማቶቷ ላይ አስቀመጠች:: ከዚያም ከቁጣ መሸጫ ቤት የተገዛውን ትንሽ ከሰል ካቀጣጠለች በኋላ እጣን ጣል አደረገችበት:: ከሰሚራ በስተቀኝ ሶስቱ ወንዶች ተደርድረዋል:: አይዳ የአክስቷን ልጅ ሀያትን በሀዘን ተውጣ እያየቻት ከአልጋው አጠገብ ተቀምጣለች:: እየሞቀ የሚቀዘቅዘውን የሀያትን እግርም በረጃጅም ጣቶቿ ትደባብሳለች::

ቡናው ተቀዳ:: ፍስሃ ያጋባውን ስኒ ለሰሚራ እየሰጠ ወደከሪም ዞር ብሎ በቀስታ፣

«አይዳን ትላንት ምሽት ምን እንዳጋጠማት ታውቃለህ?» አለው::

«ምን ሆነች?» ሲል አርአያ ቀድሞ ጠየቀው::

«ሀፊዝ ዘንድ ሔዳ ...»::

«አዎን፣ እኔ ነበርኩ ከቤቷ ወደኔ ቤት ያመጣኋት» አለ አርአያ::

«ታዲያ ምን ተፈጠረ?» አለ ከሪም በጉጉት::

«ሰውየው ሳዲስት ሆኖ ተገኘ::»

ሁለቱ ወንዶች በመደነቅ ወደአይዳ ዞሩ:: አይዳ በቅሬታ ፈገግ ብላ፣ «እቆሳስሎ ላከኝ» አለቻቸው::

የከሪም ፊት ቅጭም አለ:: ሀያት ፊት ይህን ጉዳይ ማንሳቱ አደገኛ ስለመሰለው ሀያትን ተመለከታት:: እያፈራረቀች ትመለከታ ቸዋለች:: «በቃ ይህን ርዕስ ቀይሩ» አለ ጫን ብሎ:: አይዳ ይህን ስትሰማ አንዳች ነገር ጉሮሮዋን ያነቃት መሰላት::

ፍሰሃ ካጉነበሰበት ቀና አላለም:: የማታውን ጣፋጭ ቅፅበት አስታወሰ:: ከአይዳ የተሰጠው ምላሽ አላስከፋውም ነበር:: እልፎ

አልፎ በሚቆጠቁጣት ቁስል የተነሳ ፊቷን ታጥቁር እንጂ በፊገግታ ነበር ያዳመጠችው፡፡ ከንፈሯን ፈልጐም አልነፈገችውም፡፡

«ራት የሚሰራው ማነው?» የአርአያ ድምፅ ፍስሃን ርቆ ከሔደበት መለሰው፡፡

«ዛሬማ ሴቶቻችን አሉልን፡፡ እኔ ከሱፐር ማርኬት የዶሮ ስጋ አመጣለሁ፡፡ ፍሰሃ እኔኪሽ ሒድና የሀበሻ እንጀራ ግዛ» አለ ከሪም ከተቀመጠበት እየተነሳ፡፡

ምሽቱ ሞቃት ነበር፡፡ ማዕድቤት የገባችው ሰሚራ በሀሳብ ተውጣ ራት ለማዘጋጀት ተፍ፣ ተፍ ትላለች፡፡ የፍሰሃና የአይዳ የሌሊቱ ድርጊት፣ የሀፊዝ «ሳዲስትነት»፣ የአዲሷ ልጅና የአይዳ ዝምድና አስገርሟታል፡፡ «በርግጥ ሀፊዝ ሳዲስት ይሆን?» ስትል ራሷን ጠየቀች፡፡ እስከዛሬ ካወቀቻቸው ወንዶች ሳዲስት ሊባል የሚችል አንድም አላጋጠማትም፡፡ እስከዛሬ ያጋጠሟት ከልክ በላይ ወሲብን እየደጋገሙ ለመፈፀም ጠይቀዋት ፈቃደኛ ሳትሆንላቸው ስትቀር የሚደባደቡ ናቸው እንጂ ፍቅር ላይ እያሉ የመጨረሻውን እርካታ ለመጉንጨት ስቃይን የሚዘሩና ጭካኔን እየጋቱ የሚቧችሩ አይደሉም፡፡ በድሮው ፍቅረኛዋ ቅር የምትሰኘው በዚህ እንደነበር አስታወሰች፡፡ ፍቅር ላይ የሚቦጫጭቅ፣ የሚነክስና ጠንከር ያለ ክንድ የሚያሳርፍባት ወንድ ግን እስካሁን አላገኘችም፡፡ ሁሌም ግን ያን ጭንቀት ትፈልገዋለች፡፡ እዚህም አገር መጥታ ይሄ ፍላጐቷ አልረካም፡፡ በመሆኑም ተስፋ በመቁረጥ ላይ ነበረች፡፡ የሀፊዝን ታሪክ ስትሰማ ግን እየሞተ የነበረው ስሜቷ ተቀሰቀሰ፡፡ በስለታም ጥፍሮች መቦጫጨርና፣ በጥርሶች መነከስ አማራት፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

አርአያ ሰውነቱን ሊታጠብ ፎጣ ፍለጋ ወደመኝታ ክፍሉ ሲያመራ ስልኩ ተንጫረረ። በብስጭት ፀጉሩን እየቆፈረ አነሳው። ስልኩ የተጠሪው (ከፊሉ) አቡበከር ኢብኑማሊክን መሞት አረዳው። ከልቡ አዘነ። አቡበከር ባለውለታው ነበር፤ የከፋ ቀን ደራሹ። አቡበከር በልብ ካንሰር ሲሰቃይ እንደነበር ቢያውቅም እንዲህ በፍጥነት ይሞታል የሚል ግምት ግን ስላልነበረው አልጠየቀውም። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ራሱን አረጋግቶ አስር ሰአት ላይ በሚፈፀመው የቀብር ስነስርአት ለመገኘት ወደመካ ከነፈ።

ታላቁ የካዕባ መስጊድ ሀረም የሚገኝባት የመካ ከተማ በአመት ሶስት ጊዜ ከተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚመጡ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮችን ታስተናግዳለች። በየሰፈሩ ሳይቀር ተሰግስገው የሚገኙት የትናንሽ መስጊዶች ቁጥርም ከመኖሪያ ህንፃዎቹ ጋር የሚፎካከር ነው። በመንገዶቹ ዳርና ዳር አልፎ አልፎ የሚታዩት አሸዋማ ኮረብታዎችና ትላልቅ የድንጋይ ቋጥኞች ከህንፃዎቹ ግድግዳዎች ጋር ተጣብቀው ሲታዩ ከጊዜ በኋላ የበቀሉ ይመስላሉ።

አርአያ የመካን ከተማ መሀል ለመሀል ሰንጥቆ ከጀበል ኡመር ተራራ ጀርባ እሚገኘው አቡበከር ቤት ደረሰ። ጥቂት የሟች ዘመዶችና ወዳጆች ተሰብስበዋል። በመሃላቸው ፀጥታ ሰፍኗል። ድምፅ ሳታወጣ እንባዋን የምታፈሰው የሟች ባለቤት ከሴቶች ሳሎን በሶስት እህቶቿና በባሏ እናት ተከባ ተቀምጣለች።

አርአያ መኪናውን ደጅ አቁሞ ወደወንዶች ሳሎን ገባ። በቀብሩ ስነ-ስርአት ላይ እንዲገኙ የተጠሩት ሀያ ወንዶች ተሰባስበዋል። የአስር ሰአቱ ሰላት ሲቃረብ ወንዶቹ አስከሬኑን አጅበው ወደሀረም ሔዱ። ከሰላት በኋላ ለአስከሬኑ የሚደረገው የፀሎትና የስግደት ስነስርአት ተፈፅሞ እንዳበቃ ጉዞ ወደመቃብሩ ስፍራ ተጀመረ።

አርአያ የአቡበክርን ታናሽ ወንድም አትኩሮ ተመለከተው። ለሟች ወንድሙ በተሰማው ሀዘን የዳመነ ፊቱን ወደመሬት አቀርቅሮ ከአስከሬኑ ኋላ በዝግታ ይጓዛል። አስከሬኑን ያጀቡት ሰዎች አቀርቅረው በቀስታ «አላሁ አክበር! ላኢላህ ኢለላህ!» ይላሉ። የአስከሬኑን አጃቢዎች ብዛት ከሟቹ ሀብት ጋር አነፃፀረ። እንደሀብቱ ቢሆን አቡበክርን ቁጥር ስፍር የሌለው ሰው ባጀበው ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን እንዲህ ያለው ሀብታም ሲሞት አገር ነቅሎ ነው ቀብር የሚወጣው። እዚህ ግን ድንኳን ጥሎ እስከሰልስት ማልቀስ የለም። ወዳጅ ዘመድ የማፅናኛው ጊዜም አጭር ነው።

*　　　　*　　　　*

አርአያ መጀመሪያ ወደመካ የመጣው በኡምራ ፀሎት አሳቦ ነበር። ነገር ግን ወዲያው ሥራ ማግኘት አልቻለም። ከአካባቢው ባህል መላመድና፣ ከመሰሎቹ ጋር መተዋወቅ ነበረበት። ባጭር ጊዜ ከሰባት ያላነሱ ስደተኛ ጓደኞችን አፈራ። ችግሩ ጠቀም ያለ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ያለማግኘት ነበር። ለጊዜው ግን ከታላቁ የሀረም መስጊድ ምድር ቤት ውስጥ ከሚገኘው የማዑዘምዘም የተፈጥሮ ውሃ እየቀዳ መሸጥ ይችላል። ሆኖም አርአያ ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ

ስላልነበረው ከፖሊስ ጋር ድብብቆሽ የመጫወት ጥሩ ችሎታ ያስፈልገዋል:: በዚህ ብዙም አልተቸገረም::

ከሀረም በስተምዕራብ ከሚገኘው የጀበል ዑመር ተራራ ላይ ካሉት ያረጁ ህንፃዎች ግርጌ ከሚገኝ ባለ አራት ፎቅ ህንፃ ውስጥ ከሰባት ጓደኞቹ ጋር ለአንድ አመት ያህል ቆየ:: በዚሁ አጋጣሚ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ከሚኖሩ ሶስት ሱዳናውያን ጋር ተግባባ:: በተለይ ሙአዝ ከሚባለው ሱዳናዊ ጋር ኮከባቸው ገጠመ:: አብረው ሲጫወቱ ማምሸት፣ ራት ወይም ምሳ አብረው መብላት አዘወተሩ:: ቀስ በቀስም የውስጣቸውን ያለስጋት መነጋገር ቻሉ::

አንድ ምሽት ሦስቱ ሱዳናውያን እርእያን ቤታቸው ራት ጋበዙት:: የሱዳናውያኑ ቤት እንደአካባቢው ህንፃዎች ሁሉ ግድግዳው የተላላጠና በኮርኒሱ ላይ እንሽላሊት የሚንሸራሸርበት ነው:: ሳሎኑ ውስጥ አንድ የስፖንጅ ፍራሽ፣ ሁለት የተቀዳደዱና ከልክ በላይ የቆሸሹ የሶፋ ወንበሮች እንዲሁም ከእንጨት የተሰራ አነስተኛ የቡና ማስቀመጫ ጠረጴዛ ብቻ ናቸው የሚታዩት:: ወለሉ ላይ የተነጠፈው ደማቅ አረንጓዴ ምንጣፍ የተመላለጠና ወፋፍራም ክሮቹ የሚታዩ ናቸው:: ራት ተበላ:: ጨዋታውም ተሟሟቀ:: ከዚያም ሙአዝ፣ «ለመሽሎክሎክ ታስባለህ?» አለው::

«ምን ማለት ነው?» እርእያ ግራ ተጋባ::

«ሙሀጀራት ታውቃለህ?»

«እኛ እያዘዋወርን ነው» አለው ሙአዝ እንደዋዛ::

«አልገባኝም»አለ እርእያ ዝም ብለው የተቀመጡትን ሁለት ሱዳናውያን በጥርጣሬ እየተመለከታቸው::

«የሚያስፈራ ነገር አይኖርም:: እንኳን መካ ውስጥ፣ ፖሊስና ሙጠውዕ እንደአሸን በፈሉበት በጅዳ ከተማ እንኳ ከዚህ የበለጠ ህገወጥ ስራ ይፈፀማል::

«ገንዘቡን ለዚህ ተግባር የሚያውል ሰውስ የሚገኝ ይመስልሀል?» አለ አርአያ ወደሙአዝ ጠጋ እያለ::

«አትጠራጠር » አለውና እንዲከተለው ጋበዘው:: አርአያ ሙአዝን ተከትሎ የቆሸሸውን ኮሪደር አቋርጠው ማዕድቤት ገቡ::

ንፅህና የጐደለው አነስተኛ ፍሪጅ ከበሩ ትይዩ ቆሟል:: የዕቃ ማጠቢያው ገንዳ ያለማቋረጥ በሚንጠባጠብበት ሙቅ የቧንቧ ውሀ ቀለሙ ተላልጦ ዝጓል:: በረሮዎች በሚንሸራሸሩበት ግድግዳ ላይ የተጣበቁትን ባለአበባ ሸክላዎች የሚያፀዳቸው በማጣታቸው ወይበዋል::

ሙአዝ አሮጌውን ፍሪጅ ከፈተና የታችኛውን መሳቢያ ጐትቶ የታሸገ ላስቲክ አወጣ:: በጥርሱ ቀዳዳ ካበጀ በኋላም የግራ መዳፉን ዘርግቶ ትንሽ ዱቄት አፈሰሰበት::

«ይህ ደርቆ የተወቀጠ ጫት ነው» አለ መዳፉን ወደአርአያ አስጠግቶ:: አርአያ መገረሙ እንዳይታወቅበት ፈጠን ብሎ ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ:: ሙአዝ ለረጅም ጊዜ አርአያን ለመመልመል የነበረው እቅድ እንደተሳካለት አረጋገጠ:: ሀበሾች በፍጥነታቸው፣ በትጋታቸውና በታማኝነታቸው በሳዑዲዎች ዘንድ እንደሚወደዱ እነሙአዝ ያውቃሉ::

ሳምንቱ መጨረሻ ላይ ከሶስቱ ሱዳናውያን ጋር መኖር ጀመረ:: በወር አንድ ሺ ሪያል እየከፈሉ ሊኖሩበት የመረጡት አፓርትማ ከህንፃው አራተኛ ፎቅ ላይ ይገኛል:: ከሳሎኑ ሁለት ሰፋፊ መስኮቶች ባሻገር አኪሩ ሉሱስ ሰፈርን የሚያደምቁ ትላልቅ ቋጥኞች ይታያሉ:: አንድም አረንጓዴ ተክል የማይታይበትን ኮረብታ ፀሀይዋ ስትዳስሰው ያብረቀርቃል:: ወደመዲና የሚወስደው ብቸኛ

አውራ መንገድም ከተራራው በስተግራ ጥቁር ዘንዶ ይመስል ተዘርግቷል፡፡

አርአያ አልፎ አልፎ በሙአዝ ገንዘብ ወዳድነት ቢበሳጭም ከሱዳናውያኑ ጋር መስራቱን ወዶታል፡፡ እየተሽሎከሎከ ብዙ ገንዘብ ማግኘቱንና ከአደጋ በዘዴ ማምለጡን ተላመደው፡፡ ደንበኞቻቸው ከቀን ወደቀን እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡

አርአያ ያለአረፍት ለአንድ አመት ያህል ከሰራ በኋላ ህጋዊ የመኖሪያ ፍቃድ ማውጣት እንዳለበት አመነ፡፡ እናም ተጠሪ የሚሆነውን ሳዑዲያዊ ያፈላልግ ገባ፡፡ የመጠጥ ደንበኛውንና የቤንዚን ማደያ ባለቤት የሆነውን አቡበከርን አነጋገረው፡፡ ያለማመንታት ፈቃደኛነቱን ገለፀለት፡፡ አስራ ሁለት ሺ ሪያሉን ቆጥሮ በህጋዊ መንገድ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመመለስ ወደሀገር ቤት ለመሔድ ዝግጅት ጀመረ፡፡

ሆኖም በመሃሉ ያልጠበቀው ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ቤተመንግስቱን በስተግራ ትቶ ወደመዲና በሚወስደው መንገድ ዳር በአሜሪካውያን መኖሪያ ላይ የተቃጣ የዝርፊያ ሙከራ ከሸፎ አካባቢው እየታሰሰ ነበር፡፡

አርአያ ከአቡበከር ጋር ወደተቃጠረበት መኖሪያ ቤቱ ሲጓዝ ከፍተሻው መሀል ተሰነቀረ፡፡ በአራተኛው ረድፍ ላይ ከቆመችው መኪና ውስጥ ማምለጥ ነበረበት፡፡ ምክንያቱም የያዘው ሀሰተኛ መታወቂያ ነው፡፡ ከተያዘ ለአመታት ይታሰራል፡፡ ለአቡበከር ፈጥኖ ስልክ መደወል አለበት፡፡ የመኪናውን በር በቀስታ ከፍቶ በቆሙት መኪኖች መሀል እየተሽሎከለከ ከፍተሻው ለመራቅ ሞከረ፡፡

ሆኖም አንዱ ፖሊስ አይቶት ኖሮ ከቀንድ የተሰራች ቆመጡን በእልህ እያወዛወዘ ተከተለው:: አርአያ ሀረም መስጊድ ትይዩ ካሉት የህዝብ ስልኮች ወደአንዱ ተጠግቶ ቁጥሮቹን መታ:: ከአንድ ጥሪ በኋላ የወዲያኛው ጫፍ ምላሽ ሰጠው::

«ሀሎ? አቡበከር ኢብኑማሊክ» አለ ድምፁ::

«አቡበከር፣ አሰላም አለይኩም? ነቢል ነኝ» አለ አርአያ ወደሳዑዲ አረቢያ ሲገባ የተጠቀመበትን ስሙን ጣደፍ ብሎ በመጥራት::

«ወአለይኩም አሰላም ....» የሰውየው አፀፋ ሙሉ በሙሉ ሳይሰማ አንድ እጅ የአርአያን ትከሻ ተሻግሮ የስልክ እጀታ ማስቀመጫውን ተጫነ:: ስልኩ ተዘጋ:: አርአያ በጨረፍታ የተመለከተው እንግዳ እጅ የፖሊስ መሆኑን አስተዋለ:: በቀስታ ወደኋላው ሲዞር መካከለኛ ቁመት ያለው መጣጣ ፖሊስ በእርካታ ሲስቅበት ተመለከተ::

«የመኖሪያ ፈቃድ አለህ?» አርአያ ራሱን ለማረጋጋት እየሞከረ ኪሱን ይበረብር ገባ:: እጆቹ ይንቀጠቀጣሉ:: ከሸሚዙ የደረት ኪስ ትክክለኛ የሚመስል የመኖሪያ ፈቃድ መዝዞ አወጣና ወደፖሊሱ ዘረጋ::

«ጠይብ እንሒድ!» አለ ፖሊሱ የአርአያን እጅ ጥርቅም አድርጐ ይዞ ወደፍተሻው እየመራው:: «ከመኪናህ ሾልከህ የወጣህበትን ምክንያት ታስረዳናለህ» አለው::

«እሺ፣ አንዴ ወደተጠሪዬ እንድደውል ፍቀድልኝ?» ሲል ፖሊሱን ለመነው:: ፈቀደለት:: የስልኩን ምልልስ ሲጨርስ የያዘው የመኖሪያ ወረቀት የተጭበረበረ መሆኑ ተረጋግጧል:: ፖሊሶቹ የዱላ ውርጅብኛቸውን አዘነቡት:: ጉዳዩን ለበላይ አካላት አስታውቀው

ቤቱን የማስፈተሽ ትዕዛዝ እንዲተላለፍ ሲሯሯጡ አቡበከር ደረሰ። በበታች ሹማምንት እጅ የነበረውን የአርአያ ጉዳይ ተዳፍኖ የሚቀርበትን መንገድ አመቻቸ።

አርአያ ሀገሩ አንድ ወር ያህል ቆይቶ ሲመለስ ጓደኞቹን በሰላም እንደሚያገኛቸው ተስፋ አድርጎ ነበር። ግን እንዳሰበው አልሆነም። ሁለቱ ጓደኞቹ በመጠጥ ጦስ ተቀልተዋል። በህይወት የተረፈው ሙአዝ ብቻ ነበር። እሱም ቢሆን በእጻ ተዘፍቋል።

ስለዚህ የመካን ከተማ ለቀው ጅዳ ገቡ። በዚያም መጠጥ ከሚያቀብሏቸው ሦስት ናይጀርያውያን ጋር ተገናኙ። ብዙም ሳይቆዩ ናይጀርያውያኑ ታፈሱ።

ሙአዝ ተስፋ በመቁረጡ ጠጪ ሆኑ፡ መካ ከነበሩት ወዳጆቹ የተበደረውን ገንዘብ ሳይመልስ ሌላ ጨመረበት። ይኸኔ አርአያ ምልመላ እንዲያካሂድ ሀሳብ አቀረበለት። ሙአዝም በሀሳቡ ስለተስማማ አንድ የህንፃ ሥራ ፕሮጀክት ውስጥ ተቀጠረ። ከስድስት ወራት በኋላም ከሪምን መለመለ። ከዚያ በኋላ እንቅስቃሴአቸው መልክ እየያዘ፣ ተስፋቸው እየለመለመ ይሄድ ጀመረ።

በመጨረሻ ከኢኔኪሽ የእንጀራ መሸጫ ማዶ ከሚገኘው በተለምዶ የሀበሻ ምግብ ቤት እየተባለ ከሚጠራው ሳባ ሬስቶራንት ብርቱ ሰው መለመሉ። አራቱ ጓደኛሞች በዚህ መልኩ አራት አመታት በሰላም አሳለፉ። ሆኖም ሙአዝን አልጠግብ ባይነቱ አልለቅ ስላለው ከሪምና ፍስሃን ይጫናቸዋል። አርአያ ይህን ድርጊቱን ባይወድለትም የጥቅሙ ተካፋይ ስለሆነ ዝምታን መርጧል።

## ምዕራፍ አስር

ሶስቱ ሴቶች የተከራዩት ሊሞዚን ታክሲ በሁለተኛው ተደራቢ አስፋልት ወደቁለይል ይፈሳል:: ሊሞዚኑ የመከረናን መስመር ትቶ ከስረኛው አስፋልት ከሚያደርሰው መንገድ ለደቂቃዎች ተሽከርክሮ ወደግራ ሲታጠፍ ቁለይል ብቅ አለች:: ታክሲው ለሶስት ደቂቃ ተጉዞ በስተግራ የሚገኘውን ሙስተሽፋል ማዕሩፍ ክሊኒክ ከማለፉ አይዳ፣ «በስ!» ብላ አስቆመችው::

ሰሚራ በመገረም አይዳን አየቻት:: አይዳ ግን ፈጥና «ይበቃናል» አለችና የኋለኛውን በር ከፍታ ወረደች::

ቁለይል እንደወትሮዋ ነች:: በህፃናት ጫጫታና ዝላይ ደርታለች:: በጠራው ሰማይ ላይ የተኮፈሰችው ፀሀይ ከወትሮው በተለየ ዝቅ ያለች ይመስል ትለበልባለች:: የሀጅ ወር መቃረቡን የሚጠቁመው ወላፈን ይጋረፋል:: ወበቁን ለመቋቋምም በየህንፃው የተገጠሙ ያረጁ የአየር ማቀዝቀዣዎች ያጠራቀሙትን ውሀ ወደ ውጭ ያንጠባጥባሉ:: ሰሚራ ገራራው ፀሀይ ስላቃጠላት በቅሬታ፣

«ትንሽ ወደመንደሩ ገባ ብለን ብንወርድ ምን ነበረበት?!» አለች ፊቷን አጨፍግጋ::

«ባለታክሲዎች አደገኞች መሆናቸውን እስከዛሬ አታውቂም?» ስትል አይዳ መልሳ ጠየቀቻት::

«ያልሽው አልገባኝም» አለች ሀያት::

አይዳ የሀያትን እጅ እየጨመቀች «ሀገወጦች መሆናችንን ስለማንገምቱ ተከታትለው አድራሻችንን ያዩና ባሰኛቸው ቀን ሊደፍሩን ይመጣሉ።»

ሦስቱም በዝምታና በስጋት ጠባቡን መተላለፊያ አቋርጠው ተዘግቶ ያደረውን ቤት ከፍተው ዘለቁ።

ሀያት መተጣጠብ ስትጀምር የአስር ሰዓቱ ሰላት ጥሪ ከመስጊዶች ሰገነት ተሰማ። ሰሚራ አዳር ልትሄድ ተቻኩላለች። ለሁለቱ ሴቶች የገዛችውን መኮረኒና ሰላጣ ማዕድቤት አስቀምጣ የሀያትን ከመታጠቢያ ቤት መውጣት በትዕግስት እየተጠባበቀች ነው። ሌሊቱን አብሯት የሚያሳልፈውን ሰው ፍሰሃ ይሰጥሻል ካላት ገንዘብ በላይ ልትጠይቀው ወስናለች።

ሀያት የአይዳን ሙሉ ቱታ ለብሣ ከውስጠኛው ክፍል በተዘረጋላት ፍራሽ ላይ ተኛች። በሰባተኛው ቻነል ላይ የተከፈተው ቴሌቪዥን «ቡሲ» የተሰኘውን በግብፃውያን ተዋንያን የተሰራ ሳምንታዊ የፍቅር ፊልም ያስተላልፋል።

«ቤታችንን እንደምትወጂው ተስፋ አደርጋለሁ» አለች አይዳ ከሀያት ትይዩ ተመቻችታ እየተቀመጠች።

«እንዴታ» አለች ሀያት ፈገግ ብላ።

«ከአሰሪዎችሽ ቤት ጋር ስታነፃፅሪው ግን አያረካሽም» ብላ አይዳም ፈገግ አለች።

«እንደስፖንጅ ከሚደላ የወለል ምንጣፋቸው፣ በእምነበረድ ከነደደ ግድግዳቸውና በድሎት እቃ ከተሞላ ሳሎናቸው ውስጥ ሰብዓዊነትን አላገኘሁብትም» አለች ሀያት እየተንገፈገፈች።

ገርበብ ያለው በር ተከፍቶ ሰሚራ ወደውስጥ ገባች:: ከጉልበቷ በላይ የቀረውና ሰውነቷ ላይ የተጣበቀው ነጭ ጂንስ ከጥቁር ሹራቧ ጋር ተጣጥሟል:: በአጭር የተቆረጠው ለስላሳ ፀጉሯ ከግንባሯ አካባቢ በዝቶ ወደፊት ሾጠጥ ብሏል:: ፈካ ያለ ቡናማ ቀለም የተቀባው ከንፈሯ የጥርሶችዋን ንጣት አጉልቶታል:: በእጇ ያንጠለጠለችውን ጥቁር መደረቢያ አጠለቀችና ፀጉሯን በሻሽ ሸፈነች:: የአይነ ርግቡን ቁልፍ እየፈታች «አይዳ? .. አርአያ ከሁለት ደቂቃ በኋላ ይደርሳል ብዬ እገምታለሁ:: ለራት የሚሆናችሁ ምግብ ማዕድቤት አለልሽ» አለችና ሰሚራ በአይነ ርግቧ ተጋረደች::

«መሔጃሽ ደረሰ እንዴ?» አለች አይዳ ሰአቷን እያየች::

«አዎን፣ ከመግሪብ ሰላት በፊት ነው መድረስ ያለብኝ» አለችና ወደሀያት ዞራ፣

«ቻዎ ሀያትን? ነገ እመጣለሁ» ብላ እጇን ለሰላምታ ዘረጋችላት::

«ወዴት ነው?» የሀያትን ጥያቄ ተከትሎ የበሩ ደወል ተሰማ::ሰሚራ የሀያትን ጥያቄ ሳትመልስ እየተጣደፈች ሔደች::

«በምሽት የት ነው የምትሄደው?» አለች ሀያት ጥቂት ዝም ብላ ከቆየች በኋላ::

«ስራ!» የአይዳን መልስ ምፀት ተጭኖት ነበር:: «መቼም ሆስፒታል ወይም ፋብሪካ ውስጥ አለመቀጠሯን መገመት አያቅትሽም» አለች አይዳ ፀጉሯን በፍጥነት እያፍተለተለች::

«የምትዪው አልገባኝም?» አለች ሀያት የሚርበተበቱ እጆችዋን ሰብሰብ አድርጋ ግድግዳውን እየተደገፈች::

«ሥራችን ሽርሙጥና ነው» አለቻት አይዳ ለዘብ ባለ አነጋገር::

«ሽርሙጥና?!» ሀያት በድንጋጤ ጮኸች::

«አይዞሽ አትደንግጪ፤ አስልቺውን የግርድና ኑሮ እንደሆነ እስኪያቅለሽልሽን ተጋትረነዋል፡፡ ነገር ግን የተመኘነውን ገንዘብ ሊያስገኝልን አልቻለም፡፡ ታዲያ ምን እናድርግ ትያለሽ?» አለች አይዳ ረጋ ብላ፡፡

«ግን ለምን? ለምን አይዳ? ካልሆነ ወደሀገር መመለስ እየተቻለ? አባትሽ ላንቺ አንሰው ነው?»

«ሀያት ከቤተሰብ ጋር እስከመቼ ይኖራል? አንድ እድሜ ላይ ስትደርሽኮ ራስሽን መቻል አለብሽ፡፡ አንድ ጊዜ ከወጣሽ ደግሞ ወደኋላ መመለሱ መፍትሔ አይሆንም፡፡ ሁሉንም እንደአመጣጡ ተጋፍጦ ሰው መሆን ነው፡፡»

ሀያት አስቸጋሪውን ፈተና ያለፈች መስሏት ነበር፡፡ አሁን ግን ሌላ መሰናክል እንደሚጠብቃት ታወቃት፡፡

«በርግጥ ይገፍሽ ከመምጣቴ በፊት ስለማንነታችን ልነግርሽ በተገባ ነበር፡፡ ምናልባት ከሪም ቤት መቅረቱን ትመርጪ ነበር፡፡ እዛም ግን ከዚህ የከፋ ስጋት አለ» አለች አይዳ ሀያትን እያጠናቻት፡፡

«እዚያ ደግሞ ምን አለ?»

«መጠጥና ዕፅ አለ፡፡ ስለዚህም ከነከሪም ቤት የኛን መምረጥሽ ለክፉ አይሰጥሽም፡፡»

ሀያትን ፍርሀት እስከ አጥንቷ ዘልቆ እያንዘፈዘፋት ሳታስበው እንባዋ ተዝረበረበ፡፡

አይዳ አላፅናናቻትም በልቧ «ነገ ለሚጠብቅሽ መከራ፣ በቡጢ ለሚበልዘው ጉንጭሽ፣ ለሚሰባበረው ጥርስሽ፣ እነፍለዛ ለሚቸበችቡት ገላሽ አልቅሺ፤እስኪበቃሽ በእንባሽ ታጠቢ፡፡ እሾሃማው

ጠርቅ ለቧጠጣት እህትሽ እንባሽ ይንጠብጠብ፡፡ ከእኩለ ሌሊት እስከ ንጋት ስትደክሚ ላለቀው ጠዝሸስ ማልቀስ ይነስሽ? በግርድና ዘመንሽ የጌታሽን እንጉርጉሮ ስትሰሚ የሀገርሽን አንቺሆዬ በልብሽ አንጕራጉረሻል፡፡ የአሳዳሪዎችሽ የሩዝ ሽታ በእናትሽ የዶሮ ወጥ መአዛ ትዝታ አወዶሻል፡፡ የእመቤትሽን ጨርቅ ለማጠብ ውሃ ስትቀጂ የቧንቧው እንፋሎት የአባይን ጭስ አሳይቶሻል፡፡ እናም በደንብ አልቅሺ፡፡ ለኔም፣ ላንቺም ለሁላችንም አዘቅዝቀሽ ልበሺ» ትላለች፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ

«ፍሰሃ፣ ለነአይዳ ኪራይ መክፈልን ምን አመጣው?» ሲል ከሪም እንደማፌዝ እያለ ጠየቀ::

«ለምን ትጠይቀኛለህ አልልህም:: ግን ... » ፍሰሃ ከሪምን ቀና ብሎ ለማየት ያፈረ ይመስል አንገቱን ደፍቶ ፀጉሩን ማከክ ጀመረ::

«ይህን አጉል ቸርነት ትተህ ለራስህ ህይወት የምትደክም ነበር የሚመስለኝ» አለ ከሪም በተግሳፅ::

«አሁንምኮ ወደድሮው ህይወቴ የተመለስኩበት ሁኔታ አልተፈጠረም::»

«ዛሬም ያንኑ ነው እየፈፀምክ ያለኸው» አለ ከሪም በቁጣ::

«አይደለም ከሪም ... የአሁኑ ትንሽ የተለየ ነው:: አይዳን እወዳታለሁ:: ይህን ታውቃለህ::»

«ይህ ለኔ አዲስ አይደለም:: ግን አይዳ ላንተ ያላት ስሜት አንተ እንደምትገምተው ባይሆንስ? ለኔ በነበራት ስሜት ቢበረዝስ?»

«ምን ለማለት ነው?» አለ ፍሰሃ:: በከሪም ሽርደዳ ተቆጥቶ ሲጮህ የሰነዘረው ጡጫ አጠገቡ የነበረውን ኮመዲኖ ሰነጠቀው:: የነበልባል ጦር ባልደረባ የነበረው ፍሰሃ በሰሜን ኢትዮጵያ ይካሄድ በነበረው ጦርነት ተማርኮ ለጥቂት ወራት አዲስ አበባ ተሸሽጐ ከቆየ በኋላ ነው ወደሳዑዲ አረቢያ የተሻገረው:: እንዲያም ሆኖ ግን ሃይል

ከመጠቀም የተቆጠበ ስለሆነ በውትድርና ዓለም ውስጥ ማለፉን ከከሪም በስተቀር የሚያውቅ የለም::

ስለዚህ በአሁኑ ስሜቱ ከሪም ተደናገጠ:: ለፍስሃ መንገር የሌለበትን ምስጢር ዘርግፎታል:: አይዳ ከዚህ ቀደም እሱን ትወደው እንደነበረ ከሁለቱ በስተቀር የሚያውቅ ማንም አልነበረም::

«ፊሽ?! አይዳ ምርጫህ ትሆናለች ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር» አለ ረጋ ብሎ:: የፍስሃ አይኖች ደፈረሱ:: ንዴት፣ እልህ፣ ቁጭት ተናነቀው:: ማንም ሰው አይዳን በዚህ አይነት መልኩ እንዲገምትበት አይፈለግም:: አይዳ ስደተኛ በመሆኑዋና በችግር ምክንያት ክብሯንና ስብዕናዋን በሚጎዳ የዝሙት ተግባር ብትሰማራም ባግባቡ የሚይዛት ወንድ ብታገኝ ጨዋ ልጅ ነበረች:: ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳ:: «ከሪም ሁለተኛ እንዲህ እንዳትለኝ፤ ለአመታት በልቤ ኖራለች በፍቅር እክሳታለሁ:: በቃ ከእንግዲህ ስለአይዳ እንድታነሳብኝ አልፈልግም» አለው::

«ፊሽ በጣም ይቅርታ፤ ይህን ያህል ስሜትህን የምነካው አልመሰለኝም ነበር:: የኔ ጭንቀት ገንዘብህን እንዳታባክን ነው» አለ ረጋ ባለ ድምፅ::

«ለሱ አትቸገር» አለው ባጭሩ::

* * *

ፍስሃ በአነስተኛ የማዳበሪያ ከረጢት ውስጥ በዱቄት ወረቀቶች የታሸገ ዕፅ ይዞ የመግሪብ ሰላት (ስግደት) እንዳበቃ አፓርታማውን ለቀቀ:: የለበሰው ጀለቢያ ክፉኛ ወይቧል:: እናቱ ላይ ጣል ያደረገው ነጭ ሻሽ ሀይማኖቱን አክባሪ ጥቁር አረብ

አስመስሎታል። በዓይኑ ሲሞዚን ታክሲዎችን ያማትራል። ድንገት ከወዲያኛው አስፋልት ጠርዝ አራት ፖሊሶችን የጫነች ክፍት መኪና አየ። ፖሊሶቹ ቅኝት ላይ ነበሩ። ፍሰሃ ተቁነጠነጠ። ወደ ፖሊሶቹ ሲያማትር ከሾፌሩ ጋር አይን ለአይን ተጋጩ። ፖሊሶቹን የጫነችው ጂፕም ፍጥነቷን ጨምራ ወደታች ወረደች። ከተወሰነ ርቀት በኋላ ሰፊውን አስፋልት ከሚለየው ረጅም የአፈር ደሴት መሀል ስትደርስ አቅጣጫዋን ለመቀየር ስትጠመዘዝ ፍሰሃ አስፋልቱን አቋርጦ ፖሊሶቹ ወደነበሩበት ጠርዝ ተሻገረ።

አቅጣጫዋን የቀየረችው ጂፕ ፍሰሃ ቀድሞ ወደነበረበት የአውቶብስ ፌርማታ አቀናች። እሱን እያደኑት እንደሆነ ገባው። ፖሊሶቹ ተመልሰው እሱ ወዳለበት ጠርዝ እስኪመጡ ታክሲ እንደማያጣ ገመተ። ነገር ግን በአካባቢው ታክሲ አልታይ አለው። የፖሊሶቹ መኪና ተጠምዝዞ ቀድሞ ወደነበረበት ሥፍራ ተመለሰ። ይኸኔ መኪናቸውን ጥግ አስይዘው አንደኛው ፖሊስ ከመኪናዋ ወረደ። መሣሪያ ያልታጠቀው ፖሊስ አናቱ ላይ የደፋትን ቆብ ኪሱ ከቶ፣ በሱቆቹ በሮችና በአስፋልቱ ዳር በሚተላለፉት ሰዎች እየተከለለ ይገሰግሳል። ፍሰሃ ባያየውም ትከተለው የነበረችው ጅፕ መቆሟን ስላየ ፍርሀት ወረረው።

በርካታ ምግብ ቤቶች፣ ሱቆች፣ የፍራፍሬ መሸጫ ሱፐር ማርኬቶች፣ የገዛ ወኪሎች ወደሚገኙበት ጠርዝ ተጠግቶ ቆመ። «ክፍት ነው» የሚል የአረብኛ ፅሁፍ ተለጥፎበት የተዘጋ ፋርማሲ አጠገብ ሲደርስ ወደኋላው ተመለከተ። ሁለት አባያ የደረቡ ሴቶችና ሁለት ወንዶች አየ። ከጀርባቸው የፖሊስ መለያ ልብስ ያጠለቀ አረብ በጥድፊያ ወደሱ ሲገሰግስ ተመለከተ። ፈጥኖ የፋርማሲውን ደረጃ በሩጫ ወጥቶ ወደውስጥ ዘለቀ።

ፋርማሲው ይቀዘቅዛል:: ጥቁር ቆዳ ከተለበጠ ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው የኮምፒዩተሩን ቁልፎች ይነካካል:: ፍሰሃ ሲገባ ቀና አለ:: «ነአም? (አቤት?)» አለው::

«ከሬም ዲያና?» አለ ፍሰሃ ድንገት ከመስተዋቱ ውስጥ ያስተዋለውን ቅባት እየጠቆመ:: አረቡ ግራ ተጋብቶ ተመለከተው::

«ለኔ ሳይሆን ለባለቤቴ ነው» አለ የአረቡን ስሜት የተረዳው ፍሰሃ:: ወዲያውኑ የፋርማሲው የመስተዋት በር በሀይል ተበረገደ:: ቆቡን በእጁ ያንጠለጠለ ፖሊስ ወደውስጥ ገባ:: ያስከልካል:: አይኖቹ እሳት ይተፋሉ:: ወደፍሰሃ ተንደርድሮ፣

«የመኖሪያ ፈቃድ አለህ?» ሲል ጠየቀው::

«የለኝም!»

«የያዝከውስ ምንድነው?» ሲል ጠየቀ ፖሊሱ ወደማዳበሪያው እየመለከተ::

«ዱቄት» አለ ፍሰሃ::

«አሳየኝ!»

ፍሰሃ ማዳበሪያውን ከፍ አድርጐ ባንኮኒው ላይ ካኖረ በኋላ «ዱቄት» የሚል የአረብኛ ፅሁፍ ያለበት እሽግ አውጥቶ አቀበለው:: ፖሊሱ እሽጉን ተቀብሎ በጥርሱ ለመቅደድ ይታገል ገባ:: እሽጉ የመተርተር ድምፅ እንዳሰማም የፍሰሃ ሀይለኛ ቡጢ ከፖሊሱ አፍንጫ ላይ አረፈ:: ሰውየው የነከሰውን እሽግ በቁሙ ለቀቀው:: ከአፍንጫው ደም ይፈልቃል:: ቀና ሲል ሌላ ቡጢ አረፈበት:: ተንገዳግዶ ወደቀ::

ፍሰሃ ማዳበሪያውን አንስቶ ወደበሩ ሲያመራ ግን የፋርማሲው ባለቤት ተከተለው:: ፍሰሃ ጊዜ አላጠፋም:: ኮምፒዩተሩ ጉን የተቀመጠውን የአየር ማራገቢያ ሽክርክሪት አንስቶ ወረወረበት::

ጕንበስ ሲል ሽክርክሪቱ ጀርባው ላይ አረፈ:: ይኼኔ «አባክህ ተወኝ ፤ፈጣሪን ፍራ!» እያለ መለማመጥ ጀመረ:: ፍሰሃ ልመናውን አልሰማም:: ኮምፒዩተሩን ወደሰውዬው አንሸራተተው:: እየተንኳኳ ወገቡን ገጭቶ ወለሉ ላይ ተከሰከሰ::

«ያ ወይሲ! ያ ወይሲ! ይክርብ ቤተክ! ይንአል አለይክ!» እያለ ወንበር ስር ተወሸቀ:: ፍሰሃ በፍጥነት የስልኩን ገመድ በጥሶ ቀፎውን ወለሉ ላይ ከሰከሰው:: ከዚያም ማዳበሪያውን አንጠልጥሎ ወጣ:: ወደየት እንደሚሄድ እርግጠኛ አልነበረም:: ሲሽሎከለክ ቆይቶ ከአንድ አውራጎዳና ሲደርስ ያገኘውን ሊሞዚን አስቁሞ፣ «ሰፋራ ኢትዮጵያ? (ኢትዮጵያ ኤምባሲ?)» አለ በጥድፊያ:: ሹፌሩ በሩን ለመክፈት እየተንጠራራ «አስር ሪያል ትከፍላለህ» አለው:: ተስማሙ::

ፍሰሃ ሻሹን ፈትቶ ጀለቢያውን ማውለቅ ሲጀምር ታክሲዋ ወደፋርማሲው አቅጣጫ እያመራች መሆኗን ተረዳ:: ፋርማሲው በር ላይ በርካታ ሰዎች ተሰባስበዋል:: ባለታክሲው ግርግሩን ለማየት የመኪናዋን ፍጥነት መቀነስ ጀመረ:: ፍሰሃ ያወለቀውን ቀሚስ ከማዳበሪያው ውስጥ እየከተተ «ፍጠን አንተ» አለው:: አካባቢው በፖሊሶች ተወሯል:: ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ምልክት እየተሰጠ ነው:: ፍሰሃ «ፍጠን እንጂ!» አለው ሾፌሩን ድንጋጤና ቁጣ ባጋለው ድምፅ::

«ይኼኮ የኔ መኪና ነው» አለ ባለታክሲው ጠብረር ባለ አነጋገር:: ገፅታው ንቀት ይንፀባረቅበታል::

«እንኳን ደስ አለህ!» አለ ፍሰሃ በሽሙጥ::

«ጌታ አንተንም ደስ ያሰኝህ!» አለ ሾፌሩ በንቀት ፈገግ ብሎ:: ፍሰሃ እንደድንገት አንድ ፖሊስ ወደእነሱ አቅጣጫ ሲገሰግስ

ተመለከተ:: ፈጠን ብሎ እጁን ወደካልሲው ሰደደ:: ሹፌሩ መኪናዋን ወደአስፋልቱ ጠርዝ አስጠግቶ ቆሟል:: ፍሰሃ ደመነፍሱን ከካልሲው ያወጣውን ሲነጠ. ሹፌሩ አንገት ስር አስጠግቶ «አሁንስ አትነዳም?» አለው ረጋ ባለ ድምፅ:: ሹፌሩ በቅጽበት ሰውነቱ የሚሟሟ ይመስል የመኪናውን መቀመጫ ተደገፈ:: ዞሮ ማየት አልደፈረም:: በፊት መስተዋት ለማየት ሞከረ:: ፍሰሃ ጆሮ ግንዱ ስር በስለቱ ጫፍ ወጋ አደረገው::

«ጠይብ! ጠይብ!» አለና የነዳጅ መስጫውን ረገጠ::

ፍሰሃ ስለቱን ወደሾፌሩ ሸንጥ አስጠግቶ፣ «ስማ ሆድ ዕቃህን ሳላራግፍልህ ያልኩህን ፈፅም!» አለው በሚያስፈራ ድምፅ::

«ጠይብ! ጠይብ!» አለ አረቡ እየተርበተበተ:: ግንባሩ ላብ ማመንጨት ጀምሯል::

«ወደቀኝህ ታጠፍ! ፍጠን! ተደራቢው አስፋልት ላይ ውጣ!» የታክሲው ሾፌር በሚንቀጠቀጡ እጆቹ መሪውን አንቆ ወደግራ ዞረና ሽቅብ ተደራቢው አስፋልት ላይ ወጣ:: ለአምስት ደቂቃ ያህል በተለያዩ አቅጣጫዎች ሲጓዙ ቆይተው ሆየ ፈይሰልያ የመኖሪያ ሰፈርን ቁልቁል ከሚያዩበት «ፔፕሲ ኩብሪ» ከሚሰኘው ተደራቢ አስፋልት ላይ ደረሱ::

«ወደስረኛው አስፋልት ውረድ!» አለ ፍሰሃ:: ከዚህ በኋላ እንደማያስፈልግ ተረድቷል:: ታክሲዋ ጭር ወዳለ ጕዳና ከነፈች::

«በቃህ!» አለ ፍሰሃ ገንዘብ ከኪሱ አውጥቶ ለሾፌሩ እየወረወረለት:: ስንት እንደሆነ አልቆጠረውም:: በርከት ያሉ ድፍን ባለአምስት ሪያል ኖቶች እንደሆኑ ብቻ ነው የተመለከተው::

ሾፌሩ በእፎይታ ተንፍሶ ተሳፋሪው እስኪወርድለት ጠበቀ::

«ቁልፉን አምጣ?» አለ ፍሰሃ በጩኸት::

«ቁልፍ? ... የምን ቁልፍ ጌታዬ?» አለ ሾፌሩ ግራ ተጋብቶ::

«ሞተሩን አጥፋና ቁልፉን አምጣ!» አለ ፍሰሃ ስለቱን ወደሾፌሩ ሽንጥ በሀይል እያስጠጋ::

«ጌታዬ? ... ስራ...» ጉሉን የሚነካካው ስለት ጠንከር ብሉ ስጋውን ወጋ ሲያደርገው ግን መንተባተቡን አቁሞ ሞተሩን በፍጥነት በማጥፋት ቁልፉን ሰጠው::

«ነገ ጠዋት ልክ አራት ሰአት ላይ እዚያ ፔፕሲ ኩብሪወ ላይ ከማስታወቂያ ሰሌዳው አጠገብ ከተሸካሚው ምሰሶ ስር ወድቆ ታገኘዋለህ:: ለዛሬ ግን የመኪናህ ቁልፍ ከኔ ጋር ያድራል::» ፍሰሃ ይህን ተናግሮ ቁልፉን ኪሱ አስገብቶ በሩን ከፍቶ ወረደ::

«እባክህ ወንድሜ፣ ባይሆን...የቤቴን ቁልፍ እንኳ ስጠኝ:: ሚስቴና ልጆቼ ላይ በር ዘግቼ ነው የወጣሁት:: በኛ ሀገር አባወራ ከፍቶ ካልገባ በቀር ሚስትና ልጆች እንደተዘጋባቸው ነው የሚውሉት:: ነገ ጠዋት ደግሞ ልጆቼ ትምህርት ቤት መሄድ አለባቸው::» ሾፌሩ የጋቢናውን በር ከፍቶ ለመውረድ እያመነታ በተዘበራረቀ ሁኔታ ፍሰሃን ተማፀነ:: «ባለቤቴም የነርብ በሽተኛ ናት ...»

ፍሰሃ ሁለት እርምጃ ወደሾፌሩ ተራመደና «ደግሜ ድምፅህን ብሰማ ምላስህን ለሁለት እሰነጥቅልሀለሁ!» ብሎት ወደፊት ገሰገሰ:: ከጥቂት ጉዞ በሁዋላ ለእግረኞች ከተሰራው ድልድይ ደረጃ ሲደርስ ወደሁዋላው ዞሮ ተመለከተ:: ሾፌሩ የጋቢናውን በር ሳይዘጋ

ታክሲዋን ተደግፎ ትከሻው ላይ ጣል አድርጉት የነበረውን ቀይ ሻሽ በእጁ እያፍተለተለ አቀርቅሮ ቆሟል።

ፍሰሃ ፈገግ ብሎ «ምላስህን ብቆርጥልህ ደስ ይለኝ ነበር። ግን ምን ዋጋ አለው? ጊዜ የለንም። አንተ በማጂ መረቅ ለተቀቀለ ሩዝህ፣ እኔ ደግሞ ለነፍሴ የምንሮጥ ሰዎች ነን» አለና መንገዱን ቀጠለ። የእግረኛውን መንገድ አቋርጦ እንዳገባደደ የመኪናውን ቁልፍ ከኪሱ አውጥቶ። «ፈጣሪ ከፈላጊህ ጋር ያገናኝህ» ብሎ ወደፔፕሲ ኩብሪው ሽቅብ ወረወረው።

ከአስፋልቱ እንደደረሰ ያረጀች ነጭ ማዝዳ አየ። አስቁሞ ተሳፈረ። ከአስር ደቂቃ በኋላ ሀየ ሰላም ደረሰ።

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

ሀያት የደረሰባትን አደጋ ለቤተሰቦቿ በደብዳቤ ከገለፀችላቸው ሁለት እሁዶች አለፉ:: በሳምንት ሁለት ቀን እንኳ እቤት በማያድሩት አይዳና ሰሚራ ቤት ውስጥ መቀመጡን አልወደደችውም:: ኑሮን የማሸነፊያ ዘዴ አድርገው የመረጡት አደገኛ ብልሀት እርሷንም አንገቶ እንዳይጠልፋት ሰጋታለች:: በዚያ ላይ ግማሽ የእንቅልፍ ጊዜዋን የምታሳልፈው የፖሊስ ዱካ በማዳመጥ ነው:: የበር ደወል በሰማች ቁጥር ሙጠወኦች የከበቧት ይመስላታል:: በዚያ ላይ ሰስቱ ፖሊሶችም ከአዕምሮዋ አልጠፉም::

አንድ ጠዋት አይዳን « ምናለ ሥራ ብትፈልጊልኝ» አለቻት::

«ምን ጉደለብሽ?»

«አይዳ ብቻዬን እተዚጋ ክፍል መቀመጡ ያስፈራኛል» አለች ሀያት የዘመዷን ቅሬታ ለመገፈፍ ተሰላልሳ::

«እንደምታዩው በዚህ አመት በርካታ ህዝብ ወደዚህች ሀገር ገብቷል:: ለወትሮው ከሰባት መቶ እስከ አንድ ሺ ሪያል እየከፈሉ የሚቀጥሩት አሠሪዎች አሁን በገፍ የገቡትን የፓኪስታን፣ የፊሊፒንስና የኢንዶኔዥያ ሴቶች በሁለት መቶና በሦስት መቶ ሪያል ይቀጥራሉ::»

ሀያት ጃቢር ቤት ሳለች ይከፈላት የነበረውን ደሞዝ አስታወሰችና «ይሄማ በጣም ዝቅተኛ ደሞዝ ነው» አለች::

«ስለዚህ ባደሆን የሀይ ወር እስኪያልፍ ታገሽ:: ለአንቺም ጤንነትሽ እስኪመለስ መጠበቁ ይሻላል::»

የበሩ ደወል ሲያቃጭል ሁለቱ ሴቶች ተያዩ:: አይዳ ተነስታ ከፈተች:: ከሪም በፌስታል ያንጠለጠለውን ፍራፍሬ ለአይዳ ሰጥቶ ወደውስጥ ዘለቀ:: ሀያት ከትልቁ ሶፋ ላይ ቁጭ ብላለች::

«እንዴት ነሽ? ትበረቺያለሽ?» ሲል በፈገግታ ጠየቃት::

«ደህና ነኝ» አለች ሀያት ለማስመሰል እየጣረች:: በውስጧ አንዳች ነገር ሲላወስ ተሰምቷታል::

«ከእንግዲህ የሚያስጨንቀሽ ነገር አይኖርም» አለ አጠገቧ እየተቀመጠ:: ካገኛት ጊዜ ጀምሮ ስለስዋ ሲያስብ ለንዳች ስሜት ይወረዋል:: ዝም ብሎ አያት:: አታየውም:: በመሀከላቸው ፀጥታ ነገሰ::

«ፍስሃ እነአይዳን ሥራ ካላስገባችሁኝ እያልሽ እንደምትነ ዘንዢያቸው ነገረኝ» አላት ከሪም::

«አሁን ስለተሻለኝ ተወዝፎ መዋሉ ምን ይረባኛል? ደግሞ ይበልጥ ለመበርታት ስራ መግባቱ ይበጃል» አለችው ቀና ብላ::

«መጨነቅ የለብሽም፣ ሀያት:: ጅዳ የሆደ ሰፈዎች ከተማ ናት:: በየዕለቱ የሚገጥሙ አስቸጋሪ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ማለፍ የግድ ነው:: እያንዳንዱዋ ደቂቃ ለጭንቀት በሚዳርጉ የህይወት ውጣ ውረዶች ተሞልታለች:: ስለዚህ ነገሮችን እንደየአመጣጣቸው መቀበል ይኖርብሻል::»

«የምትለው ይገባኛል:: ነገር ግን ቤተሰቦቼን መርዳት ይኖርብኛል» አለችው ንግግሩን አቋርጣ::

«የወንድሞቼና የእህቴ የወደፊት ዕጣ እንደኔው ስደት እንዲሆን አልፈልግም፡፡ እኔ ያጣሁትን ትምህርት እነሱ እንዲያገኙ እፈልጋለሁ፡፡ እህቴ እንደኔ እንድትሆን ፈፅሞ አልፈልግም!» ግንባሯ ላይ ያሉት ስሮች ተግተረተሩ፡፡ አይኖቿ ደፈረሱ፡፡

«ሀያት» ከሪም እንባ እንደተናነቃት አቅፎ ወደደረቱ አስጠጋት፡፡

«እንደዚህ መሆን የለብሽም፡፡ አይዞሽ» እያለ ጥብቅ አድርጉ አቀፋት፡፡ ዝም ብላ ታቀፈችለት፡፡ መሸሸጊያ ትፈልግ ይመስል እቅፉ ውስጥ ተሸጉጠች፡፡ እንደዚያ በማድረጉ ደስ አላት፡፡ ልቡ በፍጥነት ሲመታ ተሰማት፡፡

«ሀያት?» አለ ከሪም አገጯን ቀና አድርጎ አይኑን አይኗን እያየ፡፡ «ብቅርቡ ስራ እንድትይዥ አደርጋለሁ፡፡»

ሀያት ትኩር ብላ ተመለከተችው፡፡ እሱም አያትና እቅፎ ሳማት፡፡

ገርበብ ያለው በር ተከፍቶ አይዳ ያዘጋጀችውን የማንጎ፣ የሙዝ፣ የአናናስና የፓፓዬ ድብልቅ «ፍሩት ፓንች» በሸክላ ሳህን ይዛ ስትገባ ሀያትና ከሪም ሲሳሳሙ አየች፡፡ ድንጋጤና ቁጣ ተመሰቃቀሉባትና ቆመች፡፡ ወዲያው ግን ተቆጣጠረቻቸው፡፡ ምንም እንዳልተሰማት ሁሉ ያመጣችውን «ፍሩት ፓንች» ከፊታቸው አስቀምጣ ተቀላቀለቻቸው፡፡

«ሀያት ስራ መግባት እንዳለባት አይሰማሽም?» አለ ከሪም ያንገሸበበውን መጥፎ ስሜት ለመሸሸ ፈልጎ፡፡ ሀያት ስራ ተቀጥራ መስራት እንደሌለባት ግን ከወሰነ ቆይቷል፡፡

«ይስማኛል። ግን ... ስራው ከየት ይገኛል ብለህ ነው?» አለች አይዳ ቅሬታዋን በሚያስተጋባ ድምፀት።

«ወደመካ ልልካት አስቤአለሁ» አለ።

«እዚያ ምን አለ?» አለች አይዳ በመገረም።

«ቢያንስ ጭንቀቷን የሚያስረሳ አነስተኛ ስራ አታጣም። ፈሩዝ ልታስቀጥራት ትችላለች» አለ በደስታ የበራውን የሀያትን ገፅታ ሰረቅ አድርጎ እያየ።

«እህትህ ምን አቅም አላት?» አለች አይዳ ግንባሯን ሸብሸባ።

«ብዙ ሰዎች ታውቃለች።»

ሁሉም በዝምታ ተዋጡ። ሀያት በውስጧ አይዳ ስራ መያዜን ባለመውደዷ ነው ከሪምን የምትሞግተው እያለች ስታስብ፣ አይዳ በበኩሏ ከሪም የገዛ ዘመዷን በማፍቀሩ ተብሰልስላለች። ከሪም ተንጠራርቶ ተነሳና፣

«ሀያት ከኔ ጋር ትሔዳለች» አለ አቀርቅራ ወደተቀመጠችው አይዳ እየተመለከተ።

«ወዴት?» ብላ ጠየቀችው፤ ተቃውሞ በተቀላቀለው ድምፀት።

«ገበያ ሄደን አንዳንድ ነገሮችን እንሸምታለን። ጠዋት ትመለሳለች» አላትና ሀያትን እንድትነሳ ምልክት ሰጥቷት ወጡ።

* * *

የሀፊዝ መኖሪያ እንደወትሮው ረጭ ብሏል፡፡ ከሀንፃው አናት ላይ የበሩት ባለቀለም መብራቶች የምሽቱን ድምቀት አጉልተውታል፡፡ ከማማው ላይ የተቀመጠው ዘበኛ ከጣኢፍ ከተማ የሚተላለፈውን የሬድዮ ፕሮግራም ያዳምጣል፡፡

ሁለተኛው ፎቅ የሚገኘው መኝታ ቤት በፍቅር ወረብ ደምቋል፡፡ ሰሚራና ሀፊዝ በእርካታ በታጀበ ድካም ተረትተው ሰፊው አልጋ ላይ ተኝተዋል፡፡ ሀፊዝ ደረቱ ላይ ያሸለበችውን የሰሚራን ፀጉር በጣቶቹ እያፍተለተለ በህይወቱ ደስታና ሰላምን እንዳያገኝ የተፈረደበት እስኪመስለው አብረውት ያደሩ ሴቶች ስሜቱን ሊጋሩለት አለመፍቀዳቸውን አሰላሰለ፡፡ ዛሬ ግን ለብዙ ሴቶች እንግዳ የሆነ ስሜቱን፣ ትዳሩን ያፈረሰበትን የተለየ የወሲብ ባህሪውን የምትጋራለት ሴት አግኝቷል፡፡ እሷ አንገቱ ላይ እንደነከሰችው የተረዳው የሚቆጠቁጥ ስሜት ሲሰማው ነበር፡፡ ግንባሯን ሳማት፡፡ በለስላሳ ጣቶቿ ጆርባውን በቀስታ ዳሰሰችው፡፡ ሀፊዝ በሰሚራ ምላሽ ተደስቶ አጥብቆ አቀፋት፡፡ ፈጣሪ በመጨረሻ ወደሱ የላካት መድሀኒቱ መሰለችው፡፡ አይዳ ጥላው ከሄደች በኋላ ፍሰሃ ዳግመኛ ከሌላ ሴት ጋር ሊያጣምረው የሚፈቅድ አልመሰለውም ነበር፡፡ ሌላ ደንበኛ ለማፍራት በሚያውጠነጥንበት ወቅት ግን ሰሚራ ስልክ ደውላ ተዋወቀችው፡፡

ሰሚራን ከእንቅልፏ እንዳይቀሰቅሳት በቀስታ ከአልጋው ተነስቶ ወደሳሎን ሄደ፡፡ በውድ እቃዎች የተንቆጠቆጠው ሳሎን በአራት ማዕዘን የግድግዳ ኮርኒስ ላይ በተሰኩ ጌጣማ መብራቶች ደምቋል፡፡ ከትልቁ የቪዲዮ ማስቀመጫ ወርቃማ መደርደሪያ ላይ የተቀመጠው ሰላሳ ስድስት ኢንች ቴሌቪዥን ከነዴኩ ከሰፋው ትይዩ

ተገትሯል:: የአበባ ክፈፍ ቅርፅ የያዙት ሰፋ ወንበሮች ብርቱካንማ ገላ መስኮቱ ላይ ከተዘረጋው መጋረጃ ጋር የተስማማ ነው:: እንጨት ላይ ከታተመው ባለቀለም የሀፊዝ ፎቶ በተጨማሪ ክፍሉ በአርቴፊሻል አበቦችና ከዝሆን ጥርስ በተሰሩ ጌጣጌጦች ተውቧል::

ከአንደኛው ጥግ የመጠጥ መደርደሪያ ጠርሙስ ውስኪና ሁለት ብርጭቆዎች አውጥቶ በብርማ ትሪ ደርድሮ ወደመኝታ ቤት ተመለሰ:: ሰሚራ ፊቷን ሲደባብሳት ባነነች:: ውስኪ የያዘ ብርጭቆ ሲያሳያት ፈገግ ብላ ተነስታ ተቀመጠች:: የተቀዳውን መጠጥ ወዳፋቸው ከማስጠጋታቸው በፊት «ለፍቅራችን!» አሉና አጋጭተው ተጎነጩ:: ሀፊዝ መለኪያውን ሲያጋምስ የወሲብ ስሜቱ ስለተቀሰቀሰ ከትንሿ ባለመስተዋት ጠረጴዛ ላይ ብርጭቆውን አስቀምጦ የሰሚራን ልስልስ ገላ መነካካት ጀመረ:: ላብ የማያመነጩ እጆቹ ከጭኖቿ ሲዘልቁ ወደአፏ ያስጠጋችውን ብርጭቆ ከሀፊዝ ትከሻ አሻግራ አስቀመጠች:: በመጨረሻ የሀፊዝ እጆችና ጥርሶች ሰሚራ ልስልስ ገላ ላይ ዘመቱ:: ሰሚራን የሃፊዝ ንክሻ በለስላሳ ጣቶች የመዳሰስ ያህል ደስታ ሰጣት::

ሲነጋ ምግብ ጠረጴዛ ላይ የተደረደሩትን የምግብ አይነቶች በተራቡ አይኖቿ ቃኝታ ወንበር ስባ ተቀመጠች:: የተጠበሰ እንቁላል፣ ቀዝቃዛ አይብ፣ በስሱ የተቆራረጡና የተቀቀሉ እንቁላሎች፣ የተጠበሰ ድንች፣ የዶሮ ስጋ፣ ከቆርቆሮ ወተትና ከቸኮሌት ዱቄት የተፈላ ትኩስ ካፑቺኖ ጠረጴዛውን አጣበውታል::

ከቁርስ በኋላ ሰራተኛው የተበላባቸውን እቃዎች ሲያነሳሳ ሰሚራ ጥቁር አባያዋን ተከናንባ መኪና ውስጥ ሆኖ ይጠባበቃት ወደነበረው ሃፊዝ ሄዳ ከጐኑ ተቀመጠች:: መኪናዋ የሀፊዝን

የመኖሪያ ሰፈር ለቃ ከሁለተኛው ተደራቢ አስፋልት ከወጣች በኋላ የሰላማ ሴንተርን የገበያ ማዕከል መስመር ያዘች፡፡

«ወዴት ነው?» አለች ሰሚራ ሪዙን ሙልጭ አድርጉ ተሳጭቶ ልጅ የመሰለውን ሀፌዝን እያየች፡፡

«ሱቅ ጉራ እንላለን» ሲል በፈገግታ መለሰላት፡፡ ወደመርሀባ ሱፐር ማርኬት የሚያደርሰውን ተዳፋት ጨርሰው ወደሰላማ ሴንተር የሚያዘልቀውን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሲይዙ ቁልፉ ከተፈታው አባያዋ አፈንግጠው የወጡትን ጭኖቿን እየዳሰሰ «በምድር ላይ የተፈጠረችልኝን ብቸኛዋን ልዕልት ሳልሸልም ብቀር ገሀነም እገባለሁ» አላት፡፡

የገበያው ማዕከል ጭር ብሏል፡፡ ከመኪና ማቆሚያው ሁለተኛ ረድፍ ላይ መኪናቸውን አቁመው ወደወርቅ መሸጫ ሱቆቹ አመሩ፡፡ ቀይ ከፋይ ከለበሰው መደርደሪያ ላይ የተገጠገጡት ወርቆች ቢጫ ቀርቀሮ ይመስል ያብረቀርቃሉ፡፡ ወደአንዱ ሱቅ ተከታትለው እንደገቡ፣በእጅ ቅርፅ ላይ የተሰኩ የወርቅ አምባሮች ወዳሉበት ወሰዳት፡፡

«ብይ ምረጪ» አለ በፈገግታ፡፡

ሰሚራ ለጥቂት ጊዜ የወርቅ አምባሮቹ ላይ አይኖቿን ስታንከባልል ቆይታ፣ «አይን አዋጅ ሆነብኝ፤አንተው ምረጥልኝ» አለችው፡፡

ሀፌዝ አራት መጠነኛ ውፍረት ያላቸውን አምባሮች መረጠና ሰራተኛውን ጠራው፡፡ አምባሮቹ ሰላሣ ሁለት ግራም መዘኑ፡፡ ሀፌዝ እንደዋዛ ከፍሎ የወርቅ አምባሮቹን ተረከበ፡፡ ሀፌዝና ሰሚራ ሆየ ሰላማ እሚገኘው የአርአያ አፓርታማ ሲደርሱ ስጦታውን ፈቶ

ከሰሚራ እጅ አጠለቀና እጆችዋን ሣመ። እንደገና ወጣት የሆነ መሰለውና ለመኖር በብርቱ ጓጓ።

«ጥሩ ጊዜ አብረን እንደምናሳልፍ እርግጠኛ ነኝ። የኔ ማር» አላት።

ተሰነባብተው ተለያዩ ።

* * *

አሰልቺ ጩኸት የሚያሰማው የአየር ማቀዝቀገየ በሁለቱ ሴቶች መሃል በሰፈነው ዝምታ የተነሳ ጐልቶ ይሰማል። ቴሌቪዥኑ የዕለቱን የሰበካ ፕሮግራም ያስተላልፋል።

«እባክሽ ይህን ቴሌቪዥን ዝጊልኝ?» አለች አይዳ በተሰላቸ ሥሜት ሰሚራን እያየች። ሰሚራ ቴሌቪዥኑን አጥፍታ ስትመለስ፣

«አይዳ ግን ምን ሆነሻል?» ስትል ለስለስ ብላ ጠየቀቻት።

«መናቁ ነው ያንገበገበኝ» አለቻት አይዳ። ድምፇ ሻክሯል። ሳግ እየተናነቃት ነበር።

«የምን ንቀት እባክሽ?»

«ከሪም የፈፀመው ድርጊት ነዋ» አለቻት ባጭሩ።

«አይዳ የምታወሪው ሁሉ አልገባኝም?»

«እንዴት አይገባሽም? ሀያት ከኛ ጋር እንድትቀመጥ ስለማይፈልግ በማይረባ ምክንያት ከኛ የምትርቅበትን ዘዴ አመቻችቷል።»

«ማራቅ?» ለነገሩ አዲስ የሆነችው ሰሚራ ተደናገረች።

«በሱ ቤት እኛ ተስፋ ቢስ ሸርሙጦች ነን።»

«ታዲያ ይህ ምን ያስገርማል? ተገደን የገባንበት አይደለም እንዴ?»

«ቢሆንም ከሪም ለኛ ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት እንዲህ በገሃድ በማንፀባረቅ ሥሜታችንን መጉዳት አልነበረበትም፡፡»

«የምን ዝቅተኛ አመለካከት ነው? እኔ በሌለሁበት የተናገረሽ ነገር አለ እንዴ?»

«ይሄ ራሱ ከፍተኛ ንቀት ነው፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ መሳ ትሄድ ይላል»

«ታዲያ አንቺን ምን አስጨነቀሽ?»

«ሌላም ነገር አለ አባክሽ» አለችና በረጅሙ ተነፈሰች፡፡

«ምን?» ሰሚራ በጉጉት አስገገች፡፡

«ከሪምን እኮ ከልቤ እወደዋለሁ፡፡»ከዚህ በላይ ስሜቷን መቆጣጠር አልቻለችም፡፡ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና መነፋረቅ ጀመረች፡፡

ከሁለት አመት በፊት፣ ዛሬ ከታሰሩት ጓደኞቿ ጋር አብራ ከምትኖርበት የሃየር በዋዲ አፓርትመንት ፍለሃን ተከትሎ የመጣው ከሪም በፍቅር ገዝቷታል፡፡ ገና ስታየው ትላልቅ አይኖቹ፣ ችምችም ሪዙ፣ ነጫጭና የሚያማምሩ ጥርሶቹ፣ ጉርናና አስገምጋሚ ድምፁ፣ ዘለግ ያለ ቁመቱ ስሜቷን ረታት፡፡ ሴትነቷን እየረገመች በድርጊት ፍቅሯን ለማሳወቅ ትሞክራለች፡፡ ብቻቸውን ሲሆኑ ብዙ ፍንጮች ሰጥታዋለች፡፡ ግና አንድ እሁድ ዕለት እጁን ስትደባብሰው «አዝናለሁ» አላት ቆጣ ብሎ፡፡ «አንቺና ሰሚራ እህቶቼ ናችሁ» ብሎአትም ከአጠገቧ ተነስቶ ወጣ፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሦስት

ደረቷንና እግሮቿን እርቃን ያደረገ አጭር የሌሊት ልብስ እንደለበሰች፣ የተመሰቃቀለ ፀጉሯን በረጃጅም ጥፍሮቿ እየቆፈረች ሮዝ ቀለም ያለውን ግድግዳ ተደግፋ አልጋው ላይ ተቀምጣለች:: እንቅልፍ የተራቡ አይኖችዋ ቀላልተዋል:: ለወትሮው በኩል የሚደምቀው ቅንድቧ ተዘበራርቆ ውበቱን አጥቷል:: የልብ ቅርፅ ከንፈሮቿ ነጣጥተው ደራርቀዋል፣ ውበቷ ደብዝዟል:: ውሉ ያልለየለት ሥሜት ፊቷ ላይ ይነበባል::

ፍስሃ የቤቱን በር ስትከፍትለት ባስተዋለው ለውጥ ተደናግጧል:: በሚንቀጠቀጡት ጣቶቿ የያዘችውን ያለቀ ሲጋራ በረጅሙ ሳበች::

«አይዳ» በዝግታ ተጠጋት:: ዞራ እሳት በሚተፉ ዓይኖቿ አፈጠጠችበት:: በፍርሃት አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ «ደህና አይደለሽም ?» ሲል ሥጋት በቀላቀለበት አሳዛኝ ቅላፄ ጠየቃት:: ምላሽ ነፍጋው ፀጉሯን በግራ እጇ እያመሳቀለች የተዘረጉ እግሮቿን ተመለከተች::

«አይዳ» አለ ፍስሃ ያኮረፈ ልጅ እንደሚያባብል ገር አባት ድምፁን አለስልሶ «ምን ችግር አጋጠመሽ?»

ብዙ ነገር ልትናገረው ፈልጋ ነበር:: ለሴት ልጅ ከወንድ የከፋ ጠላት የላትም:: በአስተዳደር ትበደላለች፣በሀብት ትጨቆናለች፣ በስሜት ትጐዳለች፣ በፍቅር ትታበላለች:: ከሪምም የፈጸመባት



... Library

ይህንኑ ነው:: ግን ቻለችው:: ስሜቷን ታገለችውና ቀና ብላ አየችው::

ፊቱ በሃዘን ዳምኗል:: የቦዙ ዓይኖቹን ተከሎባታል:: ፊቷን አዙራ ሲጋራውን ወደውስጥ ሳበች:: መልስ እየጠበቀ የሚያያትን ፍስሃን አሽጋግራ አየችው:: ግንባሩ ተቋጥሮ አይኑ ጠበብ ብሏል:: በወበቁ ላብ ማመንጨት የጀመረ ግንባሩ ያብረቀርቃል:: እያቃጠረ ያፈራው ወዝ ሲያብረቀርቅ በማየቷ ተናደደች::

«እባክሽን ሥቃይሽን ልጋራ?» አለ በፍርሃት፣ በልምምጥ:: ለሱ ስሜት ግምት ሳትሰጥ በጭስ ጨዋታዋን ቀጠለች::

ፍስሃ ያለቀች የትዕግስቱን እንጥፍጣፊ አሰባስቦ ጥያቄውን ደገመላት:: ሲጋራዋን ተርኩሳ የቅሬታ ፈገግታ እየታየባት «ምንም! ሰላም ነኝ::» አለችው:: ፍስሃ ሳይበጠር ውሎ ያደረ ፀጉሯን ተመለከተ:: ለወትሮው በሜካፕ የሚበራው ፊቷ ገርጥቷል::

«በቃ እንደዚህ ሆንሽ?» አለ እግሯን እየዳበሰ::

«የረከሰ ገላዋን ማንፃት የተሳናትን እንስት ያንጓልሏታል» አለች::

«ፍስሃ ምን አደረገ አሉሽ?»

«ምንም» አለች ትከሻዋን ሰብቃ::

«ታዲያ የምታወሪው ምንድነው? ፍስሃ እንደሆነ የናቃትን ሴት ከንፈር አይነካም. . .»

«ወንድሜ! አንተን አይመለከትህም» አለች ንግግሩን አቋርጣ:: እስከጭኗ አጋማሽ የተጋለጠው አጭር ስስ የሌሊት ልብስ ላይ ዓይኑን ተክሎ በተዘበራረቀ ሥሜት ሲያስተውላት ቆይቶ ጣቶቹን ወደጭኖቿ ሰደደ::

ቴሌቪዥኑ ደማስቆ ውስጥ የተሰራ በጦርቅ ሥርቆት ዙሪያ የሚሽከረከር የሶሪያን ፊልም ያስተላልፋል:: በጭኖቿ ላይ የሚላወ ሰውን እጅ በጨረፍታ አየች :: ገላዋን ለማጋል ወደጭኖቿ መሃል ለሰስ ብሎ ይዘልቅና ታፋዋ ላይ ይንሸራሸራል:: እንደገና ወደ መሃል ዘምቶ የውስጥ ሱሪዋን ነካክቶ ይመለሳል::

አይዳ ግን በከሪም ላይ የከፈተችውን ሥውር ዘመቻ በድል ለመወጣት የነደፈችው ስልት በመምከኑ የፍስሃ ገላ አላሰኛትም::

ፍሰሃ አመጸኛ ልቧን ለማስገበር፣ የሸፈተ ፍልቅልቅነቷን ለመጫርና፣ የበረደ ገላዋን ለማሞቅ ያሻሻታል:: ጣቶቹ ግን የአባ ጨጓሬን ያክል ኮስኩሰዋታል::

ፍሰሃ ያልተበጠረ ፀጉሯን፣ አንገቷንና የተራቆተ ጀርባዋን እየደባበሰ ወደጆሮዋ ተሻገረ:: አይዳ ተስፈንጥራ መነሳት ፈልጋ ነበር ግን በቸልታ ማለፉን መረጠች::

ፍሰሃ ተቻኩሎ የውስጥ ሱሪውን አወለቀ:: አይዳ ጭንቅላቷን ወደጉን በመስበር ቴሌቪዥኑን በጨረፍታ ትመለከት ጀመር:: የማሪያ ኬሪ «ሥዊት ድሪም» ዘፈን እየተላለፈ ነበር::

* * *

ፍቅር ነግሶበት ባደረው ሌሊት የወዙት ከሪምና ሃያት የዛለ ሰውነታቸውን የንጋቱ የሰላት ጥሪ ሲሰማ ለብ ባለ የቧንቧ ውሃ ተለቃልቀው ተመልሰው ከተኙበት አልነቁም::

መጠነኛ ድምፁን እያሰማ የሚሽከረከረው የአየር ማቀዝቀዣ የከሪምን ለስላሳ ኩርፊያ ውጦታል:: ነጩን ስስ መጋረጃ ጥሶ

የገባው የረፋድ ፀሃይ ክፍሉን አድምቆታል። ወንበሩና ወለሉ ላይ የተመሰቃቀሉ ልብሶች ይታያሉ። ካልጋው ፊንጠር ብላ የተቀመጠች የመስተዋት ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠው ነጭ ስልክ ሦስቴ እንደጮኸ ከሪም ባኖ መነጋገሪያውን አነሳ።

«አቤት . . . አርአያ . . . አዎን፣ አልተነሳሁም . . . ሙአዝ መጣ ነው የምትለኝ? መቼ? ጠይብ! መጣሁ» ብሎ ስልኩን ዘጋና ወደሀያት ዞረ። አይኖቿ እንደተከደኑ ናቸው። እንዳይቀሰቅሳት ተጠንቅቆ ከንፈሯን ስሞ ከአልጋው ወረደ።

ከዚያም በቅቤ ለውሶ በዘይት የጠበሰውን ዳቦና የእንቁላል ፍርፍር ምግብ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ቱርሙስ ሻይና ሁለት ስኒዎች አስከተለ።

ወደመኝታ ቤት ተመልሶም ክድን ያሉ አይኖቿን ተራ በተራ ሳመና በለሆሳስ ጠራት። በቀስታ አይኖቿን ከፍታ አየችው።

«ተነሽ ቁርስ ደርሷል» አላት ፀጉሯን እየደባበሰ። የአልጋውን ጠርዝ ተደግፋ ልትነሳ ስትሞክር አቅፎአት ከንፈሮቿን ሳመ። ያቀረበውን ቁርስ እየበሉ ሳሉ «የማታውን ነገር አሰብሽበት?» አላት ከሪም በዳቦ የቆነጠረውን የእንቁላል ፍርፍር እያጐረሳት።

«ግን ለምን?» አለች ረጋ ብላ።

«ከነዚህ ልጆች መራቅ አለብሽ!»

«ጥሩ እሔዳለሁ» አለች ሃያት ፍርሃቷን ለመከላከል እየሞከረች።

* * *

የምሽቱ የመጀመሪያ የሰላት ጥሪ ተሰምቶ እንዳበቃ ሁለቱ ሴቶች ራታቸውን መመገብ ሲጀምሩ የበሩ ደወል አንቃጨለ፡፡ ያልተለመደ ነገር ነበር፡፡ በስግደቱ ሰዓት በሚዘዋወሩ መንገደኞች ላይ ከሚዘምቱት የሃይማኖት ጠባቂዎች (ሙጠወኦች) እንዴት ሊያመልጥ እንደቻለ ተገርመው ተያዩና በአንድነት ብድግ አሉ፡፡

«በዚህ ሰዓት ማን ሊመጣ ይችላል?» አለች አይዳ እየተደ ናገጠች፡፡

«አንቺ እዚህ ቆዩ» ብላ ሰሚራ በሩን ከፍታ ወደውጭኛው ክፍል ወጣች፡፡ ኮቴዋን አጥፍታ በማጮለቂያው ቀዳዳ ስትመለከት ነጭ ሸሚዝ የለበሰ ሰው ዙሪያውን እየተገላመጠ ደወሉን ደጋግሞ ይጫናል፡፡ ስትከፍት ፈጠን ብሎ ገባና፣

«ምን ነካችሁ? ተኝታችሁ ነበር እንዴ?» አለ ፍስሃ ትንፋሹ እየተቆራረጠ፡፡

«ተኝተን ቢሆንማ ጥሩ ነበር፡፡ ሹርጣ (ፖሊስ) የመጣ መስሎን በፍርሀት አለቅን እንጂ፡፡ አብደሃል እንዴ በዚህ ሰአት የምትዘዋወረው» አለችው በሩን እየዘጋች፡፡

«ወደመንደሩ ከዘለቅኩ በኋላ አዛን አለብኝ፡፡ ወደመስጊድ መሔድ ደግሞ እንደማልፈልግ ታውቂያለሽ፡፡ ስለዚህ የሹርጣ ናዳ እንዳይወርድብኝ ፈጥኜ ወዲህ ሮጥኩ፡፡» ተከታትለው ወደውስጠኛው ክፍል ሲገቡ አይዳ የእንግዳውን ማንነት ስታውቅ ተረጋግታ ከማዕዱ ፊት ተቀመጠች፡፡

አይዳ ዛሬም ፊት እንዳትነሳው በልቡ እየፀለየ ጉንበስ ብሎ ጉንጯን ሳማት፡፡ ከዚያም ራታቸውን እየተሻሙ በሉ፡፡

ብቻቸውን እንደቀሩ ፍሰሀ «ተሻለሽ? ....» ሲል ጠየቃት።

«ታምሜ ነበር እንዴ?»

«ከመታመምም በላይ እንጂ ...» ዝም ብላ ቆየችና በመጨረሻ ‹ዛሬ የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ አለብኝ› አለች በልቧ።

«ስልክ ለመደወል ወጣ ማለት ፈልጌያለሁ። አብረኸኝ ትሔዳለህ?» አለችው እንደመነሳት ብላ።

«ወዴት? ... ወደኢትዮጵያ ልትደውዪ አሰብሽ?» አለ ኪሱ ውስጥ ያለውን ገንዘብ በሀሳቡ እያሰላ። ወደሀገር ቤት ደውላ ብዙ ደቂቃዎች ካወራች ክፍያውን ሊሸፍንላት አይችልም። ‹ቀደም ብዬ ባውቅ ኖሮ ...› አለ ለራሱ።

«አይ እዚሁ ጅዳ ነው።»

«ጅዳ? ማን ጋ?» አላት እፎይታ እየተሰማው።

«ዘመድ ጋ።»አይዳ ጥቁሩን አባያ ደረበችና ፊቷንና ፀጉሯን ተሸፋፍና ወደበሩ አመራች።

«ሰሚራ፣ በአምስት ደቂቃ ውስጥ እንመለሳለን» አለ ፍሰሃ አይዳን ተከትሎ ሲወጣ። እሱ ከፊት እሷ ከኋላ በትንሽ ርቀት እየተከታተሉ ወደአቡ አባዲ የምግብ ሸቀጣሸቀጦች መደብር ሄዱ። ከህንፃዎቹ አናት ላይ አልፈው አልፈው የተንጠለጠሉት መብራቶች የጨለመውን መንደር በደካማ ብርሀን አደብዝዘውታል። እስከ ሌሊቱ አጋማሽ የማይዘጋው የአቡ አባዲ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ መደብር በውስጡ በሚንቦገቦጉት ስድስት ረጃጅም የፍሎረሰንት መብራቶች ደምቋል።

አይዳ ወደመደብሩ ስትዘልቅ ፍሰሃ ከደጅ ቆሞ ሲጋራውን ለኮሰ። የመደብሩ ባለቤት አቡ አባዲ የአይዳን ፍላጎት እንደተረዱ ነጩን ስልክ ገፋ አደረጉላት።

«ሀሎ! ... ኡመር መውጁድ ይኖራል?» አለች ድምጿን ከፍ አድርጋ። ሆን ብላ ፍሰሃ እንዲሰማ እየጣረች ነበር። ወደውጭ ገልመጥ ብላ አየች። ፍሰሃ ሲጋራውን በፍጥነት እየሳበ ሰርቆ ይመለከታታል።

«ነኝ፤ ማን ልበል?» አለ ስልኩን የተቀበለው ጉርናና የወንድ ድምፅ።

«የቆየ ወዳጅ ታስታውሳለህ? አይዳ ነኝ» አለች።

«አንቺ ጣፋጭ የት ጠፍተሽ ተገኘሽ?» አለ ጉርናናው የኡመር ድምፅ በሳቅ እንደታጀበ።

«ቤት ቀይሬ ነው። አንተ ደህና ነህ?»

«ከተወዳጇ ፍቅረኛዬ ናፍቆት በስተቀር ደህና ነኝ። ውፍረትም ጨምሬያለሁ።»

«እውነትህን እንዳይሆን እና እንዳልጠላህ።»

«ወዳጅነታችን ከታደሰ የምትፈልጊውን ያህል ታከሽኛለሽ።» በረጅሙ ሳቀ።

«ሚስትህ ደህና ናት?»

«ስለቆሸቆሽ አሮጊት በማውራት ጊዜዬን ማባከን አልፈልግም!» የድምፁ ቃና ተቀየረ።

«ትዳርህን ዛሬም ትጠላዋለህ?»

«ብሶብኛል። በግዴታ ያገባኋትን ያክስቴን ልጅ ጠረን ከረሳሁ ስንት ዘመኔ።»

«አዝናለሁ፤ ደስተኛ አይደለህማ?»

«አንቺ ታስደስቺኛለሽ፤ ልክ እንደበፊቱ።»

«መቼ እንገናኝ ታዲያ::»

«ከነገ ጀምሮ ብንገናኝ ...»

«እኔ እንኳን አሁኑኑ ብንገናኝ ደስ ይለኝ ነበር::»

«ሚስትህ የምትለቅህ ይመስልሀል?»

«መቼም ልትቆጣጠረኝ አትችልም::»

በረጅሙ ሳቀች:: ጥግ ያለው መደርደሪያ ላይ ዕቃዎችን የሚያስተካክሉት አቡ አባዲ ግር ብሏቸው ተመለከቷት:: የምትና ገረውን ሊሰሙ ባይችሉም ደነገጠች::

«የት ነው የማገኝሽ?» አላት ኡመር::

ፈጠን ብላ «ነገ ሁለት ሰአት ላይ ሙስተሽፋል ማዕሩፍ እጠብቅሀለሁ» ብላ ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋችው:: ፍስሃ አይዳን ቤቷ በር ድረስ ሸኝቶ «ደህና እደሪ፤ ነገ ማታ እመጣለሁ» ብሏት ሄደ::

*　　　　*　　　　*

ሀገሩ ከርሞ የመጣውን ሙአዝ ከበው ሲያወጉ ያመሹት ከሪምና ፍስሃ አዳራቸውን ከከሪም ቤት ለማድረግ ሲሔዱ አርአያ ዘንድ ተቀምጦ የነበረውን የሶስት እሽግ ኮኬይን ሽያጭ ከአርአያ ተቀብለው ነበር:: ስለገንዘቡ ማወቅ የፈለገው ሙአዝ ማታ ወደመኝታው ሲሄዱ አርአያን ስለጉዳዩ ጠየቀው::

«ከሪም ከወር በፊት ኮኬይን አግኝቶ ነበር:: በራሱ ገንዘብ ነው የገዛው» አለ አርአያ::

«ለምን እኛን አላሳተፈንም?» የሙአዝ አይኖች ጠበቡ::

«ፍስሃንስ ስለዚህ ጉዳይ አነጋግረኸው ነበር?»

«እሱም የትርፉ ተካፋይ እንደሚሆን ነግሮኛል::»

«እኛስ?»

«እኛማ በገንዘብ አልረዳንም:: ፍሰሃ ግን ከገዥዎቹ ጋር ያገናኘዋል::»

«ይሄ እንኳን አይዋጥልኝም:: እስከዛሬ እንዲህ ያለ አሰራር አናውቅም:: በመጀመሪያ ደረጃ ደግሞ ስራውን ያስለመድናቸው እኛ ነን::» አርአያ ዝም አለው::

«ለመሆኑ እፁን ያመጣላቸው ማነው:»

«መጅድ::»

«ይሔ ፍልፈል! እነሱን ከእኛ ቡድን ገንጥሎ ለማውጣት የሚያደርገውን ሙከራ ዛሬም አልተወም ማለት ነዋ!? እንዲያ ከሆነ አንገቱን አስቀነጥስለታለሁ:: እነሱም ቢሆኑ ከኛ ቁጥጥር ስር አይወጧትም:: አፍንጫቸውን ይዘን ከትርፋቸው እንዲያካፍሉን እናደርጋለን!»

«የኛ ገንዘብ ሳይኖርበት?!» አለ አርአያ ተደንቆ::

«እሱ ሌላ ነገር ነው:: ከተስማሙ አሁኑኑ ድርሻችንን እናዋጣለን:: ከሽያጩ የሚያገኙት ትርፍ እንኳን ለኛ ለሌላም ይበቃል::»

«ባይፈልጉስ?»

«እኔ እንዲያካፍሉን አደርጋቸዋለሁ::»

«በምን ዘዴ?»

«ነገ ደውለህ አምስት እሽግ እንዲያመጣ ንገረው::»

«ለምን ቢለኝስ?»

«ለምን ደደብ ትሆናለህ? ፈላጊ መጥቷል ትለዋለሃ!»

አርአያ በሙአዝ ልብ የተጠነሰሰችውን ሴራ ተረድቶ ፈገግ አለ::

# ምዕራፍ አስራ አራት

ሀያትና ነህላ ሞቃታማው ዕለት ተገባዶ የአስር ሰዓት ሰላት ሊካሔድ ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት ወደሀረም መስጊድ ወርደው የምሽቱ መጨረሻ የሰላት ሰዓት ድረስ በመቆየት ቀጣሪ ይጠባበቃሉ:: የከሪም እህት ሀያት ወደሀረም እንዳትሔድ ለመከልከል ብታስብም የሀያትን ስሜት ላለመጉዳት ስትል ቸለል ብላለች::

በሀበሾች መሰብሰቢያነቱ በአረቦች ዘንድ የሚታወቀው ባበልፈትህ በስተምዕራብ ከሚገኙት የሀረም መስጊድ በሮች አንዱ ነው:: ከበሩ በስተግራ በኩል ሰብሰብ ብለው የሚቀመጡ ሀበሻ ሴቶች ከውጭ ሲገቡ የሽፈኑትን አይነርግብ አውልቀው ይቀመጣሉ:: ከዚያም አፍ ለአፍ ገጥመው ያወጋሉ::

የአስር ሰዓቱ የሰላት ጥሪ ሲያበቃ በባበልፈትህ በኩል የገቡት ሀያትና ነህላ ወደፊት ዘለቁና ከካዕባው ትይዩ ከሚገኝ ስፍራ ቦታ ያዙ::

ነፋሻው መስጊድ ዛሬም እንደቀዘቀዘ ነው:: ሀያትና ነህላ ጥቂት ጊዜ በዚያ ከቆዩ በኋላ ወደባበልፈትህ ተመልሰው ከተሰበሰቡት ሀበሾች ፊንጠር ብለው ከሚለሰልሰው ምንጣፍ ላይ እግሮቻቸውን አጣጥፈው ተቀመጡ:: ከአንዱ ምሰሶ እስከቀጣዩ ድረስ ያለው ሰፊ ቦታ በሀበሻ ሴቶች ተሞልቷል::

የምሽቱ ሰላት ተሰግዶ እስኪያበቃ አንድም ሰራተኛ ፈላጊ ወደአካባቢው ዝር ያለማለቱ ሀያትን አስገረማት:: ተስፋ የቆረጡ ሀበሾች አንድ ባንድ ወደየቤታቸው ይበታተኑ ጀመር::

ቤት ቤቱ ከመቀበም የመስጊዱን ትዝታዜ ማጣጣምን የመረጠት ሀያትና ነህላ ግን ከጥቂት ሀበሾች ጋር ተቀምጠዋል:: ምሽቱ ሊጋመስ በተቃረበበት ሰዓት አንዲት ወፍራም ሴትዮ ወደ ባበልፈትህ ተጠጋች:: ሴትዮዋ ቶሎ፣ ቶሎ ትተነፍሳለች:: ተለቅ ያለ ጠርቅማ ቦርሳም አንጠልጥላለች::

«ኢንቲ ሽቃላ?» አለች ሴትዮዋ ወደነህላ ቀረብ ብላ::

«አዎን፣ ሰራተኛ ነኝ» ስትል ነህላ ፈጥና መለሰች:: አሰሪ ሲመጣ መሻማት የተለመደ ስለሆነ በስጋት አካባቢዋን ቃኘች:: ሴቶቹ በቅናት ይመለከቷታል::

ሴትየዋ «ሶስት ሰራተኛ እፈልግ ነበር»ብላ መቆም ስላቃታት ከነህላ ፊት ተቀመጠች::

«እሷ የኔ እህት ነች:: ሌላም አንዲት ጉበዝ ሴት አመጣለሁ» አለች ነህላ ወደሀያት እየጠቆመች::

«ስራሴ፣ ለናቴና ለልጄ ነው የምፈልገው:: ታድያ ስንት ነው የምትሉት?» አለች ሴትየዋ ብስል ቀይ የውስጥ እግሯን በለስላሳ ጣቶቿ እየፈተለች::

«አንቺ ስንት ትያለሽ?» ስትል ነህላ መልሳ ጠየቀች::

«አራት መቶ ሪያል!»

«በዚህ አንስማማም ከሰባት መቶ ሪያል ሰባራ ሣንቲም አንቀንስም::»

ሴትየዋ ለተወሰነ ጊዜ አቀርቅራ ከቆየች በኋላ በመጨረሻ ፈገግ ብላ፣«ስራችሁ ታይቶ'ኮ ይጨመርላችኋል:: በዚህ ላይ የሶስቱም ቤት ስራ ቀላል ነው» አለች::

«ከባድም ቢሆን ግድ የለኝም። የመጀመሪያው ጉዳዬችን በደሞዝ መስማማት ነው።»

«መካ ከተማ እንዳለሽ ደግሞ አትዘንጊ» አለች ሴትየዋ ተኮራርታ።

«አውቃለሁ፤ለአራት አመታት ኖሬባታለሁ» ስትል መለሰች ነህላ ንዴት እየተናነቃት።

«እንደዛ ከሆነ የነዋሪዎቹን ጥሩነት ታውቂያለሽ ማለት ነው?»

«በዚህ ከተማ ያየሁት ጥሩ ነገር ቢኖር ይህን የሀረም መስጊድ ብቻ ነው» አለች ነህላ ኮስተር ብላ።

«ነዋሪዎቹም ሀረም መስጊድን ይመስላሉ። መቼም በአራቱ አመታት ውስጥ ጥቂት ቤቶች ውስጥ ሳትሠሪ እንዳልቀረሽ እገምታለሁ።»

«ጥቂት ሳይሆን በጣም ብዙ ቤቶችን አይቻለሁ።»

«ብዙ ቤት?! እንደዛ ከሆነማ በቂ የስራ ልምድ አለሽ ማለት ነዋ!» ብላ ሴትየዋ አሽካካች።

«ከልምዱ ይልቅ የከተማዋን ነዋሪዎች እንድጠላቸው አድርጎኛል።»

«ምን አልሽኝ?»

«ብዙ ቤቶች የቀያየርኩት ጥሩ ሰዎች ሊያጋጥሙኝ ስላልቻሉ ነው።»

ሴትየዋ ረገብ አለችና «እውነቱን ልንገርሽ? እኔም፣ እናቴም፣ ልጄም ሰራተኞቻችንን እንወዳለን። ይበልጥ ደግሞ እናቴ፤

የሰባ አመት የዕድሜ ባለፀጋ ናት:: በገንዘቡ ከተስማማን እናቴ ቤት እመድብሻለሁ::»

«በእድሜ የገፉ ሴቶች አይስማሙኝም:: ልክ ልክፈልሽ እንደምትዪው አራት መቶ ሪያል ቆሌ ያስርቃሉ::»

«ይህን ያህል የምለምንሽኮ ስለተቸገርኩ ነው::»

«እንግዲያው ወዲያ ማዶ የአ·ዱ ማድረጊያ ገንዳዎቹን አለፍ ብሎ ከሚገኘው ምሰሶ ስር በርካታ የእስያ ሴቶች አሉልሽ:: ወደነሱ ሒጂ» አለች ነህላ ተስፋ ቆርጣ::

«የተፈጥሮ አደጋ ሀገራቸውን ያበለቀቃቸውን እነዚያን አጫጭር ፍጥረቶች አልወዳቸውም::»

«ግን ለችግርሽ ይሆኑሻል:: በሁለት መቶ ሪያልም ቢሆን ይቀጠራሉ::»

«የነሱ ችግር ምን መሰለሽ» አለች ሴትየዋ ፊቷን አጥቁራ፣ «እነሱ ሆዳሞች ናቸው::»

«ቤትሽ ስንት ፎቅ አለው?»

«ሶስት::»

«ታዲያ እንደቤትሽ ትልቅነት ሌማትሽም ሙሉ ሆኖ መገኘት አለበት» አለች ነህላ በምፀት::

«እንዴት?»

«ሰራተኛ ማሰራት ብቻ ሳይሆን ማብላት መቻል አለብሽ!»

ሴትየዋ ሳቀች፣ «ስስት መስሎሽ ነው አይደል? እኔና ባለቤቴም ሆነን ልጆቼ ብዙ የመብላት ልምድ የለንም:: ውፍረታችንን መቀነስ እንፈልጋለን:: የምንሸምተው እስቤዛም የተመጠነ ነው::»

«ስለዚህ ሰራተኛሽን እንዳንቺ ሰላጣ እንድትበላ ፈርደ ሽባታል::»

«ያን ያህል ባይሆንም እኔ የማልፈልገውን እንድታደርግ አልፈቅድም» አለች ሴትየዋ ፈርጠም ብላ::

«እንደዛ ከሆነ ሰራተኛ ስመቅጠር አትድከሚ::»

«ሀበሾች ግን ይስማሙኛል:: ለምግብ ግድ የላቸውም:: ስራቸውን ከምንም በላይ ያከብራሉ::»

ነህላ ፈገግ አለችና፣ «ግን በርካሽ አይቀጠሩማ» አለቻት::

«በሰባት መቶ ሪያል ካልሆነ አትሔዱም?»

«አንሄድም::»

«ሀይለኛ ነሽ፣ ሀይለኛ ሴት ደግሞ እወዳለሁ:: ስለዚህ ተመልሼ እወስዳችኋለሁ:: የስራችሁ ሁኔታ ታይቶ ደካሞች ከሆናችሁ ግን ይቀነስባችኋል:: እዚሁ ጠብቁኝ መጣሁ» ብላ ሴትየዋ ሄደች::

ነህላ በአይን የምታውቃትን አንዲት ሀበሻ ጠርታ ስለሁኔታው ካስረዳቻት በኋላ አብረው መጠበቅ ጀመሩ:: ሰአታት ከነፉ:: ወፍራሟ ሴት ግን አልተመለሰችም::

«ሴትየዋ ቀረችኮ » አለች ሀያት ተጨንቃ::

«ትንሽ እንጠብቃትና እንሔዳለን:: ይህ የተለመደ ስለሆነ አያስገርምም» አለች አንደኛዋ ሀበሻ ግዴለሽ ሆና:: «በደሞዝ ካልተስማሙ አንፈልግም ማለቱን እንደውርደት ስለሚቆጥሩት ኀትረውን ይጠፋሉ::»

ሌሊቱ አጋማሽ ላይ ሶስቱ ሴቶች በሞኝነታቸው እየተሳሳቁ ወደየቤታቸው ሄዱ::

## ምዕራፍ አስራ አምስት

ሀያት ሰላሳ ደቂቃ የፈጀውን ታሪኳን እንዳጠቃለለች ነህላ በትካዜ የሀያትን ፊት ስታጠና ቆይታ «አዝናለሁ፤ የኔ እድል ደግሞ ካንቺ የከፋ በመሆኑ ሀዘኔ ይቀንሳል» አለቻት።

«እንዴት?»

ነህላ በስጨት ብላ «... እኔ የግብዝ ቤተሰቦቹ ሰለባ ነኝ» አለች። «እናቴ ከእህቶቿ ጋር ለመፎካከር ነው ወደዚህ የሰደደችኝ። አባቴም በዚህ ደስተኛ ነው። ጅዳ ከተማ የሚኖሩት ሁለቱም የእናቴ እህቶች ባለትዳሮችና የልጆች እናቶች ናቸው። ቤተሰቦቼ እንግዲህ ከነኚህ አክስቶቼ ጋር ለመፎካከር ነው ወዲህ የላኩኝ። ሁለቱ አክስቶቼ የኢህአፓ አባሎች ነበሩ። ስለዚህ ከሌሎች ጓዶቻቸው ጋር ለሁለት ወራት ያህል እኛ ቤት ተደበቁ። በመጨረሻም ሁኔታው አሳሳቢ እየሆነ ስለመጣ እናቴን ተሰናብተው በእግርና በመኪና እያቆራረጡ ጅቡቲ ገቡ። አመት ቆይተው ወደዚህ መጡ።»

«ጉብዞች!» አለች ሀያት በአድናቆት።

«ከሞት በማምለጣቸው ያደነቅሻቸውን ያህል ግን በኔ ላይ በፈፀሙት ድርጊት ታፍሪባቸዋለሽ» አለች ነህላ ቅዝዝ ብላ። «አክስቶቼ እኛ ቤት በተሸሸጉበት ወቅት ከሚያድሩበት ክፍል ወለሉን ቆፍረው የቆርቆሮ ቀለሞችን፣ ብሩሾችን፣ ፀረ-መንግሥት ይዘት ያላቸው በራሪ ወረቀቶችንና ሶስት ሽጉጦችን ቀብረው ትንሽ መደብ ሰርተውበት ነበር። ታዲያ በዚህ ክፍል ከነሱ ጋራ ተሸሽጋ የነበረች አንዲት ወጣት በደርግ ካድሬዎች ተይዛ በአረመኔያዊ ሁኔታ ሲያሰቃዩዋት ሚስጥሩን ታወጣለች። ቤታችን በልጅቷ ጠቋሚነት ተፈተሸ። የተቀበረውም ወጣ። አባቴና እናቴ ለእስር ተዳረጉ። ከብዙ

ውጣ ውረድ በኋላ ሲፈቱ የአባቴ ብቸኛ አውቶሞቢል በቀማኞች ባለጊዜዎች ተወስዳለች:: እናቴ በዚህ ተበሳጭታ ከእህቶቿ ጋር ሀይለቃል ያዘሉ ደብዳቤዎችን ተለዋወጠች:: በመጨረሻ 'መቃብሬ ላይ አትቁሙ ' ብላቸው ተቆራረጡ:: ይህን ሁሉ እያወቁ ወደጅጂ እንድመጣ የወሰኑትን ቤተሰቦቼን ሳልቃወም ከመነሳቴ ቀደም ብዬ ለአክስቶቼ ፃፍኩላቸው:: ግን መልስ አልሰጡኝም::»

«ታዲያ ጅዳ እንደገባሽ ማን ዘንድ አረፍሽ?»

«ይዞኝ የመጣው 'የውሸት ባል' በህብረት ከተከራዩ ልጆች ጋር ቀላቀለኝ» ነህላ በረጅሙ ተንፍሳ ወጓን አቋረጠች::ሀያት ዝምታዋ ስለረዘመባት «ጨርሺልኝ እንጂ?» አለቻት::

«መካ ለሶስት ወራት ተወዘፍኩ:: አራተኛው ወር ላይ 'የውሸት ባሌ' ወደእውነተኛ ባልነት ለመቀየር እየዶለተብኝ እንደሆነ ሰማሁ:: የሀገሪቱ ህግ የመኖሪያ ፈቃድ ከሌላት ሴት ጋር ትዳር መመስረትን አይፈቅድም:: ስለዚህ ተቆልፎብኝ ልጆች መቀፍቀፍ ብቻ ነበር ዕድሌ:: ከዚያ ክፉ ሰው ለማምለጥ አክስቶቼን እንዲደብቁኝ ለመንኳቸው:: የመጀመሪያ ምላሻቸው ጥሩ አልነበረም:: ተከታዩ የስልክ ጥሪዬ ግን ከለላ አስገኘልኝ:: ቤታቸው ወሰዱኝ::»

«ላንቺ የነበራቸው አመለካከትስ እንዴት ነበር?»

«እንደሰውም አይቆጥሩኝም ነበር:: በመጨረሻ ባደረብኝ ብስጭት ታመምኩ:: ሶስት ወራት አዛኝ በሌለበት መተኛት፣ ጆሮዎች በማይሰሙበት መቃተት፣ አይኖች በማያዩበት በህመም መዛል ምን ማለት እንደሆነ ይታይሽ? ....»

«አላሳከሙሽም?»

«ቀድሞውኑ የት አዩኝና ያሳክሙኛል? ሲብስብኝ ጅዳ ትኖር የነበረች አንዲት ጓደኛዬን እንዲያገናኙኝ ተማፀንኳቸው:: አልሰሙኝም:: የኩላሊትና የጨጓራ ህመም ስለተደራረበብኝ እግሮቼ

አጣብጠው መራመድ ተሳነኝ:: ተስፋ ስለቆረጥኩ ለፖሊስ እጄን ለመስጠት በወሰንኩ ጊዜ ግን እክስቴ ጓደኛዬ ቤት ለመሔድ እንድዘጋጅ አዘዘችኝ:: ሻንጣዬን ግን እዛው እንድተወው በመታዘዜ ባዶ እጄን ተከትያት ወደጓደኛዬ ዘንድ ሔድኩ:: እክስቴም ጓደኛዬ ቤት እንዳድር ፈቅዳልኝ ወደቤቷ ተመለሰች:: ተመልሳ ልትወስደኝ የገባችውን ቃል ግን አልጠበቀችም::»

«ሻንጣሽስ?»

«ደጋግሜ ጠየቅኋቸው፤ አላመጡልኝም:: ልብሴ በላዬ ላይ ነተበ:: በወቅቱ ደግሞ ጓደኛዬ ስራ ፈትታ ስለነበር እዚህ መካ ከምትኖረው ጓደኛዋ ከፊደራሩዝ ቤት እንድቀመጥ ሰደደችኝ:: ለአራት አመታት ያህል ከቦታ ቦታ ስንከራተት ቆየሁ::» የነህላ አይኖች በእንባ ተሸፈኑ::

«አይዞሽ ምንም ቢሆን ....» የሀያት ንግግር ከቀጣዩ ክፍል በሚሰማው ድምፅ ተቋረጠ::

«እህ! .... ወይኔ እናቴ! ... እህህ ... እ.እ! ኡሁ! ....»

ከሳምንት በላይ የታመመው ፈሪድ ነው:: ወደሆስፒታል እንዳይሔድ የመኖሪያ ፈቃድ የለውም:: የግል ክሊኒኮች ክፍያ ደግሞ አይቀመስም::

«ዛሬስ ጠንቶበታል» አለች ነህላ ፈሪድ ወደተኛበት ክፍል ለመሔድ እየተነሳች:: ሀያትም ተከተለቻት:: ሀያትና ነህላ ተከታትለው ሲገቡ ከፍራሹ ወርዶ መሬት ላይ ዘንበል ያለ ጭንቅላቱን ቀና አድርጐ ነህላን እየተመለከተ፤ «የመታጠቢያ ስሀን ... ፍጠኝ ... እህ ... እሁ! እሁ!» አለ በደከመ ድምፅ:: ነህላ ስሀኑን አምጥታ ወዳፉ አስጠጋችና ደግፋ አቀናችው::

ለረጅም ጊዜ ያለፋታ ሲስል ከቆየ በኋላ ተንጠራርቶ አክታውን ተፋ:: አክታው ደም ነበረበት:: ትናንሽ አይኖቹ ይስለመለማሉ:: ሀያት ቀዝቃዛ ውሀ የተነከረበት ጨርቅ አምጥታ ግንባሩንና ደረቱን አበሰችለት:: ጥቂት አቃስቶ አንቀላፋ::

እነሀያትና ሦስቱ ወንዶች ደባሎቻቸው ሌሊቱን ሙሉ ፊሪድን ሲያስታምሙ አደሩ:: ሁሉም በሀዘን ተውጠዋል:: ፊሪድ እየቆየ ለረጅም ጊዜ ይስላል:: ሣሉ ሻል ያለው ሲመስል ይወራጫል:: የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ግራ ተጋብተው በሽተኛውን ይመለከቱታል::

«መሞቴ ነው አንድ ነገር አድርጉ .... » ብሎ ፊሪድ ድንገት እንደጨው ከነጣ ፊቱ ላይ ላብ የሚጠርግለትን እጅ ጨመደደው::

«በቃ የመጣው ይምጣ ሆስፒታል ይዘንህ እንሒድ» አለ ያሲን ሀዘን ያጠላበት ፊቱን ወደበሽተኛው አዘቅዝቆ::

«ክንቱ ድካም ነው:: እናንተ ከዚህ ቤት መውጣት የለባችሁም::»

«ሌላ አማራጭ የለንማ» አለ ያሲን::

«ላበቃለት ፊሪድ ሲባል የናንተ ህይወት መበጥበጥ የለበትም:: ስለዚህ ...» ብሎ ንግግሩን አቋረጠ::

«ስለዚህ ምን?» ያሲን የራቀውን የፊሪድን ድምፅ ለመስማት ይበልጥ ወደበሽተኛው ተጠጋ::

« እኔ ... እኔ መውጣት አለብኝ»

«ምን?!» ሁሉም ጮሁ::

«ከአንድ ስርቻ ውስጥ ጣሉኝ:: ከዚያ ፖሊሶች ሬሳዬን ያነሱታል::» ሳሉ ተቀሰቀሰበት:: «... እህ... ወይኔ እናቴ ... ህልሜ

እውን ሳይሆን ... ሁሉም ነገር .... አበቃ!» ፈሪድ አረፋ መድፈቅ ጀመረ::

ምሽቱ ላይ የፈሪድ አካል ቀስ በቀስ ቀዘቀዘ:: ከአፉ እየተንኳለለ የሚወጣው አረፋ ቆሟል:: ከንፈሮቹ ከውበት መስለው ተሰነጣጥቀዋል:: ከቀትር በኋላ ገርበብ እንዳሉ ያልተገለጡ አይኖቹ ከጉድጓዳቸው ተሸሽገዋል::

የምሽቱ የመግሪብ ሰላት ጥሪ ሲሰማ ፈሪድ በስቅታ ተመታ:: ጥርሶቹ ተፋጩ:: ከፉኛ ተንዘፈዘፈ:: የመጨረሻው የኢሻዕ ሰላት ጥሪ ሲሰማ በሽተኛውን እንቅልፍ ወሰደው:: የፈሪድን በሞት መነጠቅ የተነበዩት ጓደኞቹ ሰውነት ተፍታታ:: ለአጭር ጊዜም ቢሆን ሰፍኖ የነበረው ውጥረት ረገበ::

«አባባ! አባባ! ...» የፈሪድ ጩኸት ፀጥታውን አደፈረሰው:: «ተው ዝናቡ ግንዱን አርጥቦታል ....»

«ምንድነው የሚለው?» ሀያት ያሲንን ጠየቀችው::

«አባቱ አቶ ቃሲም ዛፍ ቆራጭ ነበሩ:: እንጨት ለመቁረጥ ሲሔዱም ፈሪድን ያስከትሉት ነበር:: አንድ ቀን አቶ ቃሲም የኤሌክትሪክ ገመድ ሊበጥስ የተቃረበ ቅርንጫፍ ለመቁረጥ ዛፍ ላይ ወጡ:: ሲወርድ ያደረው ዶፍ ዛፉን አርጥቦት ስለነበር ፈሪድ በስጋት ተውጦ፣ 'አባባ ተጠንቀቅ!' ይላል እየደጋገመ:: አባቱ ግን አይሰሙትም:: መጥረቢያቸውን እያወናጨፉ ነበር:: ጥቂት እንደሠሩ መጥረቢያቸውን ቅርንጫፉ ላይ በሃይል ለማሳረፍ ግንዱን ረግጠው ሲንጠራሩ አዳልጧቸው ቁልቁል ተምዘገዘጉ:: አልተረፉም::

«ፈሪድ አባቱን በቀበረ በሶስተኛ አመቱ የጐረቤቱ ልጅ ፀዳለ ከአንዲት የክፍል ጓደኛዋ ጋር አስተዋወቀችው:: 'ሉባባ ጅዳ ለመሔድ ታስባለች' አለችው:: ሉባባ ከዓመት በፊት ወደሳዑዲ

አረቢያ ከወንድሟ ጋር ለመሄድ ሞክራ ነበር፡፡ የአዲስ አበባውን ሀጅና ዑምራ ቢሮ ፈተና ወንድሟ ማለፍ ስላልቻለ ትታው ልትሄድ ወሰነች፡፡ ፈሪድም ወንድሟን እንዲተካ ነው የተፈለገው፡፡ ሀሰተኛ መረጃ ተሰበሰበ፡፡ ሉባባና ፈሪድ ወንድምና እህት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ አገኙ፡፡ በመጨረሻም ለፈተና ቀረቡ፡፡ ለሀይማኖቱ እንግዳ ላልነበረው ፈሪድ ፈተናው ቀላል ነበር፡፡ በሉባባ ወጪ ከወር በኋላ ጅዳ ገቡ፡፡ በአራት አመቱ እነሆ ለዚህ በቃ!» አለ ያሲን በትካዜ ተውጦ፡፡ ፈሪድ አይኖቹን ከፈተ፡፡ ያሲን ፈጥኖ እጁን ያዝ አደረገ፡፡ ቀዝቅዟል፡፡ ያሲን ወደኋላው ተፈናጥሮ፣ «ሞተ!» ሲል ጮኸ፡፡

ሶስቱ ወንዶች ሴቶቹን ወደሌላ ክፍል እንዲሔዱ አድርገው የፈሪድን አስከሬን በጋቢ ጠቅልለው ምሽቱ እስኪገፋ ጠበቁ፡፡ ሌሊቱ እንደተጋመሰ ተሸክመውት ወጡ፡፡

ደብዛዛዎቹ የቤት መብራቶች ወደማይበዙበት መተላለፊያ ይዘውት ከሔዱ በኋላም በተርታ ከቆሙ የቆሻሻ በርሜሎች ጀርባ አጋደሙት፡፡ ሲነጋ ያሲን ኢትዮጵያ ኤምባሲ ደውሎ ቦታውን ይጠቁማል፡፡

* * *

«ውጣልኝ!» አለ ሙአዝ በጩኸት፡፡
«እሺ ገንዘቤን ስጠኛ?» መጅድ ለስለስ ማለቱን መርጧል፡፡
«ሰባራ ሪያል እኔ ዘንድ የለህም!»
«እርግጠኛ ነህ?» አለ መጅድ እንደተረጋጋ፡፡

«ትሰማኛለህ? እኔን ለማይረባ ገንዘብ ከምትጨቀጭቀኝ ከነከሪም ጋር የጀመርከውን ወዳጅነት አጠናክር:: ጥሩ ሸሪኮች ይወጣችኋል::»

«ካንተ የተሻልኩ አጋራቸው እንደምሆን አምናለሁ::»

«እንግዲያውስ እነሱን በስድስት ሺ ሪያል ሸጬልሀለሁ::»

«ምን?» አለ መጅድ ተደንቆ::

«ያሸፈትካቸው ጭፍሮቼ ከስድስት ሺ ሪያል በላይ ያወጣሉ::»

«ስንት ያወጣሉ?»

«የገንዘቡ ብዛት ሊያስደነግጥህ ይችላል:: ለራስህ በገንዘብ እጦት እንቅልፍ አጥተሃል:: ባይሆን ወደፊት ከነከሪም ጋር ስትሠራና ጥሩ ገቢ ሲኖርህ ጉራ ብትል እንነጋገራለን::»

«ደደብ!» አለ መጅድ በንዴት::

«እነዛን የማይረቡ ጥንቸሎች ባለመግደሌ ከደደብ በላይ ነኝ::»

«ቱፍ!» ብሎበት መጅድ ሊደባደብ ተነሳ::

ይኸኔ ጭቅጭቃቸውን በዝምታ ሲከታተል የነበረው አርአያ ብድግ ብሎ፣ «እባካችሁ ....» እያለ ይማፀናቸው ጀመር::

«ምን ለመሆን ነው?» አለ ሙአዝ መጅድ ላይ አፍጥጦ::

«አትሰጠኝም?» አለ መጅድ በዛቻ::

«እምን፣ አልሰጥህም::»

«ጥሩ!» መጅድ ጥርሱን ነክሶ ወደፊት ተራመደ:: አርአያም እስከበር ሸኘው::

# ምዕራፍ አስራ ስድስት

ከኢኔኪሽ የእንጀራ መሸጫ ፊት ለፊት የምትገኘው ሳባ ሬስቶራንት እንደወትሮዋ በበርካታ ሀበሾች ተጨናንቃለች:: የምሽቱ የመጨረሻ ሰላት ተሰግዶ ካበቃ ሰላሳ ደቂቃዎች አልፈዋል:: በስተቀኝ ጨለም ያለውን ማዕዘን መርጦ የተቀመጠው ሀፊዝ የቀጠራቸውን እንግዶች ለመጠበቅ ቀደም ብሎ ነበር ወደሬስቶራንቱ የገባው:: የቀጠሮው ሰአት አስራ አምስት ደቂቃ ቢቀረውም ሀፊዝ ግን እየደጋገመ ሰአቱን ይመለከታል:: ድንገት ሆቴሉ በር ላይ ግርግር ተፈጠረ:: በርካታ ሀበሾች እየተሯሯጡ በሆቴሉ የጓሰኛ በር ይወጡ ጀመር:: ራታቸውን በመብላት ላይ የነበሩ ሀበሾችም ማዕዱን ትተው አፈተለኩ:: ድንገት የሆቴሉ ባለቤት አሊ ከገንዘብ መከፈያው የመስተዋት ሳጥን ውስጥ ወጥቶ «ተፍቲሽ! ተፍቲሽ! (አሰሳ፣አሰሣ)» እያለ ይጮህ ጀመር:: አሊ የኤርትራና የሳዑዲ አረቢያ ተወላጅ ነው:: የአሊን ማስጠንቀቂያ የሰሙ ህገወጥ ስደተኞች መደበቂያና መሸሎኪያ ቀዳዳዎችን በፍጥነት ይጠቀማሉ:: አሊ አንዳንድ ህገወጥ ሰራተኞቹም በዚህ ግርግር እንዳይጠለፉበት ስለሚፈልግ ምንጊዜም የሆቴሉን የጓሮ በር ክፍት ያደርግላቸዋል::

ትርምሱ እንዳበቃ ጥቂት ፈቃድ ያላቸው ሀበሾችና አንዳንድ አረቦች ብቻ ምግብ ቤቱ ውስጥ ቀሩ:: ከዚያም በርከት ያሉ ፖሊሶች ወደሆቴሉ ገቡ:: ፖሊሶቹ የውጭ ዜጐችን ነጥለው መታወቂያ ይጠይቁ ነበር:: ሀፊዝ በድርጊቱ እያዘነ እንዳለ የሬስቶራንቱን በር አልፈው ወደእሱ የሚያመሩ ሁለት ሰዎች ተመለከተ::

«አሰላሙ አለይኩም፤ እንኳን ደህና መጣችሁ!» አለና ሁለቱንም ጨብጦ እንዲቀመጡ ጋበዛቸው።

«ዘገየን?» አለ አርአያ ቦታውን እንደያዘ።

«በሰአቱ ነው ከች ያልነው!» ብሎ ሙአዝ ሳቀ።

ሀፊዝ ሰአቱን እየተመለከተ«በሉ እንሂድ፣ ሰሚራ እየጠበቀችን ነው» አለ።

«ሰዎቹስ?»ሲል አርአያ ግራ ተጋብቶ ጠየቀ።

«ሰሚራ ቤት ነው የቀጠርኳቸው» በማለት ሀፊዝ መለሰለት። በመኪናቸቸው ተከታትለው ወደሀየ ሰላማ አመሩ። ሰሚራ ቤት እንደደረሱ የቀረበላቸውን ውስኪ በመጠኑ ተጎንጭተው ወደምግብ ቤቱ ሄዱ። የምሽቱ ወበቅ ያስጨነቀው ሀፊዝ ኮቱን አውልቆ ከሳሎን መስቀያ ላይ አንጠልጥሎ ሲመለስ ከሶፋው መደገፊያ የተጣሉትን የሙአዝንና የአርአያን ጃኬቶች ስለተመለከተ «ጃኬቶቻችሁን እዚህ ላይ ስቀሉ» ብሏቸው ወደምግብ ቤቱ ሔደ።

አርአያና ሙአዝ በሀፊዝ አማካኝነት ከሌሎች አዘዋዋሪዎች ጋር ተገናኝተው የመጠጥ እጥረታቸውን ለማቃለል ቸኩለዋል። ሶስቱ ወንዶች ጠረጴዛው ዙሪያ ሲሰየሙ ሰሚራ ይቅርታ ጠይቃ ተነሳች። ከምግብ ቤቱ ወጥታ ኮሪደሩን አቋርጣ በጥንቃቄ የመግቢያውን በር ቁልፍ ሶስት ጊዜ ድምፅ ሳታሰማ አዞረችው። እጀታውን ይዛ ለመክፈት መቻሉን ካረጋገጠች በኋላም ወደማዕድ ቤት ሄዳ በጠርሙስ የተሞላውን የሎሚ ጭማቂ ከአራት ብርጭቆዎች ጋር ይዛ ስትመለስ ወንዶቹ የደራ ወሬ ይዘዋል።

* * *

ፍስሃ እቅዱን ለማሳካት ዝግጅቱን አጠናቋል:: ካረጀችው ቀይ ቶዮታው መሰስ ብሎ ወጥቶ የሰሚራ አፓርትማ ወደሚገኝበት ህንፃ ተጠጋ:: ጥቁር፣ ግዙፍ ሰው ከህንፃው መግቢያ በር ላይ ተለጥፎ ቆሟል:: አጠገቡ ሲደርስ የእጅ ምልክት ሰጠው:: ከዚያም የኮቴውን ድምፅ ለመቀነስ ደረጃውን በጥንቃቄ እየረገጠ ወጥቶ ሁለተኛ ፎቅ ከሚገኘው ቀይ በር ሲደርስ ቆሞ ትንፋሹን ሰበሰበ::

በሩ አለመቆለፉን ለማረጋገጥም በቁልፉ ቀዳዳ አጮልቆ በቀስታ በሩን ገፋው:: ተከፈተ:: ለስላሳውን ምንጣፍ በጥንቃቄ እየረገጠ ገርበብ ወዳለው ሳሎን ገባ::

ከተሰቀሉት ጃኬቶች ወደአርአያ ጃኬት እጁን ሰደደ:: ባዶ ነበር:: በሌላኛው በኩል ሞከረ:: ምንም የለም:: ፀጉሩን ቆፈረና ወደሙአዝ ጃኬት ተሻገረ:: የአፍንጫው ጫፍ በላብ መወርዛት ጀምሯል:: ቀዝቃዛ የቁልፍ ስብስብ በእጁ ነካ:: ቁልፎቹን እኪሱ ከቶ እንደአገባቡ በጥንቃቄ ከአፓርታማው ወጣ:: መግቢያው በር ላይ የቆመው ሰው በተጠንቀቅ እየጠበቀ ነበር::

ወዲያውኑ ቀይዋ ቶዮታ ቀኟን ይዛ ከነፈች:: ከሰሚራ ቤት ብዙም ከማይርቀው የአርአያና የሙአዝ መኖሪያ ሲደርስ የመኪናውን ሞተር ሳያጠፋ በፍጥነት ወደአራተኛው ፎቅ ሮጠ:: በሩን ከፍቶ ሲገባ በደብዛዛ መብራት ደንገዝገዝ ያለው ሳሎን ተቀበለው:: በፍጥነት ወደማዕድ ቤት ሔደ:: ጉልበቱ ይብረከረክ ጀምሯል:: ሆኖም ፈጥነው ከወጡ ሕንፃው መግቢያ ላይ የቆመው ሰው መሰናክል እንደሚፈጥርባቸው ስላስታወሰ መልሶ ተረጋጋ:: ማቀዝቀዣውን ሲከፍት የዕፅ እሽጐች አገኘ:: በችኮላ ጃኬቱ የውስጥ ኪስ ከትቶ በሮቹን ዘጋጋና ወደመኪናው ገሠገሠ:: ሰሚራ ቤት እንደደረሰ መኪናዋን ከመግቢያው ትይዩ አቁሞ ሰአቱን ተመለከተ::

ግዳጁን በሰባት ደቂቃ ውስጥ አጠናቋል:: በቀሪዋ አምስት ደቂቃ ቁልፉን መልሶ ከአካባቢው መሰወር አለበት:: ብዙም ሳይጣደፍ ቁልፉን እነበረበት መልሶ ከህንፃው ወጣ:: በኩራት መኪናውን እያሽከረከረ የመጣበትን አስፋልት በቀኝ ትቶ በስተግራው ሱቅ ሰዋሪ የገበያ ማዕከልን አልፎ፣ ከከሪም ጋር አዲስ ቤት ወደተከራዩበት ወደ ሀየረውዳ ሠፈር ተጓዘ:: አዲሱን አፓርታማ ከፍቶ ወደውስጥ እንደዘለቀ ድሉን ለከሪም ለማብሰር ስልክ ደወለ:: ከሪም ሀየር በዋዲ ሠፈር እነሙአዝ ተከራይተውላቸው ለአመታት የኖሩበት አፓርታማ ውስጥ ቁጭ ብሎ የሱን ጥሪ እየጠበቀ ነበር::

*　　　　*　　　　*

ከሳምንት በፊት ባየችው የሞት አደጋ ልቧ በሀዘን የተሠበረው ሀያት ከአካባቢው ለመራቅ ፈልጋለች:: በየሣምንቱ ሀሙስ ለዕረፍት እየመጡ ሲንጫጩ አድረው፣ ሲንጫጩ ውለው የሚሔዱት ሴቶች ጭንቀቷን ሊገፉላት አልቻሉም:: መካ ከተማ ስራ የማግኘት ዕድሏም ተሟጧል::

ከፈሪድ ሞት በኋላም ወደሀረም መሔድ ትታለች:: ዛሬ ግን ነህላ አብረው እንዲሄዱ እየወተወተቻት ነው:: ሀያት እየቀፈፋት ለመሔድ ተስማማች::

ያሲን ያለወትሮው ቀትር ላይ ወደቤት መጥቶ በፀሀይ ብዛት ከሌላው አካሉ ለየት ብሎ የጠቆረ ፊቱን ሳይፈታ ተቀመጠ:: ነህላ ምሣ እንዲበላ ብትጠይቀው እንደማይፈልግ ገለጸላት:: ነህላና ሀያት ሲነሱ «ወዴት ልትሔዱ ነው?» ሲል የተቋጠረ ግንባሩን ሳይፈታ ጠየቃቸው::

«ወደሀረም» አሉት በአንድ ድምፅ::

«መሔድ የለባችሁም» አላቸው:: ሴቶቹ በመገረም ተያዩ::

«አንዳንድ ህሊናቸውን ለገንዘብ የሸጡ የሀገራችን ልጆች ሴቶቻችንን እያታለሉ በመውሰድ ለወንዶች መቸብቸብ ስለጀመሩ አርፋችሁ ብትቀመጡ የሚሻል ይመስለኛል:: ለምሣሌ ስራ ፍለጋ ሀረም ይቀመጡ የነበሩ ስምንት የኛ ሴቶች የደረሱበት አልታወቀም:: ሁሉም ተሸጠው መጥፋታቸውን እናምናለን::»

«ማን ነገረህ?» አለች ነህላ በቀስታ::

«አብረዋቸው ይኖሩ የነበሩት ወንዶች ናቸው የነገሩኝ::»

ህያት በዝግታ ፍራሹ ላይ ተቀመጠች:: ከዚያም ቅዝዝ እንዳለች ስልኩን አነሳች::

* * *

ከሪም የፍሰሃን የስልክ ጥሪ በተቀበለ ማግስት ማልዶ ነበር የተነሳው:: የቀሩትን የቤት ዕቃዎች ለማስጫን መኪና ያለውን ፓኪስታናዊ ወዳጁን በጠዋት እንዲመጣ ቀጥሮታል::

በሰአቱ የደረሰው ፓኪስታናዊ የቤት ዕቃዎቹን አመላልሶ እንደጨረሰ ሂሣቡን ተቀብሎ ሲሔድ የዙህር ሰላት ደርሶ ነበር:: ከሪም በየጊዜው እየገዛ ያጠራቀማቸውን የቤት ዕቃዎች የኔ ወደሚለው ቤት አሻግሮ እንደጨረሰ እፎይታ ተሰማው:: ከቤቱ ባለቤት ከአቡ ሳሚ ጋር ሒሳብ አወራርዶ፣ ክፍሎቹን እያዟዟረ አንዳችም የተበላሸ ነገር አለመኖሩን አሳያቸው:: ሁሉንም ነገር እንዳጠናቀቀ ሽማግሌው አቡ ሳሚ ሸውራራ አይናቸውን በጥርጣሬ ከሪም ላይ ተክለው፣ «ቤቱን በስሙ የተከራየው ሙአዝ አልነበረም እንዴ?» አሉት::

«አዎን፣ አዎ..» አለ ከሪም ተደናግጦ:: ሽማግሌው ሙአዝን ማግኘት አለብኝ ካሉት በትላንትናው ሌሊት የተፈፀመው ድርጊት ሳይውል ሳያድር መታወቁ ነው::

«እስካ ካርቱም እንደሔደ አልተመለሰም» አለ ከሪም በአሳማኝ ቅላፄ::

የሽማግሌው ፊት ፈታ አለና «ያኔ እቃውን ያስጫነው በወንድሜ የካርጎ ቢሮ በኩል ነበር:: እስከአሁን አልተመለሰማ!? የሀገሩ ናፍቆት አልወጣለት ብሎ ነው?» አሉ::

«እንደዚያ ቢሆን ነዋ እንግዲህ» አለ ከሪም ጀነን ብሎ::

«ለመሆኑ እቃው በደህና ደረሰለት?» አሉ ሽማግሌው ጥምጥማቸውን እያስተካከሉ::

«አዎን፣ ኸረ እንዲያውም እርሶንም፣ ወንድምዎንም እንዳ መሰግንለት አደራ ብሎኛል:: ረስቼው ነው» አላቸው::

ሽማግሌው እንደድመት ጥርስ የሾሉ ጥርሶቻቸውን ብልጭ አድርገው፣«ሹክረን! ሹክረን!»አሉ::

«መቼስ እዚህ ብንሆን ደስ ይለን ነበር:: ነገር ግን እህቶቻችን በሚቀጥለው ኡምራ ስለሚመጡ ቤት መቀየር ተገደድን:: እርሶ እንደሁ ሴት ያለበት ቤተሰብ አይወዱም» አላቸው እየተቅለሰለሰ::

«አይ! ሴት ያለበት ሙሽኪላ (ችግር) አይጠፋም:: እንኳን ሳላስቀ ይማችሁ ፍላጐቴን ተረዳችሁልኝ:: ባይሆን እንደናንተ ያለ ጥሩ ሰው ካገኘህ አምጣልኝ:: ካልሆነ አቃሪዎችን (ደላሎችን) ደጅ መጥናቴ ነው» አሉ ሰልቸት ብለው::

«አቃሪ? እስከዛም አይደርሱም። የኔ ጓደኞች ጥሩ ቤት ይፈልጋሉ። አመጣቸዋለሁ»አለ ከልብ የመነጨ በሚመስል የተቆርቋሪነት ስሜት።

ሽማግሌው ሳቅ ሲሉ፣ ስልኩ ተንጫረረ።

ከሪም ደንግጦ አነሳውና፣ «ነአም?» አለ።

«ከሪም ነህ?» የሚል የሴት ድምፅ ተሰማው።

«ነኝ ማን ልበል?»

«ሀያት ነኝ። ከሪሜ...እ..እኔ ...» ድም፧ በለቅሶ ይቆራረጣል።

«ሀያት ምን ሆነሻል?» አለ ተደናግጦ።

«ከሪም ወዳንተ መምጣት እፈልጋለሁ።።»

«ፈይሩዝ ስራ አላገኘችልሽም እንዴ?»

«ለመስራት የሚቻልበት ቦታ አይደለም» አለችው ሳግ እየተናነቃት።

«ሀያት፣ እዚህ ለጊዜው ያልተረጋጋ ሁኔታ ስላለ ለጥቂት ሳምንታት ...»

«አልችልም ከሪም! አልችልም!» ስትል ጮኸች።

«እሺ. እንድትመጪ አደርጋለሁ። አታልቅሺ፣ ነገ ሀፊዝ ስለሚመጣ ተዘጋጅተሽ ጠብቂው።።» ስልኩን ዘግቶ ቀና ሲል መጅድ በሩ ላይ ቆሟል። ሽማግሌውን ባይኑ ፈለገ። መቁጠሪያቸውን እያሽከረከሩ አቀርቅረው ያነበንባሉ።

«ፍሰሃ ህፃናቱን እየተንከባከባቸው ነው?» አለ መጅድ ፈገግ ብሎ።

«በሚገባ ...» ወደሱ እየተጠጋ መለሰለት።

«ላደረግሁለት እገዛ አላመሰገነኝም?»

«ማታ ወደቤት የወሰዳቸውን የሁለት ኒዶ ወተት ዱቄቶችን ግማሽ ዋጋ ...»

«ግማሽ ዋጋ?! እኔ የጠየቅሁትኮ የጡጦ መግዣ ብቻ ነው:: ይህ ግን ብዙ ነው:: ጉጆ ወጪዎች ሆናችሁ ይህን ያህል ገንዘብ አልወስድባችሁም::» ከሪም የተጠቀለሉ የሪያል ኖቶች አስጨበጠው:: መጅድ ጥቅሉን ኪሱ እየጨመረ «ሙአዝ ይህን ያህል ደግ መሆናችሁን ቢያውቅ ምን ይሰማዋል?» አለ::

«ህመም» ሲል መለሰ ከሪም:: ሁለቱም በአንድ ላይ ሳቁ::

* * *

ረቡዕ ምሽት ማቀዝቀዣው ውስጥ የነበሩትን እሽጉች ያጣው ሙአዝ ባዶዎቹ ብርጭቆዎች ላይ አፍጥጦ ቀረ::

'የት ገቡ?' ሲል ራሱን ጠይቆ እየተቻኮለ ወደሳሎን ተመለሰ:: ሶፋው ላይ ቁጭ እንዳለ በሲጋራው ጭስ የተሸፈነው አርአያ በሀሳብ ርቆ ሔዷል::

«አርአያ ጉድ ሠሩን!» አለ ሙአዝ ጮክ ብሎ::

አርአያ ከእንቅልፉ እንዳባነኑት «ምን አልከኝ?» ሲል ጠየቀ::

«ጉድ ተሰርተናል!» አለ ሙአዝ ይበልጥ ጮሆ::

«የምን ጉድ?»

«እሽጉቹ ተሠርቀዋል!»

«ምንድነው የምታወራው?» አርአያ ከተቀመጠበት በቀስታ ተነሳ::

«እነዚህ ዲቃሎች ሰሩልን!» ሙአዝ የሶፋውን መደገፊያ በቡጢ ነረተው::

«እንዴት?»

የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

«ቢቃ፣ መጅድን እገድለዋለሁ!»አለ ሙአዝ በቁጣ፡፡

አርአያ በመገረም «መጅድ ነው የወሰደው ነው የምትለኝ?» አለ፡፡

ሙአዝ የሚናገረው ይበልጥ እየተዘበራረቀበት «ከሶስቱ አንዱ! ...መጅድን ገንዘቡን ከልክየዋለሁ ... ፍሰሃና ከሪምም! ...» አለ፡፡

«መጅድ እንዴት አስር ሺ ላልሞላ ሪያል ሁለት እሽግ ለመውሰድ ይደፍራል?» አለ አርአያ ሙአዝን እያየ፡፡

«እሽጎቹን ቃቅፎ እንጦርጦስ ይወርዳታል! አንድ ብርስት ገዝቶ ሳይበላ ጨጓራውን አስዘክዝክለታለሁ!፡፡»

አርአያ የሙአዝን ድንፋታ ቸለል ብሎ ነገሮችን ማሰላሰል ጀመረ፡፡ በመጨረሻ በስርቆቱ ውስጥ የሀፊዝ እጅ እንዳለበት እርግጠኛ ሆነ፡፡

«ሀፊዝ ነው የሸጠን ሙአዝ»አለ ረጋ ብሎ፡፡

«ሀፊዝ? ምን እያልክ ነው? ...ባለጉዳዮቹ እነፍሰሀ ወይም መጅድ ...»

«ሀፊዝ ከእንደኛቸው ጋር ተመሳጥሯል፡፡»

«አላምንም! ሙሽ ሙምኪን (ሊሆን አይችልም)» አለ ሙአዝ ራሱን በአሉታ እየነቀነቀ፡፡

«ከመጅድ ጋር ከተጣላችሁበትና ፍሰሃንም በእሽጎቹ ላይ ያለንን አቋም ካሳወቅነው እለት ጀምረን ሀፊዝ ቤት እስከሔድንባት ምሽት ከቤታችን አልወጣንም፡፡ ከዚያም በኋላ ይኸው ሙሉ ቀን ቤታችን ነን፡፡» የአርአያ ስሮች ግንባሩ ላይ አብጠው ይታያሉ፡፡

ሙአዝ ቀጭን ፉጨት አሰማና ራሱን ነቅንቆ፣ «የመጠጥ አዘዋዋሪዎቹ ታሪክ ልብ ወለድ ነበር ማለት ነዋ?!» ብሎ ሙአዝ ሀፊዝ ቤት ስለተፈፀመው የመጨረሻ ትዕይንት ያሰላስል ገባ::

ከራት በኋላ ውስኪ እየተጐነጩ የእንግዶቹን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ሳሉ ነበር ስልኩ ያቃጨለው:: ሀፊዝ በውል ያልተሰሙ ቃላትን ተናግሮ እጀታውን ቦታው ሲመልስ፣ ፊቱ በቅሬታ ተሞልቶ ነበር:: ሰዎቹ ለመምጣት ያለመቻላቸውን ለማሳወቅ እንደደወሉ ነገራቸው::

«ግን ሀፊዝ የማን ቅጥረኛ መሆኑ ነው?» አለ ሙአዝ ረገብ ብሎ::

«ያለምንም ጥርጥር የፍሰሃና የከሪም ነው::»

«እንዴት?»

«ሀፊዝና መጅድ'ኮ አይተዋወቁም:: የሀፊዝ ወዳጅነት ከፍሰሃና ከከሪም ጋር ነው::»

«ውሾች! ከጉናቸው ያገኙዋታል! ደግሞ...» ሙአዝ እየደነፋ ወደበሩ አመራ::

አርአያ ከተል ብሎ «የት ልትሔድ ነው?» ሲል ጠየቀው::

«እጠቁማባቸዋለሁ!» ሲል ሙአዝ በፌዝ ፈገግ ብሎ መለሰለት::

«አበድክ እንዴ?»

«አትስጋ፣ ከሻምበሉ ጓደኛዬ ጋ ውስኪ ልጠጣ መውጣቴ ነው:: ብስጭቴን ማስወገድ አለብኝ» ብሎት ወጣ::

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

ምሽቱ እንደተጋመሰ በዝግ መኪና ተጭነው ወደሀየር በዋዲ ያመሩት ፖሊሶች ከህንፃው ትይዩ ተበትነው ቆሙ:: የመገናኛ ሬድዮ የያዘው የቡድኑ መሪ ትዕዛዙን ያሾጉደጉደዋል::በነጭ ቀሚሶቻቸው ውስጥ ከቁርጭምጭሚቶቻቸው በላይ በተንጠሰጠሉ አጭር ሱሪዎቻቸው የሚለዩት ፂማቸውን ያጐፈሩ አምስት የሀይማኖት ጠባቂዎች (ሙጠወእች) ከአዛዡና ከሁለት ፖሊሶች ጋር በመሆን ወደህንፃው ገቡ::

ትንሽ ቆይቶ ዝግ የፖሊስ መኪና ከመግቢያው በር ትይዩ ቆመ:: በውስጡ የነበሩት አስራ ሁለት ፖሊሶች በሁለት ረድፍ ሆነው ህንፃውን ወረሩት::

አራተኛው ፎቅ ሰባት ቁጥር መኖሪያ ቤት ላይ ነበር ያነጣጠሩት:: ለረጅም ጊዜ ደወሉን ተጫኑ:: ነገር ግን ምላሽ ታጣ:: በመጨረሻ በሀይል ተሠብሮ ሰባት ፖሊሶች ወደውስጥ ዘለቁ::

ብዙም ሳይቆይ አምስተኛው ፎቅ ዘጠኝ ቁጥር ውስጥ የሚኖሩ ሁለት የተበላሸ ሙከየፍ (የአየር ማቀዝቀዣ) አዳሽ ግብፃውያን ከፖሊሶቹ ጋር አተካራ ከፈቱ:: አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ «ህጋዊ ነዋሪዎች ነን:: ፈቃዳችን ይኸውልህ!:: ካየኸው ታዲያ ዞር በልልና ስራፈት!» ሲል የፖሊሶቹ አዛዥ ሰማው::

«እነዚህን ጥጋበኞች አምጣልኝ! እኛን ሁል ጊዜ የሚዳፈሩን ግብዎች ብቻ ናቸው። አምጣቸው!» አለ አዛዡ በቁጣ። ሁለቱ ግብዓውያን በውስጥ ሱሪዎቻቸው እንዳሉ ተይዘው አራተኛ ፎቅ ያለው አዛዥ ዘንድ ቀረቡ።

«ጌታዬ? ፈቃዳችንን አሳይተናልኮ ታዲያ ምን አድርገ ትሉናላችሁ?!» አለ አንደኛው በንዴት።

«ጨምላቆች! ማነህ?! ወስደህ ጫንልኝ!» አለ አዛዡ በጩኸት።

ፖሊሱ ሰዎቹን እየነዳ ወረደ። ሶስተኛው ፎቅ ሲደርሱ አንድ ሽማግሌ የመናዊ በራቸው ላይ ቆመው ቤታቸውን የሚበረብሩትን ፖሊሶች በታከተ መንፈስ ይመለከታሉ። በስጨት ብለው ወደመተላለፊያው ሲያመሩ በቁጥጥር ስር ከዋሉት ግብዓውያን አንዱ በማይታመን ፍጥነት ሽማግሌውን ጎትቶ ከፖሊሱ ጋር አላተማቸው። ሽማግሌውም «ዬ ...ህ!» ብለው ከወደቀው ፖሊስ ላይ ዝርፍጥ አሉ። ከዚያም ትርምስ ተከተለ።

* * *

መጅድ ለነፍሰሃ ቃል በገባላቸው መሰረት ሙአዝን በአይነቁራኛ ሲከታተለው ነበር የዋለው። ምሽት ላይ ሙአዝ ፖሊሶቹን ሰብስቦ እነከሪም ወደለቀቁት አፓርታማ ሲሔድ ተመለከተ። እናም ሆየረውዳ ሰፈር ለገቡት ለነፍሰሃ ስልክ ደውሎ ይህንኑ ነገራቸው። አልተገረሙም። ይልቁንም ፈጥነው እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ስላመኑ ፍሰሃ ስልኩን አነሳ።

በተፈላጊ ወንጀለኞቹ ምትክ ያፈሷቸውን ህገ ወጥ ነዋሪዎች በዝግ መኪኖቻቸው አጭቀው እስር ቤት ያጐሩት ፖሊሶች ለሌላ ተልዕኮ ተንቀሳቀሱ:: ሀየ ስላሳ ወደሚገኘው የስሚራ ቤት ነበር ያመሩት:: የአፓርታማው በር ተቆልፎ ሳለ የሚንቀሳቀሰው መብራት በቁልፉ ቀዳዳ ይታያል:: አዛዡ በቀኝ እጁ የያዘውን የመገናኛ ሬዲዮ ወደግራው አዞረና ተቀናጅተው ሁሉንም የአፓርታማ በሮች ለማስከፈት መዝጊያዎችን የሚደበድቡትን ፖሊሶች ቆም ብሎ አዳመጠ:: ከዚያም አንዱን ፖሊስ በሩ ላይ ጆሮውን ለጥፎ እንዲያዳምጥ አዘዘው:: ታዳኝዋ የምታዳምጠው የጆርጅ የሱፍ «ሀቢቢ ኪዳ ... » የሚለው የአረብኛ ሙዚቃ በቀጭኑ ይስረቀረቃል:: ፖሊሱ ቀና ብሎ «ሰው አለ:: ሙዚቃ ይሰማል» ሲል ለአዛዡ ተናገረ:: አዛዡ በሩ ላይ ጆሮውን አስጠግቶ ጥቂት አዳመጠና ፈገግ ብሎ፣ «ሀቢቢ ኪዳ? ...» አለ በሙዚቃው ስልት::

በአሸናፊነት ስሜት `እንደተወጠረ እምስቱን ሙጠወኦች አስጠርቶ ወደበሩ በፍጥነት ሲራመድ፣ በሂና የተኾጐረጐረ ሪዝ ያላቸው ወፍራሙ ሼክ፣ «በሩን አንኳኩ!» ሲሉ ፖሊሱን አዘዙ::

«ላ!»ሲል ተቃወመ ሻምበሉ:: «በር በማንኳኳት ጊዜያችንን አናጠፋም:: ተወዳጇን ጥንቸል ከተመሰጠችበት የሰመመን ዓለም በካቴናዎቼ መንጭቄ አወጣታለሁ» አላቸው ፈገግ ብሎ::

«ዋናው ተፈላጊ እሷ አልመሰለችኝም:: ሰውየው ነው» አሉ ሼኩ እንደተኮሳተሩ::

«እስማ ይሔኔ ከጉኗ ተዘርሯል፡፡ እሱ ለመጠጥና ለሴት እንጂ ለሙዚቃ ቁብ የለውም፡፡»

ሼኩ የሻምበሉን ትናንሽ ጥርሶች ሲመለከቱ ቆይተው፣ «ጥሩ! ስበሩት» አሉ፡፡

ሻምበሉ በሩን በርግጫ በረገደው፡፡ ሳሎን፣ መኝታቤት፣ ማዕድቤት፣ መታጠቢያ ቤት፤ ሁሉም ተበረበሩ፡፡ ታዳኞቹ ግን የሉም፡፡ ሻምበሉ በንዴት እየገለፈጠ አጠገቡ ወደቆመው ሙአዝ ዞረ፡፡ ሰሚራ መኝታ ቤት ውስጥ ብቻቸውን ነበሩ፡፡

«ጓደኞችህ ቀድመውናል»አለው፡፡ ሙአዝ ጥፍሮቹን በጥርሶቹ እየከረከመ ባለበት ደርቆ ቀረ፡፡

ሻምበሉ «አይዞህ እንይዛቸዋለን» ቢለውም ሙአዝ አልመ ለሰለትም፡፡

«ፍሰሃና ክሪምን ደካሞች አድርገህ በመገመትህ የተሳሳትህ ይመስለኛል» አለ ሻምበሉ እየሳቀበት፡፡ ሙአዝ በሻምበሉ ንግግር ይበልጥ ተናደደ፡፡

ቢሆንም ንዴቱን ዋጥ አድርጐ «እየጠጣን ብናወጋ ምን ይመስልሃል?» ሲል ጠየቀው፡፡

«ጠይብ» አለ ሻምበሉ ፈጥኖ፡፡ ብስጭቱ ያልበረደለት ሙአዝ እየተነጫነጨ «አባክህን እሱን ቴፕ ፀጥ አሰኝልኝ» አለው፡፡ ሻምበሉ ሙአዝን ለማስደሰት «በጫማ ጥፊ ወይስ ...» በማለት ጠየቀው፡፡

«ስትፈልግ በያዝከው ሰደፍ ነርተው:: ግን ፀጥ አሰኝልኝ» ብሎት ወደሳሎኑ አመራ:: ሻምበሉ ያለ የሌለ ሀይሉን ተጠቅሞ እግሩን ሰነዘረ:: ቴፑ ተሽቀንጥሮ ተከሰከሰ::

ሻምበሉና ሙአዝ ተከታትለው ሳሎኑ ሲገቡ የሶፋ ወንበሮቹ ተገለባብጠው፤ ሣጥኖች፣ መጋረጃዎች፣የቤት ጌጣጌጦችና ምንጣፎች ተመሰቃቅለው አዩ:: ፍተሻው እንደቀጠለ ነበር:: አንደኛው ፖሊስ ከሣሎኑ በር በስተጀርባ ወደቆመው ኮመዲኖ ሄዶ በጥሞና ሲያጠናው ቆይቶ ባንዱ ጥግ ያገኘውን ሽንቁር ገፋ ሲያደርገው ተንሸራተተ:: በስስ እንጨት የተሸፈነው የመስተዋት ነፀብራቅ ዓይኑን ወጋው:: አይኖቹን ባለማመን ጨፈን አድርጐ እንደገና ከፈታቸው:: በርካታ የመጠጥ ጠርሙሶች አፈጠጡበት:: ውስኪ፣ ጂን፣ የሀበሻ አረቂ .... «ሀራም አለይክ! ሀራም አለይክ!» እያለ ወደአዛገፉ ሮጠ::

*  *  *

ፍቅራቸውን ያጀበውን የአረብኛ ሙዚቃ ሳያጠፉ ነበር የተኙት:: ሀፊዝ ከእንቅልፋቸው የቀሰቀሳቸውን የስልክ ጥሪ አንስቶ በጉረነነ ድምፅ መለሠ::

«ሀፊዝ? ፍስሃ ነኝ:: ሀየ በዋዲ የለቀቅነው አፓርታማ በአሁኑ ሰአት በፖሊስ ተከቧል:: እኛን ሲያጡ ደግሞ ወደናንተ መምጣታቸው አይቀርም::»

ሀፊዝ ጆሮውን ተጠራጥሮ «ማን ጠቆመብኝ?»ሲል ጠየቀው::
«ሙአዝ ነዋ! አሁኑኑ ቤቱን ለቃችሁ ውጡ::»

በጥድፊያ ለባብሶ ተመልሳ ያሸለበችውን ሰሚራን ቀሰቀሳት:: መርዶውን እንደሰማች በደመነፍስ ፒጃማዋን አውልቃ ያገኘችውን ቀሚስ አጠለቀች:: ከአምስት ደቂቃ በኋላ ገንዘብና ጌጣጌጦች የተቀመጠበትን ሳምሶናይት ቦርሳ ይዘው ከአፓርታማው ወጡ:: ሀፊዝ መኖሪያ ቤት መኪረና ሲደርሱም ሀፊዝ በጥድፊያ ወደስልኩ ሮጠ:: አልፎ አልፎ አብሮት መጠጥ የሚጐነጨውን የሰሚራን ቤት አከራይ ለማነጋገር ነው የተቻኮለው::

«ሀሎ?» እንቅልፍ የተጫጫነው የተበሳጨ ድምፅ መለሰ::

«ፈይሰል ነህ?»

«ማነህ በዚህ ውድቅት የምትደውል? ሰአት በእጅህ የለም? አላህ ይቅር ይበልህ:: በል አሁን ስልኩን ዝጋልኝ!»

«ሀፊዝ ነኝ::»

«አ ... ሀፊዝ? ኬፍ ሐለክ:: እርግጠኛ ነኝ ሰክረሀል::» የሰውየው ድምፅ ነቃ አለና በሳቅ ታጀበ::

«አልተሳሳትክም፤ በጣም ከመረበሼ የተነሳ ከሰከረ ሰው ብሻለሁ::»

«አልገባኝም::»

«ፈይሰል ለብርቱ ጉዳይ ነው የደወልኩት:: በቅርቡ ከአንተ የተከራየሁት ቤት ውስጥ መጠጥ መኖሩን አንድ ሰው ለፖሊስ ጠቁሞ በአሁኑ ሰአት እየተበረበረ ነው::»

«ሀፊዝ ስንት መለኪያ ውስኪ ጠጥተሃል?»

«ፈይሰል እየቀለድኩ አይደለም:: እንደዛሬም ቁም ነገር አዋርቼህ አላውቅም:: ቤቱ እየተፈተሸ ነው:: ወይም ....»

«ወይም ምን??»

«እንደዛ እንደሚያደርጉ ትክክለኛ መረጃ ደርሶኛል::»

«ምን ተሻለኝ ታዲያ?» ፈይሰል በጭንቀት አቃሰተ::

«አንተን ማንም አይነካህም:: ገንዘብ ለሚከፍልህ ማንኛውም ሰው ቤትህን ማከራየት ትችላለህ:: የእኔ ጉዳይ ግን ....»ብሎ ሀፊዝ ቁና ተነፈሰ::

«ጠይብ! ቀጥል እንጂ» አለ ፈይሰል::

«ቤቱን ያከራየኸውን ሰው ማንነት ብትጠየቅ እውነቱን ማውጣት አይኖርብህም::»

«ገባኝ» አለ ፈይሰል በደከመ ድምፅ::

«ልብ አርግ! ትክክለኛውን መረጃ ብትሰጥ እኔም ገበናህን እገላልጠዋለሁ::»

«ኧረ በጭራሽ! ለማንም አልናገርም::»

«እንግዲያው የማይጠረጠር ስምና አድራሻ ስጣቸው::»

«እሺ::»

ሀፊዝ ይበልጥ ተረጋግቶ «ውለታ የምረሳ ሰው ደግሞ እንዳልመስልህ» አለ::

«አውቃለሁ::»

«ደህና እደር» ብሎ ሀፊዝ ስልኩን ዘጋው::

## ምዕራፍ አስራ ስምንት

«ሻሂውን አልነካሽውም» አለች አይዳ የሰፈነውን ዝምታ ለመግፈፍ::

«ያፈላሽው የሶሪያዎቹን ሻሂ ነው:: ቀጭን ሻሂ አልወድም» አለ ከሪም ፈገግ ብሎ::

«ረስቼው.... ለካስ እንደመስሪዎች (ግብፆች) ወፍራም ሻሂ ነው የምትመርጠው::» አንድ ሊፕተን ብርጭቆው ውስጥ ጨመረችና «እርግጠኛ ነኝ አሁን ትጠጣዋለህ» አለችው ወደቦታዋ እየተመለሰች::

ከሪም የመጣበትን ጉዳይ እንዴት መጀመር እንዳለበት እያሰላሰለ ሊፕተኑን ደጋግሞ ሻሂው ውስጥ ይነክራል:: አይዳ በበኩሏ የከሪም መምጣት የጫረባትን የስሜት መዘበራረቅ ለመቆጣጠር ትታገላለች::

«ከፍሰሃ ጋር እንደተራራቃችሁ ቀራችሁ ልበል?» አለ በመጨረሻ ጉሮሮውን አጥርቶ:: ከሪም የመጣው ለዚህ ጉዳይ ያልመሰላት አይዳ፣ «የኛ ጉዳይ ይህን ያህል ያሳስብሀል ብዬ አልገምትም ነበር» አለችው ካንገት በላይ ፈገግ እያለች::

«ሁለታችሁም ጓደኞቼ ናችሁኮ!»

«ላላ! እኔ እንኳን እህትህ ነኝ» ብላ ገለፈጠች::

«እህት መሆንሽማ ይበልጥ እንዳስብልሽ ይገፋፋኛል»አለ ብርጭቆውን ወደአፉ እያስጠጋ::

«ምስጋናዬ የላቀ ነው::»



የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

«ስለኡመር ....»ብሎ ከሪም ዝም አለ::

«ኡመር ጥሩ ወዳጄ ነው:: ከፍሰሃ እንደሚሻል አልክድም:: ጥሩ ይከፍላል» አለች አይዳ ፀጉሯን እያፍተለተለች::

«ግን ለአደጋ ያጋልጥሻል» አለ ከሪም በሚያስፈራራ ድምፅ::

«ስለፍፃሜዬ ሳይሆን በምድር ላይ ስላለኝ ጊዜ ነው ግድ የሚኖረኝ::»

«በህይወትሽ ቁማር እየተጫወትሽ ነዋ!?»

አይዳ ሳቀች:: «ለኔ ሁሉም ነገር የገበጣ ጫወታ ነው:: የመዳፍህን ጠጠር መጨረስ፤ እንደገና ማፈስ:: በቃ!»

«እሺ፤ ፍሰሃስ?»

«በአንድ ወቅት ህይወት አገናኘን እንደገናም አለያየን::»

ከሪም ከዚህ በኋላ የሚለው ነገር አልነበረውም:: የአይዳ ፊት በንዴት ፍም እየመሰለ እንደመጣም አስተውሏል:: «ሀያት ከመካ ልትመጣ ፈልጋለች» አለ ርዕስ ቀይሮ::

«መርሀባ፣ደስ ይለኛል::እንዲያውም ብቸኝነቱን ትጋራኛለች:: የስሚራን ያህል ባትሆንም»ብላ የበለጠ ፈገግታ አሳየችው::

«ማለት?» ከሪም ግራ ተጋባ::

«ሻሂህን ጨረስከው እንዴ? አምጣ ልቅዳልህ»ብላ ብርጭቆውን የመቀማት ያህል ከእጁ ላይ ወሰደችበት::

*　　　*　　　*

ሀያት ያረጀው ጥቁር ስልክ አጠገብ ከተቀመጠች አንድ ሰአት ሞላት:: ነህላ፣ ሀያት ከተቀመጠችበት ትይዩ ከተዘረጋው የስፖንጅ ፍራሽ ላይ ተጋድማ እንሽላሊቶቹ የሚንሸራሸሩበትን የወፋፍራም ጣውላ ኮርኒስ በዝምታ ትመለከታለች::

«የፈረድ አስከሬን ተነስቷል ከተባለ ማነው የሚቀብረው?» አለች ሀያት በድንገት።

«ህገወጥ የውጭ ዜጎች ሲቀበሩ አይቼም፣ ሰምቼም አላውቅም።»

«ለምን?»

«በሀገሪቱ ውስጥ የሚኖሩት ህጉን ረግጠውም አይደል? ታዲያ ለንዲህ አይነቶቹ ወንጀለኞች የመቃብር ስፍራ ማን ያዘጋጅላቸዋል።»

«ምን ይደረጋሉ ታዲያ?»

«ስንሞት አስከሬናችን ከሬሳ ማቆያ ቤት ለስድስት ወራት ያህል ይቀመጣል። ዜግነታችን ከተለየ የአገራችን ስም የተፃፈበት ካርድ እጃችን ላይ ይንጠለጠላል።»

«በጂ?»

«የየሀገራቱ የስደተኞች ጉዳይ ተከታታይ ሰራተኞች ስላሉ ተጠርተው ወደሬሳ ማቆያ ቤቶቹ ይሔዱና የዜጎቻቸውን አስከሬን እንዲለዩ ይደረጋል።»

«ከዚያስ?»

«ከሟቹ ኪስ ወይም ቦርሳ የተገኙ መረጃዎች ካሉ የኤምባሲው ሰራተኛ ወደአገሩ ደውሎ ከሟች ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት ይፈጥርና አስከሬኑን ይልክላቸዋል።»

«መረጃ ከጠፋስ?»

«እስከስድስት ወር ድረስ ፈላጊ እስኪመጣለት ወይም በሌላ መንገድ ማንነቱ እስኪረጋገጥ ይቀመጣል። ይህ ሁሉ ካልሆነ ይጣላል ወይም እንጃ! ...»

«እርግጠኛ ነሽ ነህላ?» ብላ ሃያት ስትጮኽ ስልኩም ተከትኳት ጮኸ።

ከዚያም ከሀፊዝ ጋር ወደጅዳ የመልስ ጉዞ አደረጉ::

*　　　*　　　*

«ፊይሰልን ማግኘት አለብኝ» አለ ሀፊዝ ጥቂት አሰብ አድርጐ::

ሰሚራ በድንጋጤ «እስከአሁን አልደወልክለትም?»ስትል ጠየቀችው::

«ራሱ ይደውላል ብዬ ገምቼ ነበር:: እነዚህ ሰዎች በኔም ላይ ሳይዘምቱ የሚቀሩ አይመስለኝም::»

«እነማን?»

«አርአያና ሙአዝ ናቸዋ:: ፖሊሶቹን ወዳንቺ አፓርታማ የመሩዋቸው በጨዋታው መሳተፌን ገምተው ነው::»

«ትልቁን ስህተት የሰራነው እኛው ነን» አለች ሰሚራ ስልክ የሚደውለውን ሀፊዝ እያቀፈች::

«ሀሎ፤ ፊይሰል?» ሲል ጣደፍ ብሎ ጠየቀ::

«ነኝ!»

«እንደምን አመሸህ ፊይሰል? ሀፊዝ ነኝ::»

«ሀፊዝ? .... ከዘሁር በኋላ ደውዬልህ የሚመልስልኝ አጣሁ» አለ::

«ጥሩ ወሬ ነበረህ?»

«ሰዎቹ መጥተው አነጋግረውኛል:: ያከራየሁት ሰው ኢብራሂም እንደሚባልና ስራውም ምህንድስና መሆኑን ነግሬያቸዋለሁ:: በነገራችን ላይ የቡድኑ መሪ ሻምበል ናስር ነው:: አወቅከው?»

«ሻምበል ናስር?»ብሎ ሀፊዝ በአድናቆት አፏጨ::

«መኪናውን የበላኸው::»

«አወቅሁት» አለ ሀፊዝ በከባዱ ተንፍሶ «በቁማር የበላሁዋትን ታክሲ ኮ ሽልሞ ጠዋቹባታለሁ።»

«ሻምበል ናስር ያንተን ማንነት እንዳወቀ በእልህ ሊያሳድድህ ስለሚችል ክትትሉን እንዲያቆም የምታስፈራራበትን ሰነድ መያዝ ይኖርብሃል።»

«የምን ሰነድ?»

«በስምህ ሲያዞር የተፈራረማችሁበትን ነዋ!»

«አሀ! ገባኝ፤ አመሰግናለሁ» ብሎ ሀፊዝ ስልኩን ዘጋው። ከዚያም ዞር ብሎ ሰሚራን «የኔ ወለላ ከአስፈሪው አደጋ አምልጠናል» ብሎ ሳማት።

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ከሪም የፍስሃን እምቢታ ለማለዘብ እየሞከረ፣ «ግድ የለህም አስራ ሁለቱን የመጠጥ ካርቶኖች እንመልስላቸው» አለው::

«አይደረግም!» አለ ፍስሃ በጩኸት::

«ገንዘባቸውን ብንመልስላቸው ጠባችን ይበርዳል ብዬ'ኮ ነው::»

«አይሆንም ስልህ?!»

«ፊሽ?» አለ ከሪም በልመና::

ፍስሃ የስልኩን እጀታ አንስቶ የነአርአያን ቁጥር አዞረ::

«ሀሎ!» ሲል ሙአዝ መለሰለት::

«ጤና ይስጥልኝ፣ የቤታችንን አድራሻ ብሰጥህ ደስ ይልሃል?» አለ ፍስሃ እየሳቀ::

«ፍስሃ?» አለ ሙአዝ በመደነቅ:: «እናንተ ዲቃሎች!»

«የቤታችንን አድራሻ ልነግርህ'ኮ ነው የደወልኩት::»

«ለምን ትነግረኛለህ? እኔው ራሴ ፈልጌ የወንድሜን እግር እንዳበላሹት ሙጀሌዎች አስመነግላችኋለሁ::»

ፍስሃ ሳቀ:: «ሀገርህ የሔድህ ጊዜ የገጠመህ ትልቁ ችግር የወንድምህ እግር በሙጀሌ መንሻፈፍ መሆኑን አስቀድመህ ነግረኸኝ ቢሆን ኖሮ ሶስት ጥንድ ጫማ እልክለት ነበር::»

«ይልቅ ለቤተሰቦችህ ደውልና ቀንጆ የሬሳ ሳጥን እንዲያዘጋጁልህ ንገራቸው::»

«በቅድሚያ ግን ያንተን መክፈኛ ገዝቼ ወደካርቶም እሰዳለሁ::»

«መቼስ ምላስ አትሞት?» አለ ሙአዝ በንዴት እየሳቀ::

«ቤቱን ብታውቀው እኛ ዘንድ ያሉአችሁን ካርቶኖች ትወስድ ነበር::»

«እሱንማ አንተው ራስህ ታመጣልኛለህ::»

«የነዳጅ መግገ የለኝም::»

«የዘረፍካቸው እሽጎችስ?»

«ጥሩ ትራስ ሆነውኛል:: እንዲለዩኝ አልፈልግም::»

ከሪም በፍሰሃ አቀራረብ ደስ ስላልተሰኘ ጠጋ ብሎ እጆታውን ተቀበለው:: «ሀለው ሙአዝ፣ከሪም ነኝ:: እኛጋ ያሏችሁን ካርቶኖች ብንሰጣችሁ አትደሰቱም?» ሲል ጠየቀው::

ሙአዝ በረጅሙ ሳቀና «ህይወታችሁን ብትሰጡን ነው የምንፈነጥዘው» አለው::

«ይሔ ነው መልስህ?» አለ ከሪም ብሽቅ ብሎ::

«የምንታረቀው እሽጎቹንም ስትመልሱ ነው:: ገባህ?»

«ያጨካከኑንም እነሱ ናቸዋ?!» አለ ከሪም ለዘብ ብሎ::

«ላ! ክህደታችሁ ነው::»

«ይቅር መባባል አንችልም?»

ፍሰሃ በቁጣ እጆታውን ከከሪም ቀምቶ፣ «ትሰማለህ?! ይቅርታህም፣ ጓደኝነትህም ገደል ሊገባ ይችላል:: ሻምበሉን እያንከረፈፍክ ገሃነም መግባት ትችላለህ:: ካርቶኖቹንም፣ እሽጎቹንም አንሰጥህም:: ደደብ!» ብሎ ስልኩን ዘጋው::

* * *

በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ብዙ ለውጥ የታየበት የእይዳ ቤት በሁለቱ ሴቶች ወግ ሞቃለች:: ህያት መካ ከተማ ያየችውንና

የሰማችውን ስታወጋት፣ አይዳ በበኩልዋ አዲስ የጀመረችውን ህይወት ጣፋጭነትና የኡመርን ደግነት ስትተርክላት ብዙ ቆዩ:: ጨዋታቸው እያለቀ ሲመጣ አይዳ ሀያትን ቡና እንድታፈላ ነግራት እሷ ምሳ ልታዘጋጅ ወደማዕድ ቤት ሔደች::

ሀያት የቆላችውን ቡና ወደመፍጫው ስትገለብጥ የበሩ ደወል ተንቃጨለ:: በሩን ስትከፍት ከሪም በፌስታል የተቋጠሩ ፍራፍሬዎችንና እሽጉችን እንዳንጠለጠለ በሩ ላይ ቆሟል:: ፍሰሃም አብሮት ነበር:: ወደውስጥ እስኪዘልቁም አልታገሰችም:: አንገቱ ላይ ተጠመጠመች:: ከሪም ተላላፊ መንገደኞች እንዳያዩዋቸው ፈጥኖ ወደውስጥ ገባና አጥብቆ አቀፋት:: ፍሰሃን ቅናት ዳሰስ ሲያደርገው ተሰማው:: በሩን ዘግቶ ባለብት ትቷቸው ወደሳሎኑ አመራ::

ቤቱ በእጣንና በተቆላ ቡና ሽታ ታውዷል:: ከፍራሹ አጠገብ የተደረደሩት ሲኒዎች፣ ምድጃ ላይ ተጥዳ የምትደነፋው ጀበና፣ በስፌት ተሞልቶ የተቀመጠው ፈንዲሻ አይንን ይማርካሉ:: ፍሰሃ ይህን ሲያይ ከሀገራቸው ሴቶች ጋር ተቀላቅለው በሚኖሩ ሀበሾች ይቀናል:: ሁሌም ቤታቸው ሀገርቤት፣ ሀገርቤት እንደሸተተ መኖሩ ያጓጓዋል::

ከሪም ያመጣቸው እሽጉች ተፈትተው የተጠበሰው የዶሮ ስጋ ለምሳ ቀረበ:: በፍሰሃና በአይዳ መካከል አንዳችም የቃላት ልውውጥ አልተካሄደም:: ሁለቱም የጉሪጥ እየተያዩ አልፎ፣ አልፎ ብቻ በከሪምና በሀያት ጨዋታ ጣልቃ እየገቡ ይሳተፋሉ:: ቡና መጠጣት ሲጀምሩ ስልኩ ጮኸ:: አይዳ አነሳችው:: «ሀሎ? አንተ ነህ እንዴ? ... መች? ዛሬ? ...ጠይብ ...ቻው!»

ስልኩን ዘግታ ወደቦታዋ ስትመለስ በጨረፍታ የፍሰሃን አይኖች ፈለገች። ምንም ነገር እንዳልሰማ ሁሉ ተዝናንቶ ተቀምጧል። ፊቱም ላይ ቅሬታ ወይም ቅናት አይነበብም። ተናደደች።

* * *

መጅድ ሻምበል ናስር ቤት የደረሰው ከምሽቱ ሰባት ሰአት ላይ ነበር። የመጣበትን ጉዳይ ሲነግረው ሻምበሉ አልተደነቀም። እነሙአዝ ስለከፈቱት ዘመቻ በዝርዝር ነግሮት ጉዳዩን የያዘውን ፖሊስ ማንነት እንዲገልፅለት ጠየቀው።

«እነሙአዝን አላውቃቸውም። ስለምትለውም ጉዳይ አልሰማሁም። ለማንኛውም ሁኔታውን አጣርቼ እነግርሀለሁ» አለ ሻምበሉ። መጅድ ተደስቶ ሄደ። ከአራት አመት በፊትም እሱን ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ የተመደበውን መቶ አለቃ አዋዝቶ ከአደጋ አድኖታል። መጅድ ለቀጣዩ ቀን ቀጠሮ ይዞ ወደአንድ ወዳጁ አስር አለቃ ቤት አመራ። አስር አለቃ ጀሚል ዘሎ ያልጠገበ ጉረምሣ ነው። መጅድ የመጣበትን ጉዳይ ዘርዝሮ አጫወተው። አስር አለቃው በመጅድ ሞኝነት እየሳቀ፣

«ሻምበል ናስር'ኮ የነሙአዝ ወዳጅ ነው። ጉዳዩንም የያዘው እሱ ነው። ስለዚህ አትድከም። ይልቅ ጓደኞችህ በነሙአዝ ላይ እንጠቁማለን ብለው ሞታቸውን እንዳያፋጥኑ። ሻምበል ናስር የነሙአዝ የቅርብ ወዳጅ ስለሆነ ለፍርድ እንዲቀርቡ አያደርግም። ውስኪ ማን ያጠጣዋል?» አለው።

መጅድ አስር አለቃውን ተሰናብቶ ወደቤቱ ሲያዘግም የነገሮቹ መወሳሰብ በጣም አሳስቦት ነበር።

በሀሳብ የተወጠረ አእምሮውን ለማሳረፍ በጥድፊያ ወደአልጋው ሔደ:: ብዙም ሳይተኛ ስልኩ ቀሰቀሰው::

«መጅድ? ናስር ነኝ:: ይቅርታ ከእንቅልፍህ ቀሰቀስኩህ?»

«አይ፣ አልተኛሁም::»

«ሀፊዝ ስለሚባል ሰው የምታውቀው ነገር አለ?» ሲል ሻምበሉ ኮስተር ብሎ ጠየቀው::

«እ .... አላውቅም» አለ መጅድ ተደናግጦ::

«እርግጠኛ ነህ?»

«አዎን::»

«የብዙ መጠጥ አዘዋዋሪዎች ወዳጅ ነው ብዬ'ኮ ነው::»

«እንጃ፣ እኔ አላውቀውም::»

«ጥሩ፣ ጓደኞችህን ከአደጋ ልታድናቸው ትፈልጋለህ?»

«አዎን» አለ መጅድ::

«እንደዚያ ከሆነ በውስኪ ብቻ አንላቀቅም:: ሀፊዝንም ጭምር ታስረክበኛለህ!»

«ሻምበል?!» አለ ደንግጦ::

«እንደወትሮህ ናስር ብለህ ጥራኝ:: ገባህ?! ሀፊዝን አፈላልገህ ያለበትን እንድትነግረኝ:: እነከሪም እንደሚያውቁት እርግጠኛ ነኝ::»

«በምን አወቅህ?»

«ደህና እደር::»

መጅድ ጆሮው ላይ የተዘጋውን ስልክ አፍጥጦ አየው:: አደጋው ለሱም እንደሚተርፍ ጠረጠረ::

* * *

ሙአዝና አርአያ አይዳ ቤት ሲደርሱ የቁለደል መንደር ጭር እንዳለች ነበረች::

አይዳ ኡመርን ከመኝታ ቤት እንዳይወጣ አስጠንቅቃ በሩን ከፈተችላቸው:: እንደተቀመጡ «አይዳ?» አለ ሙአዝ በሚያስፈራ ድምፅ፤ «የመጣነው የነከሪምን ቤት እንድታሳዪን ልናስገድድሽ ነው::»

«እኔኮ የቀየሩትን ቤት አላውቀውም» አለች በዝቅተኛ ድምፅ::

«ፍስሃ እስከዛሬ ወደ አልጋው ሳይወስድሽ ሰነበተ ቢባል አይታመንም» አላት በንቀት እያየት::

«መጣላታችንን አታውቁምና ነው?!»

«እንድትዋሺ አልፈቅድልሽም::»

«ሙአዝ እመነኝ፤ ቤታቸውን አላውቀውም» አለች ጫን ብላ::

ሙአዝ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና «ሀያትስ የት ነች?» ሲል ጠየቃት::

«እነሱ ጋ!»

«አንቺ ዘንድ አልነበረም እንዴ የምትቀመጠው?»

«አይ ... አዎን .... እዚህ ነው:: ግን ....» ተንተባተበች::

«ተመልሳስ ትመጣለች?»

«አዎን»

«ጠይብ! እንዲያ ከሆነ ከሪም እሷን ለማየት ወደቤትሽ ጐራ ማለቱ ስለማይቀር ከሪም ወይም ፍስሃ እንደመጡ ደውዪልን:: ገባሽ?»

«እሺ ... ግን ...» አቅማማች::

Z... Library

ሙአዝ «ልብ አድርጊ:: ይህን ባትፈፅሚ ካንዱ ጋ እንደተ ጋደምሽ በፖሊስ አስጠፍርሻለሁ!» ብሎ የአርአያን ታፋ መታ አድርጎ ተያይዘው ወጡ::

አይዳ በሩን ዘግታ ስትመለስ ኡመር በውስጥ ሱሪው ብቻ ሆኖ ይንጎራደዳል:: ያሏትን ነገረችው::

* * *

ሀያት አይዳ ዘንድ ከመጣች ሁለት ሣምንታት አለፉ:: አይዳ ስድስት ቀናት ሙሉ ከቤቷ ተሠውራ ገና ዛሬ መምጣቷ ነው:: ሀያትን ብቸኝነቱ ተጫጭኗታል:: በዚህ ላይ ከሪምና ፍሰሃም ቃል በገቡላት መሠረት መጥተው አልጠየቋትም::

አይዳ ሳሎኑ ሶፋ ላይ ተንጋለለች::

ሀያት ቡና እያፈላች «አሁንም ስራ ልታገኚልኝ አልቻልሽም?» ስትል ጠየቀቻት::

«ከሪም'ኮ ብዙ ሰዎች ያውቃል:: ለምን አያስቀጥርሽም?» አለቻት አይዳ በምፀት::

ሀያት ሽሙጡ ያልገባት በመምሰል፣ «አሁን ያለበትን ሁኔታ እያወቅሺው?» ብላት ከሰሉን ማራገቧን ቀጠለች::

«ምን ሆኗል?» አይዳ ግንባሯን ቋጥራ ወደሀያት ዞረች::

«በፖሊስ እየታደነ ነው::»

«ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም» አለች አይዳ እጇን አወናጭፋ:: ለሀያት የተቆረቆረች ለመምሰል ከንፈሯን እየመጠጠች፣ «የሚወድሽ ከሆነ ለጊዜውም ቢሆን በአነስተኛ ደሞዝ ሲቀጥሩሽ

የሚችሉ ሰዎችን ባገኘልሽ ነበር:: ግን እሱ ስላንቺ የሚያስበው...ብቻ ተይው ሁሉን ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል» አለች የተበሳጨች መስላ::

«እንዴት? ስለኔ የሚያስበው ምንድነው?»

«ሀያት እዚህ ከኔ ይበልጥ የሚቀርብሽ የለም:: ከኛ ሰዎች ጥሩ ነገር እንዳትጠብቂ ልነግርሽ ካሰብኩኝ ቆይቻለሁ:: ግን ሁሉንም በሂደት እንድታዪው ብዬ ነው ዝም ያልኩት:: ከሪም ያንቺን ስራ መግባት እንደማይፈልግ በግልፅ ነግሮኛል:: ወደመካ የሰደደሽም እኔ ሥራ በጣም ሳፈላልግልሽ እንደነበር ስለተረዳ ነው:: እዛም እህቴ ስራ ሳታስገባሽ የቀረችው አጥታ እንዳይመስልሽ፤ የወንድሟን ትዕዛዝ አክብራ እንጂ ...»

«ይህን አላምንም!» አለች ሀያት በሰለለ ድምፅ::

«እዚህ ያሉ የሀበሻ ወንዶችን ከኔ በላይ አታውቂያቸውም:: እንዲትን ሴት በወዳጅነት ይይዙና ስራ እናስገባሻለን እያሉ ቅምጣቸው ያደርጓታል፤ የጭን ገረድ ታውቂያለሽ?:: ከሪምም ...»

«እንዴ አይዳ?!»

«ሁሉም ነገር ወደፊት ይገለፅልሻል::»

«ከሪም በኔ ስራ መፍታት ምን ይጠቀማል?» አለች ሀያት ፍርሀት በነገሰበት ድምፅ::

«የስጋ ዘመዱ ስለሆንሽ ብቻ አይደለም የምቆረቆርልሽ:: ሴትም ስለሆንሽ ጭምር ነው:: ወንድ ልጅ በጓደኝነት የያዛትን ሴት በመረጠው ሰዓት ማግኘት ይፈልጋል:: አንቺ ስራ ከገባሽ ከሪም ሊያገኝሽ የሚችለው በሳምንት ወይም በአስራአምስት ቀን አለያም በወር አንዴ ነው:: ስለዚህ በፈለገው ሰዓት እንዲያገኝሽ ስራ ፈተሽ መቀመጥ ይኖርብሻል::»

«ክከሪም ይህን አልጠብቅም፡፡ በጣም ደግ ሰው ነው» አለች ሀያት እንባ እየተናነቃት፡፡

«ብርግጥ ደግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚወስደው እርምጃ ግን ከሌሎቹ ሀበሾች የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ፍሰሃ እንኳን ባቅሙ የሠራኝን ልንገርሽ፡፡ እኔን ያስስራ አስቀምጦ ሲያበቃ፣ ሁለት ሴቶች አስቀምጦ ይቀብጥ ነበር፡፡ ችግሩ ወንድ ልጅ እንደልቡ መንቀሳቀስ ሲችል፣ ሴቷ ከቤት እንዳትወጣ መደረጉ ነው፡፡ አንቺ አፍሽን ከፍተሽ ስለምትመስርቺው ትዳር፣ ስለምትወልጂቸው ልጆች ታልሚያለሽ፣ እነሱ... ኧረ ተይኝ እባክሽ!» አይዳ ጭንቅላቷን ይዛ ተንገሸገሸች፡፡

«ከሪምም ይህን ያደርጋል ብለሽ ትገምቻለሽ?» አለች ሀያት በደከመ ድምፅ፡፡

«ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን እነግርሀለሁ ነው የሚባለው፡፡ ከፍሰሃ ጋር እየዋለ እንዴት ጨዋ ሊሆን ይችላል? የማይመስለውን!» ብላ ክት ብላ ሳቀች፡፡

ሀያት በልቧ ያቆጠቆጠ ጥርጣሬዋን እያባበለች አይዳን አትኩራ አየቻት፡፡

«አንቺስ ስራ መያዝ እንዳለብኝ አታምኚም?»

«አምናለሁ፡፡ ከሪም ቢፈልግ ገደል ሊገባ ይችላል፡፡ በተቻለኝ ሁሉ ስራ እፈልግልሻለሁ፡፡ ጥቂት ግን ታገሺኝ፡፡»

«አይዳ እባክሽን እርጂኝ?» አለች ሀያት በተሰበረ ድምፅ፡፡

«እንደታላቅ እህትሽ ልትቆጥሪኝ ትችያለሽ» ብላ አይዳ ፈገግ አለች፡፡

አላማዋ ሊሳካ መቃረቡ ነበር ያስደሰታት፡፡ በርግጥ ከሪምን በቀላሉ ለነአርአያ ማስረከብ በቻለች ነበር፡፡ ነገር ግን ከሪም

እንዲሞት አትፈልግም:: ከሪም በህይወት ከቆየ የሷ የሚሆንበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል:: ማን ያውቃል? ስለዚህ መጥፋት ያለባት ሀያት እንጂ ከሪም አይደለም:: ህይወቷን ባትቀጥፈውም ሌላ ዘዴ ልትጠቀም ወሰነች::

* * *

ፍስሃ የመጨረሻዋን እሽግ ሸጦ ወደቤቱ የተመለሰው አመሻሹ ላይ ነበር:: አሁንም በስጋት እንደተዋጡ ናቸው:: «በዚህ ሁኔታ መቀጠል የምንችል አይመስለኝም ፍስሃ:: ስለዚህ በኔ በኩል ወደሀገሬ ለመመለስ ወስኛለሁ» አለ ከሪም ራት በልተው እንዳበቁ::

«የኔም ልብ ተነስቷል:: መወሰን ግን አልቻልኩም» አለ ፍስሃ ሲጋራውን እየለኮሰ::

«ለምን መቁረጥ ተሳነህ?»

«ጠቀም ያለ ገንዘብ አላጠራቀምኩም::»

«ብትቆይም ልትሰራ የምትችለው ይህንኑ ሥራ ነው::»

«መቼም ከንግዲህ ዘበኛ ወይም ሹፌር አልሆንም» አለ ፍስሃ እየሳቀ::

«መዘንጋት የሌለብህ እነሙአዝም ይህንኑ ስራ የሚሰሩ መሆናቸውን ነው:: መጠጥ በድብቅ የሚያስገቡት የተወሰኑ ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ እነሱ ዙሪያ ስትሽከረከሩ መገናኘታችሁ አይቀርም?»

«ፍስሃ ታዲያ ሞት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደር::»

«ብቸኝነትህ ደግሞ በቀላሉ ሊያስጠቃህ እንደሚችል አትጠራጠር::»

«የቆፈሩት ጉድጓድ ውስጥ እንደምቀብራቸው አረጋግጥልሀለሁ:: እንደሚያሳድዱኝ ሁሉ እኔም አራውጣቸዋለሁ:: በዚህ

ፍልሚያ ወይ ይቀድሙኛል አለያም እቀድማቸዋለሁ:: ይልቅ አንተ መቼ ለመሔድ አሰብክ?»

«የፖሊሶቹ አደን ሲቆም ወይ ሲቀዘቅዝ::»

«የሀያት ጉዳይስ?»

«ይገርት ለመሄድ ነው የማስበው::»

«ይህን ሀሳብህን ገልፀህላታል?»

«እስከአሁን አልነገርኳትም::»

ለደቂቃዎች ዝምታ ሰፈነ:: «ፍሰሃ አብረኸኝ ብትመለስ በጣም ደስ ይለኝ ነበር» አለ ከሪም በመጨረሻ::

«ከአንድ አመት በኋላ እከተላችኋለሁ::»

የፍሰሃ ንግግር በስልክ ጥሪ ተቋረጠ::

«ሀሎ?» አለ ከሪም እጆታውን አንስቶ::

«መጅድ? ... ጠፋህሳ:: በኛ ጉዳይ ... ምን?! ሻምበል ናስር? ... እርግጠኛ ነህ:: ምን? በተቻለ ፍጥነት አገሩን ለቃችሁ ሂዱ? አይደረግም! ቻው!» ስልኩን ዘግቶ ሶፋው ላይ ተዘረፈጠ::

* * *

ፊይሰል ቤቱ መጥተው የነበሩት ፖሊሶች እንደወጡለት ወደሀፊዝ ስልክ ደወለ::

«ፊይሰል ነኝ:: እነዚያ ሰዎች ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እቤቴ መጥተው ነበር::»

«የትኞቹ?» አለ ሀፊዝ ድንግርግር ብሎት::

«እነዚያ ተከላዎች ናቸዋ:: ከሻምበሉ ጋራ ሶስት ሆነው መጥተው ነበር:: ባንተ ላይ የሚያደርጉትን ክትትል አጠናክረው ቀጥለዋል::»

«እን ... እንዴት?» አለ በተቆራረጠ ድምፅ::

«ትክክለኛ ስምህን አውቀውታል:: እኔንም የተሳሳተ መረጃ በመስጠቴ ለፍርድ እንደሚያቀርቡኝ እያተቱ እውነቱን እንዳወጣ አስፈራርተውኝ ነበር::»

«ነገርካቸው?» አለ ሀፊዝ ጣደፍ ብሎ::

«እንዲያውም፤የደወልኩልህ መጠንቀቅ እንዳለብህ ላስገነዝብህ ነው» አለው ፈይሰል ጫን ብሎ::

ሀፊዝ ክፉኛ ስለተረበሸ እንቅልፍ በአይኑ ሳይዞር ነጋ:: ቁርስ ቀርቦ እንደነገሩ ከቀማመሰ በኋላ፣ «ሰሚራ፣ በፍጥነት ከዚህ ሀገር መውጣት አለብን» አላት::

«ለተወሰነ ጊዜ እዚሁ መሸሸግ ይሻለናል» ስትል ሰሚራ ተቃወመችው::

«ሊይዙኝ መቃረባቸው አይታወቅሽም?»

«ቢሆንም መደበቅ ከቻልህ ብቻ ነው ልታመልጣቸው የምትችለው:: ስትደበቅ እነፍንፈው ከደረሱበት የመጨረሻ ዱካህ ላይ የሚገቱት ፖሊሶች ወደየትም የማያደርስ ክትትላቸውን በዚያ ያበቁና ትልቅ የጥያቄ ምልክት አኑረውበት ወደተነሱበት ይመለሳሉ:: ትኩረታቸውን ወደሌሎች ስራዎች በማድረግም ፋይልህን ያጥፉሉ:: ያን ጊዜ የማምለጫ ቀዳዳ ታገኛለህ::»

ሀፊዝ በሀሳብ ተዋጠ:: የሚሸሸግባቸውን ስፍራዎች እያሰበ ነበር:: ድንገት ደግሞ ሌላ ሀሳብ ብልጭ አለበት::

«በቅድሚያ አንቺ ወደሀገርሽ ሔደሽ የመኖሪያ ፈቃድ አውጥተሽ ትመለሻለሽ» አላት ፈጥኖ::

«አልገባኝም::»

«አንድ ጓደኛዬ ከሁለት አመት በፊት ልክ እንደኔው ወደአሜሪካ ተሰዷል::«አንቺ ህጋዊ ወረቀትሽን ከኢትዮጵያ ይዘሽ

እንደመጣሽ ሰራተኛዬ ናት ብዬ ይገናሽ እሔዳለሁ፡፡ እዚያ ስንደርስ እንጋባለን፡፡»

ሰሚራ ዝም አለች፡፡

«እዚህ ያሉኝን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በሙሉ እሸጣለሁ፡፡ እናም ወደሀገርሽ ስትሔጂ ባዶ እጅሽን አትሆኚም ...» ስልኩ ሲጮህ ሀፊዝ ንግግሩን አቋርጦ ስልኩ ላይ አፈጠጠ፡፡ ደግሞ ጮኸበት፡፡ ተንጠራርቶ በሚንቀጠቀጥ እጁ አነሳው፡፡

መጅድ፣ ኡመር ያዘዘውን ጫት በስጦታ ጠረቀት ጠቅልሎ ኡመር ወደሚገኝበት አፓርታማ ገሠገሠ::

እንደደረሰ ውሃ ጠጣ እንኳ ሳይሉት ተነሱ:: የስጡት ጉርሻ ግን ከሌላው ጊዜ በሀምሳ ሪያል ከፍ ያለ ነበር:: ቀድሚቸው ሊጠጣ ሲንደረደር ኡመር «መጅድ?» ብሎ ተከተለው፤ «.... አንድ ነገር ረስቼ ነው:: ሙአዝና አርአያ ስለሚባሉ ልጆች ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀው::

«እንጃ .... » አለ መጅድ በጥርጣሬ::

«የአይዳ ጓደኞች ናቸው ወይም ነበሩ አይደል?»

«የአይዳ ጓደኞች? ይህን ጉዳይ ግን ለምን አነሳህብኝ?»

«ከሁለት ጓደኞቻቸው ጋራ ተጋጭተዋል መሰል::»

«ከነከሪም ጋር?» አለ መጅድ ድንገት ሳያስበው::

የኡመር አይኖች በሩ:: «አዎን፣ ከሪምና ፍሰሃን ሊያስ ይዟቸው ይፈልጋሉ:: እናም አይዳን በጨዋታው እንድትሳተፍ አስገድደዋታል:: በመጡ ሰዓት ደውላ እንድትነግራቸው ታዛለች:: የማትተባበራቸው ከሆነ ግን ጠቁመው እንደሚያስይዟት ገልፀ ውላታል:: ስለዚህ አንድ ውለታ ዋልልኝ:: አይዳ የመኖሪያ ፈቃድ እስክታወጣ ድረስ ከሪምንና ፍሰሃን ወደቤቷ እንዳይመጡ አስጠንቅቃቸው::»

«ከመጡስ ለነሙአዝ ጠቁማ ታስይዛቸዋለች?»

«ያን እንደማታደርግ ምላ ነግራኛለች:: ያዘዙዋትን ካልፈ ፀመች ደግሞ እነሙአዝ ይቀጧታል::»

* * *

ሀያት ከሪምን በስልክ ብታገኘውም አይዳ ስለዘራችባት ጥርጣሬ እንስታበት አታውቅም:: የተዘጋ ቤት ውስጥ ብቻዋን ተጉልታ የምትውለው ሀያት ከምንጊዜውም በላይ ተስፋ ቆርጣለች:: ሥራ ልታገኝላት ቃል የገባችላት አይዳ ብቻ ስለነበረችም ወደቤት በመጣች ቁጥር ታነሳባታለች::

እናም «አይዳ እባክሽን እንድ በይኝ?» አለቻት ከሦስት ቀን በፊት::

«ምኑን?» አይዳ ፊቷን አጨፈገገች::

«ያለስራ ከተዘጋ ቤት ውስጥ መቀመጡን አልቻልኩትም::»

አይዳ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ «ለምን ከኔ ጋር አትሰሪም?» አለቻት::

«ምን?» የሀያት አይኖች በድንጋጤ ተጉለጉሉ::

«ንግድ ነዋ!» አለቻት በዜማ መልሷን አቅልላ::

ሀያት ፊቷን በመዳፏ ሸፍና አቀረቀረች::

«ምን አለበት?» አለች አይዳ በቁጣ::

«ላንቺም ይሰማኛል::» ሀያት እንባ ባቀረሩ አይኖቿ እያየቻት ምላሽ ሰጠች::

«ባዶ ንፅህና ተሸክመሽ በችግር ከመንፏቀቅ ውበትሽን ተጠቀሚበትና ይለፍልሽ!»

ሀያት በእምቢታ ራሷን ነቅንቃ፣ «ይቅርታ አድርጊልኝ አይዳ በዚህ መልኩ የማገኘው ሃብት አያስደስተኝም» አለቻት::

«እንደዚያማ ከሆነ ተሸርሙጦ በሚመጣ ገንዘብ አርፈሽ መቀለብ ነዋ!» ብላት ወጥታ ሔደች::

አይዳ ከሁለት ቀናት በኋላ ነበር ወደቤቷ የተመለሰችው:: በፈገግታ ሰላምታ ካቀረበችላት በኋላም እንግዶች ስለሚመጡ ቤቱን

ዙማቢያዋ እንድታግዛት ጠየቀቻት፡፡ ሀያትም እርቅ በመውረዱ ተደስታ አይዳ ያዘዘቻትን ሁሉ ስታከናውን ቆየች፡፡

ምሳ ሰዓት ላይ ኡመርና ጓደኛው ሙፊድ፣ አይዳ ቤት መጡ፡፡

ሀያት ብቻዋን እሳሎን መቀመጥ ብትፈልግም አይዳ ግን «እንግዶቼን ታስተናግጂልኛለሽ» ብላ አቆየቻት፡፡ ሀያትም ዳግመኛ ከአይዳ ጋር ላለመቃቃር አብራቸው ለምሳ ቀረበች፡፡ የጫት መቃሚያው ሰዓት ሲደርስም ቡና እንድታፈላ ተመደበች፡፡ ቡናው እንዳከተመ ሀያት እቃዎቹን ለማነሳሳት ስታሰባስብ፣ «ነይ ወዲህ፡፡ እቃው ባለበት ይቆይ» አለቻት አይዳ፡፡

ሀያት ብታንገራግርም፣ «ምን የሚያስፈራሽ ነገር አለ? ወንድሞችሽ ነንኮ፡፡ ይልቅ ፍራሹ ላይ ተቀመጭ» እያሉ ጨኹባት፡፡ እንደተባለችው አደረገች፡፡ አይዳ የተቀመጠችበትን ሥፍራ ለሀያት ለቅቃ ኡመርና ሙፊድ መሀል ተቀመጠች፡፡ ወዲያውኑ ኡመርና አይዳ አፍ ለአፍ ገጥመው መንሾካሾካቸውን ቀጠሉ፡፡

ሙፊድም ወደሀያት ዞሮ «ተጫወቺ እንጂ» አላት፡፡ ዝም አለችው፡፡ ሙፊድ እጆችዋን ያዝ አድርጐ «ሳኡዲ አረቢያ ብዙ ቆየሽ?» አላት፡፡ በጭንቅላቷ የአዎንታ ምላሽ ሰጥታው ዝም አለች፡፡

«አይዳንና ኡመርን እያቸው፤ ያለማቋረጥ ያወራሉ፡፡ እኔና አንቺ ግን የተኰራረፍን ነው የምንመስለው፡፡»

«ይቅርታ አድርግልኝ፣ የአረብኛ ቋንቋ ችሎታዬ አንተን ለማዋራት በቂ አይደለም» አለች ሀያት ኮስተር ብላ፡፡

«አይዳ ዘመዴ እንደሆንሽ ነግራኝ ነበር:: እውነት ነው?» በጭንቅላቷ የአዎንታ ምላሽ ሰጥታው ፊቷን አዞረች::

«ኡመር ቀደመኝ እንጂ አይዳ ምርጥ ሴት ነበረች::»

«ምስኪን ስታሳዝን» አለች ሀያት በሽሙጥ::

«በኛ ባህል ያጧትን ሴት እየተመኙ ከመናር ዘሯን ፊልጉ ማግባት አዋቂነት መሆኑ ይነገራል:: አይዳ ደግሞ ጥሩ ልጅ እንደሆንሽ ነግራኛለች:: እስከዛሬ በወንደላጤነት የታሰርኩት ለምን ይመስልሻል? የምፈልጋትን ባለማግኘቴ ነው:: ይገርምሻል በኔ እድሜ ያሉ በርካታ ወንዶች ትዳር የመያዝ ፍላጐታቸው ሞቷል:: እንደኡመር ያሉት ባለትዳሮችም ህይወት ፍቅር አልባ ነው:: ለምን? አየሽ ብዙዎቻችን ለትምህርት፣ ለመዝናናት ወዘተ ከሀገራችን እንወጣለን:: በምዕራብ አለም ያለውን ነፃ የአኗኗር ባህልም በፍጥነት እናጣጥመዋለን:: ወደዚህ ስንመለስ ግን የዚያ ተገላቢጦሽ ያጋጥመናል:: አይቻት የማላውቃትን ያክስቴን ወይም ያጐቴን ልጅ እንዳገባ እደረጋለሁ:: ለማታፈቅረኝ ሴት ከአቅሜ በላይ የጥሎሽ ገንዘብ እንድሰጥ እጠየቃለሁ:: ግልፅነትም የለም:: ለዚህ ነው ወንደላጤነት ሥር እየሰደደ የመጣው:: ሀበሾች የዚህ ችግር መፍትሔዎች ናቸው:: የሀገራችን ህፃናት ለልደታቸው የሚያስጋግሩትን የቼኮላት ኬክ አይነት ጣዕም አላችሁ...» ብሎ ጡቶቿን ሲዳብስ በጥፊ አጮለችው:: ሙፊድ ቲማቲም የመሰለ ፊቱን በእጆቹ ሸፍኖ አቀረቀረ::

«ሙፊድ? !» አለች አይዳ ወደሱ እየተጠጋች::

«አታናግሪኝ! ፊቃደኛ ካልሆነች ለምን ከሷ ጋር ታገናኚኛለሽ? ባለጌ ነሽ!» ብሎ ወጣ::

ሀያት ሳሎኑ እንደገባች ወደከሪም ደወለች::

«ከሪም፣ በፍጥነት ከዚህ ቤት እንድትወስደኝ እፈልጋለሁ» አለችው::

«ምን ተፈጠረ?»

«ስንገናኝ እነግርሀለሁ::» አይዳ ተቻኩሎ ወደጓደኛው ሙፊድ የገሠገሠውን ኡመርን ሽኝታ ተንደርድራ ሀያት ወዳለችበት ገብታ አፈጠጠችባት::

ሀያት አይዳን ስታይ «አሁኑኑ መጥተህ ውሰደኝ» ብላ ስልኩን ዘጋችው::

«ያምሻል እንዴ አንቺ?» አለች አይዳ በንዴት እየተንቀጠቀጠች::

«አዎን፣ አብጃለሁ!» አለች ሀያት በቁጣ::

«ካላበድሽማ ሰውየውን እንዲህ አታዋርጂውም ነበር::»

«ማንም እንደአሻንጉሊቱ እንዲያየኝ አልፈቅድም::»

«እንግዳዬንኮ ነው በጥፊ የመታሽው::»

«እንግዳሽ'ኮ ጡቴን ...»

«ሀያት ግን ትክክል ነሽ?» አለች አይዳ ሀያትን ለማግባባት እየተጠጋቻት::

«እንዳትጠጊኝ!» አለች ሀያት በጩኸት፣ «ቤትሽ ይቀራል እንጂ ስልክሰክስ አልገኝም::»

አይዳ ተናደደች:: «የት ልትሔጂ አባክሽ?» አለች በንቀት::

«ከሪም ቤት!»

«እዚያ ምን ልትሆኚ ነው የምትሔጂው?! መጫወቻው እንዲያደርግሽ?»

«የፈለገውን ያድርገኝ!» ብላ ልብሶቿን ልታዘጋጅ ወደአይዳ መኝታ ክፍል ሔደች:: ሀያት ልብሷን መሰብሰብ መጀመሯን ስትመለከት አይዳን እልህ ተናነቃት::

«አይገናኟትም!» ብላም ወደሳሎን ሮጠችና ለሙአዝ ስልክ ደወለች::

*　　*　　*

«በቃ ሔደን እናምጣት» አለ ፍሰሃ::

«የሆነችውን አላወቅንም'ኮ:: ይሔኔ ከአይዳ ጋር በትንሽ ነገር ተጋጭተው ይሆናል» አለ ከሪም እያቅማማ::

«የሆነችውን እዚያው ተገኝተን ማየት አለብን:: አይዳ መጥፎ ሴት ናት:: እንደሷ ልታበላሻት ትሞክር ይሆናል::»

«እሺ እንውጣ!» አለ ከሪም ጃኬቱን እየደረበ:: መተላለፊያው ላይ መጅድን አገኙት:: ሰላምታ እንደተለዋወጡ፣ «መጥፎ ዜና ይዤ መጥቻለሁ» አለ መጅድ አፈራርቆ እያያቸው::

«ምን?» ሲል ተቻኩሎ ጠየቀው ከሪም:: መጅድ ኡመር የነገረውን አጫወታቸው::

«አይዳ ከነሙአዝ ጋር አሲራለች ነው የምትለኝ?» አለ ፍሰሃ በመገረም::

«ባትተባበርም ተገዳለች::»

«ስለዚህ ሀያትን ለማምጣት መሔዳችን .... » ከሪም የጀመረውን አረፍተነገር አንጠልጥሎ ተወው::

«አሁን አይዳ ቤት ልትሔዱ ነበር ማለት ነው?» አለ መጅድ በድንጋጤ:: ሁለቱም በአዎንታ መለሱለት::

«ለምን?»

ፍሰሃ በዝርዝር አስረዳው:: መጅድ ከልቡ አዝኖ፣ «በሉ እናንተ አርፋችሁ ቤታችሁ ተቀመጡ:: እኔ አመጣታለሁ» ብሎ ጥሏቸው ሄደ::

*　　*　　*

ሙአዝና ሻምበል ናስር ከአቡ አባዲ ቡፍያ በስተቀኝ መኪናቸውን ጨለማ ውስጥ አቁመዋል:: አንድ መኪና የአይዳን ቤት ተጠግቶ እንደቆመ ሻምበሉ በፍጥነት ወደሰውየው ገሰገሰ:: ሰውየው የበሩን ደወል እየተጫነ ነበር::

«ጤና ይስጥልኝ ጓደኛ» አለ ሻምበሉ የመጅድን ጀርባ ቸብ አድርጎ:: መጅድ ዞር ሲል የሻምበል ናስርን አስቀያሚ ጥርሶች ተመለከተ::

«ናስር?» አለ መጅድ ለመረጋጋት እየሞከረ:: በዚህ መካከል በሩ ተከፈተ:: አይዳ ስታያቸው በድንጋጤ ደርቃ ቀረች::

ሻምበሉ መጅድን ይዞ ወደውስጥ ዘለቀ:: ከዚያም «ነፃ የሆነ ክፍል ትጠቁሚንን?» አላት አይዳ ላይ አፍጥጦ::

ከዚያም ወደመጅድ ዞሮ፣ «ሀፊዝን እንደማታውቀው አረጋግጠህልኛል አይደል?» አለው::

«አንተም እነሙአዝን እንደማታውቃቸው ገልፀህልኛል::»

«ስለዚህ እኩል ለኩል ነን ነው የምትለኝ?»

«አዎን::»

«ጥሩ፣ እንግዲያውስ ሀያትን ይዘሃት አትሔድም» አለ ሻምበሉ ፍርጥም ብሎ::

«ለምን?»

«ሀያት በጣም ትጠቅመኛለች::»

«አልገባኝም::»

«እነከሪም ሀፊዝን ካላስረከቡኝ ሀያት ከአይዳ ቤት ንቅንቅ እንደማትል ንገራቸው::»

«ልጅቷ'ኮ ... »

«አውቃለሁ:: ከምንም አይነት የወንጀል ድርጊት ነፃ ነች:: የማቆያት ሀፊዝን ለማግኘት እነከሪም ስለሚያስፈልጉኝና እነከሪምን ደግሞ ለማግኘት ሀያት ስለምትጠቅመኝ ነው::»

«ናስር? እነሙአዝ ያዘመቱህኮ .... »

«እነከሪምን ከዚያም ሀፊዝን እንድይዝላቸው ነው:: እኔ ደግሞ ሀፊዝን በተለይ በራሴ ምክንያት አሳድደዋለሁ:: እሱን ካገኘሁ ለነሙአዝ ጩኸት ጆሮዬን አልሰጥም:: እነከሪም በሰላም አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ ሁኔታዎችን አመቻችላቸው ነበር::»

«ናስር ግራ አጋባኸኝ:: እዚህ የመጣኸው ከሪምንና ፍሰሃን ለመያዝ አይደለም እንዴ?»

«ነው:: ግን ሙአዝ አብሮኝ ስላለ ብቻ ነው እነሱን ለመያዝ ያደፈጥኩት:: ብቻዬን ብሆን ምን እንደማደርግ ታውቃለህ? ሀያትን ቤቱ ወስጄ እነከሪም ሀፊዝን እንዲሰጡኝ እደራደርባት ነበር::»

«ላ! ላ! ናስር እጅህን ከሷ ላይ አንሳ:: ከሪምና ፍሰሃ አሁኑኑ እንዲያነጋግሩህ አደርጋለሁ::ቤትህ ይደውሉልህል ትደራደራላችሁ::»

«ጠይብ! አሁን ወደምትሔድበት ሒድ:: ሀያት ግን ከዚህ ቤት ንቅንቅ አትልም::»

ሻምበል ናስር መጅድን አሰናብቶ አይዳን ጠራትና «ሀያትን ለነከሪም ብትሰጪ ወዮልሽ!» ብሏት ወጣ::

የበሩ ደወል ደጋግሞ ሲያቃጭል አይዳ ተንደርድራ ወደበሩ ሔደች::

«ማን?»

«እና ... እብጋ ሺቃላ (እኔ ነኝ፣ ሰራተኛ ፈልጌ ነው)» አለች አንዲት ሴት:: አይዳ በጥርጣሬ በቀዳዳው አጮልቃ ከተመለከተች በኋላ በሩን ከፈተች::

ከፊቷ በቀር ሁለመናዋን በጥቁር ልብስ የተሸፋፈነች ሴት በሩ ላይ ቆማለች::

«የሀበሾች ቤት ነው ይሄ?» አለች እንግዳዪቱ::

«ነው::»

«ሠራተኛ ፈልጌ ነጡ:: ትቀጠሪያለሽ?»

«እኔ እንኳን ስራ አለኝ:: ግን ስራ የፈታች እህት አለችኝ::»

«እንግዲያው ልውሰዳታ!»

አይዳ አመነታች:: መልሳ ደግሞ ቆረጠች:: «እሺ ልጥራት» ብላ እሳሎን ስትገባ ሀያት በፍርሀት ተኮራምታለች::

ሀያት ስራ ተገኝቶልሻል:: አሁኑኑ ብትሔጂ ጥሩ ይመስለኛል:: ሻምበሉ ተመልሶ ሲመጣ ከሪም እንደወሰደሽ እገልፅለትና ከሪም ደግሞ እንዲረጋጋ ስለሁኔታው አስረዳዋለሁ» አለች አይዳ ተቻኩላ::

«አይ ... እ ... እኔ .. ም..ም» ሀያት ትንቀጠቀጣለች::

«እንዴ? ምን መሆንሽ ነው? ... እኔኮ ... » ስልኩ ጮኸ::

አስፈሪውን የሻምበል ናስር ድንፋታ ላለመስማት እንዳችም እንቅስቃሴ አላሳየችም:: ስልኩ ለሶስተኛ ጊዜ ሲጮህ ሀያት አነሳችው::

«ሀሎ አይዳ፤ የምነግርሽን በጥንቃቄ አዳምጪ» ትንፋሹ የሚቆራረጥ የወንድ ድምፅ ይሰማል::

«ማነህ?» አለችው ሀያት::

«አርአያ ነኝ:: ሀያት ቤትሽ ለአንድ ሌሊት እንኳን ብታድር በሙአዝና በሻምበል ናስር እጅ መውደቋ አይቀርም:: እኔ ...»

«እንዴ! ለምን? ወይኔ! እማይዬ...»

«ማነሽ አንቺ? አይዳ አይደለሽም እንዴ?»

«ሀያት ነኝ:: አርአያ፣ እኔ ግን ምን አደረግኋችሁ?»

መልስ ከማግኘቱ በፊት አይዳ ስልኩን ነጠቀቻት።

«አርአያ? አይዳ ነኝ። ምን ተፈጠረ?» አለች በችኮላ።

«የምልሽን በፍጥነት ፈፅሚ። እነከሪም ሀፊዝን አሳልፈው እንዲሰጡት ሻምበል ናስር ይፈልጋል። እነሱ ደግሞ ሀፊዝን አሳልፈው እንደማይሰጡት እርግጠኛ ነኝ። ከግማሽ ሰዓት በፊት ከነሙአዝ ጋር ነበርኩ። ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ ከነከሪም ጋር በስልክ ይደራደራሉ። ድርድሩ እንዳሰበው ካልሄደለት ሀያትን በቁጥጥር ስር ሊያደርጋትም ሻምበሉ ወስኗል። እኔ ደግሞ ሀያት በማታውቀው ነገር እንድትሰቃይ አልፈልግም። ስለዚህ ሰራተኛ እንደሚፈልግ ከወር በፊት የነገረኝ ወዳጆቼ ቤት ደውዬ ያንቺን ቤት ጠቁሚያቸዋለሁ። ክፍያቸው ዝቅተኛ ቢሆንም ሀያትን ከዚህ አደጋ የማዳን ግዴታ ያለብን ይመስለኛል። ቤትሽ ድረስ መጥታ የምታነጋግርሽ ሴትዮ ስም ሲሀም ይባላል። እንደደረሰች ከሀያት ጋር አግባብተሽ ሸኛት።»

አይዳ ስልኩን ዘግታ ስትመለስ ሴትየዋ ተስላችታ ትንጉራደዳለች።

«ሀያት? ከሴትየዋ ጋር መሔድ አለብሽ» አለቻት አይዳ ፊርጠም ብላ።

«መሔድ አለብኝ? እሺ!» ብላ ሀያት ተነሳች።

* * *

ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ላይ ከሪም፣ ፍስሃና መጅድ አዲሱ አፓርታማቸው ውስጥ ተቀምጠዋል። ከሪም እሻምበሉ ቤት ደውሉ ምላሹን ሲጠባበቅ፣ «ሀሎ፣ ሻምበል ናስር!» በማለት ስልኩን ያነሳው ሰው ራሱን አስተዋወቀ።

«ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ? የመጅድ መልዕክት ደርሶን ነው የደወልንልህ» አለ ከሪም በትህትና::

«አንተ ማንኛው ነህ?» አለ ሻምበሉ ቆጣ ብሎ::

«ከሪም ነኝ::»

«የመደራደሪያ ነጥባችንን አውቀኸዋል?»

«ግልፅ አልሆነልኝም ጌታዬ?»

«ጌታዬ አትበለኝ:: ጌታ አላህ ብቻ ነው:: ሻምበል ናስር ብለህ ጥራኝ::»

«እሺ::»

«የማቀርብልህ ሀሳብ ከነሙአዝ የተሰወረ ነው::»

«አሁን ከነአርአያ ጋር አይደለህማ ሻምበል?!»

«ሙአዝን ለራት የሚሆነን ምግብ እንዲገዛ ልኬዋለሁ:: አርአያ ግን ከቤቱም አልተንቀሳቀሰ::»

«ብጄ!?»

«እኔ የምፈልገው ሀፊዝን ብቻ ነው::»

«ከሚያሳድዱን ሰዎች ጐን ቆመህ እንዴት ይህን ትላለህ?»

«በርግጥ ሙአዝን ላለማስከፋት በዚህ ጉዳይ ላይ ውድ ጊዜዬን አጥፍቻለሁ:: ሰስተኛው ተፈላጊ ሀፊዝ መሆኑን ካወቅሁ በኋላ ግን ሀሳቤን ቀይሬአለሁ::»

«አልገባኝም ሻምበል::»

«አትቀልድ ሰውዬ:: ሀፊዝን የምፈልገው ለበቀል ነው:: እንደዛሬ ለስልጣን ሳልበቃ አንዲት መኪናዬን በቁማር በልቶኝ ከእናቴ ጋር እስከመጨረሻው እንድቆራረጥ አድርጐኛል:: እናቴም እንደከዳችኝ ሞተች:: በወቅቱ ችግሬን ነግሬው ከናቴ ጋር እንድታረቅ የበላኝን ሊሞዚን ታክሲ እንዲመልስልኝ ብማፀነው ተፍቶብኝ ነበር የሔደው:: ለዛ ብልግናው ሊቀጣ ይገባል:: እናንተ ግን በፈለጋችሁት መንገድ ወደአገራችሁ እንድትገቡ አደርጋለሁ:: ተግባባን?»

ከሪም በድንጋጤ ብዛት ፀጥ ብሎ ቆየ::

«ሀሎ ከሪም?» ሻምበሉ በጩኸት ቀሰቀሰው::

«አ ... አለሁ ሻምበል::»

«ታዲያ መልስህ ምንድነው?»

«ሻምበል ያንን ማድረግ አልችልም» አለ በሞተ ድምፅ::

«ምን አልክ?»

«አልችልም::»

«ጥሩ! ከጉንህ ታገኛታለህ» ብሎ ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋው::

ከሪም ፊጥኖ አይዳ ጋ ደወለ::

«አይዳ? ሀያትን አገናኚኝ::»

«ሀያት የለችም ከሪም::»

«ምን?»

«ከአንድ ሰዓት በፊት ስራ አስገባኋት::»

«ብምርሽ ነፍሴን አላህ አይማራት!»

«ረጋ በል እንጂ:: ስራ ያስገባኋት'ኮ ከተዘረጋው ወጥመድ እንድትድን ነው::»

«ከስራ የምትመጣው መቼ ነው?»

«ከአስራአምስት ቀን በኋላ::»

«እሺ፣ የቀጣሪዎቿን ስልክ ቁጥር ስጭኝ?» ሰጠችው::

ስልኩን ዘግቶ ከሻምበል ናስርና ከአይዳ የተነጋገረውን ቃል በቃል ነገራቸው::

ቀጥሎ ስልክ መደወል ሲጀምር ፍስሃ ተገርሞ፣ «የት ነው የምትደውለው?» ሲል ጠየቀው::

«ሀያት ጋ ነዋ!» በማለት መለሰለት::

«ያምህል እንዴ? ሌሊቱ ተጋምሷል'ኮ» አለ መጅድ በጩኸት::

«ምን ላርግ ታዲያ?» አለ ከሪም::

«ነገ ትደውልላታለህ። በደረቅ ሌሊት ወንድ ያወሰለ... ሰው ያባርራትና ታርፈዋለህ።»

ከሪም ተስፋ ቆርጦ ስልኩን አቀፎው መለሰው።

*　　*　　*

የሀፊዝ የመኝታ ክፍል እንደወትሮዋ አይደለችም። ያ ሁሉ ሳቅና ጨዋታ በትካዜና በዝምታ ተተክቷል። ሰሚራና ሀፊዝ ኮሽታ በሰሙ ቁጥር መደንበር ከጀመሩ ከራረሙ። ዛሬም ራት መብላት እጅግም አላሰኛቸውም።

ሀፊዝ ከሳኡዲ አረቢያ ስለሚወጣበት መንገድ በጥልቅ ያስባል። በመኪና መሔድ ካለበት ሪያድ ሄዶ ወደኩዌት ይዘልቅ ይሆናል። ከዚያስ? ግራ ተጋባ። ምናልባት በባህር ቢጓዝ ይሻል ይሆን? በርግጥ በመጀመሪያ ጂዛን ይገባል። ከዚያስ? ወደየመን ማምራት ይሻላል ወይስ ወደኤርትራ? በአየርስ?...

ሰሚራም በበኩሏ ሀገሯ የምትገባበትን ቀን መናፈቅ ጀምራለች። የቤተሰቦቿ አቀባበል ምን ሊመስል እንደሚችል ታውጠነጥናለች። በመሃሉ ኤርምያስ ትውስ አላት። ለመሆኑ ሚስቱ ምን ትመስል ይሆን? ቅናት ዳበስ አደረጋት። ስልኩ ሲጮህ ተደናግጠው ተያዩ።

«አንሳው እንጂ?» አለች ሰሚራ በዝቅተኛ ድምፅ። ሀፊዝ ሰአቱን ተመለከተ። ሌሊቱ ገስግሷል። ቅር እንዳለው እጆታውን አነሳ።

«ጤና ይስጥልኝ! የሀፊዝ ቤት ነው?» የሚል ወፍራም የወንድ ድምፅ ከወዲያኛው ጫፍ ተሰማ።

«ነ ... አ... አይደለም» የሀፊዝ አንደበት በድንጋጤ ተጠላለፈ::

«ለስራ ጉዳይ ነበር የፈለግነው:: አባክዎን ካለ ያቅርቡልን?»

«ተሳስተዋል!»

«... እስልክ ማውጫ ላይ ያገኘናቸውን ሀፊዞች አነጋግረን ጨርሰናል:: የመጨረሻው ሀፊዝ የሚገኘው በዚህ ስልክ ነው:: ስለዚህም ተፈላጊው እዚህ እንዳለ እናምናለን::»

«ትሰማኛለህ?! ይህ የሀፊዝ ቤት አይደለም ማለት አረብኛ ነው! ይልቅ ምናለ ሰላሜን ባትነሳኝ?» አለ ሀፊዝ በጩኸት::

«ይቅርታ እየጠየቅሁ ጥቂት ላወጋህ እወዳለሁ» አለው ደዋዩ::

«ትርፍ ጊዜህን በማይረባ ቀልድ ከምታባክን ይልቅ ሴት ወደምታገኝበት ቤት ደውለህ 'የስልክ ፍቅር' ጥምህን ብታረካ ይሻልሃል» አለ ሀፊዝ ደዋዩን በከተማ ውስጥ እንደአሸን ከፈሉት ሴቶችን በስልክ እየተገናኙ በቀጭኑ ሽቦ የፍቅር ቁጠማ እየነሰነሱ የሴት ፍላጐታቸውን ከሚያረኩ ስድ ወንዶች ጋር ለማመሳሰል እየሞከረ::

«ማድረግ ያለብኝን ስትነግረኝ ያንተንም ማንነት እያሳወቅኸኝ ነው» አለ ደዋዩ በፌዝ::

«እኔ ጌታዬ፣ ለሀይማኖቴ ያደርኩ .... »

«ለማያውቅህ ታጠን!»

«ምን አልከኝ?» አለ ሀፊዝ በጥፊ የተመታ ያህል ደንግጦ::

«ሀፊዝ ማለት አንተ ነህ!»

«ትሰማኛለህ? ... » አለ ሀፊዝ ለመረጋጋት እየሞከረ፣ « ... እኔ ይህንን ቤት ከሁለት ወር በፊት ነው ከሼህ አብዱልሀሚድ የገዛሁት:: በማይረባ ንትርክ ጊዜህን ከምታባክን ሼህ አብድልሀሚድን

ፈልገና የምትለውን ሰው እንዲያገናኙህ ጠይቃቸው» ብሎ የስልኩን እጀታ በሀይል ወርውሮ በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

*　　　　*　　　　*

ሻምበል ናስር አይዳ ቤት የደረሰው የንጋቱ የሰላት ጥሪ ለመሰማት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩት ነበር፡፡ አይዳን ገፍትሮአት ሰተት ብሎ ወደቤቱ ውስጥ ዘለቀ፡፡ በነከሪም ድፍረት ጨሷል፡፡

ቤተሰቡ ለድህነት ተዳርጉ እርሱም ፖሊስ እንዲሆንና እናቱ በብስጭት ራሳቸውን እንዲያጠፉ ያደረገውን ሀፈዝን እሳልፈው የማያስጡት ከሆነ ሁሉንም ያጠፉቸዋል፡፡ የተዘጋጀላቸውን የበቀል ፅዋ ሁሉም ይጨልጧታል፡፡

ሻምበል ናስር ክፍሎቹን ፈትሾ እንዳበቃ ተቻኩሎ ወደአይዳ ተመለሰ፡፡ «የታለች አንቺ?!»

«ማ...ማንና...»አይዳ ተንተባትባ ዝም አለች፡፡

«ያቺ የከሪም ቅምጥ! የታለች?!» አለ በጩኸት፡፡

«የ..የ..ሻምበል ... ጌታዬ .. እኔ ... »

«ድንቢጧ የታለች?»

«የ .. የለችም፡፡»

«ምን? የለችም? እንዴት የለችም?!» ሻምበሉ ተንደርድሮ አነቃት፡፡

«ሻምበል? ... እ .. እኔ ... »

ሻምበሉ ስስ ፒጃማዋን በሁለት እጆቹ ይዞ ተረተረው፡፡ «ተናገሪ አንቺ ሽርሙጣ! ደውለሽ ነግረሽው ወስዳት ወይስ አንቺው

ነሽ የወሰድሽለት? በስንት ሰዓት ላይ ነው ይሄ የተፈፀመው? ተናገሪ!» ጡቶቿን ጎትቶ ጨምድዶ ያዛት፡፡

«አ ... እሺ፣ ልንገርህ ... ቆይ ልንገርህ ... ስራ አስገባኋት፡፡»

«ውሸታም!» ብሎ በጥፊ አጮላት፡፡

«እውነቱን ነው፡፡እናንተ እንደሔዳችሁ አንዲት ሴት ሰራተኛ ፍለጋ ስትመጣ ...»

«ለምን እንድትሔድ ፈቀድሽላት?»

«ካልሔድኩ አለችኝ፡፡ አንተ ያስገባሽኝን ግዴታ ከነገርኳት ደግሞ በተኛሁበት እንዳትጠፋ ሰግቼ ዝም አልኩ፡፡»

«የተቀጠረችበትን ቤት አድራሻ ንገሪኝ?»

«አላውቀውም፡፡»

አገጬዋን በቡጢ ሲመነግለው አፏን ጨው ጨው አላት፡፡ «ስልኩን ብቻ ነው የተቀበልኩት» አለች ፈጠን ብላ፡፡

«በይ በፍጥነት ፅፈሽ አምጪ» ብሎ ገፈተራት፡፡

* * *

ረፋዱ ላይ ፍሰሃ ሀፊዝንና ሰሚራን አስከትሎ ከሪም ዘንድ መጣ፡፡ ከሪም እንግዶቹን እንዲቀመጡ ጋብዞ ወደማዕድቤት ገባ፡፡ ፍሰሃ የለኮሳትን ሲጋራ እንዳጋመሰ ከሪም በአራት ብርጭቆዎች ጭማቂ ይዞ ተመለሰ፡፡

«ሀፊዝ በጣም ነው የምናዝነው፡፡ ለዚህ አይነቱ ችግር የዳረግንህ እኛ .... »

«ላእ! ...» አለ ሀፊዝ ፍሰሃን አቋርጦ፣ «ጓደኝነታችን ከስጋ ዝምድና የላቀ ነው፡፡ የናንተን ውለታ ... »

«እኛ ደግሞ ምን ዋልንልህ?» ከሪም ጣልቃ ገባ፡፡

«ሌላው ቢቀር ስሚራን ያገኘሁት በናንተ ነው:: ስሚራ ደግሞ ለኔ ልዩ ሴት ነች! ዛሬ በከባድ ወንጀለኛነት በምታደንበት ክፉ ሰዓት እንኳ አልሸሽችኝም::» የሀፊዝ አይኖች እንባ አቀረሩ::

በቡና ጠረጴዛው ዙሪያ የተቀመጡት አራት ሰዎች በሀዘን አንገታቸውን ደፍተው ዝም አሉ::

«አሁን መውሰድ ስላለብን እርምጃ እንነጋገር» አለ ፍሰሃ ጥቂት ቆይቶ::

«አንድ ያልገባኝ ነገር ግን የደዋዮቹን ማንነት እንዴት ልታውቅ እንደቻልክ ነው» አለ ከሪም::

«እነሱ ናቸው እባክህ» አለ ሀፊዝ በተሰላቸ ድምፅ::

«እንዲያማ ከሆነ ቤት መቀየር ይኖርባችኋል» አለ ፍሰሃ::

«ልክ ነህ ከነገ ጀምሮ ደግሞ ስሚራ ካገር ለመውጣት እንቅስቃሴ ታደርጋለች» አለ ሀፊዝ የሰሚራን ክንድ እየደባበሰ::

«ውጥረቱ እስኪረግብ እሷ የመኖሪያ ፈቃድ አውጥታ ትመለሳለች:: ከዚያም ከሳኡዲ አረቢያ እንወጣለን::»

«ሀፊዝ፣ ሻምበል ናስር አንተን አሳልፈን እንድንሰጠው ጠይቆናል:: ካልሆነ ሀያትን ካለችበት አስሶ ... » ከሪም የጀመረውን መጨረስ ስለተሳነው ዝም አለ::

ሀፊዝ ለከሪም ከሀያት እንደማይበልጥበት ያውቃል:: ስለዚህ ምርጫው ግልፅ ነው የሚሆነው:: እናም ህይወት አልባ አይኖቹን ከሪምና ፍሰሃ ላይ አንከባለለ:: «እናዝናለን፣ መቼስ ሀያት መሞት የለባትም!» እስኪሉት ነበር የሚጠብቀው::

ከሪም ግን ረጋ ብሎ «ሀፊዝን መቼም አሳልፈን አንሰጥህም ብለነዋል» አለ::

ሀፊዝ በዝግታ ከወንበሩ ተነሳ:: ጉንጮቹ በእንባ ርሰዋል:: «እኔ ... » ብሎ ከሪም ላይ ተጠመጠመበት::

*　　　*　　　*

ሻምበል ናስር ስለተደረገው የፍተሻ ጥሪ ሪፖርት አዳምጦ ሲጨርስ የተጠረጠረው ስልክ ቁጥር የሚገኝበት ቤት ባፋጣኝ ተፈልጐ ሀያ አራት ሰዓት ባይነ ቁራኛ እንዲጠበቅ አዘዘ:: የከሪም መኪና ሰሌዳ ቁጥርም ለትራፊክ ፖሊሶች እንዲበተን አደረገ::

ከዚያም ወደነሙአዝ ቤት ገሰገሰ:: ከነሙአዝ ጋራም ስለእንቅስቃሴያቸው በሰፊት ከተወያየ በኋላ ሀያትን በቁጥጥር ስር ማዋል እንደሚፈልግ ገለፀላቸው::

«ሀያትን ለኔ ተውልኝ:: ካለችበት ፈልፍዬ አመጣልሀለሁ» አለ ሙአዝ ፈጥኖ:: ሻምበሉ አልመለሰለትም:: «ቀላል'ኰ ነው:: የቤቱን አድራሻ ማወቅ አያዳግትም:: ባለቤቶቹን ደውሎ መጠየቅ ነው» አለ ሙአዝ በስሜት::

«ማነኝ ብለህ ትጠይቃለህ? የማንንም አድራሻ ለማወቅ'ኰ ምክንያት ያስፈልጋል» አለ አርአያ ጣልቃ ገብቶ::

«በሴት ማስደወል ይቻላል:: የሀያት ዘመድ መሆኗን ገልፃ አድራሻቸውን ትቀበልልናለች::»

«ከዚያስ?» ሲል አርአያ ጠየቀ::

«ከዚያማ አንጠልጥሎ ማምጣት ነዋ!»

«የማይደረገውን» አለ ሻምበሉ ተደናግጦ:: «ከአንድ ሳዑዲ ዜጋ ቤት ሰተት ብለን ገብተን ሰራተኛውን ልንወስድ አንችልም:: የፍርድ ቤት ትዕዛዝ አለያም የከፍተኛ ባለስልጣን ደብዳቤ ያስፈልገናል::»

ሙአዝ ጨሰ። ፈጥኖ ሲጋራውን አቀጣጥሎም ይምገው ጀመር።

«ይልቅዬ በእረፍት ቀኗ ጌቶቿ ይዘዋት ሲጠጡ መንገድ ላይ ጠብቀን መያዝ እንችላለን» አለ ሻምበል ናስር።

«ላ! ላ!» ሲል አርአያ ተቃወመው።

«የተሻለ ሀሳብ አለህ?» አለ ሻምበሉ ።

«አዎን፣ አለኝ። እረፍት ስትወጣ ቀጥታ የምትሔደው አይዳ ቤት ነው። አይደለም?» ሁለቱም በአዎንታ መለሱለት።

«ያኔ ከአይዳ ቤት በቀላሉ እናፍናታለን። መንገድ ላይ ይሁን ካልን ግን ፈታሽ ፖሊሶች አብረውን ሊኖሩ ይገባል። ሻምበል ናስር እንዳይፈፅመው ከደረጃው ጋር የማይመጣጠን ሥራ ነው» በማለት አርአያ አብራራ።

«ልክ ነህ» አለ ሻምበሉ ተከራርቶ። «ከአይዳ ቤት እንወስዳታለን።»

## ምዕራፍ ሀያ አንድ

የሀያት አሠሪ አርአያ በነገረው መሰረት ሀያትን አርብ ጠዋት ወደአይዳ ቤት ለማድረስ ተስማም:ቷል:: ዛሬ ምሽቱ ላይ ግን ከሻምበል ናስርና ከሙአዝ ጋር ሀያትን ሊያጠምዱ አይዳ ቤት ይሔዳሉ:: ስለዚህ ምሽቱ ከመድረሱ አስቀድሞ አይዳ ዘንድ ስልክ ደወለ::

«ሀያት ነገ ጠዋት ቤትሽ ትመጣለች:: ጊዜ ሳታጠፊ ከከሪም ጋር አገናኚያት» አላት::

«ድንገት ሙአዝና ሻምበል በአካባቢው ቢኖሩና ... »

«እሱ አያሳስብሽ፣ ከሻምበሉና ከሙአዝ ጋር ሆነን ዛሬ ማታ ቤትሽ እንመጣለን:: ሀያት ስለማትኖርም መበሳጨታቸው የማይቀር ነው:: ያኔ በንዴት ይጦፋሉ::ይኸኔ አረጋግቼ ውስኪ እግታቸዋለሁ:: እስከንጋት ስለሚጠጡ በጠዋት አንቺ ቤት ሊመጡ አይችሉም:: ገባሽ?» አላት::

«አዎን፣ ገብቶኛል» ብላ ስልኩን ዘጋች::

* * *

አርብ የእረፍት ቀን ስለሆነሱቆች፣ መስሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የግልና የመንግስት ተቋማት ይዘጋሉ:: በዚህም የተነሳ መንገዶቹ ጭር ብለዋል:: የረፋዷ ፀሀይ መግረር ጀምራለች:: አንድ ነጭ ዳትሰን ከቁለይል መንደር በውስጥ ለውስጥ መንገድ አቆራርጦ የአቡ አባዲን ቡፍያ በቀኝ ትቶ ወደአይዳ ቤት እየከነፈ

ነበር:: ስማያዊውን በር አልፍ ብሎ ሲቆም ሀያት የኋለኛውን በር ከፍታ አካባቢውን በስጋት እየቃኘች ወደአይዳ ቤት ሮጠች::

በሩን የከፈተችላት አይዳ ነበረች:: አይኖቿ ቀልተዋል:: ለተወሰነ ጊዜ ተፋጠጡ:: ሀያት፣ የአይዳ ስሜት በፍጥነት እየተለዋወጠ መሆኑን ከገፅታዋ አነበበች:: ጉትታ ወደውስጥ አስገብታት በፍጥነት አባያዋን ደረበች:: ሀያት በአይዳ ሁኔታ ስለተረበሸች፣ «አይዳ ምን ሆነሻል?» በማለት ብትጠይቃትም አይዳ ግን ጊዜ አልነበራትም:: «እንውጣ! ፍጠኝ!» አለቻት::

ቤቱን ከውጭ ቀልፈውም በቁለይል መንደር ቁልቁል ወረዱ:: «መክተብ አቃሪ» የሚል ፅሁፍ ከተለጠፈበት የደላሎች ቢሮ ሲደርሱ ወደቀኝ ታጥፈው ካረጀ ህንፃ ስር የሚገኝ ቤት አንኳኩ:: አንዲት ወፍራም ሴት በሩን ከፈተችላቸው:: ሴትየዋ ፀጉሯን ልቅም አድርጋ ሹሩባ ተሰርታዋለች::

«እነአርአያ ማታ መጥተው ነበር?»ስትል ሴትየዋ አይዳን ጠየቀቻት::

«እስከምሽቱ ስድስት ሰአት ሲጋራቸውን ሲያቦነብኝ አመሹ:: ከዛሬ ጀምሮም ቤቴን በአይነቁራኛ እንደሚያስጠብቀው ሻምበሉ ዝቷል::»

«ታዲያ አሁንስ የተመደበው ሰው አይቷችሁ ከሆነ ምን ይውጠናል? ... ቤቱ ውስጥኮ አረቄ ....» ሴትየዋ ሀያትን አየት አድርጋ ዝም አለች::

«ይሐኔ ገና ከእንቅልፋቸውም አልነቁም እባክሽ:: አርአያ ሌሊቱን ሙሉ ሲያጠጣቸው እንደሚያድር ነግሮኛል» አለቻት አይዳ ዘና ብላ::

የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

ሀያት ፍራሹ ላይ ተደላድላ እየተቀመጠች፣ «ከዚህ በኋላስ ምንድነው የምናደርገው?» አለች::

«ነገ አስር ሰአት ላይ ሙስተሽፋል ማዕሩፍ ክሊኒክ ከከሪም ጋር ትገናኛለሽ::»

«ለምን እስከነገ እንቆያለን?» አለች ሀያት ግንባሯን ቋጥራ::

«ምክንያቱም ዛሬ የዕረፍት ቀን ስለሆነ እነሙአዝ ከሪምን በቀላሉ ሊያዩት ይችላሉ:: ቅዳሜ ግን የስራ ቀን እንደመሆኑ ሻምበሉ ፖሊሶቹን ቢያሠማራም የሚያተኩሩት የኔ ቤት ላይ ነው::»

ሀያት እንደገባት ለማሳወቅ ራሷን ነቀንቃ ዝም አለች::

«ሀያት አመርኩ የመኖሪያ ወረቀት ገዛልኝ» አለች አይዳ ፍንድቅ ብላ::

ሀያት «እንኳን ደስ ያለሽ!» ብላ ሳመቻትና፣ «... ወደሀገር ቤት ልትሔጂ ነዋ?»ስትል ጠየቀቻት::

«አዎን፣ ነገ ወደኤምባሲ እሔዳለሁ:: መፍጠን ግን ይኖርብኛል:: አለያ በናንተ ጦስ እኔም መጨፍለቄ አይቀርም::»

«ልክ ነሽ::»

«እንደምታዪው ሴትየዋ በጣም ተደናግጣለች:: ስለዚህ ነገ አብረሽኝ ኤምባሲ ትሔጃለሽ:: በዚያው ሙስተሽፋል ማዕሩፍ እንገባለን:: ከሪምንም በዚያ እናገኘዋለን:: ምን ይመስልሻል?» አለች አይዳ::

«የሴትየዋ ፍርሀት ሊጋባብኝ ስለሚችል እኔም መሄዱን እመርጣለሁ » ስትል ሀያት ፈጥና መለሰች::

«ጥሩ እንግዲያው ከሪም ዘንድ ደውዬ ልምጣ»ብላ አይዳ ተነስታ ወጣች::

* * *

ለሁለት ቀናት የሚከራይ ቤት ፍለጋ ያደረገው ሩጫ ያልተሳካለት ፍሰሃ የዕለተ አርብን ምሽት ከቤቱ ለማሳለፍ በጊዜ ወደአፓርትማው ተመለሰ:: ረቡዕ እለት ኢትዮጵያ ኤምባሲ የሄደችው ስሚራ ለሳምንት ተቀጥራ ስለመጣች ወደሀገር ቤት ይዛው የምትሔደውን ዕቃ ለመግዛት የሚያስፈልጋትን ገንዘብ ከሀፊዝ ጋር እያሰላች ነበር::

ፍሰሃ ሰላምታ አቅርቦላቸው ወደመኝታ ክፍሉ ገባ::

«ፊሽ፣ ዛሬም አልቀናህም?» አለ ከሪም ተቻኩሎ::

«ምን ይቀናኛል? ሳባ ሬስቶራንት ሔጄ ያነጋገርኳቸው አቃሪዎች በሙሉ የሚከራይ ቤት ያለው ሰው አያውቁም» አለ ፍሰሃ በታከተ መንፈስ::

«ሌላስ ቦታ አልሞከርክም?»

«ያልዞርኩበት የለም:: ኪሎ ሰብአ ሰፈር ግን ሊኖር እንደ ሚችል አንዱ ጠቁሞኛል ስለደከመኝ ግን ወደቤቱ መጣሁ::» አለው

«የሀፊዝን የቤት ዕቃዎች ወደዚህ ብናመጣቸውስ ምን ይመስልሀል?» አለ ከሪም ትንሽ አሰብ አድርጎ::

«ይሄማ እብደት ነው!»ብሎ ፍሰሃ ከተንጋለለበት ተነሳ::

«እንዴት?»

«በስልክ ያነጋገሩት ሰዎች ይሄኔ መረባቸውን ጥለዋል:: ስለዚህ እቃውን ማጋዝ ብንጀምር በቀላሉ ስለሚያጠምዱን ቢያንስ ለሁለት ሳምንታት ያህል መታገስ ይኖርብናል::»

ከሪም በመስማማት ራሱን ነቀነቀና ጥቂት ሲያስብ ቆይቶ፣ «ከነአርአያ ጋር መደራደር አለብን»አለ በርጋታ::

ፍሰሃ ጆሮዎቹን ማመን አልቻለም:: «አይደረግም!» አለ በጩኸት:: ከአንድ ሰአት በላይ የፈጀው ይኸው ጭቅጭቅ በከሪም አሸናፊነት ተጠናቀቀ::

ስልኩን ያነሳው ሙአዝ ነበር::

«አንተ ከሀዲ!» ብሎ ጮኸ ሙአዝ::

«አዝናለሁ፣ ሙአዝ» አለ ከሪም በቀስታ:: «በእልህ ተነሳስተን ለፈፀምነው ስህተት ... »

«ዝጋ!»

«ስለጥንቱ ፍቅራችን ስትሉ ይቅር በሉን:: በርግጥ ልንዳ ፈራችሁ ባልተገባ ነበር» አለ ከሪም:: ይሄን ያክል ሊለማመጠው የወሰነው ፍሰሃ ብቻውን ስለሚቀር ላደጋ እንዳይዳርጉት በማሰብ ነበር::

«ከከሃዲዎች ጋር መደራደሩ ያዳግተኛል» አለ ሙአዝ እየተዝዝና::

«ይልቅዬ ልንክሳችሁ ስለወሰንን አንዱን እሽግ ኮኬይን ወስዳችሁ ዕርቅ ይውረድ::»

«ባንድ እሽግ አንታረቅም!» አለ ሙአዝ ቆጣ ብሎ::

ከሪም ላፍታ ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ፣«እኛ ዘንድ የነበሯችሁን የመጠጥ ካርቶኖች ሽያጭም እንጨምራለን::»

«ከነእሽጋችሁ ገደል ግቡ!»አለው ሙአዝ::

«እንግዲያውስ» ብሎ ከሪም ንግግሩን ሲያቋርጥ፣ «ቀጥል! እንጂ» ብሎ ሙአዝ ጮኸበት::

«ስማ፣ ሻምበል ናስር በቁማር ስለተበላችው ሊሞዚን ማስታወስ ይኖርበታል:: በስም ዝውውሩ ወቅት ፊርማውን ያስፈረባቸው ወረቀቶች በሀፊዝ እጅ ይገኛሉ::»

«ምን?»

«ስልኩን ዘግቼ ወደሚመለከተው አካል ከመደወሌ በፊት... »

«ቆይ፣ ቆይ!»ብሎ ሙአዝ አቋረጠውና የስልኩን መነጋገሪያ አፍና ለአርአያ ጉዳዩን ባጭሩ ገለፀለት። ባልጠበቁት አቅጣጫ መጥተውባቸዋል። «ብቃ፣ ያላችሁን አስረክቡንና እርቅ ይወርዳል!» ብሎት እየተከነ ስልኩን ዘጋ።

# ምዕራፍ ሀያ ሁለት

በደረሱበት ስምምነት መሠረት ፍስሃ ቅዳሜ ጠዋት ሁለት ሰዓት ላይ ሀየ ሰላማ አፓርትማ ሲደርስ አርአያ በበሩ ሽንቁር አየው:: ፍስሃ የበሩን ደወል ሲጫን ከሙአዝ ጋር ተጠቃቅሰው አርአያ መዝጊያውን ከፈተ:: ፍስሃ ወደውስጥ ሲዘልቅ አርአያ አስቁሞ ፈተሸው::

«አርአያ እመነኝ» አለ ፍስሃ በርጋታ::

«እሞክራለሁ::»

ኳላና ፊት ሆነው ወደሳሎኑ ዘለቁ:: ሙአዝ እጁን አጣምሮ ቆሟል::

«ኬፈክ?» ብሎ ፍስሃ እጁን ዘረጋ::

ሙአዝ በጥርጣሬ እንደተዋጠ ጨበጠው::

«ብል ያመጣኸውን አስረክበን» ሲል አርአያ ፍስሃን አዘዘው::

«በቅድሚያ ይቅርታዬን ተቀበሉ» አለ ፍስሃ ሁለቱንም አፈራርቆ እያየ::

«ወሬ አታብዛ!»ብሎ አርአያ እየገፋ ወደመኝታ ቤት ወሰደው:: ሙአዝ በፍስሃ ጅልነት እየሳቀ ከሳሎን በተጠንቀቅ ወደሚጠብቀው ሻምበል ዘንድ ስልክ ደወለ::

ከሰባት ደቂቃዎች በኋላ ከሰላሳ የሚበልጡ ፖሊሶች የነአርአያን አፓርታማ ወረሩ:: ሙአዝና ሻምበሉ አምስት ፖሊሶች አስከትለው እየተጀነኑ ወደመኝታ ቤት አመሩ::

ሙአዝ በሩን ገፍቶ ሲገባ ወለሉ ላይ አንድ ሰው ተዘርግቷል:: «አርአያ?!» ሙአዝ በድንጋጤ ደርቆ ቀረ::

እርእያ አልመለሰለትም:: መስኮቱ ተከፍቶአል:: «ወንጀለኛው ....» ብሎ ሙአዝ ወደተከፈተው መስኮት አመለከተ:: ሻምበል ናስር ታዳኙ በመስኮት ማምለጡን ተረዳ::«ፍጠኑ! አካባቢውን አስሱ!» ሲልም ፖሊሶቹ ላይ ጮኸ::

* * *

ፍስሃ ሊውጠው ስለነበረው አደጋ፣ ለከሪምና ለሀፌዝ ከተረከላቸው በኋላ በቀዝቃዛ ውሀ ታጥቦ ወደነሙአዝ ስልክ ደወለ::

«ዛሬ መደወል አልነበረብህም» አለው እርእያ በቁጣ::

«አውቃለሁ:: ልዝጋው እንዴ ታዲያ?»

«ላ! ላ! ደግነቱ ብቻዬን ነኝ::»

«ያ ዲቃላስ የለም?»

«ፍስሃ ታረም!» እርእያ ጮኸበት::

«ይቅርታ፣ስላደረክልኝ ውለታ ላመሰግንህ ነው የደወልኩት::»

«ለምን እንዳደረግሁት ግን ገብቶሀል?» እርእያ ጠየቀው::

«የአንድ ወንዝ ልጆች ስለሆንን ነዋ::»

«በዚያ ብቻ ይመስልሀል?»

«ሌላ ታዲያ ምን ምክንያት ይኖራል?»

«ላጠፋህም ላድንህም እንደምችልና ካንተ የተሻልኩ መሆኔን ላረጋግጥልህም ጭምር ነው:: ገባህ? ደግሞም በጣም የጅል ስራ ስለነበር የሰራችሁት አዝኜላችሁ ነው::»

«ገባኝ:: በርግጥም ያን ያህል የዋህ መሆን አልነበረብንም ለምን ግን ይህን ውለታ እንደዋልክልኝ በትክክል አልገለፅክልኝም::» አለ ፍስሃ እየሳቀ::

«ፍስሃ ይሄ ግጭት ያልፋል። እኛ ግን ዞረን ሀገራችን መገናኘታችን አይቀርም። ስለዚህ ጊዜያዊ እልሄን ለማብረድ ስል እንደሙአዝ አምርሬ ላስገድላችሁ አልጥርም። ቢሆንም ግን ሙአዝ እስኪበርድለት ባላንጣዎች እንደሆንን ስለምንቀጥል ደግመህ እንዳትደውል።»

«ጠይብ፣ ግን ጉዳሀህ?»

«ማለፊያ ኮማንዶ እንደነበርክ እመሰክርልሀለሁ» አለው አርአያ እየሳቀ።

«እሱን ተወው! ከመኝታ ቤቱ በስተጀርባ ያለውን በር ቁልፍ ባትሰጠኝ ኖሮ ከሦስተኛ ፎቅ ዘልዬ ማምለጤ የማይታሰብ ነበር። ለመሆኑ ከወጣሁ በኋላ በበሩ ቀዳዳ ያሾለኩትን ቁልፍ አግኝተኸዋል?»

«አግኝቼዋለሁ። እናንተ ግን ሀያትን ስለምን እስከአሁን በእጃችሁ አላስገባችኋትም? አይዳ ትላንቱኑ እንድታስረክባችሁ አስጠንቅቂያት ነበር» አለ አርአያ ፈጠን ብሎ። የበሩ ደወል ሲንቃጨል አርአያ ንግግሩን ገትቶ «ቻው!» ብሎ ስልኩን ዘጋው።

# ምዕራፍ ሀያ ሦስት

አይዳ ብዙ አውጥታ አውርዳ ሀያትን ለነክሪም ላለመስጠት ወሰነች:: እነሙአዝ እጅም ውስጥ መውደቅ ግን የለባትም:: «ትንሽ ሥጋ እንደመርፌ ትወጋ» እንዲሉ ሀያትን ማጥፋት ሳይሆን የሚበጀው በሠላም ወዳገሯ እንድትላክ ማድረግ ነው የሚሻል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሳለች::

ወደዋናው መንገድ ከሚያስወጣው የቁለይል መንደር የመጨረሻ ቅያስ የወጡት አይዳና ሀያት ከላይ እስከታች በጥቁር ልብስ ተሸፍነዋል:: የአስፋልቱን ጠርዝ ተጠግተው ከሚጓዙት ሊሞዚን ታክሲዎች አንዱ አጠገባቸው ቆመ::

«ሰፋራ ኢትዮጵያ?» አለችው አይዳ::

«አሸራ ሪያል::»

አይዳ የኋላውን በር ከፍታ ገባች:: ሀያትም ተከተለቻት:: ታክሲው የቁለይልን መንደር ግማሽ ክብ ዞሮ ወደግራ ታጠፈና በሁለተኛው ተደራቢ አስፋልት ወጥቶ ወደኢትዮጵያ ኤምባሲ ከነፈ::

የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከየመኪናውና ከየታክሲው እየወረዱ ወደውስጥ በሚዘልቁ ባለጉዳዮችና ከምላ በሚመለሱ የኤምባሲው ሰራተኞች መሙላት ጀምሯል:: ነጭ ቀለም የተቀባው ባለሶስት ፎቅ የኤምባሲው ህንፃ ከግቢው በስተግራ የሚገኘውን የግንብ አጥር ተጠግቶ የተሰራ ሲሆን፣ መጠነኛ ስፋት ያለው ግቢው ውስጥ ካፌቴሪያ ይታያል:: የካፌቴሪያውን ግድግዳ የሚጋራው የመኪና ማቆሚያ በሁለት መኪኖች ተይዟል፡፡

የህንፃው መተላለፊያዎች በባለጉዳዮች ተጨናንቀዋል። ባለጉዳዮቹ ያለማቋረጥ በአማርኛ ያወራሉ። ህያት ኢትዮጵያ የገባች መሰላት። አይዳ ወደቆንሲሉ ቢሮ እንደማምራት ብላ ወዲያውኑ ግን ሃሳቧን በመቀየር ወደህያት ዞራ «ጨርሼ እስክመጣ ካፊቴሪያ ጠብቂኝ» ብላ አንድ ሪያል እጇ ላይ አኖረችላት።

ካፊቴሪያውን አልፎ፣ አልፎ ከሚታዩ የውጭ ዜጎች በስተቀር የሞሉት ሀበሾች ናቸው። የካሣ ተሰማ 'ትዝታ' ባዳራሹ ውስጥ ይንቆረቆራል። ወንዶችና ሴቶች ጠረጴዛ ከበው ይሳሳቃሉ፣ ይጐነታተላሉ። ሴቶቹ አባያቸውን አውልቀው፣ማራኪ ቅርፃቸውን የሚያሳዩ ልብሶችን እንዳጠለቁ ለስላሳ መጠጦችንና የቆርቆሮ ጭማቂዎችን እየመጠጡ ይዝናናሉ።

ህያት እበሩ አጠገብ ወዳየችው ያልተያዘ ጠረጴዛ አምርታ የቆርቆሮ ሰቨን አፕ አዘዘች። ከዚያም የአባያዋን ዚፕ ከፈተች።

ባልና ሚስት እንኳ ፊትና ኋላ እንዲሔዱ በሚገደዱበት ሀገር ከጣራ በላይ የሚስቁና፣ አፍ፣ ለአፍ ገጥመው የሚንሾካሾኩ ሰዎች በማየቷ ተገረመች። ከሪያምን እየናፈቀች አንዱን ስትጥል ሌላውን ስታነሳ ጊዜው ነጐደ።

ህያት ካፊቴሪያው ውስጥ የቀሩት ሰዎች ጥቂት መሆናቸውን ስታስተውል ነበር የአይዳ መዘግየት የታወቃት። ሰአቷን አየችና በድንጋጤ አንዱን ሪያል ጠረጴዛ ላይ ወርውራ ወጣች።

መተላለፊያውን አጨናንቀውት የነበሩት ባለጉዳዮች የሉም። ከሥራ የመውጫ ሰአት በመድረሱ የኤምባሲው ሰራተኞች ወደየቤታቸው ለመሔድ እየተጣደፉ ህንፃውን በመልቀቅ ላይ

ናቸው። ሀያት እየሮጠች ደረጃውን ወጥታ፣ ኮሪደሩን በማቋረጥ የቆንሲሉን ቢሮ ሳታንኳኳ ዘው አለች። የኢትዮጵያን ባንዲራ ለበሰው ግድግዳ ጀርባውን ሰጥቶ ከትልቅ ባለመስተዋት ጠረጴዛ ኋላ የተቀመጠው ራሰ በራ ሰው በመገረም ቀና ብሎ ተመለከታት። ክፍሉን እንደሌ ቃኘችው። ከቆንስሉ በስተቀር አንድም ሰው ማየት አልቻለችም። የሚያደነቃቅፋትን ረጅም ቀሚስ በእጇ ሰብስባ ይዛ በሩጫ ከቢሮው ወጣች። ከዚያም ካፊቴሪያውን፣ የመኪና ማቆሚያውን ተዘዋውራ አየች። በገንዘብ መክፊያ፣ በፎቶግራፍ ማስረከቢያ መስኮቶች አጮለቀች። አዳራሹን አሰሰች። ከሥራ ለመውጣት ከሚዘጋጁ ሰራተኞች በስተቀር ማንም የለም።

ሠባራ ሣንቲም ሳትይዝ አይዳ ከማታውቀው ቦታ ጥላት በመሄዷ አዘነች። የሚተናነቃትን እንባ አምቃ ወደሰማይ አንጋጠጠች። ፀሀይ ወደማደሪያዋ እያዘገመች ነው። እሷ ግን ማደሪያ የላትም። ወደሀንዳው ተመልሳ ሮጠች። መብራቶቹ ጠፍተዋል። ደረጃዎቹን ሁለት እጥፍ እየዘለለች ወደቆንሲሉ ቢሮ አመራች። ተቆልፏል። በሩን ደበደበች። መልስ የለም። ደገመችው። ምንም። እንባዋ ተዝረበረበ።

ፊቷን በመዳፏ ሸፍና መተላለፊያው ውስጥ ካሉት ደረቅ ወንበሮች በአንዱ ላይ ተቀመጠች። አብሮ አፈር ፈጭቶ፣ ውሀ ተራጭቶ ያደገና በስጋ ዝምድና የተሳሰረ የወንዝ ልጅ በባዕድ ምድር እንደዚህ ያለውን ጭካኔ ሲፈፅም ማየት ምንኛ ልብ ያቀዘቅዛል?

ድንገት የጫማ ድምፅ የሰማች መሰላትና ቀና አለች። አንዲት ሴት በአንድ እጇ ባልዲ፣ በሌላኛው መወልወያ ይዛ ደረጃውን ስትወርድ ተመለከተች። ከተቀመጠችበት በፍጥነት ተነስታ በሚቆራረጥ ድምፅ « እ ...እባ ...ክሽ...የእኔ...እመ...ቤት .... ዘመዴ

ጥላኝ ሔደች ....የ ...የዛ..ሬ .. ን . ማደሪ ... ያ ካለሽ ...ወይም ስልክ... »

ሴትየዋ «የማውቀው ነገር የለም::» ብላት እየተቆናጠረች ህንፃውን ለቃ ሄደች::

* * *

ሻምበል ናስር ግራ ተጋብቷል::ህያትን እንዲያመጡ ወደአዚዝ ቤት የተላኩት ፖሊሶች ከሁለት ሰዓታት በኋላ የሰጣቸውን የማዘዣ ወረቀት ይዘው ተመልሰዋል:: ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ በር ላይ የገተረቻቸው ሲሆም ባሏ ከመስሪያ ቤት እስኪመጣ መጠበቅ ነበረባቸው:: ባለቤቷ እንደመጣ ፖሊሶቹ እያንዳንዱን ክፍል ቢፈትሹም ተፈላጊዋ ሰራተኛ ግን አልተገኘችም:: አዚዝ የፍርድ ቤት ማዘዣውን በጥንቃቄ መርምሮ ሲመልስላቸው ህያትን ከአንድ ቀን በፊት ቀድሞ ወዳገኛት ቤት እንደመለሳት ነገራቸው:: ሻምበል ናስር ፖሊሶቹን በቁጣ ከቢሮው አባረራቸው::

ከዚያም ሙአዝን ይዞ ወደአይዳ ቤት በረረ:: ያለማቋረጥ ይደበደብ የነበረውን በር አይዳ በድንጋጤ ስትከፍተው ሻምበል ናስር ተንደርድሮ ወደውስጥ ዘለቀ:: ህያትን ፈለጋት፤ አላገኛትም:: በጥፊ አላግቶ «ህያት የታለች?!» ሲል ጠየቃት::

«እነከሪም ወስደዋታል አይደል? ተናገሪ!» ብሎ ጮኸ ሙአዝ በበኩሉ:: ጭንቅላቷን በአሉታ ወዘወዘች::

«የት ወሰድሻት ታዲያ?!» ሻምበሉ ፀጉሯን ጨምድዶ ያዛት:::

«ኢ. .. ኢትዮጵያ ኤምባሲ.» አለች እየቃሳተች::

ሻምበሉ በቀስታ ፀጉሯን ለቀቀ፣ «ምን አልሽ?» አላት በሞቀ ድምፅ::

ሙአዝ ተንደርድሮ በጥፊ አጮላትና «ማን አባሽ አዘዘሽ?! ከሪም ነው?» ሲል ጮሆ ጠየቃት::

«አይደለም፣ ራሴ ነኝ የወሰድኳት::»

«ለቆንሲሉ ነው ያስረከብሻት?» አለ ሻምበሉ በዝቅተኛ ድምፅ::

«ለማንም አላስረከብኳትም ጥያት ነው የጠፋሁት:: ሀያት ዘመዴ ስለሆነች እንድትጐዳ አልፈልግም:: በነከሪም የተነሳ ከምትጐዳብኝ ፖሊሶች እጅ ወድቃ ብትባረር ደስ ይለኛል ...»

አይዳ የጀመረችውን ሳትጨርስ ሻምበል ናስር ሙአዝን «ተከተለኝ» ብሎት ተነሳ:: የነሙአዝ መኪና መንደሪቱን መሀል ለመሀል ሰንጥቃ ወደዋናው መንገድ ስታቀና የመጅድ መኪና ወደነሱ እየተቃረበች ነበረች:: ሙስተሽፋል ማዕሩፍ ጉራ ብሎ ሀያትንና አይዳን ሳያገኝ የቀረው መጅድ ወደአይዳ ቤት እየከነፈ ነበር:: የነሙአዝን መኪና በሩቁ ሲመለከት ፍጥነቱን ቀንሶ እስኪያልፉለት ጠበቀና ወደአይዳ ቤት ገሰገሰ:: አይዳን ያገኛት በጥፊ የተቃጠለ ፊቷን እያሻሸች በሯን ገርበብ አድርጋ ቆማ ስትተክዝ ነበር:: ልክ እንዳየችው «ጫፌን እንዳትነካኝ:: ሁሉንም ነገር እነግርሀለሁ» አለችው:: በርግጥም የሆነውን ሁሉ ነገረችው:: እነሙአዝን ተከትሎ በረረ::

*   *   *

ህያት በሃዘን ተውጣ ሳለች ሌላ የዕዳት ሰራተኛ ደረጃውን ስትወርድ አየች፡፡ «እ .. አባክሽ .. የ..ኔ እመቤት ... ዘ .. ዘመ ዘመዶቼ ... » እያለች ስትነፋረቅ፣

«ምን ሆነሽ ነው የኔ ልጅ?» በማለት አቋርጣ ጠየቀቻት፡፡

«እንዲት ዘመዴ ... እዚህ ጥላኝ ሔደች፡፡»

«ለምን?»

«ምን አውቄ? ቪዛ አስመትቼ እመጣለሁና ካፊቴርያ ጠብቂኝ ብላ በዚያው ጠፋች፡፡»

«ቤቷን አታውቂውም?»

«አውቀዋለሁ፡፡ ዳግመኛ ግን ወደሷ ቤት መሔድ አልፈልግም፡፡ ሌሎቹ የሀገሮቼ ልጆች ዘንድ ነው መሄድ የምፈልገው?»

«የነሱንስ ስልክ ይዘሻል?»

«አዎን ፤ይዣለሁ፡፡»

«እንግዲያው ዛሬ ከኔ ጋር ታድሪያለሽ፡፡ ማታ እንደውልላቸውና ነገ እንዲወስዱሽ አደርጋለሁ፡፡» ሴትየዋ ህያትን እያፅናናች ሳለች ሽማግሌው ዘበኛ ከማደሪያቸው ብቅ ብለው፣

«ምን ሆናችሁ ሽዋዬ?» ሲሉ ጠየቋት፡፡ ወዲያውኑ ከወደበሩ የመኪና ጥሩምባ ስለተሰማ ሴትየዋ፣ «ይቅርታ ነገ አጫውቶታለሁ፡፡ አሁን ባለቤቴ መጥቷል» ብላ የህያትን እጅ እየጐተተች ውጪ ቆሞ ወደሚጠብቃት ቮልስዋገን አመራች፡፡

* * *

ጭር ካለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ደጅ ቆማ የነበረችው ቮልስ ስትንቀሳቀስ አንድ መኪና ከኤምባሲው የመጨረሻ አጥር በስተቀኝ

ታጥፎ ወደበሩ ተጠጋ:: የኤምባሲው ዘበኛ ሼህ ኬሬ የግቢውን በር በመዝጋት ላይ ነበሩ::

ሻምበል ናስር ከመኪናው ዘሎ ወርዶ፣ «አሰላሙ አለይኩም?» በማለት ሠላምታ አቀረበላቸው::

ሽማግሌው ትኩር ብለው እያዩት «ወአለይኩም አሰላም» አሉት::

«እባክዎትን እንዲት ዘመዳችንን ፈልገን ነበር» አለ ሻምበሉ::

«አሁንማ ማንን ታገኛለህ ልጄ? ሰራተኞች በሙሉ ወጥተ ዋል'ኮ:: ለመሆኑ የየትሀገር ሰው ነች?» አሉ ሽማግሌው እንደዋዛ::

«ሀበሻ ናት» አለ ሙአዝ ጣልቃ ገብቶ::

«ታዲያ እናንተ እንዴት ልትዛመዷት ትችላላችሁ?» አሉ ሽማግሌው በምፀት ፈገግ ብለው::

«እንዴት መሰለዎት .... »ብሎ ሙአዝ ለማስረዳት ሲሞክር አቋርጠውት፣

«አንተኛው የሳኡዲ አረቢያ ሰው አይደለህም?» አሉት ሻምበሉን:: በአዎንታ ሲመልስላቸው፣ ወደሙአዝ ዞር ብለው፣ « አንተኛው ደግሞ ከአነጋገርህ ሱዳናዊ ትመስለኛለህ» አሉት:: ሙአዝ ጥርሱን ነክሶ «ነኝ!» አላቸው::

ሻምበሉ መታወቂያውን አሳይቷቸው፣ «ልጅቷን የማያቀርቡልኝ ከሆነ ገብቼ እፈትሻለሁ!» አላቸው በቁጣ::

«ያን እንኳን ማድረግ አትችልም:: የተከበረ ኤምባሲ ቅዕር ግቢ መሆኑን ረሳው እንዴ ይሄ!? ይልቅዬ ድንፋታህን ተወውና የምትላት ልጅ ከግማሽ ደቂቃ በፊት እዚህ ከምትሰራ ሴት ጋር መሄዷን እወቅ!» ብለው በሩን በሀይል ዘጉት::

*   *   *

መኝታ ክፍሉን ዘግቶ እየሰገደ ጌታውን የሚማፀነው ከሪም በገዛ ለቅሶው ደከመ:: ፈጣሪው የለመነውን የሰማ አልመሰለውም:: መጅድ ከሔደበት ሳይመለስ ፀሀይ ጠለቀች:: ከሳሎን የተቀመጡት ፍሰሃና ሀፊዝ እንባዋን በዝምታ እያፈሰሰች፣ የማይሰማ ነገር የምታነበንበውን ሰሚራን ለማረጋጋት አልቻሉም::

በፀጥታው መሀል የበሩ ደወል እሪ ብሎ ጮኸ:: ለመክፈት የደፈረ ግን አልነበረም:: ከሪም ከመኝታ ክፍሉ እንዴት እንደወጣ ሳያውቀው፣ በሩን ከፍቶ የመጅድን ፊት እንዳየ፣

«ያዟት?!»ብሎ ጮኸ::

መጅድ በርጋታ ወደውስጥ ዘልቆ ከሶፋው ላይ ተቀመጠ::

«የሆነውን ንገረን?» አለ ፍሰሃ በደከመ ድምፅ ::

«አይዳ ለነሙአዝ እሳልፋ ሰጥታታለች» አለ መጅድ በሻከረ ድምፅ:: «ኢትዮጵያ ኤምባሲ ወስዳ ተሰወረችባት::»

ከሪም ወደመኝታ ክፍሉ ሲንደረደር ፍሰሃ ተከተለው::

«ምን ልትሆን ነው? አይዳ ቤት ደውለህ እንዳትም ቃል እንዳትተነፍስ:: አሁኑኑ የጂን እሰጣታለሁ:: ይልቅ ስልኩን አቀብለኝ» አለ ፍሰሃ ቁና ቁና እየተነፈሰ::

«የምደውለው እሷጋ ሳይሆን ሻምበል ናስር ዘንድ ነው» አለ ከሪም ቅዝቅዝ እንዳለ::

«ለምን?»

«ሀፊዝን አስረክበዋለሁ:: ከፈለገ ራሴንም ጭምር:: ሀያትን ግን ይልቀቃት::»

«ከሪም? !» ፍሰሃ በድንጋጤ ጮሆ የመኝታ ክፍሉን ዘጋው::

«አይሆንም! ሀፊዝን አሳልፊህ አትሰጥም!» ብሎም የስልኩን እጀታ ነጠቀው።

«እና ምን ይሁንልህ?» አለው ከሪም በእንባ በተሸፈኑ አይኖቹ አፍጥጦበት።

«በቃ፣ እኔና አንተ እጃችንን እንሰጣለን።»

«ሻምበሉኮ ከኛ ይልቅ የሚፈልገው ሀፊዝን ነው። ስለዚህ...»

ስልኩ ጮኸ።

«ሀሎ?» አለ ከሪም ባልተረጋጋ ድምፅ።

«ከሪም ይኖራል እባክዎ?» የሴት ድምፅ ነበር።

«ነኝ፤ ማን ልበል?»

«ሀያት የምትባል ልጅ ያውቃሉ?»

«ሀ .. ሀ .. ሀያት ... አዎን ... እመቤቴ ... አውቃታለሁ»

አለ እየተርበተበተ።

«በአሁኑ ሰዓት እኔ ዘንድ ትገኛለች።»

«ምን .. ም ...? » ከሪም ተደነጋገረ።

«አይዞት አይደንግጡ ደህና ነች። እንዲያውም ላገናኝዎት።»

«ከሪም?» የሀያት ድምፅ እየተቆራረጠ ጆሮው ደረሰ።

«ሀያት?! ደህና ነሽ? የት ነው ያለሽው? አሁኑኑ እመጣለሁ»

አለ ከሪም በሲቃ።

«ቆይ እንጂ?» ብላው ጥቂት ከቆየች በኋላ፣ «ከሪም፣ ሽዋዬ እንደምትለኝ ከሆነ ቤቷ የሚገኘው ሻሪዕ ፍልስጤም ጉዳና ነው። እዚያ ደግሞ ድልድዩ ላይ ቋሚ ፍተሻ አለ። ስለዚህ በዚህ ሰዓት ሴት ጭንህ ልታልፍ አትችልም እና ... » ሀያት ዝም አለች።

«እና ምን?» አለ ከሪም በችኮላ።

«ነገ ኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ላይ ቢሮ ቁጥር ስድስት ከሽዋዬ ጋር ሆነን እንጠብቅሀለን።» ከሪም ቅር

እንደተሰኘ ስልኩን ዘግቶ «ይቺ አረመኔ!» በማለት ተራግሞ ወደሳሎኑ አቀና፡፡

የከረም ብስጭት የተጋባበት ፍሰሃ ሲያቅማማበት የነበረውን ሀሳብ ለመተግበር ወደስልኩ አመራ፡፡

«ሀሎ?» የሚል የሴት ድምፅ እንደሰማ፣ «አሰላሙ አለይኩም ያ አመቲ ... መዳም አይሻ?» አለ፡፡

«ወአለይኩም አሰላም፡፡ አይሻ ነኝ፡፡»

«መዳም ስለደፈርኩሽ ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡ ግን የጋራ ጉዳያችን በመሆኑ ነው የደወልኩልሽ፡፡ ባልሽ የሚስቴን ልብ አሸፍቶብኝ፣ሚስቴ ደግሞ ያንቺን ባል ልብ አሸፍታዋለች፡፡ እና ...»

«ምን እያወራህ ነው ሰውዬ?»

«የኡመርን ልብ ያሸፈተችው ሀበሻ ሚስቴ ነች ነው ያልኩሽ»

ፍሰሃ፣አይሻ በጥሞና እንደምትሰማው እንዳረጋገጠ የአይዳን አድራሻ ሳይቀር ነገራት፡፡

# ምዕራፍ ሀያ አራት

የሥራ መግቢያ ሰዓት ባለመድረሱ የተዘጋጉት ቢሮዎች ህንፃውን ሰው አልባ አስመስለውታል፡፡ እየተንጠባጠቡ የሚመጡት ባለጉዳዮች የሚያመሩት ቀደም ብሎ ወደሚከፈተው ካፊቴሪያ ነበር፡፡ መጅድ መኪናውን ከኤምባሲው በር ትይዩ አቁሞ እየተቻኮለ ወደዘበኛው ቤት አመራ፡፡ እነሙአዝ ከሄዱ በኋላ ከሼህ ኬር ጋር የተገናኘው መጅድ ሽማግሌውን በትህትና ስለቀረባቸው ተጠቃሿ ሽዋዬ ከምትባለው የኤምባሲ ሠራተኛ ጋራ ማደሯን ገልፀውለት ከሱ በፊትም ፖሊሶች እያደኗት እንደነበር አስረድተውታል፡፡ «አንተም ሰላይ ከሆንክ ይህንኑ ነው የነገርኳቸው» ነበር ያሉት፡፡ እናም ጠዋት ሲያዩት «መጣህ?» ሲሉ ጠየቁት፡፡

«አዎን፣ ዘገየሁ እንዴ?» አለ መጅድ ቁና፣ ቁና እየተነፈሰ፡፡

«ሰዎቹ እዚሁ አካባቢ ነው ያሉት፡፡ ከግማሽ ሰዓት በፊት ካፊቴሪያውን ቃኝተው ሲወጡ አይቻቸዋለሁ አሉት፡፡»

መጅድ ክፉኛ ደነገጠ፡፡ ይኼኔ ሽማግሌው ኮምጨጭ ብለው፣ «ከኤምባሲያችን ቅጥር ግቢ ማ የሚወስዳት ወንድ አይኖርም፡፡ ሆኖም ምናልባት ስትወጣ አድፍጠው፣ አሊያም ከፍርድ ቤት ትዕዛዝ አጽፈው ይሞክሩ ይሆናል፡፡»

«የሽዋዬን የቤት ስልክ ሊሰጡኝ ይችላሉ?»

«አዬ ... በዚህስ የምረዳህ አይመስለኝም፡፡ ምናልባት አስናቁን ብታናግራት» አሉት፡፡

«አስናቁ ማናት?»

«የፅዳት ሰራተኛ ናት፡፡ ቢሮዋ ሶስተኛው ፎቅ ላይ ካሉት ክፍሎች እጥጉ ላይ ነው፡፡»

መጅድ ደረጃዎቹን እንዴት እንደወጣ አያውቀም:: በሩን ሲያንኳኳ እጁን ሲሰነዝር አንዲት ሴት አፈጠጠችበት::

«ምን ፈለግህ?!»

«ይቅርታ የኔ እህት፣ አስናቀችን ማግኘት ብችል?»

«ለምን ፈለግሀት? መጅድ መልስ ሳይሰጣት በሩን ማንኳኳቱን ቀጠለ::

«ስማኝ ሰውዬ! አስናቀች የለችም:: ለምን እንደፈለግሀት ብትነግረኝ ግን ... »

«ቢሮ ቁጥር ስድስት የምትሰራዋን ሽዋዬን እንድታገናኘኝ ነው የፈለግኋት» ብሎ ሴትየዋን ሊገላምጣት ሲዞር በእጆቿ ያንጠለጠለቻቸውን ባልዲና መወልወያ ተመለከተ::

«አንቺ ነሽ እንዴ አስናቀች?» ሲል በመገረም ጠየቃት::

በጭንቅላቷ አዎንታዊ ምላሽ ሰጠችው:: መጅድ ይቅርታ ጠይቆ ጉዳዩን በዝርዝር ነገራት:: አስናቀች ከሱ ይበልጥ ተቻኩላ ወደሁለተኛው ፎቅ ስትሮጥ መጅድ ተከተላት:: ቢሮ ቁጥር ስድስት ሲደርሱ አስናቀች ስልኩን ወደመጅድ ገፋችና ቁጥሮቹን ነገረችው::

«ሽዋዬ?» ሲል መጅድ ጠየቀ ስልኩ እንደተነሳ::

«ነኝ::»

«አስፈሪ አደጋ እያንዣበበብን ነው:: ለሁሉም ከሪም ደውሎ እንዲያናግራችሁ አደርጋለሁ:: በቀጠሮው ሰዓት ግን ሀያትን ወደኤምባሲው ይዘሻት እንዳትመጪ:: ባለችበት ትቆይ» ብሎ ስልኩን ዘጋና ወደከሪም ደወለ:: የመለሰለት ግን ሀፊዝ ነበር::

«በትክክል ስንት ሰዓት ላይ እንደወጣ አላየሁም:: ከመኝታዬ ስነሳ፣ አልነበረም» አለ ሀፊዝ::

መጅድ ክው ብሎ ቀረ:: ከሪም ወደኤምባሲው እየመጣ ነው ማለት ነው:: አስናቀችን አመስግኖ እግሮቹን እየጐተተ ከግቢው ወጣ:: እመኪናው ለመግባት በሩን ሲከፍት የተጠቀለለች ቁራጭ ወረቀት ወንበሩ ላይ አየ:: «ከንዲህ ዓይነቱ ጨዋታ እጅህን ብታወጣ ይመረጣል:: አለያ ለሚደርስብህ ችግር የሚደርስልህ ወዳጅ አታገኝም:: ሻምበል ናስር» ይላል::

መጅድ የነሙአዝዝን መኪና ባይኖቹ ፈለጋት:: አላገኛትም:: መኪናውን አስነስቶ ወደ ሀየ ረውዳ አቀና:: ከሪም ወደቤቱ ተመልሶ እንደሆነ ለማወቅ ስልክ እየፈለገ ነበር:: ዱዌሪ ጠያራ አደባባይን እንዳለፈ ከአውቶቡሱ ፌርማታ ጐን በርቀት የመስተዋት ቤት አየ:: ስልኩን አንድ ሰው እየተጠቀመበት ነበር:: መጅድ ሊታገስ ስላልቻለ ሌላ ስልክ ፍለጋ ሲያማትር ለአመታት የሚያውቃት ነጭ ቶዮታ እየተከተለችው መሆኗን ተመለከተ:: ለመረጋጋት እየሞከረ የኋላ መመልከቻ መስተዋቱ ላይ አተኮረ:: መኪናዋን የሚነዳት ሙአዝ መሆኑን እንደለየ የመደወሉንም ሃሳብ ሰረዘና ወደሳባ ሬስቶራንት አመራ::

* * *

ሳባ ሬስቶራንት በተመጋቢዎች ተሞልቷል::ፍስሃ ሬስቶራንቱ እንደገባ ጭብጨባ ሰማ:: የቀጠሩት ሁለት ፓኪስታናውያን በእጅ ምልክት ጠሩት:: ተቀላቀላቸው:: ከዚያም ቁርስ አዝዞ ተመቻችቶ ተቀመጠ:: ኪሎ ሰብአ ሰፈር ያገኙትን የሚከራይ አፓርትማ ሊያሳዩት እንደሚችሉም ደግመው አረጋገጡለት:: ቁርሳቸውን በልተው ሲያበቁ አንደኛው ፓኪስታናዊ ታክሲ ሊኮናተር ወጣ::

ፍሰሃ ቤቱን ዛሬውኑ አግኝቶ ሀፊዝና ስሚራን ወደዚያ ለመውሰድ ተጣድፏል:: በዚያች ቅፅበት መጅድን ወደሬስቶራንቱ ሲገባ አየው:: የነሙአዝ መኪና ሬስቶራንቱ መግቢያ ወደሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ስፍራ እየተጠጋች ነው:: ሙአዝ እየተንጠራራ ክፍት የመኪና ማቆሚያ ቦታ ይፈልጋል:: መጅድ ፈጥኖ ባንኮኒው ላይ ወደተቀመጠው ስልክ በመሄድ ወረቀት ላይ እየሞነጫጨረ ሒሳብ የሚያሰላውን ሰው ፈቃድ እንኳን ሳይጠይቅ መነጋገሪያውን አንስቶ ቁጥሮች ነካካ::

«ሀሎ? ሙአዝ መኪናውን ውጭ ስላቆማት አሁኑኑ መውጣት ይኖርብሃል! እንዳይጠብቅህ፤ ገባህ?!» አለ::

ሻምበል ናስርና ሙአዝ በርጋታ ወደበሩ እያመሩ ናቸው:: አይኖቹን ፍሰሃ ወደነበረበት ጠረጴዛ መለሰ:: ፍሰሃ የለም:: በእፎይታ ስልኩን ቦታው መልሶ ሮጦ አንድ ወንበር ብቻ ካለበት ጠረጴዛ ተቀመጠ:: ሙአዝና ሻምበሉ ሲገቡ አጠገቡ ከቆመው አስተናጋጅ የተቀበለውን የምግብ ዝርዝር ማገላበጥ ጀመረ:: የሙሉህያ ወጥ አዝዞ ቀና ሲል ከሻምበሉ ጋር አይን ለአይን ገጠሙ:: ሻምበሉም ትኩር ብሎ ተመልክቶት ጭንቅላቱን በዛቻ ነቀነቀና ከሙአዝ ጋራ ተያይዘው ወጡ::

እንደሄዱለት መጅድ ወደሬስቶራንቱ የጓሮ በር ሄደ::

«ችግር ተፈጥሯል ወዳጄ:: ለመሆኑ ከሪም ወደየት ነው የሔደው?» አለ መጅድ ተቻኩሎ::

«ኢትዮጵያ ኤምባሲ::»

«እንዳትሔድ ብዬው?» አለ መጅድ ደንግጦ::

«አሻፈረኝ አለ እባክህ::»

«ጥሩ፤ ፈጥነህ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውልና ሀያትን አግኛት::» መጅድ ቁራጭ ወረቀት አውጥቶ ለፍሰሃ ሰጠው::

«ክሪምን የገባህበት ገብተህ አግኘው:: እኔ እነሙአዝዝን ይዤ ከተማዋን እዞራለሁ» አለ::

«ምን?» አለ ፍስሃ ግራ ተጋብቶ::

«እየተከተሉኝ ነው:: የጅዳን ከተማ እስካስጐበኛቸው ክሪምን ፈልገህ ሁሉንም ነገር አስረዳው» አለና ወደፊት ራመድ ብሎ እንደገና ቆመ፤ «በፊት ለፊቱ በር ለመውጣት ደግሞ እንዳትሞክር:: በሩን እንቀው ይዘውታል:: የአምስት ደቂቃ ጊዜ ስጠንና በጓሮው በር ውጣ» ብሎት ሔደ::

መጅድ መኪናውን አስነስቶ ወደበሪማ እስር ቤት አመራ:: የነሙአዝዝም መኪና ተከተለው:: ከሳባ ሬስቶራንት የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ተከታትለው የተነሱት ሁለት መኪኖች የከተማዋን እንብርት ሰንጥቀው አለፉና ወደሸረፊያ ሰፈር ከነፉ:: የመጅድ መኪና የበሪማን እስር ቤት አጥር ተጠግታ መዞር ስትጀምር ሻምበሉ መሞኘቱን ተረዳ::

«ይሔ ጉማሬ እስከአሁን የተጫወተብን ይበቃል:: ወደ ኢትዮጵያ ኤምባሲ እንመለስ» አለ::

መጅድ ብዙ ከተጓዘ በኋላ ፍጥነቱን ቀንሶ በኋላ መመልከቻው መስተዋት የነሙአዝዝን መኪና ፈለጋት:: የለችም:: እንደነቁበት ገባው:: ወደኤምባሲው በረረ:: በርግጥም መኪናቸው ከመግቢያው ፊንጠር ብላ ቆማለች:: ውስጧ ሰው የለም::

ግቢውን ሲያቋርጥ ሸማግሌው ዘበኛ፤ «ሰዎችህ ሸዋዬ ዘንድ ናቸው» አሉት በቀስታ::

መጅድ አስናቀችን ለማግኘት እየተጣደፈ ሔደ:: ሁኔታውን ሲገልፅላት ባለበት እንዲጠብቃት ነግራው ወደቁጥር ስድስት ቢሮ ወረደች:: መጅድ ተከትሏት ስለነበር አስናቀች በሩን ከፍታ ስትገባ፣

«ነገርኩህኮ ሻምበል፤ የማውቀው ነገር የለም!» የሚል የሴት ድምፅ ሰማ:: ፊጥኖ በሩ ላይ ተለጠፈ::

«ልጅቷን ይዘሽ ወደቤትሽ አልሔድሽም?»

«ገንዘብ ስላልነበራት በታክሲ አሳፍሬያታለሁ» አለች ሽዋዬ ጫን ብላ::

«ልጅቷ አንቺ ዘንድ ስላለመኖሯ እርግጠኛ መሆን እንድንችል ቤትሽን ታሳይናለሽ?» አለ ሙአዝ ለስለስ ብሎ::

«ቤቴንማ አላሳያችሁም!»

«የፍርድ ቤት ማዘዣ አመጣለሁ»አለ ሻምበሉ በማስፈራራት::

«አንድ አይደለም አስር አምጣ ህጋዊ ሰው ነኝኮ:: እንዲያውም አሁኑኑ ከዚህ ግቢ ካልወጣህ ለሃላፊዬ አሳውቃለሁ!» አለችው::

«ቆይማ አንዴ» አለች አስናቀች ጣልቃ ገብታ:: «ቤቷን ታሳያችኋለች!»ብላ ጠቀሰቻት::

«ስራዬን ስጨርስ አሳያችኋለሁ» አለች ሽዋዬም ተከትላ::

«መልካም፤ ሥራሽን እስክትጨርሺ ከግቢው ውጭ መኪናችን ውስጥ እንጠብቅሻለን» የሚለውን የሻምበሉን ድምፅ መጅድ እንደሰማም ቀልጠፍ ብሎ ፊት ለፊቱ ወዳለው ቢሮ ዘሎ ገባ::

«ምን ልርዳህ?» አለው ወጣቱ ሠራተኛ በመገረም::

መጅድ የአረብኛ ቋንቋ ችግር ያለበት ይመስል እየተንተባተበ « እ .. እ ... ብዙም አረብኛ አላውቅም:: እንግሊዝኛ ትሞክራለህ?» አለው ሰውየውን::

«አዎን፣ ምን ልርዳህ?»

«የአስናቀችን ቢሮ ሳገኘው አልቻልኩም:: ልታገናኘ ትችላለህ?» አለ መጅድ በትህትና:: ሰውየው አሰብ አድርጎ ይዞ

ወጣ:: መጅድ በዝግታ ከቢሮው ሲወጣ የሙአዝን ትከሻ በደረጃው ቋሚ ብረቶች አጠገብ ውልብ ሲል አየው:: በተዝናና መንፈስ የሚመራውን ሰው ተከትሎም ጥቂት ተራመደና ሰውየው ቢሮዋን አመላክቶት ሲመለስ እሱ ቁጥር ስድስት ጥልቅ አለ::

ሁለቱ ሴቶች ሲጨቃጨቁ ነበር የደረሰው::

«ይኸው መጣ» አለች አስናቀች መጅድን እንዳየች:: «ልጅቷን ከምሳ በፊት ከሸዋዬ ቤት እንድትወስዳት» አለችው::

መጅድም ስልክ ደውሎ ፍሰሃን ከሸዋዬ ጋር አገናኘው::

* * *

ከሪምና ፍሰሃ የሻሪፅ ፍልስጤም ጉዳናን ሽቅብ ወጥተው ከዋናው መንገድ ገባ እንዳሉ በርካታ ሰዎች ምሽቱን የሚያሳልፉበት የሺሻ ማጨሻ ቤት ደረሱ:: መኪናቸውን በዚያ አቁመውም ሶስት ህንፃዎችን አልፎ ከተንጣለለው ሜዳ ፊት ለፊት ወደሚገኘው ትንሿ መስጊድ ጉን ወዳለው ያረጀ ህንፃ አመሩ:: የህንፃው ሽክላዎች ተሰነጣጥቀዋል፣ አልፎ አልፎም ተፈርፍረው ወጣ ገባ ሆነዋል:: እነከሪም ፈጥነው ወደቁጥር አንድ መኖሪያ ቤት ገሰገሱ:: ትጠብቃቸው የነበረችውን ሀያት ይዘው ሲወጡ ሲጋራ ሊገዛ ቀድሞ የወጣው ፍሰሃ ትራፊክ ፖሊስ መኪናቸውን እየተዟዟረ ሲመለከታት አየ:: ፖሊሱ ወረቀት ከኪሱ አውጥቶ ከታርጋው ጋር ካገናዘበ በኋላ የመገናኛ ሬዲዮኑን አውጥቶ መነጋገር ጀመረ::

ፍሰሃ ሮጦ ወደመኪናዋ የሚያዘግሙትን ሀያትና ከሪምን አስቆማቸው:: «እናምልጥ!» እያለ ፍሰሃ በሶስተኛው ቅያስ ሽቅብ ሮጠ:: ከሪምና ሀያት ግራ እንደተጋቡ ተከተሉት:: የሻሪፅ ፍልስጤም ጉዳና ተዳፋት እንደደረሱ ግን ፍሰሃን አጡት::

«ፍስሃስ?» አለች ሀያት እያለከለከች፡፡

«የገባበትን አሳህ ነው የሚያውቀው» አለ ከሪም ዙሪያውን እየቃኘ፡፡

ወዲያውኑ አንድ ታክሲ አጠገባቸው ቆመ፡፡ ፍስሀ «ግቡ እንጂ!» ብሎ ጮኸ፡፡ ታክሲዋም የሻሪዕ ፍልስጤምን ጉዳና ለቃ በመንደር ውስጥ መንገዶች እየተሽሎከለከች በረረች፡፡

# ምዕራፍ ሀያ አምስት

ሻምበል ናስር የሸዋዬን ቤት ፈትሾ ሀያትን ካጣት ስአት ጀምሮ መጅድ ምን ያህል እንደተጫወተበት ተረድቷል:: መጅድን በምን መልኩ ሊበቀለው እንደሚችልም ማሰላሰል ጀምሯል:: በቀጥታ ቢያስይዘው የሱም ሚስጥር ይወጣል:: ይህ ደግሞ መዘዙ ብዙ ነው:: በሱ ብቻ የሚወሰን አይሆንም:: ዳፋው ለብዙ ወዳጆቹ ይተርፋል:: በስልጣናቸው ተጠቅመው መጠጥ ወደሀገሪቱ በድብቅ የሚያስገቡ ወዳጆቹ ሳይቀሩ አብረውት መቀመቅ ይወርዳሉ:: ስለዚህ የሚሻለው መጅድን እጅ ከፍንጅ ማስያዝ ነው:: ከአንድ ደንበኛው መጠጥ ሲቀበል፣ አለያም ከጓደኛው ከአስር አለቃ ጀሚል አፓርታማ ተቀምጦ ውስኪውን ሲጋት መያዝ ይቻላል:: ይህን ለማሳካት ደግሞ አስር አለቃው መሞት አለበት:: ሻምበል ናስር ለአስር አለቃው ህይወት ደንታ አልነበረውም:: የሱና የበርካታ ወዳጆቹ ኑሮ ከሚናጋ አስር አለቃው ቢሞት ይቀላል::

«አስር አለቃ ጀሚል፣ ቢሮዬ እፈልግሀለሁ» አለው ስልክ ደውሎ::

«ሻምበል፣ አለቃዬ አጣዳፊ ስራ ሰጥቶኛል:: በሻሪዕ ቁረይሽ ጉዳና ዕፅ የሚያዘዋውሩ የሱማሌ ዜጎችን በቁጥጥር ስር እንዳውል ታዝዣለሁ::»

«ጥሩ የፈለግሁህ ለግል ጉዳይ ነው:: መጅድን ፈልጌው ነበር:: ላገኘው ግን አልቻልኩም:: ለዚያ ለምናውቀው ጉዳይ ... »

«እም» አለና እስር አለቃው ሳቅ ብሎ «እኔ አገኘዋለሁ፤ መልዕክት ልንገርልህ» አለ።

«ላ! ላ! እንደዛ አይደለም። ባለፈው ዋጋ አሳንሺ አስከፍቼዋለሁ። ስለዚህ አስታራቂም መፈለጋችን አይቀርም» አለ ሻምበሉ እየሳቀ።

«እንግዲያው ነገ ማታ ከኢሻዕ በኋላ እኔ ቤት እንጠብቅሀለን።»

ሻምበሉ «መልካም። እኔም በኩዌት በኩል የሚመጡትን ካርቶኖች ለመጅድ እንዲሆኑ አደርጋለሁ» አለና ስልኩን ቀፎው ሲመልስ ፖስታ አየ። ጐትቶ አወጣው። ለወትሮው ተላላኪው ፖስታዎቹን ፊት ለፊት ነበር የሚያስቀምጥለት።

ሻምበሉ ተላላኪውን ጠርቶ ከገሠፀው በኋላ ፖስታውን ከፈተ። ከአመታት በፊት በቁማር የተበላች ታክሲውን ከሀፊዝ ጋር የተረካከበባቸው ሰነዶች፣ ሀፊዝ የበላውን ታክሲ እንዲመልስለትና ከእናቱ እርቅ እንዲፈጥር የሀፊዝን እርዳታ የተማፀነበት ደብዳቤ፣ እንዲሁም ታክሲዋ ወደሀፊዝ ንብረትነት ስትዛወር ታክሲዎችን የሚቆጣጠረው ኩባንያ የሚጠይቀውን የአመት ክፍያ የፈፀመበት ደረሰኝ ... ሁሉም ፎቶ ኮፒ ተደርገው ተልከውለታል። ሻምበል ናስር በመጨረሻ በአንድ ወረቀት ላይ የሰፈረውን መልዕክት ማንበብ ጀመረ።

«ወዳጄ ናስር፣ የደረሱህን ሰነዶች ፎቶ ኮፒዎች በጥልቀት መርምራቸው። መቀመቅ የሚከቱህ ናቸው። ይህ ፖስታ ከደረሰህ ሰአት ጀምሮ ክትትልህን ባታቆም ማስረጃዎቹን ይዤ እጄን እሰጣለሁ። ከዚያም እኔና አንተ በሪማ እስር ቤት እንገናኛለን።

በመጨረሻም በለድ መስጊድ ፊት ለፊት በምዕመናን ተከበን በጠራራ ፀሀይ እንቀላለን:: ገባህ? ይህ እንዳይሆን ከፈለግክ እኛን ለቀት አድርገን:: ሀፊዝ» ይላል::

ሻምበል ናስር ወረቀቶቹን እኪሱ ከቶ እየተንጉራደደ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ያሰላስል ጀመር:: ብዙም ሳይቆይ ግን የመካ ፖሊስ አዛዥ ባስቸኳይ እንዲመደብላቸው ማስጠሰናቸውን አለቃው በስልክ ገለፁለት::

«በርካታ ማስረጃዎችን በጁ ስላስገባሁ የሁለት ሣምንት ዕድሜ ቢሰጠኝ የዕፅ አዘዋዋሪዎቹን መረብ በጣጥሼ በሄድኩ ነበር» አለ ሻምበሉ በቅሬታ::

«ላ! ላ! እዚያ ያለው ሁኔታ ይበልጥ አሳሳቢ ስለሆነ የያዝከውን ጉዳይ ለመቶ አለቃ ዑስማን አስረክበህ ዛሬውኑ ወደመካ ሂድ!»

«ግልግል!» አለ በልቡ::

*                *                *

ባዲስ መንፈስ ክትትሉን የጀመረው መቶ አለቃ ዑስማን መኪናውን ከቀድሞ የሀፊዝ ቤት መግቢያ አስጠግቶ አቆመ:: የለበሰው የሲቪል ልብስ ነው:: መጥሪያውን እንደተጫነው የበሩ የማጮለቂያ መስኮት ተከፈተች::

«ምን ፈለጉ?» ሲል ዘበኛው ጠየቀው::

«ሀፊዝን ፈልጌ ነበር:: ቅድም ካርጉ (የዕቃ ማስጫኛ) ቢሮው ሔጀ ላገኘው አልቻልኩም:: ተኝቷል እንዴ?»

ዘበኛው ዝም አለው::

«ምነው ደህና አይደለም እንዴ? ስልክ ብተጠቀጥ፣ ብቀጠቅጥ የሚመልስልኝ በማጣቴ ነው የመጣሁት::»

«አይ እሳቸውማ ከቤት ከወጡ'ኮ ሰነበቱ» ብሎ ዘበኛው አቀርቅሮ በጫማው ጫፍ የአስፋልት ንጣፉን ይቆረቁር ጀመር::

«ወይኔ ወንድሜን! ስንት ጊዜ ሆነው? ለመሆኑ አሁን የት ይሆን የማገኘው?»

«እሱንማ ለኔ እንዴት ይነግሩኛል:: ዘበኝነት እንጂ ወዳጅነት ወዲህ አላመጣኝ?!»

«ትላንት'ኮ ካርጐ (የዕቃ ማስጫኛ) ቢሮው ሔጀ አግኝቸዋለሁ:: እንዴት ቤቱን ጥሎ መውጣቱን አልነገረኝም?»

«ትላንት ሌሊትማ ብቅ ብለው ነበር» አለ ዘበኛው ፈገግ እያለ::

«በጄ?» አለው መቶ አለቃውም ፈገግ ብሎ እንዲናገር እያበረታታው:: «ስራህን ትለቃለህ ብለውኛል:: ቤታቸውን ሊሸጡት አስበዋል::»

«ለነገሩ የቤት መሸጡን ጉዳይ ለኔም ነካክቶልኝ ነበር:: ግን ከወር በፊት ስለነበር ጉዳዩን ያጫወተኝ ይህን ያህል ጊዜ ሳይሸጠው በመቆየቱ ሀሳቡን የቀየረ መስሎኝ ነበር:: የቤት ዕቃውንስ አስጭኗል?»

«በዚህ ሳምንት እንደሚያስጭኑ አብሯቸው ከመጣ ሰው ጋር ሲያወሩ ሰምቻለሁ:: እንደኛውን ታክሲ የሚገዛቸው ሰውም አግኝተዋል:: ነገ ለገዢው አስረክባለሁ ሲሉ ነበር::»

« ታክሲውንም ሸጠ? ምን ነካው እባክህ?»

«በትክክል አላወቅሁም:: ግን ፖሊሶች እየፈለጉዋቸው መሰለኝ::»

«ፖሊስ ... ለምን?»

«ምናባቴን አውቄ ብቻ ትላንት ማታ ሲመጡ እሳቸውም ሆነ ጓደኞቻቸው የሴት አባያ ለብሰው ነበር፡፡ ተሸፋፍነው ሳያቸው ረጃጅም ወይዛዝርት መስለውኝ ነበር፡፡ ማንነታቸውን ልጠይቅ ስል ግን የጌታዬን ድምፅ ሰማሁ፡፡» ዘበኛው ከት ብሎ ሳቀ፡፡

መቶ አለቃውም አብሮት ከሳቀ በኋላ «በል ወንድሜ፣ ደህና ሁን፡፡ እኔም ሌላ የካርጎ ቢሮ ማነጋገር አለብኝ፡፡ ስለረዳኸኝ አመሰግናለሁ» ብሎት ሄደ፡፡

መቶ አለቃ ዑስማን ቢሮው ተመልሶ ታዳዎቹን እንደምን እንደሚያጠምዳቸው እያሰላሰለ ሳለ፣ «ሻምበል ናስርን ፈልጌ ነበር» የሚል ጽምፅ ሰማ፡፡

«ሙአዝ ነህ?» አለ መቶ አለቃው ፈጠን ብሎ፡፡

«ነኝ፡፡»

አንድ ፖስታ ሰጥቶት መዝገብ ያገላብጥ ጀመር፡፡ ሙአዝ ደብዳቤውን አንብቦ መጨረሱን እንደተመለከተ መቶ አለቃው ወደ ሙአዝ ቀና ብሎ «አይዞህ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንይዛቸዋለን፡፡ አንተም እንደቀድሞህ ሙሉ ትብብር ልታደርግልን ይገባል» ብሎ አሰናበተው፡፡

ከዚያም መዝገቡ ላይ «ሁለት ሴቶች ከሀፊዝ መኖሪያ ገብተው ከግማሽ ሰአት በኋላ ተመልሰው ወጥተዋል፡፡ ምናልባት በሀፊዝ መጥፋት የተሸበሩ ዘመዶቹ ይሆናሉ ብለን ገምተናል፡፡ ሲገቡም ሲወጡም በእጃቸው ካንጠለጠሉአቸው የሴቶች ቦርሳዎች በስተቀር ምንም አዲስ ነገር አላየንም፡፡ ዘበኛውም እነሱን ከሸኘ በኋላ ከማማው ላይ ወጥቶ የጣኢፍን ሬድዮ ጣቢያ ሲያዳምጥ አንግቷል» የሚለውን ሪፖርት እንዳነበበ በንዴት ፊገግ አለ፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

የሀፊዝ ቤት ጭር እንዳለ ነው:: ዘበኛው ከማማው ላይ ቆሞ ስራ እንዴት እንደሚያገኝ ያሰላስላል:: የመለስተኛ ጭነት መኪና ጥሩምባ ድምፅ እንደሰማ በሩን ከፈተ::

ቤቱን የገዛው ሰው ከሁለት ቀን በኋላ ቁልፉን ይረከባል:: ሀፊዝ ቤቱን ከገዛው ከአህመድ መደኒ ትላንት ማታ የተረከበው ቼክ መኖሩን ለማረጋገጥ የደረት ኪሱን ዳበስ አደረገና ፈገግ አለ:: ከአንድ ሰአት በኋላ ከሳኡዲ-አሜሪካ ባንክ ሰላማ ቅርንጫፍ ገንዘቡን ይረከባል:: እንደተረከበም ከባንኩ ጉን ካለው የሹኤብ መስጊድ ጉራ ብሎ በረመዳን ፆም ወቅት ለድሆች የሚታደል እርዳታ ከሚሰበስብበት ሳጥን ሁለት ሺ ሪያል ሊያኖር ወስኗል::

ፍሰሃና ሀፊዝ እቃዎቹን በወጉ አደራጅተው ወደሁለተኛው ፎቅ በመውረድ ላይ ሳሉ ከግቢው ውጪ የሞተር ድምፅ ሰሙ:: ከዚያም የግቢው ብረት በር በሀይል ተዘጋ:: ፍሰሃ ደረጃዎቹን እየዘለለ ወርዶ ከታችኛው መተላለፊያ ሲደርስ ዘበኛውን እያለከለከ ወደነሱ ሲከንፍ አገኘው::

«ያኢላሂ! ያኢላሂ! (የፈጣሪ ያለህ፣ የፈጣሪ ያለህ!) ተከበናል ጌታዬ:: ተከበናል!» በማለት ዘበኛው እየተንቀጠቀጠ ነገረው::

«ምን?» ፍሰሃ አንባረቀበት::

«የተጫነውን መኪና ላስወጣ በሩን ስከፍት ፖሊሶች አየሁ:: ለማጣራት ማማው ላይ ወጥቼ ሳይም የህንፃው ዙሪያ በፖሊሶች

መከበቡን አረጋገጥሁ:: ጌታዬ ተበድሬ የመጣሁበትን ገንዘብ እንኳ ሳልከፍል ... »

ፍስሃ የሚቀባጥረውን ዘበኛ ጥሎ ወደላይ ወጣ:: ሀፊዝ በድንጋጤ እንደተዋጠ ደረጃው ጫፍ ቆሟል:: ፍስሃ ጥቂት ሲያስብ ቆየና በመጨረሻ ወደ ሀፊዝ ዞሮ «ዘበኛውን በፊት ለፊቱ አጥር ወደውጭ እንዲዘል እዘዘው:: ፊቱንም በከፊል በሻሽ ይሸፍነው» ሲል በቁጣ አዘዘው::

«ያልከው አልገባኝም?» አለ ሀፊዝ ግራ ተጋብቶ::

«እንግዲያውስ ገደል ግባ!» ፍስሃ ጮኸበት:: በንዴት አይኖቹን እያጉረጠረጠበት «ምን መሆን ፈለግህ ታዲያ?!» አለ የአፍንጫውን ጫፍ እየጠራረገ:: «ይልቅ ሂድና ዝለል በለው!»

ሀፊዝ ትዕዛዙን አስተላልፎ እንደተመለሰ ትልቁ የብረት በር በሀይል ተደበደበ:: ተደናግጦ የነበረው ዘበኛ ከማማው ላይ ተወርውሮ አሸዋው ላይ ተጠቅሏል::

ፖሊሶቹና መቶ አለቃ ኡስማን እየተጯጯሁ ወደወደቀው ሰው ሲያመሩ ግቢው ውስጥ አድፍጦ የነበረው ህንዳዊ ሾፌር በሩን ከፍቶ አፈተለከ:: የአጥሩን ቀኝ ይዘው የቆሙት ፖሊሶችም እሱን ለመያዝ ተንቀሳቀሱ:: ይሄኔ በሥርዓት ታቅዶ የነበረው ከበባም ትርምስምሱ ወጣ::

ሁለተኛው ፎቅ ላይ ያደፈጡት ሁለት ሰዎችም ዕድሉን በመጠቀም በመስኮት ዘለሉ:: ሀፊዝ ቀኙን ሲይዝ ፍስሃ በተቃራኒው መንገድ ሸመጠጠ:: ፖሊሶቹ ተከተሏቸው::

ሀፊዝ ጥቂት እንደሮጠ ደከመ:: እግሮቹ እየተወላከፉ መጋጨት ሲጀምሩ ከፊት ለፊቱ ሁለት ፖሊሶች አየ:: ወደኋላው

ቢዞርም ሌሎች አሉ። በቀጭኑ አፋጭቶ ቆመ።ፍስሃ በበኩሉ ቅጣ ጫውን እንደገና ቀይሮ ሮጠ። የሚከተለው ሰው አልነበረም። በስተቀኝ ያለውን ቅያስ አልፎ ጥቂት እንደሮጠ የአንድ ህንፃ ምሰሶ ሥር የተሸሸገ ሰው ትከሻ ተመለከተ። እሱም ያለከልካል። ፍስሃ በፍጥነት እጁን ወደካልሲው ሰዶ አውቶማቲክ ሴንጢውን አወጣ። ቀና ሲል ሙአዝ ወደሱ እየተንደረደረ ነበር። ፍስሃ የሴንጢውን ስለት አስፈንጥሮ እጁን ወደሙአዝ ሰነዘረ።

ሙአዝ «እ...እ ... » ብሎ ሆዱን እንደጨበጠ መሬት ላይ ተዘረረ።

## ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ዑመር፣ አይዳ ሀገሯ ደርሳ እንድትመለስ የሚያስችላትን ገንዘብ ሰጥቷታል:: አገር ቤት መጠነኛ የሹራብ መስሪያና መሸጫ ሱቅ ማቋቋም የሚያስችል ገንዘብ ነው:: እሷ ግን ሀገሯ የመቅረት ሃሳብ የላትም:: ህጋዊ ነዋሪ ሆና በጅዳ መንገዶች እንዳሻት ልትቦርቅ ታስባለች:: ያኔ የማንንም ድጋፍ አትሻም:: በራሷ ስም ቤት ተከራይታ ሌሎች ደባሎችን አሰባስባ ተዝናንታ ትኖራለች:: አስራሁለት ሰአት ላይ ተነስታ ዑመርን ቁርሱን አብልታ ከሸኘች በኋላ የተቋረጠ እንቅልፏን ለመቀጠል ወደአልጋዋ ስትሄድ ይህንኑ ውጥኗን እያሰላሰለች ነበር::

አይኖቿን ከድና እንቅልፏን እያባበለች ሳለች ግን የበሩ ደወል ተንቃጨለ:: ሰአቷን ተመለከተች:: በዚህ ሰአት ማን ሊመጣ ይችላል? በማጮለቂያው ስትመለከት አንድ መልከመልካም ሰው አየች:: አታውቀውም:: እያመነታች«ማን?» ስትል ጠየቀች::

«ዑመር ልኮኝ ነው:: አብዱ ነኝ» አለ::

አይዳ በሩን ከፍታ «ምን አለህ?» ስትል በፈገግታ ጠየቀችው::

«ቁልፍ ጥያለሁና አምጣልኝ ብሎኝ ነው» አለ ክፍሉ መሀል ቆሞ::

«እሺ፣ ልፈልግልህ»ብላ ወደመኝታ ክፍሏ ሄደች:: ቁልፉን ግን ልታገኘው አልቻለችም:: ወደሳሎን ለመሔድ ክፍሉን ለቃ ስትወጣ ግን እንግዳ ነገር ተመለከተች:: ሰውየው ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ከውጪኛው ሳሎን ቆሟል:: አንደኛው ፓኪስታኖች የሚለብሱትን አጠር ያለ ቀሚስና ሰፊ ባጊ ሱሪ ለብሷል:: ሁለተኛው

የሞሮኮ ተወላጅ ይመስላል:: ረጅምና ግዙፍ ሰውነቱ በስፖርት የዳበረ ነው:: ጉርጥ ያስመሰሉት ትላልቅ አይኖቹ ያስፈራሉ:: ዘርዘር ያሉት ትላልቅ ጥርሶቹ ወፋፍራም ከንፈሮቹን አልፈው አገጥጠዋል:: ሰፊና ድፍጥጥ አፍንጫው የተነፋ ይመስላል::

በሩን ያስከፈታት ወጣት ግንባሩን ሳይፈታ፣ «ምን ይገትርሻል ቁልፉን ፈልገሽ ስጪኝ!» ሲል ጮኸባት::

«እናንተ እነማን ናችሁ?» አለች አይዳ ወደኋላዋ እያፈገፈገች:: «ምንስ ትፈልጋላችሁ?»

«እንተዋወቅ፤ እኔ ረፊቅ እባላለሁ:: የዑመር ሚስት ወንድም ነኝ::»

የአይዳ አይኖች ተጉለጎሉ:: ለመጮህ ስትሞክር ፓኪስታናዊው በጥፊ ፀጥ አደረጋት:: ዞረባት:: ደመነፍስዋን «ሁለተኛ በደረሰበት አልደርስም» ብላ ቀና አለች:: ሌላ ጥፊ:: ከግድግዳው ጋር ተላተመች:: በጥርሶቿ የተቀረጠፈው ምላሷ መድማት ጀምሯል::

«አልደርስበትም፤ እውነቱን ነው አለች::»

ሰፊ ቀዳዳዎች ያሉት አፍንጫ ተጠጋት:: ተወራጨች:: ጥርሶቹ ቀድመው ታዩዋት:: ጠብደሉ ሰውዬ የሱሪ አዝራሮቹን ሲፈታ ይታገላል::

«እባካችሁ ማሩኝ፣ ባይሆን ገንዘብ ልስጣችሁ» እያለች ትማፀናቸው ጀመር::

«አርፈሽ ተኚ! ሽርሙጣ!» ብሎ ረፊቅ ጮኸባት::

«ዑመር ያረከሰውን ገላሽን እኔ አፀዳልሻለሁ ... እሀ ... ሀ .. ሀ ... » ብሎ ጠብደሉ ሰውዬ እያለከለከ ከላይዋ ሲከመር ታገለችው:: ሙታንታዋን ቀደ ጣለው::

«ልቀቀኝ! አንተ ኢጋሰስ! ቱፍ ... »ብላ ምራቋን ስደፈችበት፡፡ ስውየው በፈገግታ ከአይኑ ስር የተለደፈ ምራቋን በጣቱ ጠርጕ ላሰው፡፡ አይዳን አንዳች ነገር አቅለሸለሻት፡፡ እንዳያስመልሳት ስትታገል ጠብደሉ በሰፊው አፉ ከንፈሮቿን ጕረሳቸው፡፡ በከንቱ ተወራጨች፡፡ በዚህ መልኩ ሦስቱ ወንዶች ተፈራረቁባት፡፡

መጨረሻ ላይ የተገናኛት ረፊቅ ከአይዳ ላይ ሲነሳ ራሷን ስታ ነበር፡፡ ሞርኮአዊው ወደማዕድ ቤት ሔዶ ቀዝቃዛ ውሀ ይዞ ተመለሰ፡፡ አይዳ አልነቃችም፡፡ ውሀውን ላይዋ ላይ ቸለሰው፡፡ አቃስታ ለመነሳት ስትሞክር በቡጢ ተመታች፡፡ ጮኸች፡፡ ሀይለኛ ጥፊ ተከተሰ፡፡ ይኸኔ ከተሰነጠቀው ከንፈሯ ደም መነጨ፡፡ አቃስታ ወለሉ ላይ ተዘረጋች፡፡ በአፍ በአፍንጫዋ ደም ይንዠቀዠቃል፡፡ የቀኝ አይኗ አብጦ ወደመከደኑ ተቃርቧል፡፡

«ይበቃታል!» አለ ረፊቅ ተዝለፍልፋ የወደቀችውን ሴት እየተመለከተ፡፡ «በል አሁን አሰናብታት!» አለ በመጨረሻ፡፡

ጠብደሉ በደረቷ የተዘረረችውን ሴት ማጅራት ጨምድዶ ካነሳት በኋላ በቀኝ እጁ የያዘውን ስለት ከደረቷ ሰደደው፡፡ ስለቱ ከጡቷ ስር ሲሸቀሸቅ፣ ሰቅጣጭ ጩኸት አሰምታ ወደቀች፡፡ አይዳ ከጡቷ ስር በሚፈልቀው ትኩስ ደም መራስ ስትጀምር ሶስቱ ሰዎች ቤቱን በፍጥነት ለቀው ወጡ፡፡

አይዳ እየተጕተተች ወደ ስልኩ ተጠጋችና ከሁለት ሙከራ በኋላ ወደነከሪም ዘንድ መደወል ቻለች፡፡ ፍስሃ አነሳው፡፡ «ገድለውኛል፣ ሀያትን ...» እንዳለች ስልኩ ተቋረጠ፡፡ «ገደሏት! አይዳን ገደሏት!» ብሎ ፍስሃ እንደገደል ማሚቶ አስተጋባ፡፡ ሰሚራና ሀያት በድንጋጤ ያዩታል፡፡ ወዴት መሄድ እንዳለበት መወሰን

እቃተው:: ወደአይዳ ዘንድ መሄዱ ይሻላል ወይስ ወደፀሎጦር ቤት? የከሪም ያለመኖር ይበልጥ አናደደው:: የጥፋተኛነት ስሜት፣ የበቀል ጥማት፣ ቁጣ ... ሲፈራረቁበት ቆየና ዘሎ ወጣ::

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

የአ·መር ባለቤት ሳሎኗ ውስጥ የወንድሟንና የጂሌዎቹን ገድል እያዳመጠች እግሯን እያነሳች ትስቃለች፡፡ ፊቷ በእርካታ ፈክቷል፡፡

ረፊቅ «ቀጣዩ ባልሽ ነው» ሲላት አመዷ ቡን አለ፡፡

እየተርበተበተች «ከእንግዲህ እንዳይባልግ እነግረዋለሁ፡፡ ካልታረመ ... » ስትል የበሩ ደወል ተንቃጨለ፡፡ በሩን ከፍታ የመጣውን እንግዳ ለማየት አንገቷን ብቅ ስታደርግ አባያ የለበሰች ሴት በሩ ላይ ቆማ አየች፡፡

«ማነሽ?» አለች አይሻ ግራ ተጋብታ፡፡ ከሳሎኑ የሚመጣው ሳቅና ሙገሳ ይሰማል፡፡ ሴትየዋ ወደውስጥ ዘልቃ አይሻን ገፋ አድርጋ በሩን ዘጋችው፡፡

«ማነሽ አንቺ?» አይሻ ተቆጣች፡፡ የእንግዳዋ ሽፍንፍን ሲወልቅ ግን አይሻ ደንገጥ አለች፡፡ «ውል ነበረን አይሻ» አለ ፍሰሀ እየተጠጋት፡፡

አይሻ ግድግዳውን እየታከከች «ፍሰሃ ምን ፈለግህ?» አለችው የባሏን የቀድሞ ወዳጅ በጥርጣሬ እየተመለከተች፡፡

«ስልክ ደውዬ ባለቤትሽን ስላስከበለለችው ዘማዊ ሚስቴ የነገርኩሽ እኔ ነኝ፡፡ ባላንጣሽን ከቀጣሽ በኋላ ክፍያ እንደምትፈፅሚ ቃል ገብተሽ ነበር» አላት ፍሰሃ ለስለስ ብሎ፡፡

አይሻ ፈገግ ብላ:: «እረ ግዴለም፣ ቃሌን እጠብቃለሁ:: ሳሎን ግባና ከወንድሜ ጋር እየተጫዋወትክ ጠብቀኝ» አለችው መንገድ እየጀመረች::

«ሌላ ጊዜ እንተዋወቃለን!» አይሻ ደንግጣ አየችው:: በስጨት ማለት ጀምሯል::

«ይልቅ ፍጠኚ» ብሏት የሳሎኑን በር ተጠግቶ ቆመ::

«አበሻ ሲባል ውሻ ነው! ሀገራችንን አረከሱትኮ:: ውሾች!» ሳቅ ተከተለ:: «በደንብ ተዝናንተንባት ባንጨርሳት ኖሮ በቆጨኝ ነበር» የሚል ወፍራም ድምፅ ደግሞ ተሰማ::

ፍሰሃ ስሜቱን መቆጣጠር ስለተሳነው በሩን በርግዶ አሳሎኑ ገባ:: እንገባ ባቀረሩ አይኖቹ ሶስቱንም አፈራርቆ እያያቸው፣ «በሴት ልጅ ተጫውቶ ህይወቷን ማጥፋት ወንድነት ከመሰላችሁ ውሾቹ እናንተው ናችሁ» ብሎ እጁን ከቀሚሱ ኪስ አውጥቶ የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ ረፊቅ ላይ አነጣጥሮ ተኰሰ:: ረፊቅ ሶፋው ላይ እንደወደቀ ሌሎቹንም አከታትሎ መታቸው::

ፍሰሃ ወደበሩ ሲዞር አይሻን ተዝለፍልፋ ስትወድቅ አያት:: ፈጥኖ ትንሿ ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ስልክ አነሳ:: ገመዱን በጣጠሰው፤ ቀፎውንም ወረወረው:: ከዚያም ፊቱን በአይነርግብ ሸፍኖ ወጣ::

* * *

«ጁምጁም» የተባለው አለታዊ ጋዜጣ ከወጠኒ ገበያ አዳራሽ በስተጀርባ ካለው መንደር አንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ትላንት ምሽት ሶስት ሰዎች መገደላቸውን ዘገበ:: ከዜናው በታች «ይፈለጋል» ከሚል ፅሁፍ ስር ፍሰሃ ከሶስት አመት በፊት እነሙአዝ ቤት

የተነሳው ፎቶ ታትሟል:: ከፎቶው ግርጌ የወንጀለኛው ስም፣ እድሜ፣ ዜግነትና ሀጥያቱ ታትቷል:: ወንጀለኛው ከሳምንት በፊትም አንድ ሰው ገድሎ እንደተሰወረ ፖሊስ ገልፆ ወንጀለኛውን ይዞ ለፖሊስ ላስረከበ ወይም አድራሻውን ለጠቆመ መንግስት ሀያ ሺ ሪያል እንደሚሸልም አስታውቋል:: የሀገሪቱ ሁለት የቴሌቪዥን መስመሮችም ይህንኑ መግለጫ እየደጋገሙ አስተላለፉ:: ፍስሃና ከሪም ተራርቀው እንደተቀመጡ ማስታወቂያዎቹን ተከታተሉ:: ከሪም ተከዟል:: ፍስሃ ግን ዘና ብሎ ሲጋራውን በላይ በላዩ ያቦነዋል::

«ፎቶዉን ከየት አባታቸው አገኙት?» ሲል ፍስሃ በቁጣና በገረሜታ ከሪምን ጠየቀው::

«እርእያ ነው የሰጣቸው» አለ ከሪም ቀዝቀዝ እንዳለ::

«እንዴት አወቅህ?»

«አስር አለቃ ጀሚል ነገረኝ::»

«እርሱንም እደፋዋለሁ » አለ ፍስሃ ረጋ ብሎ::

ከሪም ባለበት ደርቆ ቀረ:: ፍስሃን ትክ ብሎ ተመለከተው:: ወንጀለኛ አይመስልም::

«ፍስሃ ተለመነኝ፤ከንግዲህ ደም ላታፈስ ቃል ግባልኝ:: እንደዚህ መኖር ስለማንችል ፈጥነን ወዳገራችን መመለስ አለብን» አለው::

የፍስሃ ፊት በሀዘን ተዋጠ:: «አይ ከሪም፣ ሁሉን ነገር በሰላም የምትፈታ ይመስልሃል አይደል? በል እሺ ካገር እንድንወጣ ፈቃድ እንዲሰጠን ኤምባሲ ለሚሰራው ወዳጃችን ደውልለት::»

«ኢትዮጵያ ኤምባሲ»ሲል መለሰ ስልኩን ያነሳው ሰው::

«ጤና ይስጥልኝ? እባክዎትን ሰይፉን ፈልጌ ነበር» አለ ከሪም በትህትና::

«ሰይፉ ነኝ:: ማን ልበል?»

«ከሪም ... »

ስልኩን ጆሮው ላይ ጠረቀመበት::

«ዘጋው'ኮ እባክህ» አለ ከሪም ተገርሞ::

ፍስሃ ፈገግ ብሎ፣ «አንተ ሻወር እየወሰድክ ሳለህ ደውዬለት ነበር:: በኔ ላይ የፈፀመውን ነው ባንተም ላይ የደገመው» አለና ተቀመጠ::

* * *

የአርቡ የጁምአ ሰላት እንዳበቃ በለድ ከሚገኘው መስጊድ ውስጥ ተሰብስበው የነበሩት ምዕመናን እየተጋፉ መውጣት ጀምረዋል:: ከመስጊዱ ትይዩ ሙጠወአችና ፖሊሶች ተሰብስበዋል:: ግዙፍ ሰውነት ያለው ረጅም ስዑዲያዊ እጆቹን ወደኋላ አጣምሮና እግሩን አንፈራጦ ቆሟል:: ከመስጊድ የሚወጡት ምዕመናን ባሻገር የሚታዩትን ሰዎች እንደተመለከቱ በቅዱስ ቤቱ በር ላይ እጅብ ብለው ቆሙ:: መስጊዱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ወጥተው እንዳበቁም የቀትሯን ፀሀይ ለመከላከል ግንባራቸውን በመዳፋቸው ከልለው ቀጣዩን ሁኔታ ይከታተሉ ጀመር::

አጠር፣ ወፈር ያሉት ሰውዬ ሪዛቸውን እየሞዠቁ ወደተሰ በሰበው ህዝብ ቀረብ ብለው መናገር ጀመሩ::

«በዛሬዋ እለት የቁርአንን ህግ በመጣስ ሀይማኖቱን ሲያጕድፍ የተገኘ ሰው ላይ የተበየነ ፍርድ በዚህ ሥፍራ ይፈፀማል:: ምዕመናን ሆይ! የአላህንና የነብዩ ሙሀመድን ትዕዛዝ የጣሰ ማንኛውም ወንጀለኛ ቅዱስ ቁርአን በሚያዘው መሰረት ፍርዱን ያገኛል:: እጅ የቀረጠ፣ እጁን ያጣል:: አይን ያጠፋ፣ አይኑ

ይጠፋል። ሲሰርቅ የተገኘ የሰረቀበትን እጁን ይነጠቃል! .... ሁላችሁም እንደምታውቁት ወንጀለኞች በየጊዜው በጁምአ ዕለት ፍርዳቸውን ሲቀበሉ ቆይተዋል። ማንኛውም የውጭም ሆነ የሀገሪቱ ዜጋ በጥፋቱ ልክ ቁርአን የሚሰጠውን ብይን ሲቀበል ኖሯል።

«በዛሬዋ እለትም መጠጥ ሲያዘዋውርና በቤቱ ውስጥ አከማችቶ ሀራም ሲሰራ፣ ፅፅ ሲጠቀም፣ በቁማር ገንዘብ ሲያግበሰብስ እንዲሁም ኒካህ (ቃልኪዳን) ካላሰረላቸው ሴቶች ጋር ዝሙት ሲፈፅም የኖረ ሰው ከብዙ ድካም በኋላ እጃችን ገብቷል። ወንጀለኛው የሳዑዲ አረቢያ ዜጋ ነው .... »

የህዝቡ ጉምጉምታ የተናጋሪውን ድምፅ ዋጠው። ሰውየው ጥቂት ታግሰው ፀጥታ ሲሰፍንላቸው ንግግራቸውን ቀጠሉ። «ለአመታት ሲፈፅማቸው የነበሩ ወንጀሎችን አጣርተንና በመረጃ አስደግፈን ቁርአን የሚበይነውን ፍርድ ለመፈፀም ወደዚህ አምጥተነዋል። ስሙም ሀፊዝ አብዱል መጅድ ይባላል። እንግዲህ ከዚህ በኋላ ብይኑ ይፈፀማል» ብለውም ከመሰሎቻቸው ጋር ተቀላቀሉ።

የሀፊዝ እጆች ወደኋላ እንደታሠሩ በሁለት ፖሊሶች ታጅቦ ብቅ አለ። ፀጉሩ በሚገባ ተበጥሯል። የለበሰው ልብስ የተጨማደደ ቢሆንም ንፁህ ነበር። አይኖቹ በጥቁር ጨርቅ ተሸፍነዋል።

ፊቱን ወደተሰበሰበው ህዝብ አዙሮ እንዲቆም ተደረገ። ፀሎት እንዲያደርግም ጥቂት ደቂቃዎች ተሰጡት። በርካታ ጭንቅላቶች በማየት ጉጉት ብቅ ጥልቅ ይላሉ።

ገዳዩ ፈገግ ብሎ «አላሁ አክበር!» ሲል ጮኸ። ህዝቡ ያንኑ መልሶ አስተጋባ። ደገመው። ህዝቡም እንዲሁ። ለሶስተኛ ጊዜ

«አላሁ አክበር!» ብሎ ተሽከርክሮ ወደሀፊዝ ሲዞር ረዳቱ የሀፊዝን ሽንጥ በያዘው የብረት ዘንግ ወጋ አደረገው:: ሀፊዝ ተሸማቆ ቀና ሲል አንገቱን ለይቶ ያገኘው ገዳይም በቀላሉ ቀላው::

ይኸኔ ከሪም ፊቱን ሸፍኖ ከህዝቡ መሀል እየተሽሎከለከ አካባቢውን ለመልቀቅ ተጣደፈ:: ጥርሱ ይንገጫገጫል:: መስጊዱ ጀርባ ሲደርስ የማያውቀው ሰው አየ:: ሰውየው ፊቱን በከፊል አናቱ ላይ ጣል ባደረገው ሻሽ ሸፍኗል:: ሰርቆ ከሪምን ተመለከተ::

ከሪም ጠጋ ብሎ፣ «መጅድ፣ ሀፊዝን አረዱት» አለው:: መጅድ ግራ ቀኙን ተገላምጦ «ፈጣሪ ካልጠበቀን በቀር የሁላችንም ዕጣ ይኸው ነው» ብሎት ተሠወረ::

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ፍራፍሬና ሸቀጣሸቀጥ ከሚያመላልሱት መኪኖች እየቀደመች የምትገሰግሰው አይሱዙ ወደጂዛን እየከነፈች ነበር።

ትንሿ የወደብ ከተማ ጂዛን ሲገቡ ከተማዋ በቅዝቃዜ ተቀበለቻቸው። ወደቡ ከመድረሳቸው ጥቂት መቶ ሜትሮች ርቀት ላይ ከሪም ሾፌሩን አስቁሞ በግማሽ ሰአት ውስጥ እንደሚመለስ ነግሮት ሄደ።

ከአምስት ደቂቃ የእግር ጉዞ በኋላ የመናዊውን ፋአድን አገኘው። አድሜውን ትናንሽ ጀልባዎች ላይ የፈጀው ፋአድ ጠያቂ አጥቶ የከረመውን መጠጥ የሚወስድለት ደንበኛ በማየቱ ተፍለቅልቋል።

«ምነው ጠፋችሁ ጻል?» አለው ከሪምን ወደቤት ውስጥ እንዲገባ እየጋበዘ።

«ስራ ሞቷል እባክህ» አለው ከሪም በረጅሙ ተንፍሶ ደረቁ ወንበር ላይ እየተቀመጠ።

በመልሱ የተናደደው ፋአድ «ምን ልታዘዝ ታዲያ?» አለው።

«እርዳታህን ፈልጌ ነው የመጣሁት።»

ፋአድ በብስጭት እጆቹን ሲያወናጭፍ፣ ከሪም፣ «በነፃ እንዳይመስልህ። ሁለት ሺ ሪያል ይከፈልሀል»ብሎት ንግግሩን አቋረጠ። የመናዊው ትንፋሹን ውጦ ፀጥ አለ።

«ጓደኛዬን ወደአሰብ ታሻግርልኛለህ?»

ፋአድ መልስ አልሰጠውም።

«ስማ፣ ጓደኛዬ መጠጥ እንደሚሸጥ ተደርሶበት ለጥቂት አምልጧል:: ቢያዝ ኖሮ አንተም፣ እኔም፣ እነሙአዝም ያበቃልን ነበር:: አሁንም ...»

ፋአድ አቋርጦት «እሺ፣ አሻግርልሃለሁ» አለው::

«እንግዲያው የዛሬ ሳምንት በኔ ልክ የጀልበኛ ልብስ አሰፊተህ እዚሁ ጠብቀኝ::»

«የምትታደነው አንተ ነህ እንዴ?»

«ሳ! ሳ! » አለ ከሪም ሳቅ ብሎ፤ «የጓደኛዬ ውፍረት ከኔ ጋር ተመጣጣኝ ስለሆነ ነው:: ቁመቱ ግን ትንሽ አጠር ይላል» አለው::

«እንግዲያውስ ውፍረቱ ባንተ፣ ቁመቱ ደግሞ በኔ ተገምቶ ይሰፋለታ» አለ አረቡ ተረጋግቶ::

«በጣም ጥሩ:: ለዚህ ቀና ትብብርህ ደግሞ አምስት መቶ ሪያል ይጨመርልሀል» አለ ከሪም የየመናዊውን ጀርባ ቸብ፣ ቸብ አድርጎ:: በመጨረሻም ከሪም አምስት መቶ ሪያል ሰጥቶት በተከራየው መኪና ወደጅዳ ተመለሰ::

* * *

ፍስሃ የከሪምን እቅድ ሲሰማ በረጅሙ ተንፍሶ «ሃሳብህ ድንቅ ነበር:: ነገር ግን ...» አለና ዝም አለ::

«ግን ምን?»

«አይሳካም::»

«ለምን አይሳካም?»

«ወደጂዛን ስትሄድ ኬላ ላይ ፖሊሶች ፎቶዬን ይዘው እንደነበር ያጫወትኸኝን ረሳኸው?!»

«ልክ ነህ:: የግድ የቤት መኪና ያስፈልገናል» ብሎ ስልኩን አነሳ ከሪም::

«ሀሎ፣ መጅድ? ከሪም ነኝ» አለ ስልኩን እንዳይዘጋበት እየፀለየ::

«ከሪም ያን ስራ እንደሆን ትቻለሁ!»ብሎ ጮኸ መጅድ::

ከሪም በዝግታ «አድማጌ ለፍሰሃ፣ እኔም ትቻለሁ» አለው::

«ታዲያ ለምን ደወልክ?»

«መኪናህን ለአንዲት ቀን እንድታከራየኝ ፈልጌ ነው::»

«ወዳጄ እኔ ከናንተ ጋር አንዳችም ግንኙነት እንዲኖረኝ አልፈልግም:: ከናንተ የተነካካ ሁሉ ሞት አይቀርለትም:: ስለዚህ...»

«መጅድ ኸረ አባክህን ለለጥንቱ ጓደኝነታችን ስትል እርዳኝ?» በማለት ከሪም ይለማመጠው ገባ::

«እሺ፣ ለመቼ ነው የምትፈልጋት?» አለ መጅድ እያቅማማ::

«ለቅዳሜ ማታ::»

«ጠይብ፣ መደኒ ጋራዥ ታገኛታለህ:: ቁልፉን ዘበኛው ዘንድ አኖርልሀለሁ::»

«መጅድ መቼም ምስጋናዬ የላቀ ነው:: ደህና ሁንልኝ!» አለው::

ከሪም ስልኩን ዘግቶ ሲቀመጥ፣ ፍሰሃን ግራ ተጋብቶ በጥያቄ ዓይን ሲመለከተው ስላየ፣

«በቃ፣ ኬላውን በሀይል እንጥሰዋለን!» ብሎ ፀጥ አለ::

* * *

አስር አለቃ ሁሴን «ጁምጁም» ጋዜጣን እያገላበጠ በችኮላ መንገዱን ተሻግሮ ወደሥራው እየሄደ ሳለ ቀይ ሻሽ ጭንቅላቱ ላይ ያጠለቀ አንድ ወጣት «ጋዜጣ ላይ የወጣውን ተፈላጊ ወንጀለኛ

አውቀዋለሁ» አለው:: አሥር አለቃው ጋዜጣውን ዘርግቶ «በርግጥ ይህን ሰው ታውቀዋለህ?» ሲል ጠየቀው:: ወጣቱ እርግጠኛ ነበር:: በትክክልም እርሱ ከሚኖርበት አፓርታማ ላይ ነበር እነከሪም የሚኖሩት::

አሥር አለቃው ሽጉጡን እያስተካከለና የሚሸለመውን ሪያል እያሰመ፣ «እኔና አንተ እንበቃለን:: አፓርታማውን ብቻ አሳየኝ!» አለው:: ብዙም ሳይሄዱ ከሪምን አገኙት::

«ይሄ ወዳጄ ዱሮ ስለሚያውቀው በሩን በቀላሉ ሊያስከ ፍትልን ይችላልና አብሮን ይሂድ» አለ ወጣቱ:: ከሪም እንደመግ ደርደር ሲል አሥር አለቃው ገሠፀው:: ከሪም ውሳኔውን በቅሬታ ተቀበለው::

አፓርታማው እንደደረሱ ፖሊሱ የበሩን ደወል ተጫነው:: ፍሰሃ በዝግታ ተነስቶ ከሶፊው ጐን የተቀመጠውን ኮመዲኖ ሳበው:: ከሶስት ቀናት በፊት አስቀምጦት የነበረው ሽጉጥ በቦታው የለም:: ፍሰሃ በከሪም ደደብነት እየተበሳጨ ሳለ ደወሉ በድጋሚ ጮኸ::

«ማነህ?» አለ በሩን ተጠግቶ::

«እኔ ነኝ» ሲል ከሪም መለሰ::

ተረጋግቶ በሩን ሲከፍተው ግን ሽጉጥ ተደገነበት:: «ከሪም አንተም ከዳኸኝ!» ብሎ ፍሰሃ ዝም አለ::

«አዝናለሁ» አለው ከሪም በዝግታ::

«እጅ ወደላይ!» ብሎ አስር አለቃ ሁሴን ሽጉጡን ሲያስተካክል ፍሰሃ ሁለት እጆቹን ከጭንቅላቱ በላይ ዘረጋ::

«ቁጭ በል!»አለው አስር አለቃው በቁጣ::

ይኸኔ ከጀርባ የቆመው ከሪም አስር አለቃውን «ሽጉጥህን ወደመሬት ጣለው» ብሎ ጮኸበት:: ዞር ሲል የከሪም ሽጉጥ

ጭንቅላቱ ላይ ተነጣጥሮ አየ:: በድን ሆነ:: የከሪም ሽጉጥ አንገቱ ስር ሲጠጋ በተሰማው ቅዝቃዜ የተነሳ ግን ሁኔታውን አገናዝቦ ሽጉጡን ወደመሬት ለቀቀው:: ከዚያም «ብል ፍጠንና የወዳጅህ የአሥር አለቃ ጀሚልን ስልክ ስጠኝ» አለው ከሪም ወደስልኩ እየሄደ::

## ምዕራፍ ሰላሳ

ጂዛን መጠጫ ፍተሻ ጣቢያ ላይ አፍንጫቸውን ለጂዛን የሰጡ ሽቀጣሽቀጥ የጫኑ መኪኖች ተሰልፈዋል:: የኬላው ፓውዛ ምሽቱን ቀን አስመስሎታል:: በፍተሻው የተማረሩ ሾፌሮች በመኪናቸው ጡሩምባ ጣቢያውን ያደባልቁታል::

ከጅዳ ከተማ የመጣው ፋሚሊ ፔጆ ሾፌር ጉን የተቀመጠው ፖሊስ እናቱ ላይ ጣል ካደረገው የሳኡዲ አረቦች መለያ ከሆነው ቀይ ሻሽ በላይ የፖሊስ መለዮ ደፍቷል::

በአፍንጫው ባስማገት የሰመመን መድሀኒት ራሱን ከሳተ በኋላ ከወንበሩ ጋር ተጠፍሮ ታስሮ ከአፓርታማቸው ሳሎን ከተቆለፈበት እስር አለቃ ሁሴን የተገፈፈውን መለዮ ልብስ የለበሰው ፍስሃ ነበር:: ሾፌሩ ከሪም ነው::

ፔጆዋ ወደኬላው እንደተቃረበች ፍስሃ ጥቁር መነፅሩን አጥልቆ እጁን መቀመጫው ስር ወደሸጎጠው መሳሪያ ሰደደ::

«ነገሮች እስካልተበላሹ ድረስ እንዳትተኩስ:: የምትናገረው አረብኛ ደግሞ የገጠሬ ሳኡዲ አረቢያዊ አይነት ይሁን» አለ ከሪም ረጋ ብሎ::

አንድ ወፍራም ፈታሽ ተጠግቷቸው፣ «የመኖሪያ ... » ሲል፣ ፍስሃ በቁጣ፣ «ባልደረባህ እንዴት ከሀገሩ ጠላቶች ጋር ይሔዳል ብለህ ትገምታለህ?!» አለው::

ፈታሹ ይበልጥ አስር አለቃውን አተኩሮ አየው:: ፍስሃ ስለመሆኑ ተጠራጥሯል:: «አሥር አለቃ ጀማል፣ አትደናገጥ ፍስሃ ነኝ:: በተነጋገርነው መሠረት ይፈፀም» አለው በዝግታ:: ከሁለት ቀን በኋላ ባንክ ሒሳቡ ውስጥ ሁለት ሺ. ዶላር እንደሚያስገቡለት እነከሪም ቃል ገብተውለታል:: ቢሆንም የሳኡዲ አረቢያ መንግስት የመደበው ሀያ ሺ. ሪያል ከዚያ እንደሚበልጥ ስለሚያውቅ ጀማል ወላውሏል::

«ስስራ ጉዳይ እየተጣደፈኩ ነው:: ጊዜዬን አታቃጥልብኝ!» አለ ፍስሃ ጮክ ብሎ:: ፈታሹ ወደኋላው ገልመጥ ብሎ የስራ ባልደረቦቹን አያቸው:: ሌሎች መኪኖችን በመበርበር ስራ ተጠምደዋል:: ጉሮሮውን ጠራረገና «አዝናለሁ» አለ::

የፍስሃ ከንፈሮች ተንቀጠቀጡ:: ከሪም እጁን ወደኪሱ እየሰደደ፣ «እንግዲያው እኔም አዝናለሁ፤ ቃልህን ብታጥፍ በዚህ» ብሎ ድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ ጫፍ ወደሱ አዞረ:: «እኛ እንደሆንን ተስፋ ቆርጠናል:: ስለዚህ ከሞትን ብቻችንን አንሞትም!»

«በጣም ይቅርታ ... ልሳሳት ነበር ... » ተርበተበተ አሥር አለቃ ጀማል::

«ለፈጣን እርምትህ ተጨማሪ አንድ ሺ. ዶላር አስገባልሀለሁ» አለ ከሪም ፈገግ ብሎ::

አሥር አለቃው ባልተረጋጋ መንፈስ እየሳቀ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጣቸውና የብረቱ አጥር እንዲነሳላቸው አዘዘ:: ፍስሃ የሞት ኬላውን ተሻግሮ በህይወት ባህር ላይ ቀዘፈ::

*          *          *

ሆዶት እንደታሰረች በጣም ታማ ነበር:: አሁን ግን የእሥር ቤቱን ኑሮ እየለመደችው ነው:: ፊት ለፊት የሚታየው የመፀዳጃ ቤት በር የለውም:: እስረኞቹ ካርቶን እየጋረዱ ነው የሚፀዳዱት:: ቧንቧዎቹ ውሀ የሌላቸውና በጣም የዛጉ ናቸው:: በየቦታው የህፃናት ሰገራ ይታያል:: የአየር ማቀዝቀዣዎቹም ተዘግተው ይውሉና ሌሊት ላይ ይከፈታሉ::

በዚህ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ህገወጥ ስደተኞች ታጉረዋል:: ከአዳራሹ ፊንጠር ብሎ ደግሞ የወንዶቹ ማጉሪያ ይገኛል:: ያለመኖሪያ ፈቃድ ሲንቀሳቀሱ የተያዙ፣ በወንጀል ተይዘው ፍርዳቸውን የጨረሱ...ወዳገራቸው ሊሸኙ የሚጠራቀሙበት ሥፍራ ነው::

ኢትዮጵያውያን፣ ኤርትራውያን፣ ሱዳናውያን፣ ሱማሌዎች፣ ጋናውያን፣ ፓኪስታናውያን፣ ህንዳውያን፣ ኢራናውያን ... መደዳውን በየሀገራቸው ተቧድነው ተቀምጠዋል:: ፊሊፒኖች፣ ኢንዶኔዥያውያንና ባንግላዴሾች ከተቀሩት እስረኞች በቁጥር ስለሚልቁ የውስጠኛውን አዳራሽ ሞልተውታል:: ወደውጪኛው አዳራሽ ብቅ የሚሉትም በምግብ እደላ ሰአት ብቻ ነው::

ቆሻሻው የሲሚንቶ ወለል ላይ የተቀመጡት እሥረኞች አልፎ አልፎ የተቀዳደደ ካርቶን ጣል አድርገው ከተጋደሙቱ በስተቀር፣ ቀዝቃዛውን ግድግዳ ተደግፈው ወግ ይጠርቃሉ:: ከመካከላቸው አብዛኞቹ ሲጋራ የሚያጨሱ ናቸው::

ከሀገራቸው ሰዎች ጋር የማይቀላቀሉት ኢራናዊት አሮጊት ከሀበሾች በስተቀኝ ተቀምጠዋል:: ቀልመም ያለ አፍንጫ ያላቸው የኒህ ሴት ትናንሽ አይኖች በአዳራሹ ውስጥ ይራወጣሉ:: የታችኛዎቹ የፊት ጥርሶቻቸው በማለቃቸው ስሱ የታችኛው

ከንፈራቸው ወደውስጥ ገብቷል:: በአፋቸውና በአይኖቻቸው ዙሪያ ያለው ቆዳ ተሸብሽቧል:: ወፍራም ናቸው:: ለረጅም ሰአታት ከተቀመጡበት ሳይነሱ ነው የሚውሉት:: ለስላሳው ፀጉራቸው ከሻሻቸው ስር አፈትልኮ ይታያል:: አርጊቷ በስተቀኛቸው የተቀመጠችውን ሀያት ጉንተል አድርገው ዞር ስትል ሲጋራ ጋበዟት:: ሀያት ግራ እንደተጋባች ተቀበለቻቸው::

ከሰሚራ ጉን የተቀመጠችው ሀበሻ የሚያለቅሰውን የአንድ አመት ልጇን ጡት አጉርሳ ለሀያት ስለአርጊቷ ማስረዳት ጀመረች::

«እኚህ ሴት ከታሰሩ ስድስተኛ ወራቸውን ይዘዋል:: ብዙ ጊዜ በመቀመጣቸውና የወለሉም ቅዝቃዜ ተጨምሮበት መቀመጫቸው ተላልጦ እየቆሰለ ነው» አለቻት::

ሀያት የተሰጣትን ሲጋራ እያፍተለተለች «ለምን ይህን ያህል ጊዜ አሰሯቸው?» ስትል ጠየቀቻት::

«አንድም የሚያስታውሳቸው ሰው የለም:: እኔ እንደሚመስለኝ ፋይላቸው ጠፍቷል ... አንቺን የሳቸው ነው የገረመሽ? ከአመት በላይ የታሰረች ሴትዮም አለች:: ያችውልሽ እንዲያውም...» ብላ አመልካች ጣቷን ወደፓኪስታናውያኑ መስብ ሰቢያ ቀሠረች:: ፓኪስታናዊቷ እግሮቿን ዘርግታ ከሚያውካኩት የሀገሯ ሴቶች ፈንጠር ብላ ተቀምጣለች:: ልጅ እግር ስትሆን ከሲታና የገረጣች ነች:: አጠገቧ የሲሚንቶው ወለል ላይ ጣል ከተደረገ ካርቶን ላይ ተኝቶ እግሮቿን የሚያወራጭ ጨቅላ ይታያል::

«ምንድነው ሆኖባት?» አለች ሀያት በጉጉት::

«ብታስረኝበት ወቅት ነፍሰ ጡር መሆኗ በፖሊሶች ታውቆ ስለነበር የአባቱን ማንነት ለመናገር ፈቃደኛ ሳትሆን በመቅረቷ ነው» አለች፡፡

«አንቺንስ የት ያዙሽ?» አለች ሀያት ወደአሸረቃ ቀረብ እያለች፡፡

አሸረቃ እንቅልፍ የጣለውን ልጇን ከጭኗ ላይ አንስታ ካርቶን ላይ እያጋደመች ፈገግ ብላ ሀያትን ተመለከተቻት፡፡ «እኔ እንኳን በራሴ ጥፋት ነው የተያዝኩት» አለች፡፡ «ወደጅዳ የመጣሁት ከሶስት አመት በፊት ነበር፡፡ ለአንድ አመት ያህል ሶስት ቤቶች ተቀጥሬ ሰራሁ፡፡ ሁለተኛው አመት ላይ ከዚህ ልጅ አባት ጋር ፍቅር ጀመርን፡፡ በመጨረሻም ስስት ክፍል ቤት በርካሽ ተከራይተን ስንኖር ይህን ልጅ አፈራን፡፡ ታዲያ አንድ ቀን ቀትር ላይ የበሩ ደወል አቃጨለ፡፡ ባለቤቱ ከስራ የሚመለስበት ሰአት በመሆኑ በማጮለቂያው እንኳን ሳልመለከት በሩን ከፈትሁት፤ የማላውቀው ሰው ነው፡፡ ሮጬ መኝታ ቤቱን ቆልፌ በሌቦች መከበቤን ለፖሊስ ሪፖርት አደረግሁ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፖሊሶች ሲደርሱ ማንም አልነበረም፡፡»

«ከዚያስ?»

«የመኖሪያ ፈቃድ ጠየቁኝ፡፡ ከነልጄ ይዘውኝ ሲወጡ ባለቤቱ ከስራ እየመጣ ነበር፡፡ ስለዚህ ባለቤቱም ከኔና ከልጁ ጋር ተዳብሎ ከነቤት እቃዎቻችን ወደዚህ ተወረወርን፡፡»

ሀያትና ሰሚራ አንገታቸውን ደፉ፡፡

«አሁን የጨነቀኝ» አለች አሸረቃ በምፀት ፈገግ ብላ «የቤተሰቦቼን አይን እንዴት እንደማይ ነው፡፡ ስለማግባቴም ሆነ ልጅ ስለመውለዴ የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ከአንድ አመት በኋላ የተቋረጠውን እርዳታዬን እየጠበቁ ባሉበት ሰአት ሁለት ራሴን ሆኜ ስመለስባቸው!...» ብላ ፀጥ አለች፡፡

ሀያት ድምጿን ሳታሰማ እያነባች ነበር። ሰሚራ ደንግጣ «ምነው ሀያት? ወዳገርቤት በሠላም መሄድ ያስለቅሳል?!» አለቻት

«ሰባራ ሳንቲም ሳልይዝ ስመለስ እንዴት አላዝንም?!»

«ሀያት ደግመሽ ስለገንዘብ አታንሺብኝ። እኛ በቂ ገንዘብ ስላለን አብረን እንሰራለን።»

«እግዜር ባይጨክንብኝ ምን ነበረበት? ምናለ ...»

ድንገት ትልቁ የብረት በር መዝጊያ ተከፈተ። የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሰ አጭር ጥቁር ሳዑዲ አረቢያዊ በሩ ላይ ቆመና «ያሀበሽያ! ያኤርትሪያ!» ሲል ተጣራ። ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን እየተጣደፉ ጓዞቻቸውን እንደተሸከሙ ወደበረንዳው ወጡ። የተጓዥ እስረኞች የስም ዝርዝር ተጠርቶ እንዳበቃ በሰልፍ ወደግቢው እንዲወጡ ተደረገ። ከአዳራሹ ፊት ለፊት ሁለት ዝግ መኪኖች ቆመዋል። ሴቶቹና ወንዶቹ ለየብቻ ተሳፈሩ።

ሁለቱም ዝግ መኪኖች እስረኞቹን ጭነው የጅዳን ጎዳናዎች እያቆራረጡ ወደጅዳ አየር ማረፊያ ገሰገሱ። ጅዳ በምሽቱ ድምቀት እንደተዋበች ነች። ብዙዎቹ እስረኞች የከተማዋን ስም እየጠሩ የስንብት ቃላት ሲወረውሩ ይሰማሉ። ቀይ ባህርን በስተግራ ትተው ወደአየር ማረፊያው ያቀኑት መኪኖች ለእስረኞች ተሽከርካሪ መግቢያ በተመደበው በር አልፈው ገቡና ያጨቋቸውን እስረኞች አራገፉ። ፍተሻና ሌሎችንም ሥርዓቶች ሲያሟሉ ጉሀ ቀደደ።

አየሩን እየሰነጠቀ ወደማረፊያው ሜዳ ያዘቀዘቀው አውሮፕላን ሥፍራውን እንደያዘ እስረኞቹ በሠልፍ ወደአውሮፕላኑ መዝለቅ ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ከህንፃው በስተቀኝ ከሚገኘው የይለፍ ክፍል ሰዎች ወጡ። ከሪምና አንድ ፖሊስ አይዳን ደግፈው ወደአውሮፕላኑ እየመጡ ነበር። እንደደረሱም ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ገቡ።

አይዳን ከባለሁለቱ መቀመጫ ረድፍ፣ በመጀመሪያው ጥግ አስቀመጧት፡፡ ከሪም ፖሊሱን አመስግኖ ከአይዳ ኋላ ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡ ሀያትና ስሚራ እየተጣደፉ ሲገቡ ከሪም ተነስቶ «እንኳን ለዚህ አበቃን!»ብሎ አቅፎ ሳማቸው፡፡ ሀያት ወደአይዳ ቀረብ ስትል ገርበብ ያሉት የአይዳ አይኖች ተገለጡ፡፡ «ሀያት? ... ይ-ቅ-ር-በይ-ኝ ... » አለች እያቃሰተች፡፡

«አይዳ፣ ይቅር ብዬሻለሁ» አለች ከእንባዋ ጋር እየታገለች፤ « ... ያለፈውን እርሺው!» ሀያት ከከሪም ጐን ተቀመጠች፡፡

ወዲያውኑ «ክቡራትና ክቡራን ተጓዦቻችን የወገባችሁን ቀበቶ እሠሩ!» የሚል ጣፋጭ የሴት ድምፅ ተሰማ፡፡ ከሪም እጆቹን ሀያት አንገት ዙሪያ ጠምጥሞ፣ «ሀያት አንድ ነገር ልንገርሽ?» ሲል ጠየቃት፡፡ፈገግ ብላ በፍቅር አይን እያየችው «ምንድነው?» አለችው፡፡

«አንቺና ስሚራን ጠቁመን ያስያዝናችሁ እኔና ፍሰሀ ነን፡፡»

አይኖቿ ፈጠጡ፡፡ «ለምን?» ብላ አንባረቀችበት፡፡

«ወደሀገርሽ መመለስ እንዳለብሽ ስላመን አደረግነው፡፡ አንቺ ደግሞ በወቅቱ ወዳገርሽ ለመግባት ፈቃደኛ አልነበረሽም፡፡» አልመለሰችለትም፡፡

እንደተኰራረፉ አውሮፕላኑ የኤርትራን ህገወጥ ስደተኞች ለማራገፍ አስመራ አየር ማረፊያ እንዳረፈ እሪታ ተሠማ፡፡ ስሚራ እጆቿን ከአናቷ በላይ ዘርግታ ታርገበግባለች፡፡ ከሪምና ሀያትም እያነቡ ናቸው፡፡ አይዳ ለሀገሯ ምድር ሳትበቃ እስከዘለአለሙ አሸለበች፡፡ ሦስቱ ጓደኞቿም እሾሃማ ወርቅ ቧጥጦና ቀረዳድዶ በኮረዳነቷ ለቀጫት አይዳ ከልብ አለቀሱ—አገራቸው አዲስ አበባ እስኪደርሱ፡፡

...ዝ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋ ብር 13.75